
# ትምህርተ መለኮት





አዘጋጅቶ ያቀረበው

ዓምራት ገብረማርያም



፲፱፻፹፫ ዓ.ም.

« ዐውቀውትስ ቢኾኑ የክብርን ጌታ ባል ሰቀሉትም ነበር » ። ፩ኛ ቆሮ ም፪ ቁ፰



ዓሥራት ገብረ ማሪያም

እሳትንና ውሃን በፊትህ አኑሮልሃል እጅህን ወደ መረጥኸው ክተት ሰው በፊቱ ህይወትና ሞት አሉለት ከኹለቱ መካከል እርሱ የመረጠው ይሰጠዋል (ሢራክ ም ፲፭ቁ ፲፮ ፲፯)



# ማ ው ጫ


ገጽ

መቅድም - - - - - - - - - - - - - - - ፲

## ምዕራፍ አንድ ፤

## ትምህርተ እግዚአብሔር

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - - - ፲፪

ለ) የእግዚአብሔር ህልውና - - - - - - - - - ፲፫

1. የፍጥረቱ ሥነ ሥርዐት - - - - - - - - ፲፫
2. የኅሊና ምስክርነት - - - - - - - - - ፲፬
3. የሰው ልጆች የተፈጥሮ ዝንባሌ - - - - - - ፲፮
4. የቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ምስክርነት - - - ፲፯

ሐ) የእግዚአብሔር ጠባዮች - - - - - - - - - ፲፯

1. የእግዚአብሔር መንፈስነት - - - - - - - ፲፯
2. የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት - - - - - - ፲፰
3. የእግዚአብሔር ኹሉን ቻይነት - - - - - - ፲፱
4. የእግዚአብሔር አለመለወጥ - - - - - - - ፳፫
5. የእግዚአብሔር ምሉእነት - - - - - - - ፳፬
6. መለኮታዊ ጥበቃው - - - - - - - - - ፳፭
7. ዐዋቂነቱና ጥበቡ - - - - - - - - - - ፳፮
8. የእግዚአብሔር ቅዱስነት - - - - - - - ፳፱
9. የእግዚአብሔር ደግነት - - - - - - - - ፴
10. የማንንም እርዳታ አለመፈለጉ - - - - - - ፴፱

ገጽ

## ምዕራፍ ኹለት ፤


ምሥጢረ ሥላሴ - - - - - - - - - - - - ፵፩

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - - - ፵፩
ለ) ምሳሌዎች - - - - - - - - - - - - - ፵፪
የመጀመሪያው ምሳሌ - - - - - - - - - - ፵፫
ኹለተኛው ምሳሌ - - - - - - - - - - - ፵፬
ሦስተኛው ምሳሌ - - - - - - - - - - - ፵፬
ሐ) የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች - - - - - - - - ፵፬
መ) የሲኖዶሶች ምስክርነት - - - - - - - - - - ፵፮
ሠ) የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት - - - - - - - - ፵፱
ረ) ሥርጸት - - - - - - - - - - - - - - ፶፩


## ምዕራፍ ሦስት ፤

## የቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፍ ጉባኤዎችና ውሳኔዎቻቸው ፤


መግቢያ - - - - - - - - - - - - - - - ፶፯
የኢየሩሳሌም ጉባኤ ፶፩ ዓ. ም. - - - - - - - - ፶፯
የኒቅያ ጉባኤ ፫፻፳፭ ዓ. ም. - - - - - - - - - ፶፱
የትንሣኤ በዓል - - - - - - - - - - - - ፷፭
መላትዮስ - - - - - - - - - - - - - - ፷፭
የመናፍቃን ጥምቀት - - - - - - - - - - - ፷፯
ክህነትና የድንግልና ኑሮ - - - - - - - - - ፷፯
የኒቅያ ጉባኤ ቀኖናዎች - - - - - - - - - - ፷፯
የቍስጥንጥንያ ጉባኤ ፫፻፹፩ ዓ. ም. - - - - - - - ፸፪
አቡሊናርዮስ - - - - - - - - - - - - - ፸፪
አውሳብዮስ - - - - - - - - - - - - - - ፸፫
መቅዶንዮስ - - - - - - - - - - - - - - ፸፫
የቍስጥንጥንያ ጉባኤ ቀኖናዎች - - - - - - - - ፸፭

ገጽ

የኤፌሶን ጉባኤ ፬፻፴፩ ዓ. ም. - - - - - - - - - - ፸፯
ቢላግዮስ - - - - - - - - - - - - - - - ፸፯
ንስጥሮስ - - - - - - - - - - - - - - - ፸፰
የኤፌሶን ጉባኤ ቀኖናዎች - - - - - - - - - ፹
ኹለተኛው የኤፌሶን ጉባኤ - - - - - - - - - - ፹፫
የአውጣኬ ክሕደት - - - - - - - - - - - - ፹፫


## ምዕራፍ አራት ፤


ምሥጢረ ሥጋዌ - - - - - - - - - - - - ፹፭
መግቢያ - - - - - - - - - - - - - - - - ፹፭
ለምን ሰው ኾነ? - - - - - - - - - - - - - ፹፭
ሰው ኹሉ ኀጢአተኛ ነው - - - - - - - - - - - ፺
የእግዚአብሔር ውሳኔ አለመለወጥ - - - - - - - - ፺፪
እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሐሪ ነው - - - - - - - - ፺፫
ጌታ ከአዳም ኀጢአት ጋር አልተወለደም - - - - - - ፺፬
የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት - - - - - - - - - ፺፯


## ምዕራፍ አምስት ፤


የመድኀኒታችን መለኮታዊ ክብር - - - - - - - - ፻፪

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - - - ፻፪
ለ) እግዚአብሔር ለክብሩ ቀናተኛ ነው - - - - - - ፻፫
ሐ) የነቢያት ምስክርነት - - - - - - - - - - ፻፲
መ) የእግዚአብሔር ስሞችና ክብሩ - - - - - - - ፻፲፭
ሠ) የሃይማኖት ጸሎት - - - - - - - - - - - ፻፲፯
ረ) የመ ክራክሪዎ ጥቅሶችና መልሶቻቸው - - - - - - ፻፳፰

ገጽ

## ምዕራፍ ስድስት ፤


ምሥጢረ ተዋሕዶ - - - - - - - - - ፻፶፪

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - - ፻፶፪
ለ) የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት - - - - - - - ፻፶፪
ሐ) የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት - - - - - - - ፻፶፯
መ) የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል - - - - - - - ፻፶፱


## ምዕራፍ ሰባት ፤


ሥነ ፍጥረት - - - - - - - - - - - ፻፷፫

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - - ፻፷፫
ለ) የስድስቱ ቀን አፈጣጠር - - - - - - - - ፻፷፩
ሐ) የመላእክት አፈጣጠር - - - - - - - - - ፻፷፯
ሊቀ መላእክት - - - - - - - - - - ፻፷፱
መ) የሰው አፈጣጠር - - - - - - - - - - ፻፸፩


## ምዕራፍ ስምንት ፤


የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት - - - - ፻፸፯

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - ፻፸፯
ለ) የትንቢቶች ተፈጻሚነት - - - - - - - ፻፸፰
ሐ) የተቃዋሚዎች አለማስተባበል - - - - - - ፻፸፱
መ) የተቃዋሚዎች ምስክርነት - - - - - - - ፻፹
ሠ) በተቃዋሚዎች ላይ ያገኘው ድል - - - - - - ፻፹
ረ) የጥንታዊ ቅርስ ማስረጃነት - - - - - - - ፻፹፩
ሰ) ለሥነ ምግባር ተፈላጊነቱ - - - - - - - ፻፹፭
ተከራካሪዎች ያልተቀበሉአቸው መጻሕፍት - - - - ፻፹፯
በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የቀረቡ ተቃውሞዎችና የተሰጡ
መልሶች - - - - - - - - - - ፻፺፪




ገጽ

## ምዕራፍ ዘጠኝ ፤


ቤተ ክርስቲያን - - - - - - - - - - - ፻፺፰

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - - - ፻፺፰
ለ) ለምን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሄዳለን? - - - - - ፪፻
ሐ) የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዐት - - - - - - - ፪፻፩
መ) ማማተብና ትርጉሙ - - - - - - - - - ፪፻፫
ሠ) የኅብረት ጸሎት ሥነ ሥርዐት - - - - - - - ፪፻፬
ረ) ዕጣን ፣ መቅደስና መጋረጃ - - - - - - - - ፪፻፮


## ምዕራፍ ዐሥር ፤


ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን - - - - - ፪፻፰

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - - ፪፻፰
ለ) ምሥጢረ ጥምቀት - - - - - - - - - - - ፪፻፱
ሐ) ምሥጢረ ሜሮን - - - - - - - - - - - ፪፻፲፯
መ) ምሥጢረ ቍርባን - - - - - - - - - - - ፪፻፲፰
ሠ) ምሥጢረ ክህነት - - - - - - - - - - - ፪፻፳፯
ረ) ምሥጢረ ንስሐ - - - - - - - - - - - ፪፻፴
ሰ) ምሥጢረ ተክሊል - - - - - - - - - - ፪፻፴፩
ሸ) ምሥጢረ ቀንዲል - - - - - - - - - - ፪፻፴፬


## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ ፤


የሰው ነፍስና ትንሣኤ ሙታን - - - - - - ፪፻፴፯

ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - - ፪፻፴፯
ለ) የሰው ነፍስ - - - - - - - - - - - - ፪፻፴፰
ሐ) ትንሣኤ ሙታን - - - - - - - - - - - ፪፻፵
መ) ዘላለማዊ ፍርድ - - - - - - - - - - - ፪፻፵፫
ሠ) ሺሕ ዓመት - - - - - - - - - - - - ፪፻፵፯

ገጽ

## ምዕራፍ ዐሥራ ኹለት ፤

እምነትና ሕግጋት - - - - - - - - - - ፩፻፶

## ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት ፤

የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ - - - - - - - ፩፻፶፯
ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - - ፩፻፶፯
ለ) የተከራካሪዎች ተቃውሞና የተሰጠው መልስ - - ፩፻፶፯
ሐ) ለኹሉም እንደየሥራው - - - - - - - ፩፻፶፱
መ) የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች - - - - - - ፩፻፷፫

## ምዕራፍ ዐሥራ አራት ፤

የቅዱሳን አማላጅነት - - - - - - - - ፩፻፷፬

## ምዕራፍ ዐሥራ አምስት ፤

ቅድስት ድንግል ማርያም - - - - - - - ፩፻፷፱
ሀ) ድንግልናዋ - - - - - - - - - - ፩፻፷፱
የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት - - - - - - ፩፻፸፱
ለ) የአምላክ እናትነትዋ - - - - - - - - ፩፻፹
የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት - - - - - - ፩፻፹፩
ሐ) ክብርዋ - - - - - - - - - - - ፩፻፹፩

## ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት ፤

ጾምና ጸሎት - - - - - - - - - - - ፩፻፹፬
ሀ) መግቢያ - - - - - - - - - - - ፩፻፹፬
ለ) የጾምና የጸሎት ውጤት ማስረጃዎች - - - - ፩፻፹፯
ሐ) የተከራካሪዎች ተቃውሞና መልሶቻቸው - - - ፩፻፹፱



ገጽ

## ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት ፤

መንፈሳዊ በዓላትና የቀን አቈጣጠር - - - - - ፩፻፺፫
የቃላት ትርጉም - - - - - - - - - - - - ፪፻
የ በዓላትና የአጽዋማት አቈጣጠር - - - - - - - ፪፻፩
ያለተውሳክ የሚገኙ በዓላትና አጽዋማት - - - - - ፪፻፯

## ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት ፤

ጸሎተ ፍትሐት - - - - - - - - - - ፪፻፲፫
የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች - - - - - - ፪፻፲፫
የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ማጠቃለያ - - - ፪፻፲፯
ለጽሑፉ ድጋፍ የኾኑ መጻሕፍት ዝርዝር - - - - - ፪፻፳፩

# መ ቅ ድ ም ፤

ትምህርተ መለኮት ኹለት ዐላማዎች አሉት ። የመጀመሪያው ዐላማ የቤተ ክርስቲያን ደንብንና ሥነ ሥርዐትን አዘጋጅቶ ስለሚያቀርብልን ብዙ መጻሕፍትን ሳናገላብጥ በቀላሉ ተረድተን የቤተ ክርስቲያን ጸሎታችንን እና አገልግሎታችንን በሥርዐት እንድናካኼድ ይረዳናል ። ኹለተኛው ዐላማ ደግሞ በትምህርተ መለኮት አማካይነት እምነታችንና የሃይማኖት ትምህርታችን ማእከላዊነትን ያገኛል ። ማእከላዊነት የሌላት ቤተ ክርስቲያን ጥንካሬዋና ዘላቂነትዋ አስተማማኝ አይኾንም ። በማእከላዊነት የተመሠረተ አንድ የትምህርተ መለኮት መመሪያ ከሌለ የቤተ ክርስቲያን ምሁራንና ካህናት ስለ ሃይማኖት በሚጠየቁበት ጊዜ ለራሳቸው የመሰላቸውን መልስ ስለሚሰጡና የእንዳቸው መልስ ከሌላው ስለሚለይ ቤተ ክርስቲያን የመናፍቃን መሳለቂያ ትኾናለች ። ለቤተ ክርስቲያን ደኅንነትና ጥንካሬ ትምህርተ መለኮትን መመሪያ ማድረግ በጥንታውያኑ አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ የተለመደ ባህል ነው ። ከቤተ ክርስቲያን ቅጽል ስሞች መካከል አንዲት የሚለው ቃል ይገኝበታል ። አንዲት የተባለችውም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንድ ዐይነት እምነት ብቻ እንዲኖራት እንጂ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ኹሉ በየበኩላቸው የመሰላቸውን የእምነት መመሪያ በመመሥረት እንዲለያዩ አልነበረም ፤ ጥንታውያኑ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶችም በየሲኖዶሶቻቸው አማካይነት የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና የደነገጉትና ከሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እምነት ያፈነገጡትን ኹሉ ያወገዙት ምእመናን ኹሉ አንድ ዐይነት እምነት እንዲኖራቸው አስበው እንጂ ያለምክንያት አልነበረም ።

በመጽሐፉ ውስጥ ከተጠቀሱት ጥቅሶች መካከል አንዳንዶቹ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ የማይኾኑበት ጊዜ ይኖራል ፤ ይህ ሊኾን የቻለባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ። የመጀመሪያው ምክንያት አንዳንድ ጥቅሶች ምን ማለታቸው እንደኾነ የአማርኛው ትርጉም ለአንባቢ የማይገባ ስለኾነ እንዲገባ ተደርጎ



በማስተካከል የቀረበ በመኾኑ ነው ። ኹለተኛው ምክንያት አንዳንዶቹ ጥቅሶች ወደ አማርኛው በትክክል ያልተተረጐሙ ስለኾኑ ትርጉሙን ማስተካከል አስፈላጊ ኾኖ በመገኘቱ ነው ። ሦስተኛ ደግሞ በተለየ መጽሐፈ መቃብያንን በሚመለከት የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ መጽሐፈ መቃብያን የሚገኝበት ሲኾን በብዙዎቹ በሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኙት አንደኛና ኹለተኛ መጽሐፈ መቃብያን ብቻ ናቸው ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከመጽሐፈ መቃብያን የተጠቀሱት ጥቅሶች ኹሉ የተወሰዱት አንደኛና ኹለተኛ መጽሐፈ መቃብያን ብቻ ካሉት መጽሐፍ ቅዱስ ስለኾነ ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር አይገናኙም ።

ትምህርተ መለኮትን የሚያኽል ሰፊና ጥልቅ ትምህርት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በአጠቃላይ መልኩ እንጂ በዝርዝር እንዳልቀረበ መታወቅ አለበት ። በዝርዝር ቢቀርብ ኖሮ በዚህ በቀረበው በአንድ መጽሐፍ ብቻ ባልተወሰነም ነበር ። ስለዚህ ሌሎች የሃይማኖት ምሁራን በመንፈሳዊ ቅናት ተነሣሥተው ስፋትና ጥልቀት ያለው የትምህርተ መለኮት ዝግጅት እንደ ሚያቀርቡ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ሙሉ ተስፋ ነው ።

ዓሥራት ገብረ ማርያም

# ምዕራፍ አንድ ፤

## ትምህርተ እግዚአብሔር

### ሀ) መ ግ ቢ ያ ፤

እግዚአብሔር ተብሎ ወደ ግእዝ የተተረጐመው በዕብራይስጡ ቋንቋ ኤል ወይም በብዙ ቁጥር ኤሎሂም የሚለው ቃል ነው ። ኤል ማለት ኀያል ማለት ነው ። ኤልሻዳይ ሲል ደግሞ ኹሉን ቻይ ማለት ነው ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌሎችም የእግዚአብሔር ስሞች ይገኛሉ ። ለምሳሌ ያህዌ ማለት የነበረ ፣ ያለና የሚኖር ማለት ነው ። አዶናይ ማለት ደግሞ ጌታ ማለት ነው ።

እግዚአብሔር የሚለው የግእዝ ቃል ወደ አማርኛ ሲተረጐም የሀገር ወይም የዓለም ጌታ ማለት ነው ።

እግዚአብሔር የሚለውን ቃል ለመወሰን ኹሉም በየቋንቋው ይለያይ እንጂ ፍጥረትን ኹሉ የፈጠረና የየዕለት እንቅስቃሴውን የሚመራ አንድ የማይታይ ትልቅ ኀይል ያለ መኾኑን በማመን በዓለም የሚገኙ ብዙዎቹ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ወገኖች ይስማማሉ ። ይኹን እንጂ ወደ ዝርዝር ኹናቴው በሚገባበት ጊዜ እያንዳንዱ ሃይማኖት የራሱ የኾነ መመሪያና ትምህርት አለው ። በዚህም መሠረት የክርስቲያን ትምህርተ መለኮት ወይም ትምህርት ሃይማኖት (ዶግማ) ስንል ስለ እግዚአብሔር ህልውና ፣ ስለጠባዮቹ ፣ ስለመለኮታዊ አንድነቱ ስለ ሦስትነቱ ፣ ለፍጥረቱ ስለሚያደርገው ጥበቃ (መግቦቱ)፣ ስለልጁ ፣ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ ከሰው ጋር መዛመዱና በአጠቃላይም ለዚህ ኹሉ ትምህርት ምንጭ በኾነው አምላካዊ መጽሐፍ የተገለጸውን ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት የሚመረምር ትምህርት ማለታችን ነው ።



### ለ) የእግዚአብሔር ህልውና ፤

ቀና ብለን ወደላይ ብናይ ጐንበስ ብለን ወደመሬት ብንመለከት ወደ ቀኝና ወደ ግራ ዞር ዞር ብንል — ዘላለማዊ የኹሉም ገዢ ፣ ዐዋቂ ብልኅ ፣ በኹሉም ቦታ የሚገኝና ቦታ የማይወስነው አንድ ኗሪ ለመኖሩ ግልጽ የኾኑ ምልክቶችንና ማስረጃዎችን እናገኛለን ሰማይና ምድር እንዲሁም የእግዚአብሔር ክንዋኔዎች ኹሉ በአንድ ድምፅ ኾነው የፈጠራቸውና ሥነ ሥርዓትን ያስያዛቸው አንድ አምላክ መኖሩን በግልጽ ይመሰክራሉ ።

ቃለ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡ "ወፎችንና እንስሳትን ብትጠይቋቸው ብዙ ሊያስተምሩአችሁ በቻሉ ነበር ። በምድር ላይና በባሕር ውስጥ የሚኖሩትን ፍጥረታት ጥበብ እንዲያስተምሩአችሁ ብትጠይቋቸው ኹሉም እግዚአብሔር እንደሠራቸው ያስረዱአችኋል ። የፍጥረቶቹን ሕይወት የሚመራ እግዚአብሔር ነው ፣ የእያንዳንዱ ሰው ነፍስ በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ነው ።» (ኢዮ. ም ፲፪ ቍ ፯ — ፲)

በተለየ ለእግዚአብሔር ህላዌ ማስረጃነት ከሚቀርቡት አራት መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

አንደኛ/ የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓትና አሠራሩ ፣
ኹለተኛ/ የኅሊና ምስክርነት ፣
ሦስተኛ/ የሰው ልጆች የተፈጥሮ ዝንባሌ ፣
አራተኛ/ የቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ምስክርነት ።

1. <u>የፍጥረቱ ሥነ ሥርዐት</u> ፡ እግዚአብሔር አምላክ የሰው ልጆች እንዲያውቁት ያደረገው በቅዱሳት መጻሕፍቱ አማካይነት ብቻ አይደለም ። የፈለጉትን ለመወሰን ነጻ ፈቃድን ፈቀደላቸው እንጂ በህልውናው እንዲያምኑ አላስገደዳቸውም ። ይኹን እንጂ የጥበበኛነቱንና የኀያልነቱን ምልክቶች እንዲሁም ደግነቱን በሥራው በማሳየት ህልውናውን ገለጸላቸው ።

ዘመናዊው የሳይንስ ዕውቀት የሚሠራቸው መሣሪያዎች አገልግሎታቸውን የሚሰጡት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው ። ከዚያ በኋላ ግን

በእርጅና ወይም በሌሎች ምክንያቶች ይበላሻሉ እንጂ ዘላቂዎች አይደሉም ። የማያረጅ የማይበላሽና የማይለወጥ የፍጥረትን ሥነ ሥርዓት የሚፈጥርና የሚያዘጋጅ ግን ዘላለማዊው ፈጣሪ አምላክ ብቻ ነው ። የሰው ልጅ ዕድሜውም ኾነ ዕውቀቱ ውሱን በመኾኑ ሥራዎቹና ፍልስፍናዎቹም ውሱኖች እንጂ ዘላቂዎች ሊኾኑ አይችሉም ።

የክረምትና የበጋው ፣ የቀንና የሌሊቱ ፣ የብርሃንና የጨለማው ፣ የሙቀትና የብርዱ ፣ የዝናብና የብራው ፣ የልምላሜና የድርቁ ፣ የዘርና የመከሩ ጊዜያት መፈራረቅ እንዴት ጊዜውን ጠብቆና ሥነ ሥርዓትን ተከትሎ የሚካኼድ እንደመኾኑ ይህ ኹናቴ ያለ አንድ የበላይ ጠባቂ እና ተቈጣጣሪ ሊካኼድ የማይችል መኾኑን ያስገነዝበናል ። እንዲሁም የሰው ልጅ አፈጣጠር ፡ — አወላለዱ ፣ አስተዳደጉ ፣ የሰውነት ክፍሎቹ ሥነ ሥርዓት ማለት በእግሩ ለመራመድና ለመኼድ ፣ በእጁ ለመዳሰስ ፣ ለመያዝና ለመሥራት ፣ በዐይኑ ለማየት ፣ በጆሮው ለመስማት ፣ በአንደበቱ ለመናገርና ለመቅመስ ፣ በአፉና በጥርሱ ለመብላትና ለመጠጣት ፣ በአፍንጫው ለማሽተት እንዲችል ኾኖ መፈጠሩ የእግዚአብሔርን ያፈጣጠር ሥነ ሥርዓት ያሳየናል ።

የአፈጣጠሩ ድንቅነትና የማይዛባ የተፈጥሮ ሥነ ሥርዓት የሚያመለክቱት የእግዚአብሔርን ክብር ለመኾኑ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር ፲፱ ቍ. ፩ ላይ “ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ፤ የሰማይ ጠፈሮችም የእግዚአብሔርን ሥራ ያውጃሉ » በማለት አድናቆቱን ገልጾአል ። እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፩ ቍ. ፳ ላይ ፣ «ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለሰዎች የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና አምላክነቱ እርሱ በፈጠራቸው ነገሮች ግልጽ ኾኖ ታይቶአል» በማለት ፍጥረቶች እንዴት ስለ እግዚአብሔር ህላዌ ማስረጃ እንደ ኾኑ ይገልጻል ።

2. የኅሊና ምስክርነት ፤ ኅሊና ማለት በሰውነት ውስጥ የሚገኝ ግብረገባዊ የኾነ የስሜቶች አባል ነው ። ለምሳሌ ከሰውነታችን የአካል ክፍሎች አንዱ የኾነው ዐይናችን አንዱን ነገር ከሌላው የመለየት ችሎታ ያለውን ያኽል እንዲሁም ኅሊናችን ክፉና ደግ አድራጎቶችን የመለየት ችሎታ አለው ። ይህም በመኾኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ላላነበበ ሰው እንኳ ቢኾን ኅሊናው የእግዚአብሔርን ህላዌ



ይገልጽለታል ማለት ነው ። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም ፪ ቍ. ፲፬ እና ፲፭ ላይ የሚቀጥለውን ማረጋገጫ የሰጠው ፣ «የሙሴ ሕግ የሌላቸው አረማውያን በተፈጥሮአቸው ሕግ የሚያዝዘውን ነገር ይፈጽማሉ ። በዚህም ምክንያት የሙሴ ሕግ ባይኖራቸውም የራሳቸው የተፈጥሮ ሕግ ስላላቸው ማድረግ የሚገባቸውን ያውቃሉ ። ይህም ኹኔታቸው የሙሴ ሕግ የሚአዝዘው ነገር ኹሉ በልባቸው የተጻፈ መኾኑን ያሳያል ። ደግሞም ኅሊናቸው ይመሰክርባቸዋል ። ምክንያቱም ኅሊናቸው አንዳንዴ ይወቅሳቸዋል ፤ አንዳንዴም ይደግፋቸዋል ።»

ለሰው ኹሉ እንደየሥራው ዋጋውን የሚከፍለውና እንዲሁም የሰውን ኹሉ ጸሎት ሰምቶ ተገቢውን መልስ የሚሰጥ አንድ አምላክ መኖሩንና ከሞት በኋላ ሌላ ሕይወት መኖሩን አምኖ መኖር ደግሞ ለኅሊና ዕረፍትንና ሰላምን ይሰጣል ። ስለዚህ ነው ጌታ «ልባችሁ አይጨነቅ ፣ በእግዚአብሔር እመኑ ፣ በእኔም እመኑ » ያለው ። (ዮሐ. ም. ፲፬ ቍ. ፩)

በእግዚአብሔር ከሚያምኑት ሰዎች የማያምኑት ሰዎች ይልቅ ጭንቀት ያጠቃቸዋል ከሞት በኋላ ሌላ ሕይወት ስለማይጠብቁ ሞትን በጣም ይፈሩታል ። ይኹን እንጂ ብዙዎች በእግዚአብሔር የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሔርን ቅር የሚያሰኝ ሥራ ቢሠሩ በጽሑፍ የቀረበላቸው የሃይማኖት ሕግ አይኑራቸው እንጂ በሰውነታቸው ውስጥ የሚገኘው የተፈጥሮ ዳኛ ማለት ኅሊናቸው እየፈረደባቸው ሲያስጨንቃቸው ይኖራል ። ለዚህም የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት ።

አንጥያኮስ የተባለው ንጉሥ የመሞቻው ጊዜ መቃረቡን ስለ ጠረጠረ ቤተሰቡንና ባለሟሎቹን ጠርቶ «ከዐይኖቼ እንቅልፍ እየጠፋና ልቤም እየደነገጠ ብኝ ነው ። በሥልጣን ዘመኔ በጣም ቸርና ተወዳጅ የነበርኩት እኔ ለምን አሁን እንዲህ ያለ ታላቅ ጭንቅ ተ ደረሰብኝ ብዬ ራሴን በጠየቅሁት ጊዜ በኢየሩሳሌም ላይ የፈጸምኩትን በደል ማስታወስ ጀመርኩ ። የብሩንና የወርቁን ዕቃዎች የወሰድሁትና የይሁዳ ሕዝብም እንዲፈጅ ትእዛዝ ያስተላለፍኩት ያለምንም ምክንያት ነበር ። ዩህ አሁን በባዕድ ሀገርና በጭንቀት የመሞት ዕድለቢስነት ያጋጠመኝ በፈጸምኩት በደል ምክንያት ለመኾኑ እርግጠኛ ነኝ» በማለት ኑዛዜውን ያሰማ መኾኑን በአንደኛ መጽሐፈ መቃ

ብያን ም. ፪ ቁ. ፲-፲፫ እንመልከት ። ምንም እንኳን ይህ ንጉሥ በጽሑፍ ላይ የሰፈረ የሃይማኖት ሕግ ባይኖረው የሰውን ክፉ ሥራ የሚበቀል አንድ ትልቅ ኀይል ያለ መኾኑን በማሳወቅ የተፈጥሮው ሕግ ወይም የተፈጥሮው ዳኛ ማለት ኅሊናው እንደገለጸለት ልንረዳ እንችላለን ።

3. <u>የሰው ልጆች የተፈጥሮ ዝንባሌ</u> ፤ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኝ ሰው ኹሉ እርዳታውና ጥበቃው የሚፈለግ ፍጹምነትን የተመላ ፥ ደግ ፥ ኹሉን ቻይ ፡ ሰውን የሚወድ ፥ ሊወደድና ሊሰገድለት የሚገባ አንድ አምላክ ያለ መኾኑን ይስማሙበታል ። ዓለምን የዞሩ ሰዎች እንደመሰከሩት ይህ በሰው ልጆች ዘንድ ያለው የእምነት ዝንባሌና ስሜት ለሕይወት አስፈላጊ ከኾኑት ከሌሎቹ የተፈጥሮ ፍላጎቶች ምንም ልዩነት የሌለው ኾኖ እናገኘዋለን ። ይህም ማለት የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መኖር የሚያምነው በጽሑፍ የቀረበለትን የሃይማኖት መጽሐፍ በማንበብ ወይም የሃይማኖት አስተማሪ ስለ ሚሰብክለት ብቻ ሳይኾን የተፈጥሮ ስሜቱ ፡ ፍላጎቱ ወይም ዝንባሌው ስለሚገፋፋውም ጭምር ነው ። ይህንኑ የሰውን ልጅ ሃይማኖታዊ ዝንባሌ በመጠቀም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በአቴና ከተማ ውስጥ በሚገኝ በአንድ የአምልኮ ቦታ ለማይታወቅ አምላክ ተብሎ ተጽፎ ያገኘውን ጽሑፍ መነሻ በማድረግ አርዮስፋጎስ በተባለው ስፍራ የክርስትናን ሃይማኖት ለመስበክና አንዳንድ ሰዎችን ለማሳመን የበቃው ። (የሐ. ሥ. ም. ፲፯ ቁ. ፳፪-፴፩

4. <u>የቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ምስክርነት</u> ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ልዩ ትንቢቶች ተነግረው እነዚያም የተነገሩት ትንቢቶች በየጊዜያቸው የተፈጸሙ መኾናቸው በታሪክም ጭምር የተረጋገጠ ነው ። ወደፊት የሚደርሰውን ኹናቴ አስቀድመው እንዲናገሩ በልዩ ልዩ መንገድ ለነቢያት የገለጸላቸው እግዚአብሔር ነው ። በልዩ ልዩ ጊዜያት ለተለያዩ ነቢያት ወደ ፊት የሚኾነውን ኹናቴ የገለጸላቸው እግዚአብሔር የነበረ ፡ ያለና የሚኖር ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስም ስለ እግዚአብሔር ህልውና ካረጋገጠባቸው ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት ።

ኃጢአተኛ ስለ እግዚአብሔር ግድ የለውም በትዕቢቱም እግዚአብሔር የለም ብሎ ያስባል ።» (መዝ ፲ ቁ. ፬)



«ሞኝ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል ።» (መዝ. ፲፬ ቁ. ፩)

«በሚታዩት መልካም ነገሮች አማካይነት ፡ እግዚአብሔርን ሊያውቁና ማንነቱንም ሊረዱ ያልቻሉ ወይም ሥራውን በማጥናት ሠሪውን ለማወቅ ያቃታቸው ፤ ሰዎች ኹሉ በተፈጥሮአቸው የአእምሮ ብስለት የጐደላቸው ናቸው ። (ጥ. ሰ. ም. ፲፫ ቁ. ፩)

ሐ) <u>የእግዚአብሔር ጠባዮች</u> ፤

እግዚአብሔር ከማንኛውም ሌላ ኹናቴ የተለየና የላቀ በመኾኑ የእርሱን መልክ ለመግለጽ አይቻልም ። ከአስተሳሰባችንና ከችሎታችን በላይ ነው ። ለእግዚአብሔር ምሳሌነት ብቁ የሚኾን ምንም ነገር የለም ። በመለኮታዊ ክብሩ ለዘላለም በራሱ የሚኖር ነው ። ኹሉን ነገር የሚሰጥ እርሱ እንደመኾኑ ከማንም ምንም አይፈልግም ። መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ ነው ። በኹሉም ቦታ የሚገኝ ሙሉ ነው ።

ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ጠባዮች ከሰው ልጆች ኹናቴ የተለዩ ቢኾኑ ለጊዜው እኛ በሚገባን ቋንቋ ለመግለጽ በእግዚአብብሔር መንፈስነት ፡ ዘላለማዊነት ፡ ኹሉን ቻይነት ፡ አለመለወጥ ፡ ምሉእነት ፡ መለኮታዊ ጥበቃው ፡ ዐዋቂነቱና ጥበቡ ፡ ቅዱስነቱ ፡ ደግነቱና የማንንም እርዳታ አለመፈለጉ በሚሉት አርእስት ይከፋፈላሉ ።

1. <u>የእግዚአብሔር መንፈስነት</u> ፡ እግዚአብሔር መንፈስ በመኾኑ በሕዋሳታችን አማካይነት ልናውቀው አንችልም ። ልዑል አምላካችን መንፈስ እንጂ ግዙፍ አካል ያለው ወይም የአንድ ነገር አንድ ክፍል ወይም ኹሉም አይደለም ። መቀላቀል ወይም መደባለቅ ፡ መዋሐድ ወይም መበታተን የለበትም ። የሰውነት አካል ወይም መልክ እኛ በሚገባን ዐይነት የሌለውና በዐይንም የማይታይ በመኾኑ ለግዙፍ ወይም ለቁስ አካል መግለጫ የሚኾኑት እንደመጠን ትልቅነትና እንደ ሚዛን ክብደት የመሳሰሉትን መግለጫዎች ለእግዚአብሔር መግለጫ ማድረግ አግባብ አይደለም ። ከፍጥረቱ መካከል ምንም ለእርሱ ምሳሌ የሚኾን ነገር የለም ። ስለዚህ ነው ቃለ እግዚአብሔር «እግዚአብሔርን ከማን ጋር ታነጻጽሩታላችሁ? ከማንስ ጋር ታመሳስሉታላችሁ?» በማለት እግዚአብሔርን የሚመስል ነገር እንደሌለ ያረጋገጠው ። (ኢሳ. ም. ፵ ቁ. ፲፰

እንዲሁም የእግዚአብሔርን መንፈስነት የሚመሰክሩ ኹለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንመልከት ።

«እግዚአብሔር መንፈስ ነው ፤ በእውነት የሚሰግዱለትም በመንፈስ ሊሰዱለት ይገባቸዋል ።» (ዮሐ. ም. ፬ ቍ. ፳፬

«ጌታ መንፈስ ነው የጌታም መንፈስ ባለበት ነጻነት አለ ።» (፪ኛ ቆሮ ም ፫ ቍ. ፲፯)

2. <u>የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት</u> ፤ እግዚአብሔር በዘመናት የሚቈጠር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ ነው ። ቀድሞ የነበረ ፥ አሁንም ያለና ወደ ፊትም የሚኖር ነው ። «በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺ ዓመት ሺ ዓመትም እንደ አንድ ቀን ነው ።» (፪ኛ ጴጥ. ም. ፫ ቍ. ፰)

ለእግዚአብሔር ዘላለማዊነት ከሚቀርቡት ማስረጃዎች መካከል በዚህ ዓለም ላይ ምንም ዘላለማዊ ፍጡር አለመኖሩን የሚገልጸው የሳይንስ አባባልና የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ናቸው ።

የዘመናዊው ሳይንስ ጥናትና ምርምር እርሱም የመሬት ጥንታዊ ኹናቴ ጥናት (ጂኦሎጂ) እንዳረጋገጠው ዓለም አሁን ባለበት ኹናቴ ኹልጊዜ የነበረ አይደለም ። ሕይወት አዲስ ነገር ነው ። አሁን ያለው የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓት በአንድ ጊዜ የተገኘ ሳይኾን ከአንድ ኹናቴ ወደሌላ ኹናቴ በመለወጥ የተገኘ ነው ። መሬት አንድ ጊዜ ምንም ሕያው የኾነ ፍጡር አይታይባትም ነበር ። ሜዳዎችዋም ከአትክልትና ከአዝርዕት ጌጥ የተራቈቱ ነበሩ ። ምንም የእንሰሳትና የአራዊት ድምፅ የማይሰማበት ጸጥታ ነበር ። ተራሮችና ሸለቆዎችም አልነበሩባትም ። ከዚያ በኋላ በመሬት ላይ ውሃ የተከማቸባቸው ባሕሮችና ጕድጓዳ ሥፍራዎች መታየት ጀመሩ ። ቀጥሎ ደግሞ ዓሣዎች ወፎችና እንስሳት መታየት ጀመሩ ። የሰው ልጅ ዱካ የተገኘው ግን በመጨረሻ ላይ ነው ።

እነዚህ የጂኦሎጂ አባባሎች ከእግዚአብሔር በቀር ዘላለማዊ ነገር አለመኖሩንና ግኝቶቹም የተከሠቱት በየጊዜው እንጂ በአንድ ጊዜ አለመኾኑን ሲያመለክቱ ፥ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ላይ የተዘረዘረውን የፍጥረትን ታሪክ ማረጋገጣቸው ነው ።



ለእግዚአብሔር ዘላለማዊነት ሌላው ማስረጃ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ። ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት ።

«ተራራዎችን ከመሥራትህና ዓለምንም ከመፍጠርህ በፊት የዘላለም አምላክ ነህ ፤ ከእንግዲህ ወዲህም የዘላለም አምላክ እንደ ኾንክ ትኖራለህ ። (መዝ ፺ ቍ. ፪)

«አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማዮትም የእጅህ ሥራ ናቸው ፥ እነርሱ ይጠፋሉ ፥ አንተ ግን ትኖራለህ ፤ ኹላቸውም እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ ፤ ይለወጡማል ፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም ።» (መዝ ፻፪ ቍ. ፳፭-፳፯)

«መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት ፥ ግዛት ህም ለልጅ ልጅ ነው ።» (መዝ ፻፵፭ ቍ. ፲፫)

«የእስራኤል ንጉሥና አዳኝ የኾነ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፤ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም እኔ ነኝ ፤ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም ።» (ኢሳ ም ፵፬ ቍ. ፮)

«ያለው፥የነበረው፥የሚመጣውም ኹሉን የሚችል እግዚአብሔር አልፋና ዖሜጋ ፥ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ ይላል ።» (ራ. ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፰)

3. <u>የእግዚአብሔር ኹሉን ቻይነት</u> ፥ ሕጸጽን ወይም ደካማነትን በማመልከታቸው የማይፈቅዳቸው ካልኾነ በቀር ለእግዚአብሔር ምንም የሚሳነው ነገር የለም ። ኀያልነቱ ማንም የማይቃወመው ፥ ሥልጣኑም ከኹሉ በላይ ነው ። በፈቃዱ መሠረት እርሱ የፈለገውን ነገር ያደርጋል እንጂ የማንንም እርዳታ ወይም ምክር አይጠይቅም ይህም የሚኾንበት ምክንያት ኀያልነቱ ከወሰን በላይና ታላቅነቱም ከኹሉም በላይ ስለኾነ ነው ። በአድራጎቱ ፥ በትእዛዙና በፍርዱ ማንም ሊቃወመው አይችልም ። ምንም ዐይነት ሥራ በሚሠራበት ጊዜ ሐሳብ አቅርቦለት ወይም ምክር ሰጥቶት ሊሠራ ያቀደውን ሊያስለውጠው የሚችል የለም ።

የእግዚአብሔርን ልዕልና ከሰው ልጅ ከንቱነት ጋር ሲያወዳድር ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሏል ፤ «እነሆ አሕዛብ በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው ፤ በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ ተቈጥረዋል ። አሕዛብ ኹሉ በፊቱ እንዳልነበሩ ናቸው ፤ ከምናምን እንደሚያንሱ እንደ ከንቱ ነገርም ይቈጥራቸዋል ።» (ኢሳ. ም. ፵ ቁ. ፲፭ እና ፲፯

በሰው ዘንድ ምንም የማይቻል መስሎ የሚገመተው የተፈጥሮ ሕግ ኺደት በእግዚአብሔር ዘንድ አስፈላጊ ኾኖ በሚገኝበት ጊዜ የሚለውጠው መኾኑን ለመረዳት የሚከተሉትን ምሳሌዎች እን መልከት ።



«ሙሴም እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ እግዚአብሔርም ግብጻውያንን በባሕሩ መካከል ጣላቸው ።» (ዘፀ. ም. ፲፬ ቁ. ፳፯)

የመጀመሪያው ምሳሌ እስራኤላውያን ከምድረ ግብጽ ከወጡ በኋላ ከሚያሳድዱአቸው ከግብጻውያን ለማዳን ብሎ ባሕሩን ለኹለት በመክፈል እንደ ግድግዳ አቁሞላቸው ካለፉ በኋላ ግብጾችን ግን ያሰጠ ማቸው መኾኑን በኦሪት ዘፀአት ም. ፲፬ ቁ. ፳፩-፳፱ እንመልከት ።




ኹለተኛው ምሳሌ ፡ አናንያ ፡ ሚሳኤልና አዛርያ የተባሉ ሦስት አይሁዳውያን ወጣቶች በአምልኮ ጣዖት ላለመርከስና በፈጣሪአቸው አምነትና አምልኮት ጸንተው ለመኖር በወሰኑ ጊዜ በናቡከደነፆር ትእዛዝ በሚነድድ እሳት ውስጥ ቢጣሉም የእሳቱ ነበልባል ኀይለኛ ከመኾኑ የተነሣ እነርሱን ወደ እሳቱ ውስጥ የጣሉአቸውን አቃጥሎ ሲገድል እነርሱ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ቃጠሎ ሳያደርስባቸው ከእሳቱው ውስጥ ወጥተዋል ። (ዳን. ም. ፫ ቁ. ፲፱-፳፯



«ንጉሡም እነሆ እኔ እሳቱ ምንም ሳይጐዳቸው ከእስራት ተፈትተው በነበልባሉ ውስጥ የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ ፤ አራተኛውም የአማልክትን ልጅ ይመስላል አለ ።» (ዳን ም. ፫ ቁ. ፳፭)

ሦስተኛው ምሳሌ ፡ አብርሃምና ሣራ እንዲሁም ዘካርያስና ኤልሣቤጥ ልጅ የመውለጃ ዕድሜአቸው ካለፈ በኋላ በስተእርጅና እን ዲወልዱ ተደርገዋል ። (ዘፍ ም. ፳፩ ቁ. ፪ ፤ ሉቃ. ም. ፩ ቁ. ፲፫

<u>አራተኛ ምሳሌ</u>፡ በትንቢተ ኢሳይያስም ፴፰ ቁ. ፰ ላይ በእግዚአብሔር ፈቃድና ውሳኔ መሠረት የፀሐይ ጥላ ዐሥር ወደኋላ እርምጃ እንዲመለስ መደረጉ ተገልጾአል ።



«መልአኩም እንዲህ አለው ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ ፡ ሚስትህ ኤልሣቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ፡ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ።» (ሉቃ ም. ፩ ቁ. ፲፫)

የእግዚአብሔርን ኹሉን ቻይነት ከሚያመለክቱት ማስረጃዎች መካከል ዓለምን ከምንም ፈጥሮ ከመጥፋትና ከመሟሸሽ መጠበቁ ማለት ሕይወት ላለውና ሕይወት ለሌለው ፍጥረት ኹሉ ጥንቃቄ ማድረጉና እንዲሁም የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ይገኙባቸዋል ።

«ከቶ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?» (ዘፍ. ም. ፲፰ ቁ. ፲፬



«በሰማይና በምድር እንዲሁም በባሕርና በጥልቆች እግዚአብ ብሔር የፈቀደውን ኹሉ አደረገ ። (መዝ ፻፴፭ ቁ. ፮)

«አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፡ እነሆ አንተ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኀይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል ፡ ለአንተም የሚሳንህ ነገር የለም ። (ኤር ም. ፴፪ ቁ. ፲፯

«ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ኹሉ ይቻላል ።» (ማቴ. ም. ፲፱ ቁ. ፳፮

«ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ።» (ሉቃ ም. ፩ ቁ. ፴፯

4. <u>የእግዚአብሔር አለመለወጥ</u>፡ ተወዳዳሪ የሌለው ፍጹም በመኾኑና ከዚያ የበለጠ ፍጹምነት ሊኖር ስለማይችል የበለጠ ፍጹም ለመኾን አይለወጥም ። አሁን ካለው ደግነት ፡ መሐሪነት ፡ ትክክለኛ ፍርድ ፈራጅነት ፡ ቅዱስነት ፡ ዐዋቂነት ፡ ብልኀነትና ኀያልነት ፡ አይጨምርም ወይም አይቀንስም ። ፍርዱም በጊዜና በኹናቴ የሊተወሰነ በመኾኑ ሐሳቡን መለወጥና ውሳኔውን ማሻሻል አያስፈልገውም ።

እግዚአብሔር በውሳኔው የሚጸናና የማይለወጥ ከኾነ ለምን ታዲያ በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ትሞታለህ ብሎ ካስጠነቀቀው በኋላ ተመልሶ በዕድሜው ላይ ዐሥራ አምስት ዓመቶች ጨመረለት ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል። (ኢሳ.ም. ፴፰ ቁ. ፩-፭) ንጉሥ ሕዝቅያስ ራሱን ዝቅ አድርጎ ጸሎቱን ለእግዚአብሔር የሚያቀርብ ቢኾን በዕድሜው ላይ ዐሥራ አምስት ዓመቶች እንዲጨመርለት በእግዚአብሔር ዘንድ ቀድሞ ተብሎ የተሰጠ ዘላለማዊ ውሳኔ ነው እንጂ ሐሳቡን የለወጠ ኾኖ አይደለም ። ንጉሥ ሕዝቅያስም ምርር ባለ ለቅሶ ስለጸለየ የተወሰነው የዐሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ ተጨምሮለታል ።

በትንቢተ ዮናስ ም. ፫ ቁ. ፲ ላይ የነነዌ ከተማ ሰዎች ከክፉ ሥራቸው እንደተመለሱ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገባቸውም ማለቱ የእግዚአብሔር ሐሳብ የሚለወጥ መኾኑን ለማሳየት አይደለም ። ከክፉ ሥራቸው ንስሐ

በመግባት የተለወጡት የነነዌ ከተማ ሰዎች ናቸው እንጂ የእግዚአብሔር ውሳኔ አይደለም ። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ነጻ ፈቃድን ስለሰጠው በጎ ተግባርን መርጦ በደግ መንገድ ከኼደ ደኅንነት የሚጠበቀው ሲኾን የጥፋትን መንገድ ከተከተለ ደግሞ ጥፋት ይጠብቀዋል ። ኹሉም ይድን ዘንድ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ፈቃዱ በመኾኑ እግዚአብሔር ለነነዌ ከተማ ሰዎች ነቢዩን ዮናስን በመላኩ ንስሐ ገብተው ከጥፋት ለመዳን በቅተዋል።ንስሐ ለሚገባ ይቅርታን፣ለሚበድልና በዚያው በበደሉ ለመኖር ለሚፈልግ ሰው ደግሞ ቅጣትን ማዘጋጀቱ የማይለወጠው የእግዚአብሔር ጠባይ ነው ። የነነዌ ከተማ ሕዝብም በኀጢአተኛነቱ ቢቀጥል ኖሮ ጥፋት ይጠብቀው የነበረ ሲኾን ንስሐ በመግባቱ ግን ሊድን ችሏል ። ተጸጸተ የተባለው ለሰው ልጅ በሚገባ ቋንቋ ለመነገር ስለተፈለገ ነው እንጂ እግዚአብሔር የሚጸጸት ኾኖ አይደለም ። ወደፊት የሚኾነውን ማንኛውንም ኹናቴ አስቀድሞ የማያውቅ እንደመኾኑ አይጸጸትም ።

እግዚአብሔር የማይለወጥና የማይጸጸት መኾኑን ከሚያረጋግጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም ፡ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም ።» (ዘኁ. ም. ፳፫ ቊ. ፲፱)

«የእስራኤል ክብር እንደሰው የሚጸጸት አይደለም ።» (፩ኛ ሳሙ. ም. ፲፭ ቊ. ፳፱)

«እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም (ሚልም . ፫ ቊ. ፮)

«ሰማይና ምድር ያልፋል ፥ ቃሌ ግን አያልፍም ።» (ማቴ. ም. ፳፬ ቊ. ፴፭)

«እግዚአብሔር ከመረጠና ጸጋውን ከሰጠ በኋላ ባረገው ነገርደ አይጸጸትም ። (ሮሜ ም. ፲፩ ቊ. ፳፱

5. <u>የእግዚአብሔር ምሉእነት</u> ፥ ልዑል እግዚአብሔር በኹሉም ቦታ ፥ በሰማይና በምድር ከዘላለም እስከ ዘላለም የኖረና የሚኖር ነው ። ነዋሪነቱም በአንዲት በተወሰነች ቦታ ብቻ አይደለም ። እግዚአብሔር የሚከፋፈልና የሚበታተን ሳይኾን በኹሉም ቦታ መኖሩ ተመሳሳይ



የሌለው ኹናቴ ነው።ይህ በኹሉም ቦታ መገኘቱ እንደ ብርሃንና እንደ ነፋስ መለኮቱ እየተሰፋፋ አንዱ ክፍል አንድ ቦታ ሌላው ክፍል ደግሞ ሌላ ቦታ እንደመገኘት ያለ አይደለም ። እግዚአብሔር የሚከፋፈልና የሚበታተን አካል ያለው አይደለም።ነገር ግን በፍጹም መለኮቱ እሱው ራሱ በኹሉም ቦታ ይገኛል ። የእግዚአብሔር በኹሉም ቦታ መገኘት ነፍስ በሰውነት ክፍል ኹሉ ከመገኘትዋ ጋር ተመሳሳይ ነው ።

የእግዚአብሔርን በኹሉ ቦታ መገኘት በሚመለከት ባትንቢተ ኤርምያስ ም. ፳፫ ቊ. ፳፫-፳፬ ላይ የተገለጸውን እንመልከት ።

«እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም፤ሰው በስውር ቢሸሸግ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የመላሁ አይደለሁምን ? ይላል ጌታ እግዚአብሔር ።»

6. <u>መለኮታዊ ጥበቃው</u> ፥ በእርሱ ፈቃድ ፥ በእርሱ ትእዛዝ ወይም በእርሱ ጥበቃ ካልኾነ በቀር ትልቅም ኾነ ትንሽ ድርጊት አይኾንም ፥ አይደረግም ወይም አይደርስም ። በከሃሊነቱና በጥበቡ አማካይነት በማንኛውም ቦታ የሚደርሱትን ድርጊቶች የሚያዘጋጅ እርሱ ነው ። በአጋጣሚ ፥ በዕድል ፥ በስምምነት ፥ ወይም በግዴታ ተደረጉ የሚባሉት አነጋገሮች ትክክል አይደሉም ። እርሱ በጥበቡ ሕይወት ባለውም ኾነ ሕይወት በሌላው ፍጥረት አማካይነት ድርጊትንና እንቅስቃሴን ያዘጋጃል ። ጥበቃ የማያስፈልገው ትንሽ ነገር መስሎ የሚታየን ጉዳይ እንኳን በእርሱ ዘንድ ጥበቃ ይደረግለታል ። ስለዚህ ነው መድኃኒታችን ፥ «የእናንተ ግን የራስ ፀጕራችሁ እንኳ የተቈጠረ ነው ።» ብሎ ያረጋገጠው ። (ማቴ. ም. ፲ ቊ. ፴)

በእግዚአብሔር የማያምኑ ነገሥታትና ሊዑላን በሥልጣኑ ሥር ናቸው ። በእነርሱ አማካይነት የሚደረግ ማንኛውም ደግ ድርጊት በእርሱ ትእዛዝ የሚደረግ ሲኾን ክፉ ድርጊትም ከኾነ ያለ እርሱ ፈቃድ አይደረግም ። ለምሳሌ ሰይጣን በኢዮብ ላይ እጁን ለመዘርጋት የቻለው እግዚአብሔር ከፈቀደለት በኋላ ብቻ ነው (ኢዮ. ም. ፩ ቊ. ፲፪ ።) ኢዮብ ለእግዚአብሔር ያለው ታማኝነት ተረጋግጦ የጠፋበት ኹሉና ጤንነቱ ከተመለሰለት በኋላ ግን ሰይጣን ምንም ለማድረግ አልደፈረም ፥ ምክንያቱም አልተፈቀደለትምና ።

አንዳንድ በሰዎች ላይ የሚደርሱ ክፉ ኩነቴዎች በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚደርሱበት ምክንያት እግዜአብሔር የራሱ የኾነ ዕቅድ ስላለው ነው ። ለምሳሌ በወንድሞቹ እጅ ወደ ጉድጓድ ውስጥ የተጣለውን በኋላም የተሸጠውንና ቀጥሎም በሰይጣን ተገፋፍታ ለጥፋቱ በተሰለፈችለት ሴት እማካይነት ባልፈጸመው ወንጀል በእስር ቤት ለብዙ ጊዜ እንዲያሳልፍ የተደረገውን የዮሴፍን ታሪክ እናስተውል ። በወንድሞቹ ተጠልቶ ጉድጓድ ውስጥ መጣል ፣ ከዚያም እንደ ባሪያ መሸጥና በተወሰደበት አገርም በሐሰት ክስ መታሰርን የመሳሰሉት ችግሮች ከደረሱበት በኋላ እግዚአብሔር እነዚያን ኹሉ ኩነቴዎች ለውጦ ከንጉሡ ቀጥሎ ባለ ኹለተኛ ማዕረግ የግብጽ ገዢ ያደረገው ብቻ ሳይኾን ለግብጽ ሕዝብ እንዲሁም ለአባቱና ለወንድሞቹ ኹሉ የረኀብ መድኀኒት ያደረገው መኾኑን በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ እስከ አርባ አምስት እንመልከት ።

አንድ መርሳት የሌለብን ጉዳይ ግን የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ እንዲሁም ፈቃዱና ዝግጅቱ የሰውን ልጅ ነጻ ፈቃድ የማይቃረን መኾኑን ነው ። ይህማ ባይኾን ኖሮ የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ባልጠፉም ነበር ፣ የነነዌም ሰዎች ባልዳኑም ነበር ። (ዘፍ. ም. ፲፱ ቁ. ፳፫-፳፰ ፣ ዮና. ም ፩ — ፬)

7. <u>የእግዚአብሔር ዐዋቂነቱና ጥበቡ</u> ፤ እግዚአብሔር በኹሉም ቦታ የሚገኝ እንደመኾኑ በሰማይና በምድር ሙሉ ነው ። እርሱም የማይለወጥና በመለኮቱም ውሱን ያልኾነ ነው ። ለዐዋቂነቱም ውሱንነት የለውም ። ይህንኑ እውነት ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጸው እንዲህ ብሏል ። «እግዚአብሔር በጥበብና በዕውቀት ምንኛ ባለጸጋ ነው ! ፍርዱና መንገዱስ ተመርምሮ ለመታወቅ የማይቻል ምንኛ ጥልቀት አለው ።» (ሮሜ. ም. ፲፩ ቁ. ፴፫)

የእግዚአብሔርም ዐዋቂነት የራሱ ጠባይ እንጂ በትምህርት ወይም በጥናት ከሌላ የተወሰደ አይደለም ። ስለዚህ ነው ጌታን በተራ ሰውነቱ እንጂ በአምላክነቱ የማያውቁት አይሁዳውያን በትምህርቱ ተደንቀው ይህ ሰው ሳይማር እንዴት ይህን ኹሉ ሊያውቅ ቻለ ብለው ላቀረቡት አስተያየት መልስ ሲሰጣቸው እንዲህ ያለው ፦ «የእኔ ትምህርት ከላከኝ ከአብ የተገኘ ነው ፣ እንጂ ከእኔ አይደለም ። የላከኝን ፈቃድ



ማድረግ የሚፈልግ ቢኖር ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር የተገኘ ወይም እኔ ከራሴ የተናገርኹ መኾኔን ለይቶ ያውቃል ።» (ዮሐ. ም. ፯ ቁ. ፲፮-፲፯)

የተፈጸሙትም ኾኑ የሚፈጸሙት ክንዋኔዎች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይፈጸማሉ እንጂ የሚታረሙ ወይም የሚሻሻሉ አይደሉም ። ያለፈውም ኾነ ወደ ፊት የሚኾነው ድርጊት በአሁኑ ጊዜ እንዳለ ኹናቴ ነው እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለፈው የሚረሳና ወደፊት የሚኾነው ኹናቴ ደግሞ የማይታወቅ አይደለም ። የእግዚአብሔር ዕውቀትም ያልተወሰነ ነው እንጂ ታላቅ ወይም ታናሽ ድርጊት ነው ተብሎ የተለያየ ግምት የሚሰጠው አይደለም ። ስለዚህ ነው ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም. ፬ ቁ. ፲፫ ላይ «እኛን በሚቈጣጠር በእርሱ ዐይኖች ፊት ኹሉ ነገር የተራቈተና የተገለጸ ነው እንጂ ከእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» የተባለው ። ነቢዩ ዳዊትም እንዲህ ብሏል «እግዚአብሔር አያዩም የያዕቆብ አምላክ አያመለከትም አሉ ፤ እናንተ የማይገባችሁ ሞኞች ይህንን አስተውሉና ይግባችሁ ፣ ጆሮን የተከለው አይሰማምን? ዐይንን የሠራው አያይምን?» (መዝ. ፺፬ ቁ. ፯-፱)

የሚከተሉት ጥቅሶች የእግዚአብሔርን ዐዋቂነት የሚቃረኑ መስለውን ሊያስናክሉን አይገባም ።

«እግዚአብሔር የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ ።» (ዘፍ. ም. ፲፩ ቁ. ፭)

««እግዚአብሔርም አለ ፣ የሰዶምና የገሞራ ጩኸት እጅግ በዝቶአልና ፣ ኀጢአታቸውም እጅግ ከብዷልችና ፣ ስለ እነርሱ የሰማሁት ነገር ኹሉ እውነት መኾኑን ለማረጋገጥ ወደ እነርሱ እወርዳለሁ ።» (ዘፍ. ም. ፲፰ ቁ. ፳-፳፩)

«ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው ።» (ዘፍ. ም. ፳፪ ቁ. ፩)

ከላይ የቀረቡትን ጥቅሶች ትክ ብለን ካላስተዋልናቸው እግዚአብሔር ፍጹም የኾነ ዕውቀት እንደሌለው የሚገልጹልን ይመስለን ይኾናል ። እነዚህ ጥቅሶች ግን ሌላ ትርጓሜ አላቸው እንጂ እንዲሁ በነጠላቸው የሚወሰዱ አይደሉም ።

የጥቅሶቹ ትርጓሜ ከመቅረቡ በፊት ግን በቅድሚያ ማወቅ የሚገባን ነገር ለእኛ የሚቀርበው የቅዱሳት መጻሕፍት አገላለጽ እኛ በምናውቀውና በሚገባን ቋንቋ ከመኾኑ በቀር የሰው ልጅ ቋንቋ የእግዚአብሔርን ጠባይ በትክክል ሊገልጽልን የማይችል መኾኑ ነው ።



የአብርሃም ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥነት (ዘፍ ም. ፳፪ ቁ. ፲፪)

አንድን ኹናቴ በቦታው ተገኝቶ ማየት ስለኹናቴው ከመስማት የበለጠ ትክክለኛ ዕውቀት እንደሚሰጥ የታወቀ ነው ። በዚህም መሠረት የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ የተባለው አንድ ሰው በቦታው ተገኝቶ በማየት ለማወቅ የሚችለውን ያኽልና እንዲያውም ከዚያ በበለጠ ኹናቴ ሥራቸውንና ዐላማቸውን ዐወቀ ለማለት ነው እንጂ እግዚአብሔር በኹሉም ቦታ ሙሉ እንደመኾኑ መውጣትና መውረድ የለበትም ።



አንድ ትክክለኛ ዳኛ አንድን የፍርድ ሐሳብ ከመመሥረቱ በፊት በተከሳሽ ላይ የቀረበውን ክስ በጥንቃቄ መመርመር ያለበት መኾኑ ግልጽ ነው።እንደጩኸትዋ አድርገው እንደኾነ ወርጄ አያለሁ ያለው ትክክለኛ ዳኛ በጥንቃቄ ከመረመረ በኋላ ወደ ትክክለኛው ሙብጥ የመድረሱን ያኽልና ከዚያም በበለጠ ኹናቴ በሰዶምና በገሞራ ላይ የቀረበው ክስ በእግዚአብሔር ዘንድ ጠንቅቆ የታወቀ እውነት መኾኑን ለመግለጽ ነው ። ስለዚህም በሰዶምና በገሞራ ላይ ትክክለኛ ፍርዱን አስተላልፎአል ።

የልብን ጥልቅ ሐሳብ የሚመረምር ኾኖ ሳለ እግዚአብሔር አብርሃምን መፈተኑ የአብርሃምን እምነት የማያውቅ ኾኖ አይደለም ነገር ግን አብርሃም የሸምግልና ልጁን እስከመሰዋት ድረስ የነበረውን ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥነትና በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን ከፍተኛ እምነት ለወደፊቱ ትውልድ ለማሳየት ብሎ ነው ። በዚህም ምሳሌና አርአያ ለመኾን በቅቶአል ። አብርሃም ተፈትኖ የፈተናው ውጤት ባይታይ ኖሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው የፍቅር መጠን ምን ያኽል እንደኾነ በሰው ኹሉ ዘንድ ባልታወቀም ነበር ። እግዚአብሔርም ዐዋቂ ብቻ ሳይኾን ጥበበኛም ነው ። በዚህም መሠረት የአብርሃም እምነትና ታዛዥነት በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ መኾኑ ባያጠራጥርም በሰው ልጆች ዘንድ የዘወትር ምሳሌ እንዲኾን ስለፈቀደ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው ።

8. <u>የእግዚአብሔር ቅዱስነት</u> ፡ ጽድቅ የኀሊና ቀጥተኛነትና ፍጹምነት በቅዱስነት ውስጥ ይጠቃለላል ። ቅዱስነት ከውስጣዊ ርኵስትና የክፋት ስሜት የነጻ ኾኖ ፍቅርን የሚያገናኝፍ ጸጋና ክብር ነው ።

የእግዚአብሔርን ቅዱስነት የምንረዳው የመንፈሳዊና ግብረ ገባዊ ድርጊቶቹ ክፋትና ርኵስት የሌለባቸው ፡ ንጹሕነትና ፍጹም ደግነት የእርሱ ብቻ መኾናቸው ፡ የፍርዱና የትእዛዙ ትክክለኛ መኾን ፡ ምሕረቱ ብዙና ታጋሽ ፡ ለቀጣ የሚዘገይና ለትክክለኛ ዳኝነቱ ታማኝ ፡ ፍጥረቶቹን የሚወድና ጸጋውን ያገናጸፋቸው በመኾኑ ነው ።

የእግዚአብሔርን ቅዱስነት በሚመለከት ቅዱሳት መጻሕፍት ከተቀረቡአቸው ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ጥቅሶች ይገኙባቸዋል ።

«አቤቱ ከአማልክት መካከል...በቅድስና የከበረ እንደ አንተ ያለ ማነው?» (ዘፀ ም ፲፭ ቍ. ፲፩)

«ሰውነታችሁን ቀድሱ ፤ ቅዱሳንም ኹኑ ፡ እኔ ቅዱስ ነኝና ።
(ዘሌ. ም ፲፩ ቍ. ፵፬)

«እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለም ።» (፩ኛ ሳሙ. ም. ፪ ቍ. ፪)

9. የእግዚአብሔር ደግነት ፤— የእግዚአብሔር ደግነት ሲባል ቅዱስነቱ ፡ ፍቅሩ ፡ ርኅራኄው ፡ ትክክለኛ ፍርዱ ፡ ጸጋውና እንዲሁም ለፍጥረቱ የሚያደርገው ጥበቃ ማለት ነው ። ለምሳሌ በዘላለማዊ ፍጹምነቱ ለዘላለም ብቻውን መኖር ሲችል ነፍስ ያለውንና ነፍስ የሌለውን ፍጥረት መፍጠሩ በጸጋውና በመለኮታዊው መልካም ፈቃዱ ላይ የተመሠረተ አድራጎት ነው እንጂ እርሱ ከዚህ ከፈጠረው ዓለም የሚፈልገው ነገር ኖሮት አይደለም ።

በተለየም የሰውን ልጅ በመልኩና በምሳሌነቱ ፈጥሮ ለማሰብና ለመናገር የሚችል ፍጹም የፈቃድ ነጻነት ያለው የማይሞትና የማይጠፋ ነፍስን በመስጠት ጸጋውን አበዛለት ። እንዲሁም ለሕይወቱ አስፈላጊ የኾኑትን እንደ አየር ፡ ውሃ ፡ ፀሐይንና የዕርሻ ውጤቶችን በቂ በኾነና በማያልቅ መጠን በመስጠት ጠብቆታል ።

የሰው ዘር የደረሰበትን የሞትና የእርግማን ፍርድ በልጁ ቤዛነት አስወግዶ የተፈጥሮ ጠባያችንን ከፍ ማድረጉ የእግዚአብሔርን ደግነት ያሳያል ።

ይኹን እንጂ የኀጢአት መኖር ፡ የፈተናና የችግር በዚህ ዓለም ላይ መኖር ፡ በሚመጣው ዓለም ደግሞ የዘላለም ስቃይ መኖር ከእግዚአብሔር ደግነት ጋር ተቃራኒ ነው ተብሎ ክርክር ይቀርብ ይኾናል ።

ምንም እንኳን የኀጢአት ውጤት በጣም የሚጐዳና ተስፋ የሚያስቆርጥ መኾኑ ቢታወቅ የሰው ልጅ በፍላጎቱና በዝንባሌው ለኀጢአት የተሸነፈ በመኾኑ በዚህ ረገድ በእግዚአብሔር ላይ ሊያጉረመርም አይገባውም ። እግዚአብሔር ኀጢአትን የሚጠላ በመኾኑ የሰው ልጅ ኀጢአተኛ እንዲኾን አይፈልግም ። ኀጢአትን የማይወድ መኾኑንና



ኀጢአት የሚሠራውን ሰው ደግሞ በምን ዐይነት ቅጣት እንደሚቀጣው እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ከዚህ ቀጥለን እንመልከት ።

«ነገር ግን ባትሰሙኝ ፡ እነዚህን ትእዛዞች ኹሉ ባትፈጽሙ ፡ ሥርዓቴንም ብትንቁ ፡ ትእዛዜንም እንዳታደርጉና ቃል ኪዳኔን እንድታፈርሱ ነፍሳችሁ ፍርዴን ብትጸየፍ እንዲህ አደርግባችኋለሁ ፡ ፍርሃትን ፡ክሳትን ፡ ዐይናችሁን የሚያፈዝና ሰውነታችሁን የሚያማስን ትኩሳት አወርድባችኋለሁ ፡ ዘራችሁን በከንቱ ትዘራላችሁ ጠላቶቻችሁ ይበሉታልና ፡ ፊቴንም አከብድባችኋለሁ በጠላቶቻችሁም ፊት ትወድቃላችሁ ፡ የሚጠሉአችሁም ይገዙአችኋል ። ማንም ሳያሳድዳችሁ ትሸሻላችሁ ። እስከዚህም ድረስ ባትሰሙኝ ስለ ኀጢአታችሁ በቅጣታችሁ ላይ ሰባት እጥፍ እጨምራለሁ ። የኀይላችሁንም ትዕቢት እሰብራለሁ ። ሰማያችሁን እንደ ብረት ምድራችሁን ም እንደናስ አደርጋለሁ ። ጉልበታችሁም በከንቱ ያልቃል ፤ ምድራችሁ እኽልዋን አትሰጥም ፤ የምድርም ዛፎች ፍሬአቸውን አይሰጡም ።» (ዘሌ. ም. ፳፮ ቍ. ፲፬-፳)

እግዚአብሔር በኹሉም ቻይነቱ የሰው ልጅ ኀጢአትን እንዳይሠራ በማድረግ የደስታ ኑሮን አያድለውም ነበርን ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ። እግዚአብሔር ከፈለገ የሰው ልጅ ኀጢአትን እንዳይሠራ ባደረገው ነበር ። ይህን ቢያደርግ ግን ከሰው ልጅ ላይ የፈቃድ ነጻነትን ገፈፈ ማለት ነው ። የሰው ልጅ የፈቃድ ነጻነቱን ከተገፈፈ የማሰብ ኀይልና ሒሊና እንደሌላቸው እንደ እንስሳት ኾነ ማለት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ወደፊት የሚኾነውን ነገር ኹሉ አስቀድሞ የሚያውቅ እንደመኾኑና ኹሉን ቻይ እንደመኾኑ አንደኛ ኀጢአትና ክፉ ኹናቴዎችን ለምን በዓለም ላይ እንዲኖሩ ፈቀደ ኹለተኛ ደግሞ የሰው ልጅ ወደፊት ኀጢአተኛ እንደሚኾን እያወቀ ለምን ፈጠረው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ። እነዚህና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ግን ከሰው ልጅ አስተሳሰብ ችሎታ በላይ ስለኾኑ ማንም ሊገባው አይችልም ። ስለዚህም ነው ኢያሱ ወልደ ሲራክ የሚከተለውን ምክር የሰጠው ።

«ምንም እንኳ የጌታ ኀይል ታላቅ ቢኾን የትሑቶችን ትሕትና ይቀበላል ። ልጄ ሆይ ፡ ለአንተ አስቸጋሪ የኾነውን ነገር ለመረዳት

ወይም ከችሎታህ በላይ የኾነውን ጉዳይ ለማወቅ አትሞክር ፤ ለአንተ በተሰጠህ ላይ ብቻ አተኵር እንጂ ፤ ምሥጢር ለኾነ ነገር አትጨነቅ ። ከአንተ ችሎታ ልቆ በሚገኘው ጉዳይ ውስጥ ራስህን ለማስገባት አትሞክር ። እስከ አሁንም እንድታውቅ የተደረገኸው ከሰው አስተሳሰብ ዐቅም በላይ ነው ። ብዙዎች በከንቱ አስተሳሰባቸው ተታልለዋል ። ክፉ ጥርጣሬም ትክክለኛ ፍርድ የመስጠት ችሎታቸውን አጥፍቶባቸዋል ። የማየት ችሎታህ ከደከመ መብራት ያስፈልግሃል ። ስለ ዚህም የሌለህን ዕውቀት አለኝ አትበል ።» (ሲራ. ም. ፫ ቁ. ፳-፳፭)

እኛ ግን የምናውቀው የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው በጎ ሥራን በመሥራት እንደ እግዚአብሔር ጻድቅ እንዲኾን የነበረ ኾኖ ሳለ በተሰጠው የፈቃድ ነጻነት አማካይነት ወደ ክፉ ሥራ ማምራቱን ነው ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አክብሮ ባለመጠበቁ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ጠባዩ ከተበላሸ በኋላ ኀጢአት በዓለም ላይ ሠለጠነ ። ፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኀጢአተኞች ባይኖሩ የጻድቃን ጽድቅ ባልታወቀም ነበር ። በደለኛ ከሌለ የእግዚአብሔር ይቅርታ በምን ይታወቃል? ክፉ ሥራን የሚሠራ ሰው ከሌለ ሌላው ሰው ደግን ሥራ ሠራተብሎ እንዴት ሊታወቅ ይቻላል? ስለዚህም ነው እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ በኦሪት ዘዳግም ፴ ቁ. ፲፭ ላይ «ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካም ነገን ሞትንና ክፋትን አኖሬልሃለሁ ፡» ያላቸው ።

በዚህ ዓለም ባሉበት ጊዜ የሚደርሰው ፈተና ወይም ችግር ለመልካም ውጤት ማለት ደስታን ለሚያጐናጽፍ ሕይወት የሚያዘጋጅ መኾኑን ልንገነዘብ ይገባል ። ይህም ፈተና ወይም ችግር ለኀጢአተኞች አስፈላጊ የሚኾንበት ምክንያት ግብረገብነታቸውን ለማሻሻል ጠባያቸውን ለማረምና ኀይለኝነታቸውን ለማቀዝቀዝ የሚያስችል በመኾኑ ነው ለምሳሌ ሕመምተኛ መኾን ቀድሞ ከነበረ የወንጀለኛነት ጠባይ ሊያርም ይችል ይኾናል ። እንዲሁም ዝሙተኛ ሰው ከመደኸየቱ የተነሣ ሊታረም ይችል ይኾናል ። አብዛኛውን ጊዜ ምቾትና ምኞት ለጥፋት ምክንያት ሲኾኑ ጥቅምንና ጉዳትን ለይተው ለማያውቁ ሰዎች ደግሞ ችግር ለሥነ ሥርዓት የሚያገለግል አርጩሜ ነው ። ለምሳሌ የእስራኤል ልጆች ዕረፍትና ምቾት ባገኙ ጊዜ ኹሉ ፈጣሪአቸውን የበደሉ መኾናቸውንና ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ ኹሉ ግን በንስሓ ወደ ፈጣሪያቸው የተመለሱ መኾናቸውን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታዎች መመልከት ይቻላል ።



ችግርና ፈተናም ኀጢአተኞችን ለማረም አስፈላጊ የኾነውን ያኽል ለጻድቃንም ጠቃሚ ነው ። ለጻድቃን ግን ለዕርማት ሳይኾን ትምህርት እንዲኾ ናቸው ነው ። ይህም እግዚአብሔር የሚወዳቸው ለመኾኑ ምልክትነው ። «ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚወደውን ይገሥጻል ፣ እንደ ልጁ አድርጎ የሚያየውንም ይቀጣልና ።» (ዕብ. ም. ፲፪ ቁ. ፮)

በኢዮብ ፣ በዮሴፍና በዳዊት ላይ የደረሱትን ፈተናዎችና ከፈተናዎቹ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር ምን እንዳደረገላቸው ስናስተውል ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ በተግባር ተተረጐሞ እናገኘዋለን ።



ኢዮብና ጓደኞቹ ። (ኢዮ. ም. ፪ ቁ. ፲፩—፲፫)

ፈተናና ችግርም በጻድቃን ላይ የሚደርስበትን ዋነኛውን ምክንያት ለመረዳት ቀጥሎ ያለውን የሐዋርያው ጳውሎስን መግለጫ እንመልከት ።

«ከነዚህ ከተገለጡልኝ ታላላቅ ነገሮች ፣ የተነሣ እንዳልታበይ ሥጋዬን እንደ እሾኽ የሚወጋ ሥቃይ ተሰጠኝ ፣ ይህም የሰይጣን መልእክተኛ በመኾን እየጐሸመ በማሠቃየት እንዳልታበይ ያደርገኛል ። ይህም የሚያሠቃየኝ ነገር ፣ ከእኔ እንዲወገድልኝ ጌታን ሦስት ጊዜ ለመንሁት ። ነገር ግን እርሱ የእኔ ኀይል የሚገለጠው በአንተ



የያዕቆብ ልጆች ወንድማቸውን ዮሴፍን ሲሸጡት ። (ዘፍ. ም. ፴፯ ቁ. ፳፰)

ደካማነት ፣ ስለኾነ ጸጋዬ ይበቃሃል አለኝ ። ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል በእኔ እንዲኾን ከምን ጊዜውም ይልቅ በደካማነቴ ልመካ እወዳለሁ ። ኀይል የማገኘው ደካማ በምኾንበት ጊዜ ስለኾነ ስለክርስቶስ ስ... ክም ፣ ስሰደብ ፣ ስቸገር ፣ ስሰደድ ደስ ይለኛል ።» (፪ኛ ቆሮ ም. ፲፪ ቁ. ፯-፲)

አብዛኛውን ጊዜ ያለምንም ፈተናና ያለምንም ችግር በተደላ... ደለ ኑሮ መኖር ለሰው ልጅ ደኅንነት ጠቃሚ አለመኾኑ ሊያስገ... መን አይገባም ። የሰው ልጅ ችግር የሌለበት ኑሮ በሚኖርበት ጊ...



ፈጣሪውን የሚረሳና ከፈጣሪው የሚርቅ በመኾኑ እንደገና በተቃራኒው ወደባሰ ችግር ይወስደዋል ። የጉዳዮች ኹሉ መሳካትና የብልጽግና ብዛት ነው ናቡከደነፆርንና ንጉሥ ሰሎሞንን ያሳሳታቸው ። ናቡከደነፆር የወርቅ ጣዖት አሠርቶ ሕዝብ እንዲሰግድለት አስገደደ ። (ዳን ም. ፫ ቁ. ፩-፲፭) ። ሰሎሞን ደግሞ አምላኩን ረስቶ ለጣዖቶች ሰገደ ። (፩ኛ ነገ. ም. ፲፩ ቁ. ፩-፲፫)

ከላይ በቀረቡት መግለጫዎችና ማብራሪያዎች መሠረት ችግርና ፈተና ከክፉ ምኞትና ከክፉ ፍላጎት የተነሣ ወደ ጥፋት ለሚያመሩው የነፍስና የሥጋ በሽታ መድኀኒት ናቸው እንጂ ከእግዚአብሔር ደግነት ጋር የሚቃረኑ አይደሉም ። እግዚአብሔርም የነፍስን ደኅንነት ለመጠበቅ ፈተናን በመላኩ ደግነቱን የሚገልጽልን ከመኾኑ በቀር የደግነቱ ተቃራኒ ኾኖ መታየት የለበትም ።

ከእግዚአብሔር ደግነት ጋር ተቃራኒ ነው ተብሎ የቀረበው ሌላው የመከራከሪያ ሐሳብ ደግሞ ጊዜያዊ ለኾነው የጥቂት ዘመን ደስታ ዘላለማዊ በኾነ የገሃነመ እሳት ሥቃይ መቀጣት ከእግዚአብሔር ደግነትና የትክክለኛ ፍርድ ባለቤትነት ጋር እንዴት ሊስማማ ይችላል የሚለው ጥያቄ ነው ።

የዘላለማዊው ሥቃይ መኖር ከእግዚአብሔር ደግነትና የትክክለኛ ፍርድ ባለቤትነት ጋር ተቃራኒ አይደለም ። የእግዚአብሔር ደግነት ሲባል መሐሪነቱ ብቻ ሳይኾን ቅድስናውም በመኾኑና ኀጢአት ደግሞ ከቅድስና ጋር አብሮ ሊኖር ስለማይችል ኀጢአተኛም የግድ ከቅዱሳን አካባቢ መወገድ ይኖርበታል ። በዚህም መሠረት የአንድ ሰው ምርጫ በዘላለም ደስታና በዘላለም ሥቃይ መካከል ነው ። ይህንኑ እውነት ለመገንዘብ በኦሪት ዘዳግም ም. ፴ ቁ. ፲፭ እና በመጽሐፈ ሢራክ ም. ፲፭ ቁ. ፲፩—፲፯ ብንመለከት የሕይወትንና የሞትን መንገድ በማዘጋጀት እኛ በፈለግነው መንገድ ለመኼድ እንችል ዘንድ እግዚአብሔር ነጻ ፈቃድ የሰጠን መኾኑ ተገልጾ እናገኘዋለን ።

አንድ ኀጢአተኛ በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ ኹሉ በኀጢአቱ የሚኖር እንደመኾኑና ዘላለም ሳይሞት የመኖር ዕድል ቢሰጠውም ዘላለም በዚያው በኀጢአተኛነቱ ይቀጥላል እንጂ ወደ ጽድቅ መንገድ አይመለስም ። እንግዲህ ይህ ኀጢአተኛ በሚሞትም ጊዜ ከነኀጢአቱ (ሚሞት ቅጣቱም የግድ ዘላለማዊ መኾን ይኖርበታል ። ይህም

ማለት አንድ ኀጢአተኛ ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ በዚህ
ዓለም ውስጥ በኖረበት ጊዜ የተሸከመው ኀጢአት አይለየውም ።
ዓለም ውስጥ በኖረበት ጊዜ የተሸከመው ኀጢአት አይለየውም ።
በኼደባት ኹሉ ተከትሎት በመኼድ ለዘላለም ከእርሱ ጋር ይኖራል ።
ኀጢአትም ለዘላለም ከእርሱ ጋር እስካለ ድረስ ቅጣቱም እንዲሁ ከእ
ርሱ ጋር ለዘላለም አብሮ ይኖራል ።

ለዚህች ዓለም የጥቂት ጊዜ ዓለማዊ ደስታ ሲባል ዘላለማዊ
የኾነው ቅጣት ከእግዚአብሔር ደግነት ጋር ተቃራኒ የማይኾንበት
ምክንያት እግዚአብሔር የሚያየው የኀጢአትን ሥራ ብቻ ሳይኾን
የኀጢአተኛውን ዝንባሌ ጭምር በመኾኑ ነው ። ይህም ማለት አንድ
ኀጢአተኛ ለንስሐ ዕድል ቢሰጠውም በኀጢአቱ ለመኖር እንጂ ከኀ
ጢአቱ ለመመለስ ፍላጎት የሌለው መኾኑን እግዚአብሔር ስለሚያ
ውቀው ተገቢ የኾነውን ዘላለማዊ ፍርድ ይሰጠዋል ። ይኹን እንጂ
የእግዚአብሔር ፍላጎት ማንም እንዳይጠፋ በመኾኑ ወደ ጥፋት ከሚያ
መራው መንገድ እንዲጠነቀቅ በቅድሚያ ይነግረዋል ። ለምሳሌ
በአዳምና በሔዋን ላይ የሞት ፍርድ ከመበየኑ በፊት የተከለከለውን
ፍሬ የበላችሁ እንደኾነ ሞትን ትሞታላችሁ ብሎ አስጠንቅቆ አቸው
ነበር ። እነርሱ ግን ማስጠንቀቂያውን ችላ ብለው ትእዛዙን በማፍረ
ሳቸው የፍርዱ ውሳኔ ጸናባቸው ። (ዘፍ. ም. ፫ ቁ. ፲፱)

የጌራራ ንጉሥ አቢሜሌክ በአብርሃም ሚስት በሣራ ላይ የዝ
ሙት ኀጢአት እንዳይሠራና እንዳይፈረድበት የእግዚአብሔርን ማስ
ጠንቀቂያ ሰምቶ ኀጢአቱን ላለመሥራት በወሰነ ጊዜ ነው እግዚ
አብሔር ለአቢሜሌክ ምሕረት ያደረገለት (ዘፍ. ም. ፳ ቁ. ፲፯—፲፰)

ፈርዖን በንስሐ ተመልሶ እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደር
ግለት ሙሴንና አሮንን መላልሶ ቢልክበትም ማስጠንቀቂያውን ባለ
መቀበል በበደለኛነቱ ስለቀጠለ በግብጽ ሕዝብ ላይ የወረደው መቅሰ
ፍት ኹሉ ሊደርስ ችሏል ። (ዘፀ. ም. ፯—፲፪)

የነነዌ ከተማ ሰዎች ኀጢአት ስለበዛና እግዚአብሔርም በደግ
ነቱ በንስሐ ተመልሰው ከጥፋት ሊያድናቸው ስለፈቀደ ነቢዩን ዮናስን
በላከባቸው ጊዜ በንስሐ ስለተመለሱ ይቅርታ አድርጎ ሳያጠፋቸው
ቀርቶአል ። (ዮና. ም. ፫)



ከላይ በቀረቡትና በሌሎችም ሊቀርቡ በሚችሉ ምሳሌዎች
መሠረት እግዚአብሔር የመጨረሻውን ውሳኔና ፍርዱን የሚያስተ
ላልፈው በትዕግሥት ጠብቆ ብዙ ማስጠንቀቂያና ትምህርት ከሰ
ጠ በኋላ መኾኑን መገንዘብ አለብን ። ምንም እንኳ የተሠራው ኀጢ
አት ለተወሰነ ጊዜ መኾኑ ቢታወቅ የዚያ የኀጢአት ሥራ ፍላጎትና
ዝንባሌ በኀጢአተኛው ልብ ውስጥ ይኖራል እንጂ አንድ ጊዜ በሠ
ራው ኀጢአት ብቻ አያልቅም ። ምንም ያኽል ጊዜ በዚህ ዓለም ቢኖር
ያንኑ ኀጢአቱን እየሠራና የኀጢአት ሥራ ፍላጎቱና ዝንባሌውም
እየቀጠለ ይኼዳል እንጂ መቼ ም ቢኾን አያቋርጥም ። ኀጢአት የመ
ሥራት ፍላጎቱ እና ዝንባሌው እስካላቋረጠ ድረስ እግዚአብሔርም
የማያቋርጥ ቅጣት መስጠቱ ትክክለኛ ፍርድ ፈራጅነቱን እንጂ
ከደግነቱ ጋር ተቃራኒ የኾነ አድራጎት እንዳላደረገ መገንዘብ አለብን ።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጆችን ሕግ ብናስተውል ብዙውን
ጊዜ አንድ ሰው ነፍሰ ገዳይ ከኾነ የሞት ፍርድ ይፈረድበታል ።
ሰው የሚገደለው ከጥቂት ደቂቃዎች በማይበልጥ እንዲያውም ከደቂቃ
በሚያንስ ጊዜ ሊኾን ሲችል ገዳዩ ግን የሚፈረድበት ዳግመኛ ወደ
ማይመለስበትና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቀሪ ወደ ሚኾንበት የሞት ፍርድ
ነው ። በዚሁ በሰው ልጆች ሕግ በአንድ ነፍሰ ገዳይ ላይ የሞት ፍርድ
ከመበየኑ አስቀድሞ የገዳዩ ዝንባሌ ይመረመራል ። አስቦበትና ለመ
ግደል አቅዶ የገደለ መኾኑ ከተረጋገጠ የሞቱ ፍርድ ይጸናበታል ።
ገዳዩ ግን ሟችን ለመግደል አቅዶ ሳይኾን በድንገት ከገደለው እንደ
አሠራት ያለ ፍርድ ይፈረድበታል እንጂ አይገደልም ። የሰው ልጅ
ለፍጡር ጓደኛው አስቦ የነፍሰ ገዳይን ዝንባሌ የሚመረምር ከኾነ
የራስ ፀጉራችንን እንኳ እስከመቍጠር ድረስ የሚጠነቀቅልን ፈጣሪ
አምላክ በእኛ ላይ ዘላለማዊውን ፍርድ ከማሳለፉ በፊት ዝንባሌአ
ችንን ጠንቅቆ እንደሚያውቅ መገንዘብ አለብን ። (ማቴ. ም. ፲
ቁ. ፴)

እግዚአብሔር አምላክም የድኅነትን መንገድ በማሳየት የሰው
ልጅ ንስሐ ገብቶ ይድን ዘንድ በትዕግሥት ከጠበቀው በኋላ በንስሐ
ለመመለስ ባለመፈለግና ዝም ብሎ በኀጢአቱ ለመኖር ብቻ የሚፈል
ገውን ሰው እስከመቼም ድረስ ቢቈይ ከኀጢአቱ የማይመለስ መኾ
ኑን ስለሚያውቅ ተገቢ የኾነውን የማያቋርጥ ፍርድ ይሰጠዋል ።
ይህንንም የሚያደርገው ለሰው ልጅ የፈቃድ ነጻነትና በቂ ዕድል ከሰ

ጠው በኋላ ነው ። የእግዚአብሔር ፍላጎት ምንጊዜም ቢኾን የሰው ልጅ እንዲድን ኹናቴውን ከማመቻቸት በቀር እንዲጠፋ አለመኾኑን ከሚገልጹት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ጥቅሶች ይገኙባቸዋል ።

እኔ ሕያው ነኝና ኀጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ይሞት ዘንድ አልፈቅድም ይላል ጌታ እግዚአብሔር ። (ሕዝ. ም. ፴፫ ቍ. ፲፩)

«ጌታ ለረጅም ጊዜ ይታገሣልና ፣ ኀጢአት ሠርቼ ምን ደረሰብኝ አትበል ።» (ሢራ. ም. ፭ ቍ. ፬)

«በእርሱ የሚያምን ኹሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታል ።» (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፲፮)

«የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ኹሉ እንዲድኑና እውነትን እንዲያውቁ ነው ።» (፩ኛ ጢሞ. ም. ፪ ቍ. ፬)

«አንዳንድ ሰዎች እንደሚመስላቸው ጌታ የተናገረውን ቃል ለመፈጸም አይዘገይም ፤ ግን ሰው ኹሉ ለንስሐ እንዲበቃ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ፈልጎ ስለእናንተ ይታገሣል ።» (፪ኛ ጴጥ. ም. ፫ ቍ. ፱)

ነቢዩ ዳዊትም የጌታን ደግነት በሚከተለው ኹናቴ ገልጾታል ።

«አምላክ ሆይ ፣ የሰው ዘር ኹሉ ያየው ዘንድ አንተን ለሚፈሩና በአንተም ለሚተማመኑ ያዘጋጀኸው ደግነት ምንኛ ታላቅ ነው !» (መዝ. ፴፩ ቍ. ፲፱)

«እግዚአብሔር ምንኛ ደግ እንደኾነ ቅመሱ ፤ እዩም ፣ በእርሱ የሚታመን ሰው ምስጉን ነው ።» (መዝ. ፴፬ ቍ. ፰)

«እግዚአብሔር ለኹሉም ደግ ነው ፤ ቸርነቱም ለፍጥረቱ ኹሉ ነው ። » (መዝ. ፻፵፭. ቍ. ፱)



እንግዲህ እግዚአብሔር በደግነት ጠባዩ የሰው ልጅ እንዲድን እንጂ እንዳይጠፋ ፍላጎቱ ቢኾንም የሰው ልጅ ግን በተሰጠው ነጻ ፈቃድ መሠረት የጽድቅን ሥራ ትቶ ዝንባሌውን ወደ ኀጢአት እንዲያመራ በሚያደርግበት ጊዜ የመረጠውን ዘላለማዊ ሥቃይ መስጠቱ ከእግዚአብሔር የደግነት ጠባይ ጋር ተቃራኒ ነው ማለት አግባብ አይደለም ።

## 10. እግዚአብሔር የማንም እርዳታ አያስፈልገውም

«እግዚአብሔርም ... ይኹን አለ ... ኾነ» ባለው መሠረት የተፈጠሩት ነገሮች ኹሉ የተገኙት በእርሱ ቃል ሲኾን እርሱ ግን ያለማንም እርዳታና ድጋፍ በመለኮታዊ ክብሩ የነበረ ፣ የኖረና የሚኖር ነው ። (ዘፍ. ም. ፩ቍ. ፫)

እግዚአብሔር ከማንኛውም ተፈጥሮ ጋር አይመሳሰልም ። ተፈጥሮን ማለት ፍጥረትን ከምንም ያስገኘ እርሱ ነው ። ይህም ማለት አንዳንዶች እንደሚሉት ሳይኾን ንጥረ ነገሮች በተወሰነ ዘመን የጀመሩ እንጂ ዘላለም የነበሩ አይደለም ። የሰው ዘር ፣ እንስሳት ፣ አትክልትና ሌሎችም የተፈጥሮ ንጥረ ነገሮች ከጥቂት ሺሕ ዓመታት ጀምረው እንጂ ዘላለም የነበሩ አለመኾናቸውን የጂኦሎጂ ሊቃውንት አረጋግጠዋል ። ያ ከጥቂት ሺሕ ዓመታት በፊት የተባለው ጊዜ ደግሞ በሃይማኖት አባባል በእግዚአብሔር ትእዛዝ ኹሉም ነገር የተፈጠረበት ጊዜ ነው ። እነዚህም የእግዚአብሔር ክንዋኔዎች ኹሉም በየወገናቸው ኖሩ እንጂ ወደ ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ኹናቴዎች አልተለወጡም ። (ዘፍ. ም. ፩ቍ. ፲፪)

እግዚአብሔር አምላክ የማንም እርዳታና ድጋፍ የማያስፈልገው ሲኾን ከፍጥረቱ መካከል ግን ያለ እርሱ ጠባቂነት ለመኖር ወይም የተፈጥሮ እንቅስቃሴውን ለማከናወን የሚችል የለም ። በኹሉም ቻይነቱና በጥበቡ አማካይነት ፍጥረትን ኹሉ የሚያኖርና እንቅስቃሴአቸውንም ሥርዓት አሲዞ የሚቈጣጠር እርሱው ነው ። ተፈጥሮም የእግዚአብሔርን ጠባቂነትና አንቀሳቃሽነት ካላገኘች ከመኖር ወደ አለመኖር ተዛውራ እንዳልነበረች ትኾናለች ። ይህንኑ በሚመለከት ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል ።

«እርሱ ዓለምንና በዓለም ያለውንም ኹሉ የፈጠረ ነው ፤ የሰማይና የምድርም ጌታ ነው ፤ እርሱ በሰው እጅ በተሠራ ቤት መቅደስ

አይኖርም ፤ ሕይወትንና እስትንፋስን ፥ ሌሎችንም ነገሮች ለሰው ኹሉ የሚሰጥ እርሱ ስለኾነ ምንም ነገር አይጐድለውም ፤ የሰውም እርዳታ አያስፈልገውም ።» (የሐ. ሥ. ም. ፲፯ ቍ. ፳፬—፳፭)

ወደሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም ፲፩ ቍ. ፴፬ ላይ ደግሞ እንዲህ ብሏል «የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚያውቅ ማንም የለም ፤ የእርሱ አማካሪ የሚኾንም የለም ።»

ነቢዩ ኢሳይያስም የእግዚአብሔርን ብቸኛ ኀያልነት የማንም እርዳታና ምክር የማያስፈልገው መኾኑ ፥ የሰው ልጅ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጻጸር ምን ያኽል ኢምንት እንደኾነ የገለጸውን አገላለጽ እንመልከት ።

«የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ ፥ ወይስ አማካሪ ኾኖ ያስተማረው ማን ነው ? እነሆ ፥ አሕዛብ በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው ፤ በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ ተቈጥረዋል።» (ኢሳ. ም. ፵ ቍ. ፲፫ እና ፲፭)



# ምዕራፍ ኹለት ፤

## ምሥጢረ ሥላሴ

### ሀ. መግቢያ

ዘላለማዊውን ደስታ ለመታደል በእግዚአብሔር ማመንና ለትእዛዛቱ ተገዢ መኾን አማራጭ የሌላቸው ግዴታዎች መኾናቸው ባይካድም ወደፍጹም እምነት የሚያደርሰን ቅድመ ኹኔታ ውስጥ በኾነው የማሰብ አቅማችን ላይ ብቻ በመመርኰዝ ሳይኾን ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ጠባዮች ለማወቅ እንድንችል በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት የሚደረግልንን ገልጻ በዝርዝር መመልከት አስፈላጊ ነው ።

ቀደም ተብሎ የእግዚአብሔርን ህልውና ከሚያመለክቱት ማስረጃዎች መካከል የሰው ልጅ የተፈጥሮ ዝንባሌ አንዱ መኾኑ እንደተገለጸ የሚታወስ ነው ። ይኹን እንጂ ይህ የእምነት ዝንባሌ እግዚአብሔር በሦስት አካል እንደሚገኝ የመግለጽ ችሎታ የለውም ። ይህንኑ ዕውቀት በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት እግዚአብሔር ሲገልጽልን የሚፈቅደውን ያኽል ካልኾነ በቀር ምንም ያኽል አስተዋይነት ያለን ቢመስለን ከዚያ ይበልጥ ማወቅ የማንችለው አስተሳሰባችን ውሱን በመኾኑ ነው ። ስለዚህም ነው የቂሣርያው ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ባስልዮስ ስለ አንድነትና ሦስትነት ትምህርት ገለጻ ማድረግ ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ማረጋገጫ ያቀረበው «የእግዚአብሔርን ጌትነቱን በነገር ትችት ብንመረምር ድፍረት ነው ፤ የማይመረመር ጌትነቱን ከማወቅ ልቡናችን ይደክማልና ፥ አይደርስበትምና ፤ ኅሊና መርምሮ ሊያውቀው ያልቻለውንም ቃል ገልጦ ሊናገረው አይችልምና ።» (ሃ. አበ. ገጽ ፻፲)

ፍጥረቱን በመመልከት እነዚህን ፈጥሮ ሥነ ሥርዓት ያስያዘ አንድ የበላይ ተቈጣጣሪ መኖሩን ለመገመት እንችል ይኾናል ። «ምክንያቱም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለሰዎች የማይታየው የእግዚአብሔር

ባሕርይ ፥ ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና አምላክነቱ እርሱ በፈጠራቸው ነገሮች ግልጽ ኾኖ ታይቷልና ።» (ሮሜ. ም. ፩ ቊ. ፳)

ስለ እግዚአብሔርም የምናውቀው ራሱ እግዚአብሔር ሲገልጽልን ብቻ መኾኑን ልንረዳ የምንችለው «ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ? እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ» ብሎ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ለጠየቃቸው ጥያቄ ሐዋርያው ጴጥሮስ በሰጠው መልስ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» ባለው ጊዜ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ፥ የተባረክህ ነህ ፤ ይህንን የገለጸልህ በሰማይ ያለው አባቴ ነው እንጂ ሥጋና ደም አይደለም» ብሎ የሰጠውን መልስ በመመልከት ነው ። (ማቴ. ም. ፲፮ቊ. ፲፫—፲፯)

የሰው ልጅ ኹሉን የመመርመርና የመረዳት መብት ያለው መኾኑ ቢታወቅም የፈጣሪን ባሕርይና ጠባዮቹን ለመረዳት ውሱን ከኾነው ችሎታው በላይ ስለሚኾንበት በእምነት ከመቀበል በቀር ሌላ አማራጭ ዘዴ ሊኖረው አይችልም ።

ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግና ከቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች በተላለፈልን ትምህርት መሠረት እግዚአብሔርን በአንድነትና በሦስትነት እናምነዋለን ። የእግዚአብሔርን አንድነት የምናምነው በፈጣሪነት ፥ በአምላክነት ፥ በአገዛዝ ፥ በፈቃድ ፥ በሥልጣንና እነዚህንም በመሳሰሉት የመለኮት ባሕርያት ሲኾን ሦስትነቱን የምናምነው ደግሞ በስም ፥ በውሳጣዊ ግብሮችና በአካል ነው ።

አብ ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስንል ሦስት ስሞች ናቸው ።

አብ መውለድና ማሥረጽ ፥ ወልድ መወለድ ፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ መሥረጽ ለሦስታቸው የተለያዩ ግብሮች ናቸው ።

አብ የራሱ አካል ፥ ወልድ የራሱ አካል ፥ መንፈስ ቅዱስም የራሱ አካል አለው ። ስለዚህ በአካል ሦስት ናቸው ።

## ለ. ለምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት የሚቀርቡ ምሳሌዎች

የምሥጢረ ሥላሴን ትምህርት በሚመለከት የትምህርተ መለኮት ሊቃውንት በኹለት ዐይነት አስተሳሰብ ይከፈላሉ ። የመጀመሪያዎቹ



ወገኖች በዚህ ዓለም ውስጥ በዐይናችን ልናያቸው የምንችላቸው ነገሮች ኹሉ በምንም ኹኔቴ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ወይም የእግዚአብሔርን ጠባይ ሊመስሉ ስለማይችሉ ምሥጢረ ሥላሴን በምሳሌ ማስረዳት ተገቢ አይደለም ይላሉ ።

ኹለተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ የሰው ልጅ በሚገባው ቋንቋ ሕጸጹን አስቀርቶ ፍጹምነቱን ብቻ በምሳሌነት ወስዶ ማስረዳት ጠቃሚ ነው ይላሉ ። እነርሱም ከሚያቀርቡአቸው ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

የመጀመሪያው ምሳሌ እግዚአብሔር በመልኩና በአርአያው የፈጠረው ሰው የማሰብ ፥ የመናገርና የመተንፈስ ችሎታ አለው ። ማሰብ በአብ ፥ መናገር በወልድ ፥ መተንፈስ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ ። ሐሳብ ወይም ልቡና ንግግርን ይወልዳል ። ንግግርም ከሐሳብ የሚወለደው ከሐሳብ ሳይለይና ሳይቋረጥ ነው ። ምክንያቱም ሰው ዝም ብሎም ኾነ ወይም እየተናገረ ቃላት ዘውትር ከእርሱ ጋር ናቸው እንጂ ከሐሳቡ አይለዩም ወይም አይቋረጡም ። በዚሁም ዐይነት ዘላለማዊው ወልድ ከአብ የሚወለደው ሳይለያይ እንጂ ከተወለደ በኋላ ተለያየ አይባልም ። ልቡና ወይም ሐሳብ ፥ እንዲሁም የንግግር ቃላት ነፍስ ያላቸው መኾናቸውና ይኸውም ነፍስ ሕይወታቸው መኾኑ የታወቀ ነው ። እንደዚሁም አብና ወልድ መንፈስ ወይም ሕይወት ማለት እስትንፋስ አላቸው ። እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው ። ቃል ወይም ንግግር የሚገኘው ሐሳብና ሕይወት ሲኖር ነው ። ሐሳብ ወይም ልቡና የሚኖረው በልቡና ውስጥ ካሉት ቃላትና እስትንፋስ ጋር ነው ። እንዲሁም ሕይወት ወይም እስትንፋስ ካለ ሐሳብና የንግግር ቃላት ይኖራሉ ። እንግዲህ እነዚህ ሦስቱ ኹናቴዎች ማለት ሐሳብ ፥ የንግግር ቃላትና እስትንፋስ ወይም ሕይወት አብረው እንደሚኖሩ ማለት ያንዱ መኖር ሌላውም ያለ ለመኾኑ ማስረጃ ስለሚኾን ሦስቱም በአንድነት ይኖራሉ እንጂ አንዳቸው ከሌላው በፊት አይደለም ፤ ወይም ደግሞ ሌላው በኋላ ተገኘ ለማለት አይቻልም ። ባዚሁም ዐይነት አብ ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ለቅጽበተ ዐይን ያኽል ጊዜ እንኳ አይቀዳደሙም ።

አንድ ሰው ንግግሩን ለሌላ ሰው ሊያሰማ የፈለገ እንደኾነ በአንደበቱ አማካይነት ንግግሩ ይወጣና ለሰሚዎቹ የሚደርሰው ከሐሳቡ ሳይቋረጥና ሳይለያይ ነው ። እንዲሁም ዘላለማዊው የእግዚአብሔር

ቃል ለሰው ልጆች መገለጽ በፈለገ ጊዜ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለድ መለኮትንና ትስብእትን ያዋሐደው ከዘላለማዊው አባቱ ሳይለያይና ግንኙነቱን ሳያቋርጥ ነው ።

ኹለተኛው ምሳሌ ለፀሐይ አካል ፡ ብርሃንና ሙቀት አለው ። የፀሐዩ አካል በአብ ፡ ብርሃኑ በወልድ ፡ ሙቀቱ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል ።

የፀሐዩ ብርሃንና የፀሐዩ ሙቀት ከፀሐዩ አካል የሚገኙ ቢኾኑም ኹልጊዜ ከፀሐዩ አካል ጋር አብረው ያሉ እንደመኾናቸው ተቀዳሚነትና ተከታይነት የላቸውም ። በዚሁም ዐይነት ምንም እንኳ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንዱ ከአብ የተወለደና አንዱ ደግሞ ከአብ የሠረጸ መኾኑ ቢታመን አንዱ ከሌላው የሚቀድም አይደለም ።

ሦስተኛው ምሳሌ ደግሞ ባሦስት መቅረዞች ላይ የሚቀርቡ ሦስት የሻማ መብራቶች ናቸው ። በሦስት መቅረዞች ላይ የቀረቡት ሻማዎች በቤት ውስጥ ብርሃናቸውን በሚሰጡበት ጊዜ ለቤቱ የበራው ብርሃን በአንድነት እንጂ ከአንዱ ወይም ከሌላው ሻማ የመጣ ብርሃን ነው ብሎ መለየት አይቻልም ። በዚህም ዐይነት የሦስትነት ትምህርት በአንድ መለኮታዊ ባሕርይ ይገለጣል ።

## ሐ. የቅዱሳት መጽሕፍት ማስረጃዎች

እስራኤላውያን ብዙ አማልክትን የማምለክ ዝንባሌ እንዳይኖራቸው ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ግልጽ የኾነ ማብራሪያ ባይሰጥም እንኳ ፤ በብዙ ቦታዎች ሳይጠቈም የታለፈ አይደለም ። ብዙ አማልክትን ላለማምለክ እምነታቸው በአንድ አምላክ ላይ ጸንቶ ከተጠናከረና ከተለማመደ በኋላ ግን የሕግ ጋት ፍጻሜ በኾነው በወንጌሉ አማካይነት በምሳሌና በምልክት ከሚመራው ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት የምሥጢረ ሥላሴን ትምህርት ግልጽ አድርጎ በማብራራት ወደ ሐዲስ ኪዳን መራቸው ። በብሉይ ኪዳን እየተጠቈሙ ታልፈው በሐዲስ ኪዳን በቂ ማብራሪያ የተሰጠባቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው ።



«እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ።» (ዘፍ. ም. ፩ ቍ. ፩)

እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚለው ቃል በመጀመሪያ በተጻፈበት ቋንቋ በዕብራይስጡ ኤሎሂም ይለዋል ። ኤሎሂም ማለት አምላኮች ማለት ነው ። ኤሎሂም ማለት አምላኮች ካለ በኋላ ደግሞ ፈጠረ ይላል እንጂ ፈጠሩ አይልም ። ስለዚህ ይህ በብዙ ቍጥርና በነጠላ ቍጥር አቀላቅሎ መናገር ያስፈለገው የአንድነትና የሦስትነት ምሥጢር ሊጠቈም ስለተፈለገ ነው ።

አምላኮች የሚለው ቃል ኹለት ፡ ሦስት ወይም ከዚያ በላይ ለኾኑ ቍጥሮች ተነግሮስ እንደኾነ በምን ይታወቃል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ። የእግዚአብሔር ሦስት አካላት ግን በአብ ፡ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የተገለጸ ስለኾነ ሊያሳስተን አይችልም ።

«ሰውን በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር ።» (ዘፍ. ም. ፩ ቍ. ፳፮)

በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር ሲል ሦስትነትን መጠቈሙን ቢያመለክትም አንዳንድ ተከራካሪዎች የሚያቀርቡት ክርክር «እንደ ነገሥታት ልማድ እግዚአብሔር ራሱን ለማክበር ብሎ በነጠላ ሳይኾን በብዙቍጥር ተጠቀመ እንጂ ሦስትነትን ለመጠቈም ተብሎ የተነገረ አይደለም» ይላሉ ። ይህ የመከራከሪያ ሐሳብ ትክክል ያልኾነበት ምክንያት እንደዚህ ያለው ራስን በማክበር የሚነገረው አነጋገር የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተጻፉባቸው ዘመናት በምሥራቅ አገሮች ነገሥታት ዘንድ የተለመደ ባህል ባለመኾኑ ነው ። እግዚአብሔር ደግሞ ለሰው ልጆች ሲገለጥ የሚናገርባቸው የቋንቋ ስልቶች ሕዝቡ ይረዳው ዘንድ ከጊዜውና ከህገሩ ልማድ ጋር ተመሳሳይ እንጂ የተለየ አይኾንም የጊዜውን ባህልና ልማድ ለመረዳት በፈርዖን ፡ በናቡከደነፆርና በዳርዮስ የተናገሩትን ያነጋገር ስልቶች ቀጥለን እንመልከት ።

ፈርዖን ፡ ዮሴፍን «በግብጽ ምድር ኹሉ ላይ ሾምኩህ» አለው እንጂ ሾምንህ አላለውም ። (ዘፍ. ም. ፵፩ቍ. ፵፩)

ዳርዮስ ፡ «እኔ ዳርዮስ ይህንን አዝዣለሁ» አለ እንጂ እኛ አዘናል አላለም ። (ዕዝ ም. ፮ቍ. ፲፪)

ናቡከደነፆር «የሕልሙን ፍቺ እንዲያስታውቁኝ የባቢሎን ጠቢባን ኹሉ ወደ እኔ ይገቡ ዘንድ አዘዝሁ» አለ እንጂ ወደ እኛ ይገቡ ዘንድ አዘዝን አላለም ። (ዳን. ም. ፬ቍ. ፮)

በእነዚህም ማስረጃዎች መሠረት ቀደም ተብለው የተነገሩት አነጋገሮች ሦስትነትን የሚጠቍሙ ናቸው እንጂ በነገሥታት ልማድ ራስን የማክበር አነጋገሮች አይደሉም ።

የሚከተሉት ጥቅሶች ተጨማሪ ማስረጃዎች ናቸው ።

«እነሆ ፡ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ኾነ ።» (ዘፍ. ም. ፫ቍ. ፳፪)

ይህ አነጋገር ስለ ሦስትነት የተነገረ እንጂ ራስን ለማክበር የተነገረ አለመኾኑን ልንገነዘብ የምንችለው ከእኛ እንደ አንዱ ኾነ በማለቱ ነው ። ራስን የማክበር አነጋገር ቢኾን ኖሮ እንደ እኛ ኾነ ይል ነበር እንጂ ከእኛ እንደ አንዱ ኾነ ባላለም ነበር ።

«ኑ እንውረድና ቋንቋቸውን እንደባልቀው ።» (ዘፍ. ም. ፲፩ቍ. ፯)

ይህም አነጋገር ሦስትነትን ለመጠቈም እንጂ ራስን የማክበር አነጋገር አለመኾኑን የምንረዳው ኑ በማለቱ ነው ። ራስን ለማክበር ቢኾን ኖሮ እንውረድና እንደባልቀው ከማለት በቀር ኑ ብሎ ባልጋበዘም ነበር ።

ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ሱራፌል ሲናገር በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ቆመው ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እያሉ ይጮኹ እንደነበሩ ተናግሮአል ። (ኢሳ. ም. ፮ቍ. ፫)

ቅዱስ የሚለውን ቃል ከሦስት ጊዜ በላይ ሳያበዙና ከሦስትም ሳይቀንሱ መጮኻቸው ሦስትነትን የሚያመለክት ሲኾን የሠራዊት ጌታ ማለታቸው ደግሞ የመለኮት አንድነትን ያመለክተናል ።

የእስራኤልን ልጆች ይባርኩበት ዘንድ እግዚአብሔር ለአሮንና ለልጆቹ የሰጣቸው መመሪያ ሦስትነትን ይጠቍማል ።



— «እግዚአብሔር ይባርክህ ፡ ይጠብቅህም ፤
— እግዚአብሔር የፊቱን ብርሃን ይግለጥልህ ፡ ይራራልህም ፤
— እግዚአብሔር በምሕረት ዐይን ይመልከትህ ፡ ሰላሙንም ይስጥህ ።» (ዘ ኍ. ም. ፮ቍ. ፳፬—፳፮)

ሦስትነትን ለማመልከት ባይኾን ኖሮ ሦስት ጊዜ እግዚአብሔር ብሎ ባልደጋገመም ነበር ። ቡተመሳሳይ ኹኔታ ይህንኑ ቡራኬ የሚመስለው የእግዚአብሔርን የሦስትነት ስሞች በመጥራት የቀረበው ሐዋርያዊው ቡራኬ ነው ።

— «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፥
— የእግዚአብሔርም ፍቅር ፥
— የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከኹላችሁም ጋር ይኹን ።» (፪ኛ ቆሮ. ም. ፲፫ቍ. ፲፬)

የብሉይ ኪዳኑ ቡራኬ ከሐዲስ ኪዳኑ ክርስቲያናዊ ቡራኬ ጋር ተመሳሳይ ቢኾንም ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው የእስራኤል ልጆች ብዙ አማልክትን እንዳያመልኩ ከመጠንቀቅ የተነሣ የሦስትነት ምሥጢር አልተገለጠላቸውም እንጂ አልፎ አልፎ ግን ጥቈማ ሳይደረግላቸው አልቀረም ።

መድኀኒታችን የሦስትነትን ምሥጢር ለደቀመዛሙርቱ በግልጽ ያመለከታቸው «ኺዱና የዓለምን ሕዝብ ኹሉ አስተምሩ ፤ ባአብ ፡ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው» በማለት ነው ። (ማቴ. ም. ፳፰ ቍ. ፲፱)

በማቴዎስ ወንጌል ም. ፫ ቍ. ፲፮—፲፯ እግዚአብሔር ወልድ ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ከውሃ ውስጥ ሲወጣ አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ ድምፁን በማሰማትና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል በመውረድ የሦስትነትን ምሥጢር ገልጠዋል ።

ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚሠርጽ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» ብሎአቸዋል ። (ዮሐ. ም. ፲፭ቍ. ፳፮)

ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፭ ቁ. ፯ ላይ «በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው ፤ እነርሱም አብ ፥ ቃልና መንፈስ ቅዱስ ናቸው» ብሏል ።

በእነዚህም የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መሠረት የአንድነትንና የሦስትነትን ምሥጢር አምነን መቀባል አለብን እንጂ ፤ ስለ እግዚአብሔር ጠባይ የማወቅ ችሎታ አይኖረንም ። እኛ ውሱኖች እንደመኾናችን ውሱን ያልኾነውን እግዚአብሔርን የማወቅ ችሎታችን ዐቅም እንደሌለው ማወቅ ይኖርብናል ።

መ. <u>የሲኖዶሶች ምስክርነት</u>

በአራተኛው መቶ ዓመት አካባቢ በምሥጢረ ሥላሴ ላይ ብዙ መናፍቃን በመነሣታቸው ልዩ ልዩ የዓለም ዐቀፍ ሲኖዶሶች ተሰብስበዋል ። ከእነዚህም መካከል በ፫፻፳፭ ዓ. ም. በኒቂያ ከተማ የተሰበሰበው ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት (፫፻፲፰) የዓለም ኤጲስ ቆጶሳት የተገኙበትና በ፫፻፹፩ ዓ. ም. ደግሞ በቊስጥንጥንያ አንድ መቶ ኀምሳ የዓለም ኤጲስ ቆጶሳት የተገኙበት ኹለት የዓለም ዐቀፍ ሲኖዶሶች ቀጥሎ ያለውን የእምነት ቀኖና ደንግገዋል ።

«ኹሉን በያዘ ፥ ሰማይንና ምድርን ፥ የሚታይና የማይታየውን በፈጠረ ፥ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ።

ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ በተወለደ ፥ የአብ አንድያ ልጁ በሚኾን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ ፥ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል ፥ ኹሉ በእርሱ የኾነ ፥ ስለ እኛ ስለ ሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ኾነ ፤ ሰው ኾኖም በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ ሞተ ፤ ተቀበረም በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ።



ሕይወትን በሚሰጥ ጌታ ፥ ከአብ በሠረጸ ፥ ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለት ፥ በነቢያት አድሮ በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ።

ዓለም ዐቀፋዊትና ሐዋርያዊት በኾነች በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ።

ኀጢአትን ለማስተስረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ።

የሙታንን መነሣትና የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን ፤ ለዘላለሙ አሜን ።

ሠ. <u>የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት</u>

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ፡የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስ</u>፡«አብ ፥ ወልድ ፥ መንፈስ ቅዱስ እንላለን ። . . . የእግዚአብሔር አቃኒም ስሞች ናቸው ፤ ስሞችም አቃኒም ናቸው ። የአቃኒም ትርጓሜው በገጽ ፥ በመልክ ፍጹማን የሚኾኑ ፥ ባለመለወጥ ጸንተው የሚኖሩ አካላት ማለት ነውና ባሕርዩ አንድ ሲኾን ሦስቱ አካላት ጸንተው በሚኖሩ በእሊህ ስሞች ይጠራሉ ፤ ሦስት አካላት አንድ መለኮት ናቸው ።» (ሃ. አበ. ገጽ ፴፱—፵)

<u>ሐዋርያትን መሰሉ ቅዱስ አትናቴዎስ</u>፥«በባሕርይ አንድ እንደኾኑ በሦስቱ እናምናለን ፤ እሊህም አብ ፥ ወልድ ፥ መንፈስ ቅዱስ ናቸው ፤ አብ የሚያድን ነው ፤ ወልድም የሚያድን ነው ፤ መንፈስ ቅዱስም የሚያድን ነው ። አንድ ሲኾኑ ሦስት ናቸው ፤ ሦስት ሲኾኑ በባሕርይ ፥ በመለኮት ፥ በክብር ፥ በመመስገን ፥ በሥልጣን ፥ ፍጡራንንም ኹሉ በመፍጠር ፥ በፈቃድ ፥ ኀጢአትን ይቅር በማለት ፥ በማትለወጥ ዕውቀት ፥ በረከትን በመስጠት አንድ ናቸው ። (ሃ. አበ. ገጽ ፹፭)

<u>ቅዱስ ባስልዮስ የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስ</u>፡«የሦስቱ አካላት መለኮት ፍጹም አንድነትን ልናውቅ ይገባናል ፤ የእነርሱ የሚኾን አንድ መለኮትን አንድ በማድረግ እናዋሕድ ። በአብ ወላዲነት ፥ አሥራጺነት መለኮት አንድ እንዲኾን ሃይማኖትን እንመን ፤ ወልድ ከአብ ተወልዷልና መንፈስ ቅዱስም ከአብ ተገኝቷልና ፥ አብ ከወልድ ፥ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ሳይቀድም ወልድ ከአብ በመወለዱ መንፈስ ቅዱስም ከአብ

ባመሥረጹ የፈጣሪአችን የሦስትነቱ መለኮት አንድ ይኾናል ።» (ሃ. አበ. ገጽ ፪፺፮)

<u>የሮም ሊቀ ጳጳስ አቡሊዲስ</u> «አብ ወልድን የወለደ ነውና ዳግመኛም በማይነገር ፡ በሐሳብም ባማይመረመር ግብር መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ተገኝቷልና አብ ከወልድ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ሳይቀድም ፡ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ወልድም ከአብ ወደ ኋላ ሳይኾን ነው ። ወልድም ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው ፤ መንፈስ ቅዱስም ለአብ ለወልድ እስትንፋሳቸው ነው ፤ የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ እንደኾነ በዚህ ዐውቀን ለእርሱ እንሰግዳለን ።» (ሃ. አበ. ገጽ ፪፴፯—፪፴፰)

<u>የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ዮሐንስ</u> ፤«አንድ አምላክ ብለን የምንሰግድላቸው ሥሉስ ቅዱስ በባሕርይ በመለኮት አንድ እንደኾኑ እናምናለን ፤ እሊህም አብ ፡ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው ። እሊህም ሦስቱ አካላት በገጽ ፍጹማን እንደኾኑ በሥልጣን ፡ በባሕርይ ፡ ከዘመን አስቀድሞ በመኖር ፡ በጌትነት ፡ በመፍጠር ፡ ሳይለወጡ በመኖር አንድ እንደ ኾኑ እናምናለን ፤ ይህን እንዲህ ብሎ የማያምነውን እኛ እናወግዘዋለን ።» (ሃ. አበ. ገጽ ፪፷፮)

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ በመጀመሪያ የእንዚናዙ ኤጲስ ቆጶስ ኰዚያ በኋላ ደግሞ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ</u> ፡ «ከኹሉ አስቀድሞ በአካል ልዩ ፡ በክብር አንድ የሚኾን ሦስትነትን እናስተምራለን ፤ እሊህም አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ቅዱስ ናቸው ፤ ሥላሴ በመለኮት አንድነት መለየት የለባቸውም ፤ አካላት ግን በባሕርይ መለየት ሳይኖር እያንዳንዱ አካል በገጽ ፡ በመልክ ፍጹም ነው ። ለአብ የአባትነት ስም ፡ የአባትነት ክብር አለው ፤ ለወልድም በባሕርይ ክብሩ ከአብ ሳያንስ የልጅነት ስም ፡ የልጅነት ክብር አለው ፤ መንፈስ ቅዱስም እንዲህ በክብር አይለዩም ፤ ነገር ግን ተለውጦ አብ ወልድ አይባልም ፤ በዚህ ጊዜ ተገኘ አይባልም ፤ በመለኮት እንደ አብ ፡ እንደ ወልድ ነው እንጂ ፤ እስትንፋሳቸው ነውና ፡ ሦስቱም ትክክል ናቸውና ።» (ሃ. አበ. ገጽ ፪፻፲—፪፻፲፩)

<u>ቅዱስ ቄርሎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት</u> ፡«አንድ መለኮት ፡ አንድ ባሕርይ ፡ አንድ ኀይል ፡ አንድ ልዕልና ፡ አንድ ጌትነት ፡ አንድ ክብር ከጥንት አስቀድሞ የነበረ አንድ ቀዳማዊነት ነው ፤ በሦስት አካላት ፡



በሦስት ገጻት ፍጹማን ናቸው ፤ ግዙፋን አይደሉም ፤ ያልተፈጠሩ ናቸው ፤ ድካም የማይስማማቸው ፡ የማይለወጡ ናቸው ፤ ለመገኘት ጥንት ፡ ለዘመን ፍጻሜ የላቸውም ። አብ ፡ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት በባሕርይ አንድ ነው ብሎ ማመን ይህ ነው የማይመረመር በቅድምና የነበረ» (ሃ አበ. ገጽ ፪፻፶፮)

<u>ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ፡ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት</u> ፦ «በአካል ፡ በገጽ ሦስት ነው ፤ በመለኮት አንድ ነው ፤ ሥሉስ ቅዱስ አንድ ናቸው ፤ አንድ አገዛዝ ፡ አንድ ጌትነት ፤ አንድ መለኮት ፡ አንድ መንግሥት ገንዘባቸው ነው ። አብ ከወልድ ተለይቶ የኖረበት ፡ ኖሮ ኖሮ ወልድን የወለደበት ፡ መንፈስ ቅዱስን ያሠረጸበት ዘመን የለም ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ቅዱስ በቅድምና የነበሩ ናቸው እንጂ ወልድ ከእግዚአብሔር አብ ተወለደ ፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ተገኘ ፤ ሥሉስ ቅዱስ ያልተፈጠሩ ናቸው ።» (ሃ. አበ ገጽ ፫፻፵፪)

<u>ቅዱስ ሳዊሮስ ፡ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት</u> ፦ «ሦስቱ አካላት በመልክ ፍጹማን ናቸው ፤ ሦስቱ ገጻት በክብር ፡ በብርሃን አንድ ናቸው ፤ በባሕርይ አንድ ናቸው ፤ በሥልጣን አንድ ናቸው ፤ በጌትነት አንድ ናቸው ፤ በመለኮት አንድ ናቸው ፤ በመሰገድ አንድ ናቸው ፤ በመመስገን አንድ ናቸው ፤ የታመኑ ሰዎች እንደሚያምኑት ። . . . . . በሦስቱ አካላት ውስጥ መገዛዛት ፡ መታጠቅ መፍታት የለም ፤ በማዕርግ መለኮት አንዱ ካንዱ አይበልጥም ፤ አንዱ አንዱን እንደ መልከተኛ በሥልጣኑ አያዝዘውም ፤ በአንድ መለኮት ክብር ፡ በአገዛዝ ፡ የኹሉ ፈጣሪ ገንዘብ በሚኾን በባሕርይ ዕውቀት አንድ ናቸው እንጂ ።» (ሃ. አበ. ገጽ ፫፻፶፯)

ረ — <u>ሥርጸት</u> ።

በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፭ቍ. ፳፮ ላይና በቀደምት ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጽሑፎች ፡ እንዲሁም መቅዶንዮስን ያወገዘው የቁስጥንጥንያው ጉባኤ በደነገገው የእምነት ቀኖና መሠረት መንፈስ ቅዱስ የሚሠርጸው ከአብ ብቻ መኾኑ በግልጽ የተነገረ ቢኾንም መንፈስ ቅዱስ የሚሠርጸው ከአብና ከወልድ ነው እንጂ ከአብ ብቻ አይደለም በማለት የሚከራከሩ አሉ ። ለክርክር ከሚያቀርቡአቸው ጥቅሶች መካከል ቀጥለው የተዘረዘሩት የሚገኙባቸው ሲኾኑ ለያንዳንዱም መልስ ተሰጥቶባታል ።

«ኔኔ የምልክላችሁ አጽናኝ ሲመጣ ።» (ዮሐ. ም. ፲፭ ቍ. ፳፮ ም. ፲፬ ቍ. ፲፮ እና ፳፮)

ወልድ የሚልከው ከኾነ ከወልድ ይሠረጻል ማለት ነው ይላሉ ። ይህ አባባል ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ጋር ስለማይስማማ ትክክል አይደለም ። የተከራካሪዎቹ ሐሳብ ትክክል ነው የሚባል ከኾነ ወልድም የተወለደው ከአብ ብቻ ሳይኾን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ነው ማለት ይኾናል ፤ ምክንያቱም በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፵፰ ቍ. ፲፮ ላይ «እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል» ተብሏልና ። የወልድን ከአብ ብቻ መወለድ ተከራካሪዎቹም ቢኾኑ የሚያረጋግጡት እምነት ነው ። ስለዚህ በዚህ ጥቅስ መሠረት ወልድ ከአብ እንጂ ከመንፈስ ቅዱስ ተወለደ እንደማይባለው እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ከወልድ እንደተላከ ቢነገርም ከወልድ ሠረጸ ማለት አይደለም ። መልእክቱ ደግሞ የተፈጸመው በዘመን በሚቈጠር ጊዜ ሲኾን መሥረጹ ግን ዘላለማዊ እንጂ በጊዜ የሚወሰን ግብር አይደለምና ተመሳሳይ ሊኾኑ አይችሉም ። ስለዚህም መሥረጽና መላክ አንድ ዐይነት ግብር አለመ ኾናቸውን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

«የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ነው» ። (ዮሐ. ም. ፲፮ ቍ. ፲፭)

የአብ የኾነው ኹሉ የእርሱ ከኾነ መንፈስ ቅዱስም የሚሠርጸው ከአብ ብቻ ሳይኾን ከአብና ከወልድ ነው ብለው ይከራከራሉ ።

የእግዚአብሔርን ግብሮች በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች የከፋፈል ናቸው እንደኾነ አፍአዊና ውሳጣዊ ግብሮች ብለን ልንጠራቸው እን ችላለን ። ውሳጣዊ ግብሮች የሚባሉት የሦስትነት መለያ የኾኑት መውለድ ፣ ማሥረጽ ፣ መወለድ ፣ መሥረጽ ናቸው ። ውሳጣዊ ግብሮች የተባሉበትንም ምክንያት በምሳሌ ለማስረዳት ለምሳሌ ፀሐይ ብርሃን ዋንና ሙቀትዋን ለዓለም ብታበረክትም ብርሃንዋና ሙቀትዋ ከእር ስዋ ተለይተው እንዳልቀሩና በእርስዋ ውስጥ እንዳሉ ኹሉ በዚሁም ዐይነት ወልድ ከአብ ሲወለድና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከአብ ሲሠርጽ ከአብ ተለይቶ ወይም ተከፍሎ መኼድ ሳይኾን ኹልጊዜ አብሮ መኖር ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ አብ ልብ ፣ ወልድ ቃልና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እስትንፋስ በመኾናቸው በአብ ልብነት ያስባሉ ፤ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ይኖራሉ ወይም



በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ይተነፍሳሉ እንላለን ። ይህ ነው እንግ ዲህ አንድነት በሦስትነት ሦስትነት ደግሞ በአንድነት ማለት ። በእነ ዚህ ውሳጣዊ ግብሮች በኾኑት በወላጅነት ፣ በአሥራጺነት ፣ በመወ ለድና በመሥረጽ ማናቸውም ከሌላው ጋር የማይጋራ በመኾኑ የአብን የማሥረጽ ግብር ወልድ የማይጋራው መኾኑን መገንዘብ አለብን ።

ለሦስቱም አካሎች የጋራ የኾኑት ግብሮች ማለትም መለኮታዊ አንድነትን የሚያመለክቱት ግብሮች አፍአዊ ግብሮች ናቸው ። የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ነው ያለው ዐዋቂነቱን ማለቱ ነው ። ዐዋቂነት የመለኮታዊ አንድነት ግብር እንደመኾኑ አፍአዊ ግብር ነው ። ስለዚህ ዕውቀት የአብ ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የጋራ ማለት የአንድነት ባሕርይ ነው እንጂ የሦስትነት ግብር አለመኾኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

ተከራካሪዎቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የማይደግፏ ቸው ኾነው በሚያገኙአቸው ጊዜ ወደ ዓለማዊው የፍልስፍና ክርክር ያዘነብላሉ ። ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ ግን እግዚአብሔርን ለማ ወቅ ዓላማዊው ዕውቀታችን ውሱን መኾኑን የተገነዘቡት አይመስልም መለኮታዊውን የእግዚአብሔርን ባሕርይና ስለ እግዚአብሔር ግብሮች ለማወቅ ያለን ዐቅም ውሱን ቢኾንም ከቅዱሳት መጻሕፍት የበለጠ እውነትን ሊገልጽልን የሚችል ሌላ የዕውቀት ምንጭ አለመኖሩን ማወቅ ይኖርብናል ።

«መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ አላቸው ።» (ዮሐ. ም. ፳ ቍ. ፳፪)

መንፈስ ቅዱስን ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ከእርሱ የሠረጸ በመ ኾኑ ነው ይላሉ ። እዚህ ላይ የተሰጠው መላ ምት መስመሩን የሶቀቀና ከመጽሐፉ መንፈስ ጋር ያልተዛመደ ነው ። ጌታችን ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ እፍ ካለባቸው በኋላ የሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ነው እንጂ ከሦስቱ የመለኮት አካላት አንዱን አይደለም ። የመንፈስ ቅዱስም ስጦታ መንፈስ የሚባል ስም እንደሚ ሰጠው የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች እንመልከት ።

«ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል ፤ ኮሥኩም ቍጥቋጦ ያፈራል ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ ፣ የምክርና

የኀይል መንፈስ ፡ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል ።» (ኢሳ. ም. ፲፩ ቍ. ፩—፪)

«እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚናገር እግዚአብሔር መንፈሱን በሙላት ይሰጠዋል ።» (የሐ. ም. ፫ ቍ. ፴፬)

«የሰውን ልብ የሚያውቅ አምላክ መንፈስ ቅዱስን ለእኛ እንደ ሰጠው ዐይነት ለእነርሱም በመስጠት መሰከረላቸው ።» (የሐ. ሥ. ም. ፲፭ ቍ. ፰)

«ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላችሁ ነበርን ሲል ጠየቃቸው . . . ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደና በሌላ ቋንቋዎች ተናገሩ ፤ ትንቢትም መናገር ጀመሩ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፲፱ ቍ. ፪ እና ፯)

በእነዚህም ማስረጃዎች መሠረት መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ማለቱ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ያልነበራቸውን የማሰርና የመፍታት ሥልጣን ተቀበሉ ለማለት ነው እንጂ ከአንድ ሰው እጅ ወደ ሌላ ሰው እጅ እንደ ሚቀባበሉት ዕቃ በማስመሰል ከሦስቱ የመለኮት አካሎች አንዱን እንካችሁ ውሰዱ ማለት አለመኾኑን መገንዘብ ይኖርብናል ።

«የልጁ መንፈስ ።» (ገላ. ም. ፬ ቍ. ፯)

የልጁ መንፈስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ስለሠረጸ ነው ይላሉ ። የልጁ መንፈስ የተባለው መለኮታዊ አንድነትን የሚያመለክት እንጂ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ መሥረጹን የሚያመለክት አይደለም ። የአንድነትና የሦስትነት ግብር በሚተነተንበት ጊዜ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ልቦናቸው አብ ፡ የአብና የመንፈስ ቅዱስ የንግግር ቃላቸው ወልድ ፡ የአብና የወልድ መንፈሳቸው መንፈስ ቅዱስ ነው እንላለን ።

መድኃኒታችን ወደዚህ ዓለም መጥቶ ቤዛ በኾነን ጊዜ ጸጋውን አድሎናል ። ይህም የታደልነው ጸጋ ወይም ስጦታዎቹ በቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ክፍሎች የቅድስና መንፈስ ፡ የክብር መንፈስ ፡ የጸጋ መንፈስ ፡ የጥበብ መንፈስ ፡ የኀይል መንፈስ ፡ የምክር መንፈስ በማ



ለት ተዘርዝሮ እናገኘዋለን ። እነዚህ አባባሎች መሥረጽን ያመለክታሉ ብሎ ማንም የተከራከረ የለም ። ለምሳሌ የሰው መንፈስ በሚባልበት ጊዜ መንፈስ ወይም ነፍስ ከሰው ጋር ተዋሕደች እንጂ ከሰው ተገኘች ማለት አይደለም ። (ኢሳ. ም. ፲፩ ቍ. ፩—፪ ዘካ. ም. ፲፪ ቍ. ፲ ፡ ሮሜ ም. ፩ ቍ. ፬ ፡ ፩ኛ ጴጥ. ም. ፬ ቍ. ፲፬)

የአንድ ነገር ከሌላ ነገር ጋር መዋሐድ ወይም መተባበር ውሕደት ወይም ኅብረት ያሰኘዋል እንጂ አንዱ ከሌላው ተገኘ አያሰኘውም ። የወልድ ከአብ መወለድና የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መሥረጽ ግን መጀመሪያ በቅዱስ ወንጌል ፡ ኹለተኛ በቁስጥንጥንያው ዓለም ዐቀፋዊው ሲኖዶስ የሃይማኖት ቀኖና እና ከዚያም በቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት በግልጽ የተነገረ ስለኾነ ምንም የሚያከራክር አይደለም ።

«እርሱ ያከብረኛል ! ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና ።» (የሐ. ም. ፲፮ ቍ. ፲፬)

ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስ ከወልድም የሠረጸ መኾኑን ነው ይላሉ ።

ጌታ ይህንን አባባል ለደቀ መዛሙርቱ የሰነዘረላቸው በዚያን ጊዜ የእርሱ መለኮታዊ ክብርና ከአብ ጋር ያለው እኩልነት በእነርሱ ዘንድ የታመነበት በመኾኑና እርሱ ደግሞ በቅርብ ጊዜ ከእርነሱ የሚለይ በመኾኑ በአንድ በኩል ከእርሱ በኋላ ሦስተኛው መለኮታዊ አካል አብሮአቸው የሚኖር መኾኑንና እርሱም መንፈሳዊ ብርታትን እንደ ሚሰጣቸው ፡ ወደፊት የሚኾነውን ኹናቴ እንደሚገልጽላቸው ፡ የረሱትን እንደሚያስታውሳቸውና የማያውቁትንም እንዲያውቁ የሚ ያደርጋቸው መኾኑን ሊነግራቸው ሲኾን በሌላ በኩል ደግሞ የሦስተኛው አካል ከአብና ከወልድ ጋር ያለውን መለኮታዊ እኩልነት ሊገልጽላቸው ፈልጎ ነው እንጂ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ሠረጸ ለማለት አይደለም ። ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል ማለቱ እኔ የነገርኳችሁና የረሳችሁትን ያስታውሳችኋል ፤ እንዲሁም ሳልነግራችሁ የቀረሁትን ማለትም በመለኮታዊ አንድነታችን እኔ የማውቀውን ኹሉ እርሱም የሚያውቅ እንደመኾኑ እኔ የምነግራችሁን ያኽል እርሱም ይነግራችኋል ማለቱ ነው ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሌላ በቃል የሚቀርቡ ክርክሮች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው ።

መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ካልሠረጸ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጹም የተለያዩ ናቸው ማለት ነው ፤ በመለኮታዊ አካሎች መካከል ደግሞ ፍጹም የኾነ ልዩነት አለመኖሩን እናውቃለን ብለው ይከራከራሉ ። ይህ አባባል ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ያልተናገሩትና ተከራካሪዎቹ ከራሳቸው ያፈለቁት ሐሳብ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስም ኾነ ቅዱሳን አባቶች



ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች በማጠብ ትሕትናን በተግባር እንዳስተማረ ። (ዮሐ ም. ፲፫ ቍ.፩—፲፭

ያረጋግጡልን ወልድ ከአብ እንደተወለደና መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደ ሠረጸ እንጂ ፤ ከዚያ የተለየ እስካልኾነ ድረስ የራሳችንን ግምት ሰጥተን እንደዚህ ነው ወይም እንደዚያ ነው በማለት አዲስ ሐሳብ ማፍለቅ አስፈላጊ አይደለም ።

ተከራካሪዎቹ የሚያቀርቡት ሌላው ሐሳብ ደግሞ መድኀኒታችን የመንፈስ ቅዱስን ከአብ መሥረጽ ጉዳይ የተናገረው የራሱንም ሥል



ጣን ለአብ በመስጠት ራሱን ዝቅ አድርጎ ትሕትናን ለእኛ ለማስተማርና አርአያ ለመኾን ነው ይላሉ ።

የትሕትናን ሕይወት ሊያስተምረን ፈልጎ በአንዳንድ ኹናቴዎች ራሱን ዝቅ የሚያደርግ መኾኑ ባይካድም መሠረታዊ እምነትን በሚመለከት ግን ተገቢውን ትምህርት ከመናገር ተቈጥቦ ምእመናን የተሳሳተ እምነት እንዲኖራቸው አያደርግም ። ልንከተለው የሚገባንን የእምነት አቅጣጫ ከማስተማር የተቈጠበበት ጊዜ የለም ። ለምሳሌ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፤ እኔን የሚከተል ኹሉ የሕይወት ብርሃን ያገኛል ፤ በጨለማም አይመላለስም» በሚልበት ጊዜ ከመሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርቶች አንዱ እንደመኾኑ ራሱን ዝቅ አድርጎ መናገርን አስፈላጊ ኾኖ አላገኘውም ። (ዮሐ. ም. ፰ ቍ. ፲፪)

ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መሥረጽን በመሰለ መሠረታዊ እምነት ላይ መድኀኒታችን እኛ እንድንሳሳት ያላደረገና የማያደርግም መኾኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

## ምዕራፍ ሦስት ፤

## የቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፍ ጉባኤዎችና ውሳኔዎቻቸው

### መግቢያ

ጌታ በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፯ቍ. ፳፩ ላይ «አባት ሆይ ፥ እኔ የም ለምነው ኹሉም አንድ እንዲኾኑ ነው» ብሎ ፈቃዱን በገለጸልን መሠረት ጸላኤ ሠናይ በክርስቲያኖች መካከል ገብቶ በማተራመስና ጥላቻንና የወገናዊነትን ስሜት በመፍጠር የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለኹለት እንዲከፈል እስካደረገበት እስከ አራት መቶ ኀምሳ አንድ ዓመተ ምሕረት ድረስ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ በአንድነት ኖረዋል ። መሠረታዊ እምነትን የሚቃረኑ ኹናቴዎች ባጋጠሙ ጊዜ ኹሉ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እየተሰበሰቡ ለየችግሮቹ የመፍትሔ ውሳኔ ያሳልፉ ነበር እንጂ ችግሮችን እያዩና እየሰሙ ዝም ብለው አያልፉአቸውም ነበር ። ይህም የቤተ ክርስቲያንን ችግር ለማስወገድ በጋራ መፍትሔ የመፈለጉ አሠራር ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የነበረ እንጂ በኋላ ዘመን አዲስ የተጀመረ አሠራር አይደለም ።

### የኢየሩሳሌም ጉባኤ ፶፩ ዓ. ም.

በሐዋርያት ሥራ ም. ፲፭ ላይ እንደምንመለከተው ጳውሎስና በርናባስ የአንጾኪያን ቤተ ክርስቲያን መሥርተው ብዙ አረማውያንን በክርስትና ሃይማኖት ካሳመኑ በኋላ ከፈሪሳውያን ወገን የኾኑ አንዳንድ አማኞች ተነሥተው አረማውያን እንዲገረዙና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ማድረግ ይገባል በማለት ኹከት ባስነሡ ጊዜ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመነጋገርና የመፍትሔ ውሳኔ ለመስጠት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ተሰብስበው ውይይት አደረጉ ። ከውይይቱም በኋላ ሰዎች መርጠው ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ደብዳቤ ለመላክ ወሰኑ ። የተጻፈውም ደብዳቤ እንደሚከተለው ነው ።



«እኛ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ወንድሞቻችሁ በአንጾኪያና በሶርያ ፥ በኪልቅያም ለምትኖሩ ከአረማውያን ወገን ለኾናችሁ ወንድሞቻችን ሰላምታ እናቀርባለን ። ከእኛ መካከል አንዳንድ ሰዎች ሳናዝዛቸው ወደ እናንተ መጥተው በነገሩአችሁ ቃል እንዳስቸገሩአችሁና ግራ እንዳጋቡአችሁ ሰምተናል ። ስለዚህ በአንድነት ከተሰበሰብን በኋላ መልእክተኞችን መርጠን ከተወደዱት ወንድሞቻችን ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር ወደ እናንተ ልንልካቸው ተስማማን ። በርናባስና ጳውሎስ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ናቸው ። ውሳኔአችንን በቃልም ጭምር እንዲነግሩአችሁ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል ።

ከእነዚህ ከሚከተሉት አስፈላጊ ነገሮች በስተቀር ሌላ ከባድ ሸክም እንዳንጭንባችሁ መንፈስ ቅዱስና እኛ ወስነናል ።

፩. ለጣዖት በመሠዋቱ ምክንያት የረከሰ ምግብ አትብሉ ።

፪. ሳይታረድና ደሙ ሳይፈስስ ታንቆ የሞተ እንስሳ አትብሉ ።

፫. ከዝሙት ራቁ ።

ከነዚህ ነገሮች ኹሉ ብትጠበቁ መልካም ታደርጋላችሁ ፤ ደኅና ኹኑ ።»

ይህንንም የውሳኔ ደብዳቤ ካነበቡ በኋላ ምእመናን ተጽናንተው ኖረዋል ።

### የኒቅያ ጉባኤ ፫፻፳፭ ዓ. ም.

ለኒቅያ ጉባኤ ዋና ምክንያት የኾነው የአርዮስ ክሕደት ነው ።

አርዮስ በ፪፻፹ ዓ. ም. በሊብያ ተወልዶ በትምህርት ካደገ በኋላ እንደገናም እስክንድርያ በሚገኘው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ተምሯል ። አንደበተ ርቱዕና ዐዋቂ ሰው እንደነበረ ይነገርለታል ። በዚህም ምክንያት በመጀመሪያ የዲቁና በኋላ ደግሞ የቅስና ማዕረግ ተሰጥቶታል ።

የመንፈሳዊ ዕውቀት ተሰጥዎ የሚገኘው ግን በእግዚአብሔር እርዳታም ጭምር ነው እንጂ የዓለማዊ ፍልስፍናን አጥንቶ በማንብነብ ባለመኾኑ አርዮስ በዓለማዊ ዕውቀቱ በመመርኰዝና ዓላማዊ ምሳሌዎችንም በመስጠት ወልድ ፍጡር ነው ወደሚለው ይቅርታ ወደማይደረግለት ክሕደት ውስጥ ገባ ። ይህንን ክሕደቱን የሰማው በዘመኑ የነበረው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪ ተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ ስሕተተኛነቱን ገልጾለት ከስሕተቱ ተመልሶ በኦርቶዶክሳዊት እምነት እንዲጸና ቢያስጠነቅቀው አሻፈረኝ ብሎ በክሕደቱ በመቀጠሉ ከክህነቱ ሽሮና አውግዞ አባረረው ። በዲዮቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ምክንያት ፓትርያርኩ ተይዞ በታሰረ ጊዜ ውግዘቱን ሳይፈታልኝ ይሞት ይኾናል ብሎ በመፍራቱ ይቅርታ አድርጎ ይፈታው ዘንድ ወደ ፓትርያርኩ አማላጅ ልኮ ነበር ። ፓትርያርኩ ግን አርዮስ በሰማይና በምድር የተወገዘ ይኹን ብሎ ውግዘቱን አጸና እንጂ የአማላጆችን ልመና አልተቀበለም ። የዚህን የእምቢተኛነቱን ምክንያት ለማብራራትና የኑዛዜ ትእዛዙን ለማስተላለፍ ደቀ መዛሙርቱን አርኬላኦስንና እለስክንድሮስን አስጠርቶ እንዲህ አላቸው «እግዚአብሔር የሰማያት አምላክ ሰማዕትነቴን ለፍጻሜ ለማድረስ ይርዳኝና ከዛሬ በኋላ ተመልሳችሁ በሕይወት አታገኙኝም ። አንተ አርኬላኦስ ከእኔ በኋላ ፓትርያርክ ትኾናለህ ! ወንድምህ እለስክንድሮስ ደግሞ ከአንተ በኋላ ፓትርያርክ ይኾናል ። በአርዮስ ላይ ጨካኝ የኾንኩና የተደበቀ ትንኰል ያለኝ አይምሰላችሁ ። አርዮስን ያወገዝኩት እኔ ሳልኾን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ ምክንያቱም በዚህች ሌሊት ጸሎቴን ጨርሼ በተኛሁበት ጊዜ ፊቱ እንደ ፀሐይ የሚያበራና እስከ እግሩ ድረስ ረጅም ልብስ የለበሰ አንድ ወጣት ወደ እኔ ሲገባ አየሁ ። ልብሱም ተቀድዶ የተቀደደውን ልብስ ቁራጭ በእጁ ይዞ ስላየሁት ጌታዬ ሆይ ፥ ልብስህን ማን ቀደደብህ ብዬ በመጮኽ ብጠይቀው ልብሴን የቀደደብኝ አርዮስ ነውና አትቀበለው ። ይቅርታ እንድታደርግለት ሊጠይቁህ ዛሬ የሚመጡ ሰዎች አሉና አትታዘዛቸው አለኝ ። ስለዚህ እናንተም ከአርዮስ ጋር ኅብረት እንዳይኖራችሁ» ሲል አዘዛቸው ።

ፓትርያርኩ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ከሞተ በኋላ በ፫፻፲፪ ዓ. ም. አርኬላኦስ የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን መንበር በተረከበበት ጊዜ አርዮስ በክሕደቱ የተጸጸተ በመምሰል በመንፈሳዊነት መልክ ቀረበ ። የአርዮስ ደጋፊዎችም በአማላጅነት ስለቀረቡ የቀድሞውን ፓትርያርክ አደራ ባለማጤን አርዮስን ተቀብሎ የአንድ ቤተ ክርስቲያን ክህነ



አድርጎ ሾመው ። ይኹን እንጂ አርኬላኦስ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በሞት ተለይቶ እለስክንድሮስ ስለተተካ አርዮስን አውግዞ ክሕደቱንም ተቃወመ ። የአርዮስ ደጋፊዎች ከፓትርያርኩ ጋር ሊያስማሙት ሲሞክሩ ፓትርያርኩ ወደ እነርሱ ትክ ብሎ በመመልከት እንዲህ አላቸው ። «እንዳልቀበልህ አባቴ ስላዘዘኝ ከአንተ ጋር አልገናኝምና ወደ እኔ እንዳትመጣ ብላችሁ ለአርዮስ ንገሩት ፤ ይህም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ስለኾነ ስለ ኀጢአትህ ለመድኀኒታችን ተናዘዝና እርሱ ከተቀበለህ እኔ እንድቀበልህ ያዝዘኛል ።»

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አርዮስ የክሕደት ትምህርቱን ማስፋፋትና ፓትርያርኩን እለስክንድሮስንም በግልጽ መቃወም ጀመረ ። ፓትርያርኩም የአርዮስን የጥፋት ትምህርት በትጋት ለመቋቋም አቅዶ በመንፈሳዊነቱ ፥ በዕውቀቱና በአንደበተ ርቱዕነቱ ታዋቂና በዚያን ጊዜ ዕድሜው ፳፪ ዓመት የነበረውን ሊቀ ዲያቆን አትናቴዎስን ረዳቱና ልዩ ጸሐፊው አድርጎ ሾመው ። በ፫፻፲፱ ዓ. ም. እለስክንድሮስ ሲኖዶስ ሰብስቦ አርዮስን ከምእመናን አንድነት ለይቶ አወገዘው ። እንዲሁም በ፫፻፳፭ ዓ. ም. ከእስክንድርያና ከሊብያ ፪ ጳጳሳት በተገኙበት ጉባኤ እንዲወገዝ አደረገ ።

አርዮስም ከእስክንድርያ ተነሥቶ በአስተሳሰቡ ተስማምተውለት ወደነበሩት ወደ ፍልስጥኤምና ወደ ትንሽዋ እስያ ጳጳሳት ኼደ ። እነርሱም የጥፋት ትምህርቱን እንዲያሠራጭ የፈቀዱለት ከመኾናቸውም በላይ ፓትርያርኩ እለስክንድሮስ ይቀበለው ዘንድ ጠየቁለት ። ፓትርያርኩ ግን የሐንስ ወንጌላዊው «ቃል ከኹሉ በፊት ነበረ ፤ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፤ ይህም ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ያለውን የሃይማኖት ትምህርት በሚቃረነው የጥፋት ትምህርቱ እስከቀጠለ ድረስ አልቀበለውም በማለት እንቢ አለ ። ከጳጳሳቱ መካከል ጥቂቶቹ በእለስክንድሮስ አስተሳሰብ ሲስማሙ ሌሎቹ ግን በ፫፻፳፱ እና በ፫፻፴፫ ዓ. ም. ኹለት ተከታታይ ስብሰባዎችን በማድረግ የፓትርያርኩን የእለስክንድሮስን ፍርድ የሚሽር ውሳኔ አሳለፉ ። አርዮስም ወደ እስክንድርያ ተመልሶ መርዛማ የኾነ ትምህርቱን ያሠራጭ ጀመር ፓትርያርኩ እለስክንድሮስ እንደገና አባርሮት ወደ ነበረበት ተመለሰ ። በዚህን ጊዜ የአርዮስ ደጋፊ የነበረውና በቊስጥንጥንያው ቤተ መንግሥት ተሰሚነት የነበረው የኒኮሚድያው ኤጲስ ቆጶስ ፥ አውሳብዮስ በእለስክንድሮስና በአርዮስ መካከል ባለው አለመግባባት መፍትሔ ለመፈ

ሊግ በጉዳዩ ይገባበት ዘንድ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስን ጠየቀው ። በዚህ ጊዜ ነው ንጉሡ ለጉዳዩ ትኵረት በመስጠት ኦስዮስ የተባለውን ኤጲስ ቆጶስ በወክልና ወደ እስክንድርያ የላከው ። ኦስዮስም በእለስክንድሮ ስና በአርዮስ መካከል ያለውን ኹናቴ ካጠና በኋላ ዓለም ዐቀፋዊ ሲኖዶስ እንዲሰበሰብ ለንጉሡ ሐሳብ አቀረበ ።

በኦስዮስ ማሳሰቢያ መሠረት ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በኒቅያ ከተማ ዓለም ዐቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ እንዲደረግና ለችግሩ መፍትሔ እንዲፈለግለት ለየአብየተ ክርስቲያናቱ መሪዎች ኹሉ ጥሪ አስተላለፈ በጥሪውም መሠረት በስብሰባው ለመገኘት ከመጡት ፫፻፲፰ የዓለም ኤጲስ ቆጶሳት መካከል የእስክንድርያው እለስክንድሮስ ይገኙባቸዋል ። ከእርሱም ጋር ረዳቱና የግል ጸሐፊው ሊቀ ዲያቆን አትናቴዎስ አብሮ መጥቶአል ። ይህ አትናቴዎስ ለኒቅያ ጉባኤና ለክርስቲያን ሃይማኖት ታላቅ አስተዋፅኦ ያደረገ ሰው ነው ።



ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ

በስብሰባውም ኺደት መጀመሪያ ላይ አርዮስ አቋሙን እንዲያብራራ ተጠይቆ ሲናገር «ወልድ ባልነበረበት ጊዜ አብ ነበር ፤ ወልድን ከምንም ፈጠረና የእግዚአብሔር ልጅ እንዲኾን አደረገው ይህም ማለት አብ ወልድን እንደማንኛውም ሌላ ፍጡር ፈጥሮታል ማለት ነው ። አብም ወልድን ከፈጠረ በኋላ ሥልጣን ሰጥቶት ኹሉን ነገር እንዲፈጥር አደረገው» ብሎ ሲናገር ይህ ጽርፈቱ ብዙዎቹን የጉባኤ አባላት ስላበሳጨ ላለመስማት ጆሮአቸውን የሸፈኑም ነበሩ ። በዚህ ጊዜ እለስክንድሮስ ሲጠይቀው አምልኮትና ስግደት የሚገባው ለፈጣሪአችን ነው ወይስ ላልፈጠረን ? አለው ። አርዮስም ለፈጠረን ነው ሲል መለሰ ። እለስክንድሮስም አንተ ራስህ እንደገለጽከው ፍጡር ነው ያልከው ወልድ የፈጠረን ከኾነና ፍጡር ላልኾነው ለአብ የምናቀርበውን አምልኮትና ስግደት ለወልድም ማቅረባችን ክሕደት ነው ፤ ምክንያቱም በአንተ አባባል ፍጡር ነውና ። ይህም ለትምህርትና ለእምነትህ ብልሹነት በቂ ማስረጃ ነው ቢለው አርዮስ ምንም መልስ ሳይሰጥ ጸጥ አለ ።



ከአርዮስ ደጋፊዎች አንዱ የቂሣርያው ኤጲስ ቆጶስ የኅብ እምነቱን እንዲያብራራ በተጠየቀ ጊዜ ከእርሱ በፊት ከነበሩት የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶሳት የተረከባቸው ነው በማለት ስለጌታ መለኮታዊ ክብር ግልጽ ያልኾነና በተድበሰበሰ ኹናቴ እንደሚከተለው አቀረበ ።

«ኹሉን በያዘ፥ የሚታይና የማይታየውን ኹሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ። የእግዚአብሔር ቃል በኾነ በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ፤ ከአምላክ የተገኘ አምላክ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፥ ከሕወት የተገኘ ሕይወት የፍጥረት ኹሉ በኵር አንድያ ልጅ ፥ ከዘመናት በፊት ከአብ የተወለደ ፥ በእርሱ ኹሉ ነገር ተፈጠረ ። ስለ እኛ መዳን ሥጋን ለብሶ በሰዎች መካከል ኖረ ። ሕማምን ተቀብሎ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ ። ወደ አብ ዐረገ ፤ በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በክብር ተመልሶ ይመጣል ።

በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ።»

አቀራረቡ የብዙዎችን አስተሳሰብ ባለመርካቱ ከሚስተካከሉት ጉዳዮች አንዱ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል የሚለው ሐረግ እንዲጨመርበት አትናቴዎስ ያቀረበው ሐሳብ በአርዮስ ደጋፊዎች ዘንድ ተቃውሞ ቢገጥመውም በብዙዎቹ ዘንድ ግን ተቀባይነትን አገኘ ። አትናቴዎስ ባቀረበው ሐረግ ምትክ አርዮሳውያን በመለኮቱ አብን የሚመስል የሚል ሐረግ አቅርበው ተቀባይነት አላገኘም ።

ከዚያ በኋላ ተስተካክሎ በጉባኤው የጸደቀው የእምነት ቀኖና እንደሚከተለው ነው ።

«ኁሉን በያዘ ፡ ሰማዩንና ምድርን፡የሚታይና የማይታየውን በፈጠረ ፡ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ።



ሐዋርያዊው አትናቴዎስ

ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ በተወለደ ፡ የአብ አንድያ ልጁ በሚኾን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፡ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ፡ የተወለደ እንጂ ያል



ተፈጠረ ፡ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል ፡ ኹሉ በእርሱ የኾነ ስለ እኛ ስለ ሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ኾነ ፤ ሰው ኾኖም በጰንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ ሞተ ፤ ተቀበረም ፡ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ።»

ከአርዮስ ለቀረቡ የመከራከሪያ ጥቅሶች ኹሉ መልስ ከተሰጣቸውና ብዙም ክርክሮች ከተካኼዱ በኋላ አርዮስ ተወግዞ እንዲለይ ንጉሡ አዘዘ ።

አርዮስ ተወግዞ ከተለየ በኋላ ጉባኤው ሌሎች የቀረቡ ጉዳዮችን መርምሯል ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

የትንሣኤ በዓል፣የጌታ ትንሣኤ በዓል በምሴሴንት ከቀረበው ከአይሁድ የፋሲካ በዓል በፊት መዋል ስለማይገባውና ጌታም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን በዓል ያከበረው ከስቅለቱ በፊት በመኾኑ የትንሣኤ በዓል ኹልጊዜ ከአይሁድ የፋሲካ በዓል በኋላ በሚውለው እሁድ እንዲኾን ተወሰነ ። እንዲሁም የእስክንድርያው ቤተ ክርስቲያን መሪ በየዓመቱ የትንሣኤ በዓል የሚውልበትን ቀን ለሌሎች ጳጳሳት ኹሉ እንዲያሳውቅ ብሎ ጉባኤው ውሳኔ አሳልፎአል ።

የአስዩቱ ኤጲስ ቆጶስ ፡ መላትዮስ፣በግብፅ ኛውም መንበር የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን መሪ በበታቹ ላሉ ኤጲስ ቆጶሳት የበላይ ነው እንጂ ከበታች የሚገኝ ኤጲስ ቆጶስ ተነሥቶ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጪ መኾን የለበትም ። በዚህም መሠረት መላትዮስ ከማንኛውም የክህነት ሥልጣን ተሽሮ እንደ ተራ ሰው እንዲኖር ተወሰነ ።

የመላትዮስ ጥፋት እንደሚከተለው ነበር ።

ጊዜው ዲዮቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረበት ዘመን በመኾኑ መላትዮስ ተይዞ ወደ እስር ቤት ሲወሰድ የሰማዕትነትን አክሊል ለመቀዳጀት በመዘጋጀት ፈንታ ለዚህ ዓለም ሕይወቱ በመፍራት

ሃይማኖቱን ከዶ ለጣዖት አጠነ ። በእስር ቤትም እያለ ኤጲስ ቆጶሳት ጓደኞቹ በእምነቱ እንዲጸና የማበረታቻ ምክር ልከውለት ነበር ። ይሁን እንጂ ምክራቸውን አልተጠቀመበትም ። በኋላ ግን በንስሐ ተመል ሷል ። ከዚህ ኹሉ በደል በኋላ የመንበሩን የበላይ ኀላፊ ሥራ ለራሱ አድርጎ ኤጲስ ቆጶሳትን ቀሳውስትንና ዲያቆናትን በመሾም ከእስክን ድርያ መንበር የመገንጠል ዝንባሌ በማሳየት የፓርትያርኩን ትእዛዝ የማይቀበል ኾነ ። ከዚያ በኋላ ፓትርያርኩ ተፍጻሚ ተሰማዕት ጴጥ ሮስ ጳጳሳትን ሰብስቦ በሲኖዶስ መላትዮስና እርሱ የሾማቸው ኹሉ እንዲሻሩ ወሰነ ። ፲ ዚህም ኹሉ ጋር ሥልጣን እንዳለው ኾኖ ቀጠለ እንጂ በሲኖዶሱ ውሳኔ መሠረት አላቆመም ።

የመናፍቃን ጥምቀት፣መናፍቃን ያጠመቁአቸው ሰዎች በሥሉስ ቅዱስ ስም አምነው ስለማያጠምቁ ጥምቀታቸው አይጸናም ። በቤተ ክርስቲ ያን ሕጋዊ ጥምቀት ተጠምቆ የነበረ ሰው ወደ መናፍቅነት ኮተለወጠ በኋላ እንደገና በንስሐ ቢመለስ ድጋሚ ጥምቀት አያስፈልገውም ብሎ ጉባኤው ወሰነ ።

የድንግልና ኑሮ ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ኹሉ በማንኛውም የክ ህነት ደረጃ ላይ ቢኾኑ በድንግልና መኖር አለባቸው ተብሎ ለቀረበው ሐሳብ በፍናትዮስ የተባለው ኤጲስ ቆጶስ አስተያየቱን ሲሰጥ እንዲህ አለ «ከጥቅም ይልቅ ጉዳትን እንዳያስከትል በካህናት ላይ ይህንን የመ ሰለ ቀንበር ሊጫንባቸው ተገቢ አይደለም ።» ጉባኤውም በዚህ አስተ ያየት ተስማምቶ ካህናት ሚስት ያገቡ እንዲኾኑ እንዲፈቀድና ኤጲስ ቆጶሳት ብቻ በድንግልና እንዲኖሩ ፣ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸው ካህ ናት ደግሞ እንደገና እንዳያገቡ ሲል ወሰነ ።

<u>የኒቅያ ጉባኤ ቀኖናዎች</u> ፣

ጉባኤው ከመፈጸሙ በፊት የተሰበሰቡት አባቶች የቤተ ክርስቲ ያንን አስተዳደር በሚመለከት ሃያ ቀኖናዎችን ደንግገዋል ።

፩. በሕመም ምክንያት ሐኪሞች ጃንደረባ ያደረጉት ፣ ጠላት በማ ጥቃት ጃንደረባ ያደረገው ፣ ወይም አለቃው ለቤቱ ጠባቂነት ሲል ጃንደረባ ያደረገው ሰው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቁ ኾኖ ከተ ገኘና ወደ ክህነት አገልግሎት ለመግባት ቢፈልግ ሕጉ ይፈቅድለታል ።



ራሱን በፍላጎቱ ጃንደረባ ያደረገ ሰው ማዕረገ ክህነት አይፈቀድ ለትም ። በክህነት አገልግሎት ላይ እያለ ራሱን ጃንደረባ ያደረገ ሰው ከክህነት ሥልጣን መሻር ይኖርበታል ።

፪. በጣም አስፈላጊ ኾኖ በመገኘቱ ወይም በግድ.ታ ሊኾን ቢችልም የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና የሚቃረኑ ብዙ ኹናቴዎች ተፈጽመዋል ። ከአረመኔነት ገና አዲስ የመጡ ሰዎች ጥቂት ጊዜ ብቻ ትምህርት ከተ ሰጣቸው በኋላ በቶሎ ተቀባይነት አግኝተው ወዲያው እንደተጠመቁ ለኤጲስ ቆጶስነት ወይም ለክህነት ይመደባሉ ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን እንደዚህ ያለው ጉዳይ መከልከል አለበት ። ሐዋርያው ጳውሎስም አዲስ አማኝ ከጥምቀት በኋላ በቂ የልምምድ ጊዜ ሲኖረው እንደሚ ገባ ሲያስረዳ «በትዕቢት ተነፍቶ ዲያብሎስ እንደተፈረደበት እንዳይ ፈረድበት አዲስ ክርስቲያን የቤት ክርስቲያን መሪ አይኹን» ብሏል ። (፩ኛ ጢሞ. ም. ፫ ቁ. ፮)

፫. ከእናቱ ፣ ከእኅቱ ፣ ከአክስቱ ወይም በእንደዚህ ያለ ኹናቴ ከማት ታሰብ ሴት ጋር ካልኾነ በቀር አንድ ኤጲስ ቆጶስ ፣ አንድ ካህን ፣ አንድ ዲያቆን ፣ ወይም ሌላ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከማንኛዋም የውጪ ሴት ጋር አብሮ እንዳይኖር ታላቁ ጉባኤ በጥብቅ ከልክሏል ።

፬. ኤጲስ ቆጶስ የሚሰየመው ቢቻል በሀገረ ስብከቱ በሚገኙት ኤጲስ ቆጶሳት ኹሉ እጅ ኾኖ ያለበለዚያ ግን ቢያንስ በሦስት ኤጲስ ቆጶሳት እጅ መኾን ይኖርበታል ። ለዚሁም ቀሪዎቹ በምርጫው የተስማሙ መኾናቸውን በጽሑፍ ሊያረጋግጡ ይገባል ። ኾኖም አንብሮተ እዱ በርእሰ ኤጲስ ቆጶሳቱ አማካይነት ካልኾነ አይጸናም ።

፭. በየሀገረ ስብከቶች ኤጲስ ቆጶሳት ከኅብረት ስለከለከሉአቸው ካህናት ወይም ምእመናን ወገኖች በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት እንዳያ ገኙ የሚወሰነው አስተያየት በሕጉ መሠረት ይጠበቅ ። የተከለከሉ በት ምክንያት ምንአልባት ከመንፈስ ደካማነት የተነሣ ፣ ወይም በመ ጣላት ፣ ወይም ደግሞ የኤጲስ ቆጶሱ የግል ጥላቻ እንዳይኾን ምርመራ ያድርጉ ። ተመሳሳይ ኹናቴዎችን ለመመርመር የየሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጶሳት በአጠቃላይ በዓመት ኹለት ጊዜ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል ። ኹለቱ ስብሰባዎች መካኼድ ያለባቸው አንዱ ከዐቢይ ጾም በፊት ለእግ ዚአብሔር ንጹሕ ስጦታ ለማቅረብና ኹለተኛው ደግሞ በመጸው

ነው ። በኤጲስ ቆጶሱ ላይ በደለኞች ኾነው የተገኙ ሰዎች የኤጲስ ቆጳሳቱ ጉባኤ ይቅርታ እስኪያደርግላቸው ድረስ ከኅብረት የተከለከሉ ይኾናሉ ።

፮. በግብጽ ፤ በሊብያና በአምስቱ ከተሞች ከቀድሞ ጀምሮ የነበረው ልማድ እንደተጠበቀ ይኖራል ። ይህም ልማድ የእስክንድርያው ኤጲስ ቆጶስ ሥልጣን በሦስቱ ኹሉ ላይ እንደኾነ የሮማው ኤጲስ ቆጶስም የዚሁ ዐይነት ልማድ አለው ። የአንጾኪያ መንበርና የሌሎችም ሀገረ ስብከቶች ይህንኑ ልማድ ይከተሉ ። በአጠቃላይ አንድ ኤጲስቆጶስ ያለ ርእስ ኤጲስቆጶሳቱ (ሜትሮፖሊቱ) ፈቃድ መሾም የማይገባው መኾኑን ታላቁ ጉባኤ ወስኖአል ። የኹለቱ ወይም የሦስቱ አስተያየት ከሌሎቹ ኤጲስ ቆጶሳት የተለየ ቢኾን በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት በድምፅ ብልጫ ይወሰን ።

፯. ከቀድሞ ጀምሮ ተያይዞ በመጣው ልማድና ባህል (ተውፊት) እንደተመለከተው የኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ የተለየ ክብር አለው ። ድርጊቱ ዋናይቱ ከተማ ቂሣርያ ያላትን ክብር የማይጐዳ ኾኖ ለኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ።

፰. ንጹሓን ነን የሚሉ ሰዎች ራሳቸውን ዓለም ዐቀፋዊትና ሐዋርያዊት ወደኾነችው ቤተ ክርስቲያን ሲያቀርቡ አንብሮተ እድ ተደርጎላቸው በዚሁ ኹናቴ ወደ ክህነት አገልግሎት ሊገቡ እንደሚችሉ ታላቁ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ አሳለፈ ። ከዚያ ኹሉ በፊት ግን የቤተ ክርስቲያንን አንድነት (ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ መኾንን) እንደሚፈልጉ ሥርዓትዋንም እንደሚያከብሩ በጽሑፍ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ።

፱. ኹናቴአቸው ሳይመረመር ካህናት የኾኑ ሰዎች ወይም ኹናቴአቸው ሲመረመር ስለኀጢአታቸው ከተናዘዙ በኋላ በሕገወጥ መንገድ ቢሾሙ እንደዚህ ያሉትን ቀኖናው የማይቀበላቸው ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው ንቁሑ የሌለበትን መሪ በመኾኑ ነው ። (፩ኛ ጢሞ. ምዕ. ፫ ቍ. ፪)

፲. ማንኛውም ኃጢአተኛ ሰው ማንነቱ ባለመታወቁ ወይም በሺሚዉ ዘንድ እየታወቀ አንድ የክህነት ደረጃ ቢሾም ሕግ የሚያዝዘው ይፈጸምበታል ። ይህም ማለት ከሹመቱ መሻር ማለት ነው ።



፲፩. ሳይገደዱ ፤ ምንም ንብረት ሳይወሰድባቸው ፤ ያለ ምንም አደጋ ማለት በአምባ ገነኑ (መብት ገፋፊው ፤ ፈላጭ ቈራጩ) በሊኪኒዩስ ዘመን እንደተደረገው ያለ ችግር ሳይደርስባቸው ለወደቁ ሰዎች ኹሉ ርኅራኄ ማድረግ ለጉባኤው አስፈላጊ ኾኖ ታይቶታል ። እውነተኛ ጸጸትን የተጸጸቱ ሰዎች ሦስት ዓመት ከሰሚዎች ጋር ማሳለፍ ይኖርባቸዋል ! ሰባት ዓመት ይስገዱ ። ቅዱስቍርባንን ሳይቆርቡ ለኹለት ዓመት ከሕዝቡ ጋር በጸሎት ይሳተፉ ።

፲፪. በጸጋ የተጠሩና የመጀመሪያውንም እርምጃ ያሳዩ ፤ ከዚያ በኋላ ግን ያንን ትተው እንደ ውሾች ወደ ትውኪታቸው ከተመለሱት ጥቂቶች ወደ ውትድርናው ለመመለስ ፈልገው ብርና ስጦታ የሰጡት ሰዎች ኹናቴአቸው የሚወሰነው ከሰሚዎች ጋር ሦስት ዓመት ከፈጸሙ በኋላ ዐሥር ዓመት እንዲሰግዱ ነው ። ከዚህ ኹሉ ጋር ዝንባሌአቸውና የንስሓቸው ኹናቴ ሊመረመር ይገባል ። አመላለሳቸው በፍርሀት ፤ በእንባ ፤ በትዕግሥትና በበጎ ተግባር እንጂ በማስመሰል ብቻ አለመኾኑ ከታየ የመስሚያውን ጊዜ ከፈጸሙ በኋላ በጸሎት ሊሳተፉ ይገባል ። ከዚያም በኋላ ኤጲስ ቆጶሱ ኹናቴአቸውን በበለጠ ርኅራኄ ሊመለከትላቸው ይችላል ። ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለሳቸውን ብቻ በቂ ነው ብለው የሚያስቡ ግድ የሌላቸው ሰዎች ግን የተወሰነውን ዘመን ይፈጽሙ ።

፲፫. የጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ደንብ እንደሚያመለክተው አንድ ለሞት የተቃረበ ተነሳሒ ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል የሚፈቀድለት ሲኾን ከዚያ በኋላ ከሕመሙ ቢፈወስ ግን ብቁ መኾኑ ካልተረጋገጠ በቀር በሞት አፋፍ ላይ በነበረ ጊዜ በመቍረቡ ብቻ ከዳነም በኋላ ለመቍረብ ብቁ ኾነ ማለት ባለመኾኑ ብቁ እስኪኾን ድረስ ክፍሉ ለመቁረብ ገና ከኾኑ ጸሎተኞች ጋር ኅብረት እንዲኖረው ነው ።

፲፬. የሃይማኖት ደቀ መዛሙርት በኀጢአት ቢወድቁ ሦስት ዓመት ከሰሚዎች ጋር ካሳለፉ በኋላ ከሃይማኖት ደቀ መዛሙርት ጋር እንዲጸልዩ ይፈቀድላቸው ዘንድ ታላቁ ቅዱስ ሲኖዶስ ወሰነ ።

፲፭. በብዙ ሁከትና ጠብ ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች ያለው ልማድ በፍጹም እንዲቀር አስፈለገ ። የአንድ ኤጲስ ቆጶስ ፤ የአንድ ካህን ፤ ወይም የአንድ ዲያቆን ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ መዛዋወር ሐዋርያዊውን ሕግ የሚቃረን አሠራር ነው ።

፲፮. ፈሪሀ እግዚአብሔር ሳይኖራቸውና የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ሳያውቁ ቤተ ክርስቲያናቸውን ትተው ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሚኼዱ ቀሳውስት ፣ ዲያቆናትና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በሌላ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም ። ወደ ነበሩበት ቤተ ክርስቲያን መመለስ ይኖርባቸዋል ። እንቢ ብለው ቢኼዱ ግን ኅብረት እንዳይፈቀድላቸው መደረግ አለበት ። አንድን ቤተ ክርስቲያን ትቶ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የኼደን ሰው ከመጣባት ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ሳያገኝ አንድ ኤጲስ ቆጶስ በድፍረት ክህነትን ሰጥቶ ቢቀበለው ያ ሹመቱ ዋጋ የሌለው ይኾናል ።

፲፯. «ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር . . . ለዘላለም አይታወክም» የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር ረስተው አስከፊ የኾነውን ስስትና ወራዳ የኾነውን አራጣ በመፈለግ ብዙዎች ሰዎች ገንዘባቸውን በአራጣ ያበድራሉ ። (መዝ. ፲፭ቍ. ፭)

ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ለመኖሪያው እንኳ ቢኾን ይህ ቀኖና ከተደነገገበት ጊዜ ጀምሮ በአራጣ ገንዘብ አበድሮ ቢገኝ ከሚመተ ክህነት ተሽሮ ተራ ሰው እንዲኾን ጉባኤው ወስኖአል ።

፲፰. በአንዳንድ ከተማዎችና በአንዳንድ ቦታዎች ዲያቆናት ለቀሳውስት ሥጋ ወደሙ የሚያቀብሉ መኾናቸውን ይህ ታላቁ ሲኖዶስ ለማወቅ ችሏል ። ይህ ድርጊት በሕጉም በኩል ኾነ በባህሉ ቍርባኑን ለማቅረብ ሥልጣን ያላቸው ወገኖች ከሚያቀርቡላቸው ወገኖች የጌታን ሥጋ መቀበል ከመሠረቱ ያልተረከብነው ነው ። እንዲሁም አንዳንድ ዲያቆናት ከኤጲስ ቆጶሳት በፊት እንደሚቈርቡ ታውቋል ። ይህ ኹሉ ድርጊት ቀርቶ ዲያቆናት ከወሰናቸው አይለፉ ። የኤጲስ ቆጶሳት አገልጋዮች መኾናቸውንና ደረጃቸውም ከቀሳውስት ዝቅ ያለ መኾኑን ተገንዝበው ማንነታቸውን ይወቁ ። የሚቈርቡት ከቀሳውስት ባኋላ ኾኖ የሚያቈርባቸውም ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ ነው ። እንዲያውም ዲያቆናት በቀሳውስት መካከል መቀመጥ የለባቸውም ፤ ምክንያቱም ይህ ድርጊት ሕግንና የደረጃ ቅደም ተከተልን ይቃረናልና ። ከዚህ ውሳኔ በኋላ ራሱን ዝቅ ለማድረግ የማይፈልግ ዲያቆን ካለ ከዲቁና አገልግሎት መታገድ ይኖርበታል ።

፲፱. የጳውሎስ ሳምሳጢ ተከታዮች የነበሩ ወደ ዓለም ዐቀፋዊቱ ቤተ ክርስቲያን በሚመለሱበት ጊዜ የግድ እንደገና በሥላሴ ስም መጠመቅ



ይኖርባቸዋል ። ቀድሞ ካህናት የነበሩና ነቀፋ የሌለባቸው ከኾኑ ከተጠመቁ በኋላ የዓለም ዐቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ሊሾማቸው ይገባል ። ከምርመራ በኋላ ግን ነቀፋ ከተገኘባቸው ይሻራሉ ።

፳. አንዳንድ ሰዎች በዕለተ እሁድና በበዓለ ኀምሳ በጉልበታቸው ተንበርክከው ይጸልያሉ ። በነዚያ ቀኖች ግን ሰዎች ኹሉ ቆመው እንዲጸልዩ ለኹሉም በያለበት ሕግ ይኾን ዘንድ ቅዱሱ ሲኖዶስ ወስኗል ።

የኒቅያ ጉባኤ በተፈጸመ በአምስተኛው ወር የእስክንድርያው ፓትርያርክ እለስክንድሮስ በሞት ስለተለየ በምትኩ ለኒቅያ ጉባኤ የመጨረሻ አርኪ ውጤት ታላቅ አስተዋፅኦ ያበረከተው አትናቴዎስ ተሾመ ።

እለስክንድሮስ እንደሞተ አርዮሳውያን አርዮስን ከግዞት ለማስመለስ ብዙ ሙከራ አደረጉ ። ይህንንም ሙከራ ያደረጉት የአርዮስን እምነት ተቀብላ በነበረችው ቆስጠንዲያ በተባለችው በንጉሡ ንጉሥቱ በቈስጠንጢኖስ እኅት አማካይነት ነው ። አርዮስም በንስሓ የተመለስ በማስመሰል ንጉሡን አታለለው ። በ፫፻፳፱ ዓ. ም. የአርዮስ ደጋፊ የነበረው የኒቆሚድያው ኤጲስ ቆጶስ አውሳብዮስና ሌሎች የአርዮስ ወዳጆች ስብሰባ አድርገው አርዮስ ከግዞቱ እንደተፈታ ወሰኑ ። የውሳኔአቸውንም ግልባጭ በማያያዝ አትናቴዎስ አርዮስን እንዲቀበለው መልእክት ላኩ ። አትናቴዎስ ግን አርዮስን ሳለመቀበል እምቢተኛ ኾነ ። ይህንንም በዝርዝር ለንጉሥ ንግሥቱ ጽፎ አስተላልፎአል ። አርዮሳውያን በዚህ ዕድል ተጠቅመው በአትናቴዎስና በንጉሡ መካከል አለመግባባት እንዲፈጠር አድርገዋል ። አትናቴዎስንም ለመበቀል በተጀመረው ዘመቻ በጢሮስ ከተማ አትናቴዎስ የሚገኝበት ስብሰባ እንዲደረግ ተወሰነ ። በዚህ ጉባኤ ከነበሩት አባሎች መካከል አብዛኞዎቹ አርዮሳውያን የአትናቴዎስ ጠላቶች ስለነበሩ በግፍና በተጽዕኖ አትናቴዎስ ወደ ግዞት እንዲላክ ወስነው ንጉሡም ፈቃዳቸውን በመፈጸም ትሬቭ ወደ ተባለች ከተማ አጋዘው ። ይህም በጢሮስ ከተማ ጉባኤ ላይ አትናቴዎስ በሐሰት ክስ ተከሶ ነጻ ቢወጣም እንኳ በሰበብ በአስባቡ ወደ ግዞት እንዲላክ የተደረገበት ዘመን በ፫፻፴፭ ዓ. ም. ነው ። የአትናቴዎስ ወደ ግዞት መላክ ለአርዮሳውያን አመቺ ኾኖ በመገኘቱ በምትኩ አርዮስን ለመሾም ቢሞክሩ ምእመናን ስላልተስማሙ አጥር ደው አባረሩት ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ወደቍስጥንጥንያ አስጠርቶ በጊዜው የቍስጥንጥንያ መንበር ፓትርያርክና የአትናቴዎስ ደጋፊ የነበ

ረውን እለክንድርን አርዮስን ተቀብሎ ከእርሱ ጋር አብሮ እንዲቀድስ አዘዘው ። ፓትርያኩ ግን መልሶ አርዮስ ወልድን ፍጡር ነው የሚል የተበላሸ እምነት እያለው እንዴት አድርገን ከምእመናን አንድነት ጋር እንቀበለዋለን ብሎ ቢጠይቅ አሁን አርዮስ በንስሓ ተመልሷል አለው ። ፓትርያርኩም እንግዲያውስ እምነቱን በጽሑፍ ያረጋግጥና ቃለ መሐላ ይሰጥ አለው ። አርዮስም ዋና እምነቱን በልቡ ውስጥ አምቆ የተ ጠየ ቀውን በውሸት ጻፈ ። በዚህ ጊዜ የአርዮስን ተንኰል የተረዳው ፓት ርያርክ ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ መሬት ላይ በመውደቅ እንዲህ ብሎ ጸለየ «አርዮስ መቅደስህ ውስጥ ገብቶ የሚቀድስ ከኾነ ባርያህን ከዚህ ሕይወት አሰናብተው ፤ ወይም የጥፋት ትምህርቱን ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ይዞ እንዳይገባ አርዮስን ከልክለው ።

አርዮስ ተቀባይነት እንዲያገኝ የንጉሡ ትእዛዝ ከተላለፈ በኋላ በወዳጆቹና በደጋፊዎቹ ታጅቦ በደስታ እየተነጋገረ ወጣ ። ይኹን እንጂ ወደዚያው ከእነርሱ ተለይቶ ወደ መጸዳጃ ቤት ኼደና አሽከሩ ውጪ ኾኖ እንዲጠብቀው ነገረው ። እዚያም በመዘግየቱ አሽከሩ በሩን አንኳኵቶ መልስ ስላጣ በሩን በከፈተ ጊዜ የአርዮስ ሆድ ዕቃ ተዘርግፎና ሰውነቱም በመሬት ላይ ተዘርሮ ሞቶ ተገኘ ። በዚህም የአርዮስ ፍጻሜ ይኹን እንጂ የጥፋት ትምህርቱ ግን ብዙዎችን በክሎ ስለነበረ በአትናቴዎስና በአርዮሳውያን መካከል በተደረገው ፍልሚያ አርዮሳውያን ከነገሥታቱ ጋር በመመሳጠር ቅዱስ አትናቴዎስን አም ስት ጊዜ ያኽል ከመንበሩ እየተወሰደ ወደ ግዞት እንዲላክ አድርገዋል ።

## የቍስጥንጥንያ ጉባኤ ፫፻፹፩ ዓ. ም.

በቍስጥንጥንያ የተሰበሰበው ዓለም ዐቀፋዊ ጉባኤ ሦስት ክሕደቶ ችን እንዲመረምር ቀርቦለት ነበር ። እነዚህም አንደኛ የአቡሊናርዮስ ፤ ኹለተኛ የአውሳብዮስ ፣ ሦስተኛ የመቅዶንዮስ ክሕደቶች ናቸው ።

አቡሊናርዮስ ፣ ይህ ሰው የላዖዲቅያ ኤጲስ ቆጶስ ነበር ። የፍልስፍና ትም ህርቱም ወደ ክሕደት አመራው ። የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ መለ ኮት የሥጋ በኾነች ነፍስ ቦታ ተተክቶ ሕማምን ፣ ስቅለትንና ሞትን ከሥጋ ጋር ተቀበለ ብሎ አስተማረ ። በመለኮታዊ አካሎች መካከል ደግሞ መበላለጥ መኖሩን አምኖ መንፈስ ቅዱስ ትልቅ ነው ፤ ወልድ የበለጠ ትልቅ ነው ፤ አብ ግን ከኹሉም በላይ ትልቅ ነው አለ ።



አውሳብዮስ ፣ የሰባልዮስን ክሕደት በማደስ እግዚአብሔር አንድ አካል እንጂ ሦስት አካል የለውም ። ሥላሴ በመባል ስለሦስትነት የሚነገረ ውም በዘመን ኦሪት እንደ አብ ስለተገለጠ ፣ በዘመነ ሐዲስ ሰው ኾኖ እንደ ወልድ ስለተገለጠና እንደ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በሐዋርያት ላይ ስለወረደ ነው ብሏል ።



ትልቁ ቴዎዶስዮስ

መቅደንዮስ ፣ ይህ ሰው ከአርዮስ ተከታዮች አንዱ ነበር ። በንጉሥ ቈስ ጠንስ ዘንድ አርዮሳውያን በነበራቸው ተሰሚነት በ፫፻፵፪ ዓ.ም. የቍስ ጥንጥንያ ኤጲስ ቆጶስ ኾኖ ተሾመ ። በትምህርቱም መንፈስ ቅዱስ በፍጥረቱ ኹሉ ዘንድ የተሠራጨ የእግዚአብሔር ፍጡር ነው እንጂ በአብና በወልድ ደረጃ አንድ አካል አይደለም ፤ በመላእክት መልክ ተፈጥሮ ከመላእክት ግን ከፍ ያለ ነው ብሏል ።

በ፫፻፷፪ ዓ. ም. ቅዱስ አትናቴዎስ ከግዞት ወደ መንበሩ በተመ ለሰ ጊዜ በእስክንድርያ ሲኖዶስ ሰብስቦ አውግዞታል ። ሌሎችም እን ደዚሁ አውግዘውታል ።

ታላቁ ቴዎዶስዮስም ዓለም ዐቀፋዊ ጉባኤ ተሰብስቦ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲወያይበት አዘዘ

በስብሰባው ከተገኙት አባቶች መካከል የእስክንድርያው ጢሞቴ ዎስ ፥ የአንጾኪያው መላትዮስ ፥ ነባቤ መለኮት የእንዚናዙ ጎርጎርዮ ስና የኒሲሱ ጎርጎርዮስ ይገኙባቸዋል ።

ስብሰባውም በ፫፻፹፩ ዓ. ም. በታላቁ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግ ሥት በ፻፶ ኤጲስ ቆጶሳት አባልነት ተካኼደ ።

መቅዶንዮስ እምነቱን ለጉባኤው እንዲያቀርብ ተጠይቆ በዮሐ ንስ ወንጌል ም. ፩ ቁ. ፫ ላይ «ኹሉ ነገር በእርሱ ተፈጠረ፤ ከተፈጠረው ኹሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ የለም» የሚለውን ጥቅስ መሠረት በማድ ረግ መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ነው አለ ። ጉባኤውም መልስ ሲሰጠው «አንድ መንፈስ እርሱም የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ አለ ። የእግዚ አብሔር መንፈስም የእግዚአብሔር ሕይወት መኾኑ የታወቀ ነው ። አንተ እንደምትለው የእግዚአብሔር ሕይወት ፍጡር ነው ካልን እግ ዚአብሔር ሕያው አይደለም ማለታችን ነው ። ሕያው አይደለም የም ንል ከኾነ ደግሞ ትልቁ ክሕደታችን እዚህ ላይ ነው» አለው ።

ጉባኤውም መቅዶንዮስን አሳምኖ ወደ ኦርቶዶክሳዊት እምነት ሊመልሰው ቢሞክር መቅዶንዮስ ፈቃደኛ ባለመኾኑ ካወገዘው በኋላ በኒቅያ ጉባኤ የተጀመረውን የሃይማኖት ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ እና ምናለን ከሚለው ጀምሮ እስከመጨረሻው ድረስ አድርሶታል ። ንጉሥ ቴዎዶስዮስም መቅዶንዮስ ወደ ግዞት እንዲወሰድ ፈርዶበታል ።

እምነቱን እንዲያብራራ አውሳብዮስ ባተጠየቀ ጊዜ «ሥላሴ ስንል አንድ አካል አንድ መለኮት ያለው አምላክ ማለታችን ነው እንጂ ሦስት አካል ማለታችን አይደለም» አለ ። የጉባኤው ሰብሳቢ የነበረው የእስክንድርያው ጢሞቴዎስም እንዲህ ሲል መለሰለት «ሥላሴ አንድ አካል ብቻ ከኾነ ሥላሴ የሚለው ስም አይኖርም ፤ በአብ ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቅኸው ጥምቀትም ዋጋ የለውም ማለት ነው ። እንደ አባባልህም ከኾነ ሥላሴ ሕማምን ተቀብሎ ሞቷል ማለት ነው ፤ ወልድ በዮርዳኖስ መቆሙን ፥ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መውረዱንና አብ ደግሞ በሰማይ ኾኖ መጣራቱን የሚመሰክረው የወ ንጌል ቃል ተሻረ ማለት ነው ።»



ከክሕደቱም እንዲመለስ ምክር ተሰጥቶት ስላልተመለሰ በውግ ዘት እንዲለይ ተደርጓል ።

የአውሳብዮስ ክሕደት መሠረቱ ሰባልዮስ ሲኾን የዚህ የሰባልዮስ ዕድገት ቦሊብያ ነው ። ይህንንም ክሕደቱን እስከ ሮም ድረስ አድርሶ ታል ። የሰባልዮስንም ክሕደት በ፪፻፷፫ ዓ. ም. በሮምና በ፪፻፷፩ ዓ. ም. ደግሞ በእስክንድርያ የተሰበሰቡት የየሀገሩ ሲኖዶሶች አውግዘውታል ።

አቡሊናርዮስ ደግሞ በተራው ስለ እምነቱ ተጠይቆ ሲመለስ «ወልድ ሰው የኾነው ያለነባቢት ነፍስ መለኮቱ ከሰው ልጅ ሥጋ ጋር በመዋሐድ ነው ፤ ምክንያቱም መለኮቱ በነፍስና በአስተሳሰብ ቦታ ተተክቶ ገብቷልና ነው» አለ ።

ጉባኤውም ለአቡሊናርዮስ አባባል የሚከተለውን መልስ ሰጥ ቶታል «እግዚአብሔር ወልድ ከጠባያችን ጋር የተዋሐደው ሊያድነን ብሎ ነው ። እንስሳዊ ሥጋን ብቻ የተዋሐደ ከኾነ እንስሳትን እንጂ ሰውን አያድንም ማለት ነው ። ምክንያቱም የሰው ልጅ በትንሣኤ ሙታን ጊዜ የሚነሣው ነባቢትና ዐዋቂት በኾነች ነፍስ ኾኖ የጽድቅ ወይም የኵነኔ ውሳኔ የሚቀበለው በዚሁ ነውና ። የአምላክ ሰው መኾን ጥቅሙም እዚህ ላይ ነው ። በነባቢትና ዐዋቂ በኾነችው ነፍስ ባይዋ ሐድ ኖሮ ራሱን የሰው ልጅ ብሎ ባልጠራም ነበር ።»

አቡሊናርዮስ ከክሕደቱ እንዲመለስ ጉባኤው ብዙ ቢመክረውም ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመኾኑ በውግዘት እንዲለይ ተደርጓል ።

ከዚህ በኋላ ጉባኤው ሰባት ቀኖናዎችን ደንግጎ ሥራውን ፈጽሞ አለ ።

፩. በኒቅያ የተሰበሰቡት የ፫፻፲፰ አባቶች ውሳኔ ማንም የሚቃወመው ሰው መኖር የለበትም ብለው በቍስጥንጥንያ የተሰበሰቡት አባቶች ወሰኑ ።

፪. ኤጲስ ቆጶሳት ኹሉ ከአስተዳደራቸው ውጪ በኾነ ሀገረስብከት ጉዳይ ውስጥ መግባት አይኖርባቸውም ። ማነኛውም ኤጲስ ቆጶስ ተጋ ብዞ ካልኾነ በቀር በሌላ ሀገረ ስብከት ለመሾም ወይም ሌላ ያስተዳደር ሥራ ለማከናወን መብት የለውም ። በአረማውያን ሀገሮች ለሚገኙ

የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ግን በአባቶች ልማድ መሠረት ይፈጸም ።

፫. ቍስጥንጥንያ አዲስዋ ሮማ እንደመኾንዋ የኤጲስ ቆጶስዋም ክብር ከሮማው ኤጲስ ቆጶስ ቀጥሎ የአንደኛነት ማዕረግ ይኖረዋል ።

፬. በእርሱ ምክንያት በቍስጥንጥንያ ስለደረሰው መተራመስ ኪኒቃዊው መክሲሞስ ኤጲስ ቆጶስ እንደኾነ መታሰብ አይገባውም ። ምንም የክህነት ማዕረግ የለውም ። በእርሱ አማካይነት ማዕረገ ክህነት የተቀበሉ ኹሉ ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው ።

፭. በምዕራብ የተፈጸመውን በሚመለከት በአንጾኪያም ያሉትን በአብ ፥ በወልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስ አንድ መለኮት የሚያምኑትን እንቀበላለን ።

፮. ብዙ ሰዎች ሥልጣነ ክህነትን ለማራከስና የሕዝብን ሰላም ለማደፍረስ ፈልገው ቤተ ክርስቲያንን በሚያስተዳድሩ ኦርቶዶክሳውያን ኤጲስ ቆጶሳት ላይ ከንቱ የስም ማጥፋት ክስ የሚመሠርቱት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐት የሚያቃውሱ ስለሚመስላቸው በመኾኑ በዚህ አጋጣሚ ቅዱሱ ሲኖዶስ ማለት በቍስጥንጥንያ የተሰበሰበው የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ የሚቀርበውን ክስ ሳይመረምር ምስክርነት አይሰማም ። ተቀባይነት የሚኖረውም ከ'ኹሉም አቅጣጫ የሚቀርብ ክስ አይደለም። ኤጲስ ቆጶስ የግል በደል እንዳደረሰ ተደርጎ የሚቀርብ ክስ ግን የከሳሹን ማንነትና እምነት መመልከት የለበትም ። የኤጲስ ቆጶሱ ኀሊና ከኹሉም ነገር ነጻ መኾን ይኖርበታል ። የተበደለውም ሰው ምንም ዐይነት እምነት ቢኖረው መብቱ መከበር አለበት ። በኤጲስ ቆጶሱ ላይ የቀረበው ክስ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ከኾነ ተከሳሾቹን መመርመር ያስፈልጋል ። በክሕደታቸው ተወግዘው የተለዩ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ በሚመለከት በኦርቶዶክሳውያን ኤጲስ ቆጶሳት ላይ ክስ ማቅረብ አይገባቸውም ። ከሳሾቹ ግን በውግዘት ያልተለዩ ወገኖች ከኾኑ ክሳቸውን ለሀገረ ስብከቱ የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ እንዲያቀርቡ ቅዱሱ ሲኖዶስ ያዝዛቸዋል ። የኤጲስ ቆጶሳቱም ጉባኤ ክሱን በጥብቅ መመርመር ይኖርበታል ። የሀገረ ስብከቱ የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ መፍትሔ ለመስጠት የማይችል ከኾነ ከዚያ ከፍ ወዳለ ጉባኤ ይምራው ። ከፍተኛውም ጉባኤ ከሳሾቹን አስጠርቶ ተከሳሹ ከተከሰሰበት ክስ ነጻ ኾኖ ቢገኝ ክሳቸው ሊያስቀጣ የሚችለውን ቅጣት ለመ



ቀበል ፈቃደኞች መኾናቸውን በጽሑፍ ከማረጋገጣቸው በፊት ጉባኤው ክሱን መመርመር አይጀምርም ።

የሀገረ ስብከቱን የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ በማቃለል የተሰጠውን መግለጫ በንቀት ተላልፎ ለንጉሥ ፥ ወይም ለዓለማዊ ፍርድ ቤት ፤ ወይም ለዓለም ዐቀፋዊ ሲኖዶስ ማሰማት ቀኖናዎችንና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐት ማዋረድ በመኾኑ ተቀባይነት የለውም ።

፯. ከክሕደታቸው ተመልሰው ወደ ኦርቶዶክሳዊት እምነትና ወደ ዳኑት ወገኖች ኅብረት የሚመጡትን በቀኖናው መሠረት እንቀበላቸዋለን ። የምንቀበላቸውም የቤተ ክርስቲያንን ቀጥተኛ የእምነት ቀኖና መቀበላቸውን ካረጋገጡና ከቤተ ክርስቲያን እምነት ውጪ የኾኑትን ኑፋቄዎች ካወገዙ በኋላ ነው ።

<u>የኤፌሶን ጉባኤ ፬፻፴፩ ዓ. ም.</u>

የስብሰባው ምክንያቶች የቢላግዮስና የንስጥሮስ ክሕደቶች ናቸው

<u>ቢላግዮስ</u> ፦ ይህ ሰው በ፫፻፷ ዓ. ም. በብሪታንያ የተወለደ ሲኾን ብዙ ጊዜ ወደ ሮምና ወደ ፍልስጥኤም ተመላልሷል ። ከዚያም ከመነኰሰ በኋላ የቅስናን ማዕረግ ተቀብሏል ።

የዚህ ሰው ክሕደት እንደሚከተለው ነው ። «የአዳም ኃጢአት ለልጆቹ አልተላለፈም ፤ አንድ ሰው በሚወለድበት ጊዜ አዳም በኀጢአት ከመውደቁ በፊት እንደነበረው ኾኖ ይወለዳል ። በዚህም አንድ ሰው በተፈጥሮ ጠባዩና በፍላጎቱ ወደ ከፍተኛ የቅድስና ደረጃ የሚደርሰው የእግዚአብሔርን እርዳታ ሳይጠይቅ ነው ብሏል ። ይህ አባባል የተከበረውን የድኅነት (የመዳን) ምሥጢር ዋጋ የሚያሳጣ ፥ የክርስቶስን ደም ክብር የሚቀንስና የሚከተሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች የሚቃረን ነው ።

«እነሆ ፥ በዐመፃ ተፀንስሁ ፤ እናቴም በኀጢአት ወለደችኝ ።» (መዝ. ፶፩ ቁ. ፭)

«በአንድ ሰው ምክንያት ኀጢአት ወደ ዓለም ገባ ፤ በኀጢአትም ምክንያት ሞት መጣ ፤ ይኸውም ሰው ኹሉ ኀጢአት ስለሠራ ሞት በሰው ኹሉ ላይ መጣ ።» (ሮሜ ም. ፭ ቍ. ፲፪)

«በአዳም ምክንያት ሰው ኹሉ እንደሚሞት እንዲሁም በክርስ ቶስ ምክንያት ሰው ኹሉ ሕይወትን ያገኛል ።» (፩ኛ ቆሮ. ም. ፲፭ ቁ. ፳፪)

በዓለም ዐቀፋዊው የኤፌሶን ጉባኤ እስከተወገዘበት ጊዜ ድረስ ይህ መናፍቅ ከአገር ወደ አገር እየተዘዋወረ የጥፋት ትምህርቱን ማስ ፋፋት ቀጥሏል ። -ለ-



ከምሥራቅ አገር የመጡ ጠቢባን ተንበርክከው በመስገድ የወርቅ የዕጣንና የከርቤ ስጦታ አቀረቡለት (ማቴ. ም. ፪ ቁ. ፲፩)

ንስጥሮስ — መናፍቁ ፓትርያርክ ፦ ለኤፌሶኑ ጉባኤ ዋና ምክንያት የኾነው የንስጥሮስ ክሕደት ነው ። በትምህርቱ የክርስቶስን መለኮትና የኢመቤታችንን የአምላክ እናትነት ክዷል ። የክሕደት ትምህርቱም እንዲህ የሚል ነው «የእግዚአብሔር ቃል ከኹሉ በፊት የነበረ መኾ



ኑን አምናለሁ ፤ ማርያም የአምላክ እናት ነች የሚለውን አባባል ግን አላምንም ። የክርስቶስ እናት መኾንዋን አልክድም ፤ እናትነትዋ ግን ለትስብእት ነው ። ማርያም እግዚአብሔርን አልወለደችም ፤ ነገር ግን ከሥጋ የሚወለድ ሥጋ ፥ ከመንፈስ የሚወለድ ደግሞ መንፈስ ነው ። ፍጡር ኾና የወለደችው የእግዚአብሔር መኅደሪያ የሚኾነውን ሰውን እንጂ ፈጣሪን አይደለም ። በዚህም መሠረት ጌታ ኹለት ጠባይ ፥



ቅዱስ ቄርሎስ ኸያ አራተኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ።

ኹለት አካልና ኹለት ፈቃድ አለው ። ሰብአ ሰገል ለሕፃን ጌታ ኢየሱስ መስገዳቸው ስሕተት ነው ፤ ምክንያቱም (በእርሱ እምነት) ሕፃን ጌታ ኢየሱስ መለኮት ያልተዋሐደው ሰው ነውና ።» (ማቴ. ም. ፪ ቁ. ፲፩)

እነዚህን ክሕደቶች ለመመልከት በትንሹ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግሥት በ፬፻፴፩ ዓ.ም. በኤፌሶን ከተማ ኹለት መቶ ኤጲስ ቆጶሳት በአባልነት የተገኙበት ጉባኤ ተሰብስቧል ። የጉባኤውም ሰብሳቢ የእስክንድርያው ትልቁ ቄርሎስ ነበር ።

ጉባኤው ከብዙ ውጣ ውረድ ማለት በስብሰባው እንዲገኝ ከንጉሡ የተወከለው ባለሥልጣን ከንስጥሮስ ጋር በመመሳጠር ብዙ የማስቸገር ሙከራ ካደረገ በኋላና ንስጥሮስ ደግሞ በጉባኤው እንዲገኝ ተመላልሶ የቀረበለትን ጥሪ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመኾኑ በሌለበት ከነክሕደት ትምህርቱ ተወግዟል ። እንዲሁም የቢላግዮስን ክሕደት አውግዟል ።

ከሐዲዎቹንም ከክህነታቸው በመሻርና ከኅብረት በመለየት ፍርዱን የሰጠው ጉባኤ የክርስቶስ መለኮትና ትስብእት ያለ መቀላቀልና ያለ መለያየት ከተዋሐዱ በኋላ ጌታ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ ያለው መኾኑንና እመቤታችንም የአምላክ እናት መኾንዋን በማመን የእምነት ቀኖና መቅድም ውሳኔ አሳልፎአል ። ይህም የእምነት ቀኖና መቅድም እንደሚከተለው ነው ።

የእውነተኛው ብርሃን እናት ሆይ ፥ እናከብርሻለን ፤ መጥቶ ነፍሳችንን ያዳነውን የዓለምን ኹሉ መድኀኒት ስለወልድሽልን ቅድስት ድንግል የአምላክ እናት ሆይ ፥ እናመሰግናሻለን ።

የሐዋርያት መመኪያ ፥ የሰማዕታት አክሊል ፥ የቅዱሳን ዕረፍት ፥ የቤተ ክርስቲያን መሠረት የኾንከውና ኀጢአትን የምታስተሰርይ ጌታችንና ንጉሣችን ክርስቶስ ክብር ላንተ ይኹን ።

ስለ ሥሉስ ቅዱስ እንሰብካለን ፤ እናስተምራለን ፤ ለአንድ መለኮት እንሰግድለታለን ፤ እናከብረዋለን ።
ጌታ ሆይ ፥ ይቅር በለን ፥ ጌታ ሆይ ፥ ባርከን ፤
አሜን ።

ይህ ጉባኤ ስምንት ቀኖናዎችን ደንግጓል ።

፩. በቤተ ክርስቲያናዊም ኾነ በሥጋዊ ምክንያት ከቅዱስ ሲኖዶስ ልዩነት ያላቸው ሰዎች የጉባኤውን ድንጋጌ ችላ ማለት የለባቸውም



(ውሳኔውን ማክበር ይኖርባቸዋል) ። በዚህም ለቅዱስነትዎና ለተወዳጅነትዎ የምናሳውቀው የአንድ ሀገረ ስብከት ርእሰ ኤጲስ ቆጶሳት ለዓለም ዐቀፋዊው ሲኖዶስ ውሳኔ የማይታዘዝ ኾኖ የእምቢተኛነት ጉባኤ ቢሰበስብና ተቃራኒ ውሳኔ ቢያሳልፍ ወይም ከሌሎች ተቃራኒዎች ከኾኑ ውሳኔዎች ጋር ቢስማማ ከአሁን ጀምሮ በጉባኤው ውሳኔ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ተባርሮ የተለየ በመኾኑ በሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጶሳት ላይ ምንም ውሳኔ ሊያስተላልፍ አይችልም ። ቀጥተኛ አስተያየት ያላቸው የሀገረ ስብከቱ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ከክህነት ደረጃው ያባርሩት ዘንድ ጉባኤው ወክሎአቸዋል ።

፪. የአንዳንድ ሀገረ ስብከቶች ኤጲስ ቆጶሳት ከቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ዘግይተው ወደ እምቢተኛነት ካዘነበሉ ፡ ወይም ንስጥሮስ ተወግዞ ከተለየ በኋላ ከመናፍቃን ጋር አንድ ግንባር ለመፍጠር የተስማሙ ከኾነ እንደዚህ ያሉት ሰዎች ከክህነት ማዕረጋቸው መሻር አለባቸው ብሎ ጉባኤው ወስኖአል ።

፫. ከአስተሳሰባቸው ቀናነት የተነሣ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በንስጥሮስ ወይም በተከታዮቹ አማካይነት ከክህነታቸው የተሻሩ ከኾኑ ጉባኤው በክህነት ደረጃቸው እንዲቀጥሉ ፈርዶላቸዋል ። ዓለም ዐቀፋዊና ኦርቶዶክሳዊ በኾነው በቅዱስ ሲኖዶስ የእምነት ቀኖና ጸንተ ኑ ለሚገኙ ካህናት ኹሉ የምናስተላልፈው ትእዛዝ በውግዘት ለተለዩት ኤጲስ ቆጶሳት እንዳይታዘዙ ነው ።

፬. ከካህናት መካከል እምቢተኞች ኾነው የንስጥሮስንና የካላስትዮስን የክሕደት ትምህርት በመቀበል ሕዝብም ያንን የክሕደት ትምህርት እንዲቀበል የሚያደርጉ ቢኖሩ ትክክለኛ በኾነው የቅዱስ ሲኖዶስ ፍርድ እንደተለዩ ይቈጠራሉ ።

፭. የክህነት ተግባሮችን እንዳያከናውኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ወይም በኤጲስ ቆጶሳት ለተከለከሉ ሰዎች ንስጥሮስና ተከታዮቹ በግዴለሽነት ወደ የክህነት ደረጃ ኅብረት እንዲገቡ ቢያደርጉአቸው እነዚህ ሰዎች በውግዘት እንዲኖሩ ፈርደንባቸዋል ።

፮. በኤፌሶን የተሰበሰበው ቅዱስ ሲኖዶስ ከመዘገበው ውሳኔ ተቃራኒ የኾነ ድርጊትን ለማድረግ የሚፈልጉ ቢኖሩ ኤጲስ ቆጶሳት ወይም ቀሳውስት ከኾኑ ከክህነት ማዕረጋቸው ይሻሩ ፥ ተራ ምእመን ቢኾን ግን ይለይ ።

፮. የሃይማኖትን ቀኖና በሚመለከት ፣ ማንም ቢኾን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ በኒቅያ የተሰበሰቡት ቅዱሳን አባቶች ከወሰኑት እምነት የተለየ ትምህርት መከታተል ፣ መጻፍና መድረስ አይገባውም ። ወደ አረማዊነት ፣ ወደ አይሁዳዊነት ፣ ወይም ወደ ሌላ የመናፍቃን ትምህርት ለመመለስ ለሚፈልጉ ሰዎች የእነዚያን እምነት ለማሳወቅ በድፍረት ድርሰት የሚያዘጋጁ ካሉ ኤጲስ ቆጶሳት ቢኾኑ ከኤጲስ ቆጶስነት ማዕረጋቸው ካህናት ቢኾኑ ከክህነት ማዕረጋቸው ይሻሩ ፤ ምእመናን ቢኾኑ ከኅብረቱ ይለዩ ። ኤጲስ ቆጶሳት ፣ ካህናት ወይም ሌሎች ምእመናን ስለ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ መልበስ የንስጥሮስን ትምህርት በመመርኰዝ ቄስ ካሪሲዩስ ያዘጋጀውን የክሕደት ትምህርት የተቀበሉ ወይም ያስተማሩ በዚህ ዓለም ዐቀፋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ፍርድ ኤጲስ ቆጶስ ቢኾን ከሹመቱ ተሽሮ በውግዘት ይለይ ፤ ካህን ቢኾን ከክህነት ደረጃው ይሻር ፤ ተራ ምእመን ቢኾን ከኅብረቱ ይለይ ።

፯. በኤጲስቆጶስነት ተባባሪአችንና የእግዚአብሔር ወዳጅ የቆጵሮሱ ኤጲስ ቆጶስ አርጌኖስ ፣ እንዲሁም አብረውት የመጡት የእግዚአብሔር ወዳጆች ዘይኑንና ኢዩዋግሩስ ከቤተ ክርስቲያን ደንብና ከቅዱሳን ሐዋርያት ቀኖና የተለየ ድርጊት መፈጸሙን ነግረውናል ። የአጠቃላዩ ችግር የበለጠ ጉዳት እንዳያመጣ ከፍተኛ እንክብካቤ የሚያስፈልገው ሲኾን ከቆጵሮስ የመጡት ኹላቸውም በቃልና በጽሑፍ እንደገለጹት የአንጾኪያው ኤጲስ ቆጶስ ከአሁን በፊት በቆጵሮስ ጉዳይ ገብቶ የማያውቅ ከኾነ በንጹሓን አባቶች ቀኖና እና ቀድሞ በነበረው ልማድ መሠረት በቅድስት የቆጵሮስ ቤተ ክርስቲያንና በኀላፊዎችዋ ላይ ምንም ግፊ መጋባትና ቅሚያ እንዳይደረግ ። እነርሱም ኤጲስ ቆጶሳትንና መሪዎቻቸውን ኹሉ በራሳቸው ይሠይሙ ። ይህም ጉዳይ በሌሎች ሀገረ ስብከቶች ኹሉ ይጠበቅ ። ማንኛውም የእግዚአብሔር ወዳጅ የኾነ ኤጲስ ቆጶስ የእርሱ ተከታይ ባልነበረ ወይም እርሱ በተካው ኤጲስ ቆጶስ ሥር ያልነበረውን ሀገረ ስብከት በሥሩ ለማድረግ መሞከር የለበትም ። የሌላውን ሀገረ ስብከት በድፍረት በቅሚያ መልክ በሥልጣኑ ሥር ያደረገ ካለ ያባቶችን ቀኖና ላለመቃወም ይመልስ ።

ማንኛውም ሀገረ ስብከት የተቀማውና ከቀድሞ ጀምሮ የነበረው መብቱ ይመለስለት ዘንድ ዓለም ዐቀፋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል ።



## ኹለተኛው የኤፌሶን ጉባኤ ፬፻፵፱ ዓ. ም.

የአውጣኬ ክሕደት ፦ የንስጥሮስ ክሕደት የብዙዎችን አስተሳሰብ ከመስመሩ እንዲወጣ አድርጎታል ። አንዳንዶቹን ከአትናቴዎስና ከቄርሎስ ትምህርት ተቃራኒ የኾነውን የኹለት ባሕርይና የኹለት ፈቃድ ትምህርት እንዲከተሉ ሲያደርግ ሌሎቹን ደግሞ በተቃራኒው የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ በመጠፋፋትና በመቀላቀል ትስብእት ጠፍቶ መለኮት ብቻ ቀርቷል ወደሚለው ክሕደት ወስዶአቸዋል ። ይህንን ኹለተኛውን ክሕደት የተከተለው አውጣኬ የተባለው ሰው ነው ።

ይህ አውጣኬ የተባለ ሰው በቊስጥንጥንያ አጠገብ የሚገኝ የአንድ ገዳም ኀላፊና ለሃይማኖት በጣም ቀናኢ መነኰሴ እንደነበረ ይነገርለታል ። የንስጥሮስን ክሕደት በጣም ከመጥላቱ የተነሣ ያንን የክሕደት ትምህርት ለመፋለም ባደረገው ትችት ወደባሰ ክሕደት አመራ ። የትስብእት ጠባይ በመለኮት ጠባይ ተውጦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀላቀለ አንድ ጠባይ ብቻ አለው» አለ ። በጊዜው የቊስጥንጥንያ ፓትርያርክ የነበረው ፍላፕያኖስ የሃያ ዘጠኝ ኤጲስ ቆጶሳትና የሠላሳ ሦስት ገዳማት አለቆችን ጉባኤ በራሱ ሰብሳቢነት ሰብስቦ አውጣኬን አውግዞ ከገዳሙ የሚሽርና የንስጥሮስንም ክሕደት በማደስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኹለት ባሕርይና ኹለት ፈቃድ እንዳለው የሚገልጽ ውሳኔ አሳለፈ ። አውጣኬ ግን ለንጉሡ ለትንሹ ቴዎዶስዮስና ለሮማው ኤጲስ ቆጶስ ለልዮን ይግባኝ አለ ። የጉባኤውን ውሳኔ ትክክለኛነት የሚመረምር ስብሰባ እንዲደረግ ንጉሡ ባዘዘው መሠረት ስብሰባ ተደርጎ ስምምነት ስላልተደረሰ ያለምንም ውሳኔ ተበተኑ ። ከጉባኤው አባላት አብዛኞዎቹ በፊተኛው ጉባኤ ላይ የነበሩ ሲኾኑ በንስጥሮስ ላይ ያሳለፉትን የቀድሞ ውሳኔአቸውን የመለወጥ ዝንባሌ አሳይተዋል ።

ንጉሡም የይግባኙን ጉባኤ ወሳኝነት ማጣት በተመለከተ ጊዜ ዓለም ዐቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንዲሰበሰብ ወስኖ በጊዜው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪ ለነበረው ለቅዱስ ዲዮስቆሮስ ጉባኤው በእርሱ ሰብሳቢነት ይካኼድ ዘንድ መልእክት አስተላለፈለት ።

በነሐሴ ወር ፬፻፶፩ ዓ. ም. በአንድ መቶ ሠላሳ ኤጲስ ቆጶሳት አባልነትና በቅዱስ ዲዮስቆሮስ ሊቀ መንበርነት ጉባኤው ተካኺዶ እምነቱን እንዲያብራራ አውጣኬ በተጠየቀ ጊዜ የኒቅያ አባቶችን እንዲ

ሁም የአትናቴዎስንና የቄርሎስን እምነት እንደሚያምን በጽሑፍና በቃል ዘርዝሮ ካስረዳ በኋላ ጉባኤው ምንም ጥፋት ስላላገኘበት ነጻ አድርጎታል ። ከአውጣኬ ጋር የነበሩትና በፍላፕያኖስ የተወገዙት መነኰሳትም ነጻ እንዲኾኑና ወደ ገዳማቸው እንዲመለሱ ተወሰነ ። ከዚህ በኋላ ፍላፕያኖስ ለምነቱን እንዲያብራራ ተጠይቆ የንስጥሮስን ክሕደት አድሶ በኹለት ባሕርይና በኹለት ፈቃድ እምነት ላይ ስለጸና እርሱና ስድስት ኤጲስ ቆጶሳት ተወግዘዋል ።

አውጣኬ ግን ከውግዘቱ እንዲፈታ ጉባኤው ከወሰነለት በኋላ እንደገና የቀድሞ ክሕደቱን አድሶ ስለተገኘ ለመጨረሻው የቤተ ክርስቲያን መለያየት ምክንያት ኾኗል ።



# ምዕራፍ አራት

## ምሥጢረ ሥጋዌ

### መግቢያ

ምሥጢረ ሥጋዌ ማለት ዘላለማዊው እግዚአብሔር ወልድ ሰው የኾነበት ማለት የሰውን ሥጋ የለበሰበት ምሥጢር ማለት ነው ። አዳምና ሔዋን የትእዛዝ አፍራሽነትን ኀጢአት በሠሩ ጊዜ የሞትና የእርግማን ፍርድ የተበየነባቸው መኾኑና ይኸውም ፍርድ ለሰው ዘር በሙሉ እንዲተላለፍ መደረጉ ይታወሳል ። እግዚአብሔር ግን ርኅሩኅ ከመኾኑ የተነሣ የሰው ልጅ ለዘላለም እንደተፈረደበት እንዲቀር ፈቃዱ ስላልኾነ ለሰው ልጆች ቤዛ እንዲኾን ሰው ኾኖ ከኀጢአት በቀር የሰው ልጆች የሚያልፉባቸውን የሕይወት እርምጃዎች በዚህ ዓለም ላይ አሳልፎአል ። በቤዛነቱም የሰው ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ እንዲወጣና በኀጢአት ምክንያት ያጣውን ጸጋ እንደገና እንዲያገኝ አድርጎታል። እንዲሁም ሥጋውንና ደሙን በማደል ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረን ፈቅዶልናል ። ለእኛ ሲል የተቀበለውን የሕማም መጠን ስንመለከት ምን ያኽል የሚወድደን መኾኑንና ይህንን ያኽል ሕማም ያስከፈለው ኀጢአታችን የቱን ያኽል ከባድ እንደነበረ ልንገነዘብ እስችሎናል ። ይህንንም ከባድ ሕማም መቀበሉ የዳኝነቱን አለመዛባት የሚያመለክትና ለፍጥረቱ ደግነቱን የሚገልጽ ከመኾኑም በላይ እንደምን አድርጎ መሐሪነቱን ከዳኝነቱ ጋር እንዳስማማ ለማስተዋል እንድንችል አድርጎናል ።

### ለምን ሰው ኾነ ?

ኹሉን የሚችል ፡ ኹሉን የፈጠረ ፡ ኹሉን የያዘና ኹሉን የሚጠብቀው እግዚአብሔር አምላካችን ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ ከሚገልጹት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«ከቶ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን ?» (ዘፍ. ም. ፲፰ ቁ. ፲፬)

«እግዚአብሔር ሆይ ፡ አንተ ኹሉን ነገር ማድረግ እንደምትችል ዐውቃለሁ ፤ የአንተንም ዕቅድ ማሰናከል የሚችል የለም ።» (ኢዮ. ም. ፵፪ ቁ. ፪)

«ልዑል እግዚአብሔር ሆይ ፡ በታላቁ ሥልጣንህና ኀይልህ ሰማ ይንና ምድርን ፈጥረሃል ፤ ከቶም የሚሳንህ ነገር የለም ።» (ኤር. ም. ፴፪ ቁ. ፲፯)

«ኢየሱስም እነርሱን ተመልክቶ ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ኹሉ ይቻላል አላቸው ።» (ማቴ. ም. ፲፱ ቁ. ፳፮)

«ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ።» (ሉቃ. ም. ፩ ቁ. ፴፯)

ታዲያ የሰውን ልጅ ለማዳን እርሱ የፈለገውን ዘዴ መጠቀም ሲችል ለምን የፍጡሩን የሰውን ሥጋ ለብሶ ለሕማምና ለሞት ተዳረገ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ።

ሌላ ሊቃወመኝ የሚችል ሰው እስከሌለ ድረስ እኔ የፈለግሁትን አደርጋለሁ ብሎ ከሕግና ከሥነ ሥርዐት ውጪ በስሜቱ የሚመራው ውሱን የኾነው ፍጡር ብቻ ነው ። እግዚአብሔር ግን በደንብና በሥነ ሥርዐት የሚሠራ እንጂ ሥርዐተ አልባ አምላክ አይደለም ። (፩ኛ ቆሮ. ም. ፲፬ቁ. ፴፫ እና ፵)

በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፩ቁ. ፳፮—፴ እንደተመለከተው እግዚአብ ሔር ኹሉን ነገር ከፈጠረ በኋላ በመጨረሻ ሰውን በእግዚአብሔር አምሳል ፈጥሮ በፍጥረቱ ኹሉ ላይ የበላይነትን እንደሰጠው ተገልጿ ል ። በምዕራፍ ፪ ቁ. ፰—፲፭ ደግሞ በስተምሥራቅ በምትገኘው በኤደን እግዚአብሔር ገነትን ተክሎ የፈጠረውን ሰው እዚያ እንዲኖር አደረገው ይላል ። ይህንንም ካደረገ በኋላ ለአዳምና ለሔዋን መመሪያና መለኮታዊ ትእዛዝ ሲሰጣቸው ደጉንና ክፉውን ለዩታ ከምታስታውቀዋ የዛፍ ፍሬ በቀር በኤደን ገነት የሚገኙትን የዛፎች ፍሬ ኹሉ እንዲ



በሉ ፈቅዶላቸዋል ። ደጉንና ክፉውን ለዩታ ከምታስታውቀዋ የዛፍ ፍሬ በበላችሁ ጊዜ ግን ሞትን ትሞታላችሁ ብሎ አስጠነቀቃቸው ።

የክፉ ሥራ ኹሉ ምንጭ የኾነው ሰይጣን ግን አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ መሠረት በማድረግ ትእዛዙን እንዳይ ጠብቁና ከሞት ፍርድ እንዳይድኑ የተፈጥሮ ክፉ ስሜቱ ስላስመኘው በእባብ አማካይነት አሳስቶ የተከለከለውን ፍሬ እንዲበሉ አድርጓቸ ዋል (ዘፍ. ም. ፫)



አዳምና ሔዋን ከገነት ሲወጡ (ዘፍ ም. ፫ ቁ. ፳፫)

ሰይጣንም ይህን ያደረገው እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጅ በምድር ላይ ባለው ፍጥረት ኹሉ ላይ የበላይ እንዲኾን መወሰኑን ባየ ጊዜ ቅናትና ምቀኝነት አድሮበት ነው ። በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፫ ላይ እንደተገለጸው ሔዋንን ያሳሳተ እባብ መኾኑ ቢነገርም ይህ

እባብ ግን ሰይጣን ራሱ መኾኑን ለማመልከት ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ «ታላቁም ዘንዶ ወደታች ተጣለ ፤ እርሱ ሰዎችን ኹሉ የሚያስተው ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው የቀድሞው እባብ ነው» ብሏል ። (ራ. ዮሐ. ም. ፲፪ ቍ. ፱)

አዳምና ሔዋንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሳለማክበር የሰይጣንን ምክር ሰምተው የተከለከለውን ፍሬ በበሉ ጊዜ ጸጋቸው ተገፍፎ ሰውነታቸው ስለተራቈተ ኀፍረት ተሰማቸው ። የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ አክብረው ባለመጠበቃቸው ከገነት እንዲወጡ ተደርገዋል ። (ዘፍ. ም. ፫ ቍ. ፳፫)

የተከለከለውን ፍሬ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ ተብሎ ስለተወሰነና ትእዛዙ ደግሞ ስላልተከበረ የሞቱ ፍርድ በአዳምና በልጆቹ ኹሉ ላይ ከመድረሱም በላይ ከፍተኛ እርግማንም እንደተረገሙ በምዕራፍ ፫ ቍ. ፫—፳ መመልከት እንችላለን ።

አዳምና ልጆቹም በተወሰነባቸው የእርግማንና የሞት ፍርድ ብዙ ስላዘኑና በጸሎትም ስለተማፀኑ ጌታ ከሰይጣን ተገዢነት ሊያድናቸው የወሰነ መኾኑን በነቢያት አማካይነት ገለጸላቸው ። ይህንንም ገለጻ የመድኀኒታችን መለኮታዊ ክብር በተሰኘው ምዕራፍ ውስጥ የነቢያት ምስክርነት በሚለው ንዑስ ክፍል ሥር ይመለከቷል ።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከእርግማንና ከሞት ፍርድ ሊያድነው ቢፈልግም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ለመጣው ለጥንቱ የአዳም ኀጢአት ዋስ ወይም ኀላፊ ኾኖ ዕዳውን የሚከፍል አልተገኘም ማንኛውም ተከሳሽ ለሌላ ሰው ዋስ መኾን እንደማይችል ኹሉ የአዳም ልጆችም በአጠቃላይ የአባታቸውን የአዳምን ኀጢአትና በኀጢአቱም ምክንያት የሞትን ፍርድ ስለወረሱ የፍርዱን ውሳኔ ከመቀበል አልፈው ለሌላ ሰው ቤዛ የመኾን መብት አይኖራቸውም ።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው በደልን የበደለው የሰው ልጅ ነው ። በእግዚአብሔር ቀጥተኛ ፍርድም መሠረት የኀጢአቱንም ዋጋ መክፈል ያለበት ያው ኀጢአተኛው የሰው ልጅ ነው እንጂ ሌላ ሊኾን አይችልም ። ለዚያም ለተሠራው ኀጢአት መከፈል ያለበት ዋጋ ሞት መኾኑን ሲያመለክት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፮ ቍ. ፳፫ ላይ «የኀጢአት ዋጋው ሞት ነው» ብሏል ።



የኀጢአት ዋጋው ሞት ከኾነ ሰው ኹሉ በራሱ ኀጢአት ከመሞት በቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም ማለት ነው ። ቅዱሳን መላእክት ኀጢአት የሌለባቸው ንጹሐን እንደመኾናቸው በሰው ልጆች ምትክ አንድ መልአክ ቢሞት ቤዛ ለመኾን ባልቻለም ነበር ወይ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል።ይህ እንዳይኾን ግን በአንድ በኩል ኀጢአትን የሠራው ሰው ነው እንጂ መልአክ አይደለም ፤ በሌላ በኩል ደግሞ መላእክት መናፍስት እንደመኾናቸው እንደ ሰው የሚሞቱ አይደሉም ። ሌላው የቀረው መንገድ የሰው ልጅ ሊድን የሚችለው በእግዚአብሔር አማካይነት ብቻ መኾኑ ነው ። እግዚአብሔር ግን ከኹሉ በላይና ኹሉን የፈጠረ በመኾኑ ሞት ሊያሸንፈው የማይችል ከመኾኑም በላይ ፍርዱ የተላለፈው በሰው ልጅ ላይ በመኾኑ መሞትም የሚኖርበት የሰው ልጅ እንጂ ሌላ ሊኾን አይችልም ።

ኹሉን ነገር ይኾን በማለት በቃሉ የፈጠረው ኹሉን ቻይ አምላካችን እርሱ ከፈለገ የሰው ልጅንም ኀጢአት በቃሉ ለማስወገድ ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ የታመነ ነው ። ይኹን እንጂ እግዚአብሔር ከደንብና ከሥነ ሥርዓት ውጪ የማይሠራ መኾኑ ቀደም ተብሎ ተገልጿል ።

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፪ቍጥር ፲፯ ላይ ከዚያች ፍሬ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ ተብሎ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ባለመጠበቁና የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ የማይለወጥ በመኾኑ አዳምና ልጆቹ ሞት ሠልጥኖባቸው የነበረ መኾኑ ይታወቃል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን ጸሎት ተቀባይነት ከሚያረጋግጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉትን ኹለት ጥቅሶች እንመልከት ።

«እናንተ ትጠሩኛላችሁ ፤ ኼዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ ፤ እኔም እሰማችኋለሁ ። እናንተ ትሹኛላችሁ ፤ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ ፤ ከእናንተም ዘንድ እገኛለሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ።» (ኤር. ም. ፳፱ቍ, ፲፪—፲፬)

«ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፡ ለምኑ ይሰጣችኋል ፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል ፤ ምክንያቱም የሚለምን

ኹሉ ይሰጠዋል ፤ የሚፈልግ ያገኛል ፤ በር ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል ና ።» (ማቴ. ም. ፯ ቍ. ፯—፰)

እግዚአብሔር ትክክለኛ ዳኛ በመኾኑና ፍርዱም ስለማይለወጥ ሞት በሰው ልጆች ላይ ሠለጠነ ። የሰው ልጆች ደግሞ የእግዚአብሔርን ይቅርታ በመለመናቸው ልመናቸውን ተቀበለ ። እነዚህ ኹለት ኹኔታዎች ማለት ትክክለኛ ዳኝነቱና ጸሎት ተቀባይነቱ አንዳቸውም ሳይቀሩ ኹለቱንም ሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ እግዚአብሔር ጥበበኛ ውሳኔውን አሳለፈ ።

አሁን እንግዲህ በአንድ በኩል የማይለወጠው የልዑል እግዚአብሔር ፍርድና ውሳኔ የግድ ሥራ ላይ መዋል ስላለበት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር በጸሎት ተቀባይነቱና በመሐሪነቱ ለሰው ልጅ ይቅርታ ማድረግ ስለፈቀደ በመጨረሻ የቀረው አማራጭ መንገድ በእግዚአብሔር አብ ሳኪነትና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር እግዚአብሔር ወልድ መለኮቱን ከትስብእት ጋር በማዋሐድ ያለመቀላቀልና ያለ መጠፋፋት ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ኾኖ ለሰው ልጅ ቤዛ እንዲኾን መለኮታዊ ውሳኔ ተላለፈ ።

በዚህም መሠረት ጌታ ሕማምንና ሞትን በመቀበሉ የእግዚአብሔርን ፍርድ ቀጥተኛነት ፣ የውሳኔው አለመለወጥና መሐሪነቱን ልናስተውል እንችላለን ።

አጥፊው የሰው ልጅ በመኾኑና መቀጣትም ያለበት ያው ጥፋተኛው የሰው ልጅ እንጂ ሌላ ሊኾን ስለማይችል የጥንቱን የአዳምን ኀጢአት ባልወረሰው ሰውነቱ ለሰው ልጆች ቤዛ ኾኖ የፍርዱን ቀጥተኛነት አሳይቶናል ።

ውሳኔው የማይለወጥ መኾኑን የምናስተውለው የኀጢአትን ዋጋ እርሱ ራሱ በመሞት መክፈሉ ነው ።

በመሐሪነቱና በጸሎት ተቀባይነቱም መሠረት የሰውን ልጅ ከኀጢአት ተገዥነት ነጻ አውጥቶታል ።

## ሰው ኹሉ ኀጢአተኛ ነው

የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች መሠረት ባማድረግ ሰው ኹሉ ኀጢአተኛ እንጂ አንድም ጻድቅ የሌለ መኾኑን ቤተ ክርስቲያን



የምታምነውና የምታስተምረው ትምህርት ነው ። ጌታም ሰው የኾነውና በሰውነቱ ቤዛ ኾኖ የሰውን ልጅ ከኀጢአት ተገዥነት ነጻ ያወጣው ለሰው ልጅ ቤዛ ለመኾን የጥንቱን የአዳምን ኀጢአት ያልወረሰና ፈቃደኛ የኾነ ሰው ስላልተገኘና ሊገኝም ስላልተቻለ ነው ። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፰ ቍ. ፫ ላይ «ከሥጋ ደካማነት የተነሣ ሕግ ሊፈጽም ያልቻለውን በኀጢአተኛ ሥጋ ምሳሌነት እግዚአብሔር ልጁን ልኮ በሥጋ ኾኖ በኀጢአት ላይ ፈረደ (ኀጢአትን አስወገደ)» ያለው ።

ሰው ኹሉ ኀጢአተኛ መኾኑንና ማንም ጻድቅ አለመኾኑን ከሚገልጹት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል ።

«ንጹሕ ይኾን ዘንድ ሰው ምንድር ነው ? ጻድቅስ ይኾን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድር ነው ? እነሆ ፣ በቅዱሳኑ ስንኳ አይታመንም ! ሰማያትም በፊቱ ንጹሓን አይደሉም ። ይልቁንስ አስጸያፊና የረከሰ ፣ ኀጢአትንም እንደ ውሃ የሚጠጣ ሰው ምንኛ ያንስ ?» (ኢዮ. ም. ፲፭ ቍ. ፲፬—፲፮)

«ሰውስ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ይኾን ዘንድ ፣ ከሴትስ የተወለደ ንጹሕ ይኾን ዘንድ እንዴት ይችላል ? እነሆ ፣ ጨረቃ እንኳ ብሩህ አይደለም ፤ ከዋክብትም በፊቱ ንጹሓን አይደሉም ፤ ይልቁንም ትልና ትል የኾነ የሰው ልጅ ምንኛ ያንስ» (ኢዮ. ም. ፳፭ ቍ. ፬—፮)

«በጎ ነገርን የሚሠራ የለም ፤ የሚያስተውልና እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ ፤ ኹሉ ዐመፁ ፤ በአንድነትም ረከሱ ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም ፤ አንድም ስንኳ የለም ።» (መዝ ፲፬ ቍ. ፩—፫)

«እነሆ ፣ በዐመፃ ተፀነስኹ ፤ እናቴም በኀጢአት ወለደችኝ ።» (መዝ. ፶፩ ቍ. ፭)

«ኹሉም በድለው የእግዚአብሔርን ክብር አጥተዋል ።» (ሮሜ. ም. ፫ ቍ. ፳፫)

«በአንድ ሰው ምክንያት ኀጢአት ወደ ዓለም ገባ ፤ በኀጢአት ምክንያትም ሞት መጣ ። የአንዱ የአዳም ኀጢአት የቅጣትን ፍርድ በሰው ኹሉ ላይ እንዳመጣ ፥ እንዲሁም የአንዱ የክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ብዙዎችን ከቅጣት ነጻ አድርጎ ሕይወትን ይሰጣል ።» (ሮሜ ም ፭ ቁ ፲፪ እና ፲፰)

«ኀጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን ፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም ።» (፩ኛ ዮሐ ም ፩ ቁ ፰)

ከላይ በተዘረዘሩት ማስረጃዎች መሠረት በአዳም ኀጢአት ምክንያት መድኀኒታችን ቤዛ እስከኾነበት ዘመን ድረስ ሰው ኹሉ የአዳምን ኀጢአት በመውረስ እንደ ኀጢአተኛ የተቈጠረ መኾኑን ያመለክተናል ።

## የእግዚአብሔር ውሳኔ አለመለወጥ

ያለፉም ኾኑ ወደፊት የሚፈጸሙ ድርጊቶች ያለእግዚአብሔር ዕቅድ ወይም ፈቃድ ስላልተፈጸሙ ወይም ስለማይፈጸሙና ማንኛውም ኹናቴ እርሱ በቅድሚያ ዐውቆት ስለሚያደርስ እግዚአብሔር ውሳኔውን አይለውጥም ።

ምንም እንኳ በዚህ ዓለም በፈጠረው ፍጥረት ኹሉ ላይ ከፍ በማድረግ የሰውን ልጅ ቢያከብረው ትእዛዝ የማፍረስ ኀጢአት ቢሠራ ግን በሞት እንደሚቀጣ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ተወስኖ ስለነበረ የሞቱን ፍርድ አጽንቶበታል ። ይህም የእግዚአብሔር ውሳኔ የማይለወጥ በመኾኑ ነው አምላክ ሰው ኾኖ በሰውነቱ ሞቶ የኀጢአትን ዋጋ በሰው ልጆች ቦታ ኾኖ የከፈለው ።

የእግዚአብሔር ውሳኔ የማይለወጥ መኾኑን ከሚገልጹት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም ፤ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም ፤ እርሱ ያለውን አያደርገውምን ? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን ?» (ዘኁ ም ፳፫ ቁ ፲፱)



«የእስራኤል የክብር ግርማ የኾነ እግዚአብሔር አይዋሽም ፥ አሳቡንም አይለውጥም ፤ እርሱ እንደሰው ስላልኾነ አሳቡን አይለውጥም» (፩ኛ ሳሙ ም ፲፭ ቁ ፳፱)

«እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም ።» (ሚል ም ፫ ቁ ፮)

«እግዚአብሔር ከመረጠና ጸጋውን ከሰጠ በኋላ ባደረገው ነገር አይጸጸትም ።» (ሮሜ ም ፲፩ ቁ ፳፱)

«እግዚአብሔር ውሳኔው የማይለወጥ መኾኑን ለማስረዳት ፈልጎ ለተስፋው ወራሾች ተስፋውን በመሐላ አጸናላቸው ።» (ዕብ ም ፮ ቁ ፲፯)

«መልካም ስጦታና ፍጹም በረከት ኹሉ ከእግዚአብሔር ነው ፤ ይህም የሚመጣው እንደ ጥላ መዘዋወር ወይም መለዋወጥ ከሌለበት የብርሃን ኹሉ አባት ከኾነው ከእግዚአብሔር ነው ።» (ያዕ ም ፩ ቁ ፲፯)

## እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሐሪ ነው

እግዚአብሔር አምላካችን ቀጥተኛ ዳኛና ውሳኔው የማይለወጥ ከመኾኑ ጋር ርኅሩኅነት ደግሞ ከመለኮታዊ ባሕርዮቹ አንዱ መኾኑን ከሚገልጹት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«አምላክህ እግዚአብሔር መሐሪ አምላክ ነውና አይተውህም ፤ አያጠፋህምም ፤ ለአባቶችህም የማለላቸውን ቃል ኪዳኑን አይረሳም ።» (ዘዳ ም ፬ ቁ ፴፩)

«አምላካችሁ እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ነውና ወደ እርሱ ብትመለሱ ፊቱን ከእናንተ አያዞርም ።» (፪ኛ ዜና መ ም ፴ ቁ ፱)

«እግዚአብሔር ቸር እንደኾነ ቅመሱ ፤ እዩም ፤ በእርሱ የሚታመን ሰው ምስጉን ነው ።» (መዝ ፴፬ ቁ ፰)

«አባት ለልጆቹ እንደሚራራላቸው እንዲሁም እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራላቸዋል ።» (መዝ ፻፫ ቍ ፲፫)

«እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሐሪ ከቊጣ የራቀ ፤ ምሕረቱ ብዙ ነው ።» (መዝ ፻፵፭ ቍ ፰)

«እግዚአብሔር የፍርድ አምላክ ነውና ስለዚህ እግዚአብሔር ይራራላችሁ ዘንድ ይታገሣል ፤ ይምራችሁም ዘንድ ከፍ ከፍ ይላል ፤ እርሱን በመተማመን የሚጠባበቁ ኹሉ ብፁዓን ናቸው ።» (ኢሳ ም ፴ ቍ ፲፰)

«ኺድና ይህን ቃል ወደ ሰሜን ተናገር ፤ እንዲህም በል ከዳተኛ ይቱ እስራኤል ሆይ ፤ ተመለሺ ፤ ይላል እግዚአብሔር ፤ መሐሪ ነኝና ፤ ለዘላለምም አልቈጣምና በእናንተ ላይ ፊቴን አላደርግም ይላል እግዚአብሔር ።» (ኤር ም ፫ ቍ ፲፪)

«በደልን ይቅር የሚል ፤ የርስቱንም ቅሬታ ዐመፅ የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማነው ? ምሕረትን ይወድዳልና ቍጣውን ለዘላለም አይጠብቅም ።» (ሚክ ም ፯ቍ ፲፰)

«ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ፣ቍጣው የዘገየ ፤ ምሕረቱም የበዛ ፤ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ ።» (ኢዩ ም ፪ ቍ ፲፫)

«እግዚአብሔር መልካም ነው ፤ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው ።» (ናሆ ም ፩ ቍ ፯)

ምንም እንኳ የሰው ልጅ በሥራው ኀጢአት የተፈረደበት ቢኾን አምላክ ሰው ኾኖ በሰውነቱ ሕማምንና ሞትን በመቀበል ለሰው ልጅ ቤዛ የኾነው ከላይ በቀረቡት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መሠረት እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሐሪ በመኾኑ ነው ።

## ጌታ ከአዳም ኀጢአት ጋር አልተወለደም

ሰው ኹሉ የጥንቱን የአዳምን ኀጢአት የወረሰ ከኾነና እግዚአብሔር ወልድ ደግሞ ያለመለዋወጥ ያለ መቀላቀልና ያለ መጠፋፋት ፍጹም



አምላክነቱንና ፍጹም ሰውነቱን እንደያዘ መለኮትንና ትስብእትን ያዋሐደ አምላክ ከኾነ እንዴት በትስብእቱ የጥንቱን የአዳምን ኀጢአት ሳይወርስ ቀረ ? ወርሶ ከኾነ ደግሞ እንዴት ለሰው ልጅ ቤዛ ለመኾን ቻለ ? ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ። ለዚህ ጥያቄ የእግዚአብሔር መልአክ አስቀድሞ መልስ የሰጠ ስለኾነ የእርሱን መልስ መመልከት ይጠቅማል ።



ሰላም ለከ ገብርኤል ለማርያም ኀይለ ልዑል ጸለላ ፤ መንፈስ ቅዱስ እንጽሐ ሥጋ አባላ፣ ተፈስሒ ሶበ ትቤላ

ገብርኤል ሆይ ፤ ሰላም ላንተ ይኹን ፤ ማርያምን ደስ ይበልሽ ባልካት ጊዜ የልዑል ኀይል ደልሎአት መንፈስ ቅዱስ ሰውነትዋን አንጽቶታል ።

መልአኩ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም ተልኮ እንደምትፀንስና ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ባበሠራት ጊዜ እኔ ወንድ የማላውቅ እንደመኾኔ ይህ እንዴት ሊኾን ይችላል ብላ ብትጠይቀው «መንፈስ

ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፤ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል ፤ ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» ብሎ መልስ ሰጥቷታል ። (ሉቃ ም ፩ ቁ ፴፬—፴፭)

በቤተ ክርስቲያን እምነት መሠረት በሉቃስ ወንጌል ም ፩ ቁ ፴፰ ላይ የመልአኩን ብሥራት ተቀብላ «እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይኹንልኝ» ብላ እምነትዋን በእግዚአብሔር ላይ ባሳረፈች ጊዜ ጌታን ከመውለድዋ በፊት መንፈስ ቅዱስ እመቤታችንን ቀድሶና አን ጽቶ የጥንቱን የአዳምን ኀጢአት አስወግዶላታል ። በሌላ በኩል ደግሞ የቀድሞው የአዳም ኀጢአት የሚወረሰው በወንድ ዘር አማካይነት ልጅ በሚወለድበት ጊዜ ከአባት ወደ ልጅ በመኾኑና ጌታ ግን የተወለደው መንፈስ ቅዱስ የጥንቱን ኀጢአት ካስወገደላት ከእናት ብቻ ስለኾነ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የጥንቱን የአዳምን ኀጢአት አልወረሰም። ይህንን አባባል ከሚደግፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«ምንም ወንጀል ሳይፈጽም ፡ በአንደበቱም ሐሰት ሳይገኝበት ፥ በሞት ከክፉ አድራጊዎች ጋር ተቈጠረ ።» «እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ ፤ ስለ በደላችን ደቀቀ ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ ፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።» (ኢሳ. ም. ፶፫ ቁ. ፱ እና ፭)

«ከክርስቶስ ጋር በመተባበር የእግዚአብሔር ጽድቅ እንኾን ዘንድ ኀጢአት የሌለበትን ክርስቶስን የእኛን ኀጢአት እንዲሸከም አደረገው ።» (፪ኛ ቆሮ. ም. ፭ ቁ. ፳፩)

«እግዚአብሔር አንድ ነው ፤ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለው ማእከላዊ አገናኝ አንድ ነው ፤ እርሱም ሰው የኾነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ። ሰዎችን ኹሉ ከኀጢአት ለመዋጀት ራሱን ቤዛ አድርጎ የሰጠ እርሱ ነው ፤ ይህም የእግዚአብሔርን የማዳን ፍላጎት የሚያስረዳ ምስክር ነው ።» (፩ኛ ጢሞ. ም. ፪ ቁ. ፭)

«ልጆች ሥጋና ደም ያላቸው ሰዎች እንደመኾናቸው ኢየሱስም እንደ እነርሱ ሰው ኾነ ። ይህንንም ያደረገው በሞቱ አማካይነት በሞት



ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን ለመሻር ነው ፤ እንዲሁም ሞትን በመፍራት ምክንያት ዕድሜ ልካቸውን በባርነት ይገዙ የነበሩትን ለመዋጀት ነው ።» (ዕብ. ም. ፪ ቁ. ፲፬—፲፭)

«ለእኛ የሚስማማን ቅዱስና ንጹሕ የኾነ ፡ ነውር የሌለበት ፥ ከኃጢአተኞች የተለየና ከሰማይ በላይ ከፍ ያለ ሊቀ ካህናት ነው ።» (ዕብ. ም. ፯ ቁ. ፳፮)

«ክርስቶስ የሰዎችን ኀጢአት ለመደምሰስ እንደተገለጸና ፥ እር ሱም ኀጢአት እንደሌለበት ታውቃላችሁ ።» (፩ኛ ዮሐ. ም. ፫ ቁ. ፭)

<u>የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት</u>

<u>ሐዋርያዊው አትናቴዎስ፦</u> «ኹሉን የፈጠረ እግዚአብሔርን አምላክ አይደለም ሊሉት ፥ ሕይወትንስ ሕይወት አይደለም ሊሉት እንደምን ይቻላል ? እንደ ወንጌል ትምህርት ግን የማይሞተውን ሞተ ሊሉት ይገባል ፤ በዚህም አነጋገር በመለኮቱ ሕማም ፡ ሞት የሌለበት እግዚ አብሔር በነሣው ሥጋ ሞተ ይባላል ። በምንም በምን ሕማም የሌለበት እውነተኛ የባሕርይ አምላክ ፥ እውነተኛ ብርሃን ፥ የእግዚአብሔር አብ ኀይሉ የሚኾን ለሕማም ለሞት የማይደፈር እርሱን መናፍቃን በክሕ ደታቸው እንደ ሰው በግድ ታመመ ፤ ደከመ ፤ ሞተ እንደምን ይሉታል ? ለሞቱ ሰዎች ሕይወትን የሰጠውን ፥ ሙታንን ያስነሣውን ፥ ያልነበሩ ትን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ያስገኛቸውን ታመመ ሞተ እንደ ምን ይሉታል? በሕያው እግዚአብሔር ላይ ደፍረው ይህን ነገር እን ደምን ይናገራሉ? እርሱ ሕይወት ፥ ትንሣኤ ነው ፤ እርሱ የእግዚአብ ሔር ኀይሉ ነው ፤ ከባሕርዩ ሳይለወጥ ከእመቤታችን ነፍስን ፥ ሥጋን ነሥቶ ሰው የኾነ እርሱ እንደ እኛ በላ ፤ ጠጣ ፤ ከእኛ በነሣው በሰው ባሕርይ ሰው ኾነ ታመመ ፤ ተሰቀለ ፤ ሞተ እንጂ እርሱ የባሕ ርይ አምላክ ሲኾን ሰው ኾነ ።» (ሃ. አበ. ገጽ ፸፯)

«አሁንም በተዋሕዶ ሰው የኾነ አምላክ እንደኾነ ሰምተህ ዕወቅ ፤ አምላክ ብቻ ከኾነማ እንደምን በታመመ ነበር ? ወይስ እንደምን በሰ ቀሉት ነበር ? ወይስ እንደምን በሞተ ነበር ? ይህ ሥራ (ሕማም ፥ ሞት) ከእግዚአብሔር የራቀ ነውና ። ሰው ብቻ ከኾነ በታመመ በሞተ ጊዜ ሞትን እንደምን ድል በነሣው ነበር ? ሌሎችንስ በነፍስ በሥጋ እንደ

ምን ባዳን ነበር ? ይህ ከሰው ኀይል በላይ ነውና ። እርሱ ታሞ ሞቶ ፍጥረቱን አዳነ ፤ ሞትንም ድል ነሣ ፤ ሰው የኾነ አምላክ ነውና ።» (ሃይ. አበ. ገጽ ፺፪)

ቅዱስ አቡሊዲስ የሮም ሊቀ ጳጳሳት

«ከአዳም አንሥቶ እስከ ሙሴ ሰዎችን በአዳም በደል አምሳል ያልበደሉ ሌሎችንም ሞት እንደገዛቸው ተናገረ ፤ መጀመሪያ የበደለ አዳም ነው ፤ አዳምም በበደለ ጊዜ የሚመስሉትን ያን ጊዜ ወለደ ። በዚያን ወራት አዳምን መሬት ነህ ፤ ወደ መሬትነትህ ተመለስ የሚል ከእግዚአብሔር የታዘዘ አንድ ዐዋጅ በኹሉ ላይ ተነገረ ። ሙሴም ሞትን ያጠፋ ዘንድ አልቻለም ፤ እርሱንም ያዘው ፥ ገዛው እንጂ ፤ ከእርሱ በኋላ የተነሡ ነቢያትንም ኹሉ ሞት ገዛቸው እንጂ ። ክርስቶስ ግን በቸርነቱ ለኹሉ ሕይወትን ሰጠ ። . . . . የነቢያት ፥ የመላእክት ፈጣሪ ሲኾን በሥጋ ተገለጠ ።» (ሃይ. አበ. ገጽ ፻፵፭—፻፵፮)

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ፡- «እርሱ ልዩ መድኀኒታችን በተለየ አካሉ ከሰማያት ወርዶ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን አደረ ፤ ለእኛ ድኅነትን ያደርግልን ዘንድ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ነፍስን ሥጋን ተዋሐደ ፤ በባሕርዩ መለወጥ የሌለበት ቃልም ከእርስዋ ተወለደ ። ሰው ኾነ ፤ እኛን ለማዳን ከሰው ባሕርይ ሥጋን የተዋሐደ እግዚአብሔር ቃል ይህ ነው ፤ ከአብ የተገኘ ፍጹም እርሱ ሕጸጽ የለበትም ፤ የሰውን ሥራ ፈጸመ ፤ እኛን ለማዳን ስለ እኛ ሰው ኾነ ፤ እንደ ሰው ነፍስን ፥ ሥጋን ፈጽሞ ተዋሐደ ። ከአብ የተገኘ ፍጹም አምላክ ነው ፤ ፍጹም ሰውም ኾነ ፤ በሐሰት ፥ በምትሐት አይደለም ፤ በግብረ መረፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ቃልን ከወለደችው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሊዋሐደው በእውነት ፍጹም አካልን ፈጠረ እንጂ ።» (ሃይ አበ ገጽ ፻፶፯)

ቅዱስ ጎርጎርዮስ የእንዚናዙ -፡ «በኋላ ዘመን ከሦስቱ አካላት አንድ ጥንት የሌለው የእግዘአብሔር አብ ቃል ማንም ግድ ሳይለው በራሱ በአብ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሰው ኾነ ፤ በአርያም ካሉ መላእክት ማንም ሰው መኾኑን አላወቀም ፤ ከአባትና ከእናት በተወለደች በቅድስት ድን



ግል ማርያም ማሕፀን አደረ ። ሥጋ የሌለው እርሱ ሥጋዋን ተዋሕዶ እንደ ሰው ኹሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በጌትነቱ ሳለ በማሕፀኗ ተወሰነ ፤ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀንም ከተፈጸመ በኋላ የሚወለድበት ቀን ቢደርስ በማይመረመር ግብር በጎቱም ድንግልና ተወለደ ፤ ማኅተመ ድረግልለዋም አልተለወጠም ፤ ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ተወለደ እንጂ ።» (ሃይ አበ ገጽ ፻፻፲፪)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡- «እስከዚህች ቀን ድረስ ትሩፋት የሠሩ ሐዋርያት ፥ ሰማዕታት ኹሉ እንደ አመኑት እምነት እንዲህ እኔ አምናለሁ ፤ ቃል ሥጋ ኾኖዋልና ፤ መናፍቃንም እንደ ተናገሩት በዕሩቅ ብእሲ አላደረምና ። በእርሱ ፈቃድ በአባቱና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ተዋሐደ እንጂ እርሱ ባወቀ መለወጥ በሌለበት በእመቤታችን ማሕፀን ሥጋን ፈጥሮ ተዋሐደ ። የጥልቅ ጥልቅ በኾነው ውስጥ ያለውን ያውቅ ዘንድ ከሰው ወገን ማንም ማን አይችልም ፤ ኹሉን የፈጠረ አምላክ የአብ አካላዊ ቃል ፍጹም ሰው ኾኖ ተወለደ ፤ እንደ ተጻፈ ። (ገላ ም ፬ቍ ፬)

የሠላሳ ዘመን ጐልማሳ ለመኾን እስኪደርስ ድረስ ሕፃን በመኾን ሥርዐት ሕፃናትን ፈጸመ ፤ ኹሉ የተፈጠረበት የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው ፤ ሥልጣን ኹሉ ገንዘቡ ሲኾን በራሱ ፈቃድ ብቻ ለአይሁድ ራሱን አሳልፎ ሰጠ ።» (ሃ አበ ገጽ ፻፻፲፱)

«የተነገረውን አስተውል ፤ እግዚአብሔር ከእኛ ባሕርይ የተዋሐደው ተዋሕዶ ጥቂት ክብር አይምሰልህ ፤ ይህንን ለመላእክት አላደረገውምና ፥ የመላእክት ባሕርይም አልተዋሐደችውምና የተዋሐደችው የኛ ባሕርይ ናት እንጂ ። ባሕርያችንን ተዋሕዶአል እንጂ ከባሕርያችን ከፍሎ ተዋሐደ ለምን አላለም ? ወዳጄ እንደ ኮበለለ እስኪያገኘውም ድረስ እንደ ኼደና እንደ አገኘው ሰው የእኛ ባሕርይ እንደዚህ ከእግዚአብሔር ተለይታ ነበርና ፥ ከእርሱም ፈጽማ ርቃ ነበርና ፤ ሥጋ በመኾን ገንዘብ እስኪያደርጋት ደርሶ ፈጥኖ ፈለጋት ፤ እርሷም ተዋሐደችው ይህንንም ተዋሕዶ እኛን በመውደድ እንዳደረገው የታወቀ ነው ።» (ሃይ አ፡ ገጽ ፻፻፳፩)

ቅዱስ ቄርሎስ ፥ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት « እኛስ ያለማወላወል የዶግጉን አባቶቻችንን ሃይማኖት እንይዛለን ። ከአብ የተወለደ ወልድ

ዋሕድ ሥጋን ፡ ነፍስን ነሥቶ ሰው እንደኾነ ፡ እንደታመመ ፡ እንደሞተ በሦስተኛው ቀንም ከሙታን ተለይቶ እንደ ተነሣ እናምናለን ፤ የማይ ሞት ነውና ፡ አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንደኾነ በእግዚአብሔር ቃል እናምናለን ። ከፍጥረት ኹሉ በላይ በኾነ ባሕርይ ሞት እንደ ደረሰ የሚ ናገር ማንም ዐላዋቂ አይኑር ፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተገኘ ሥጋ ሰው ኾነ ፤ ገንዘቡ ነውና ስለዚህ እኛ ተዋሕዶውን አምነን በመለኮቱ ሞት የሌለበት እርሱ ሰው እንደመኾኑ በሥጋ ሞተ እንላለን ። አምላክ ሲኾን ሰው ኾነ ፤ ከጌትነቱም ክብር ፈጽሞ አልተለየም ፤ ምንም ሰው ቢኾን እርሱ ከፍጡራን ኹሉ በላይ ነው ፤ በመለኮቱ ሕግን የሠራ ሲኾን እነሆ ፡ ሕግን በመፈጸም ተገኘ ፤ ሕግን ሲሰጥ በነበረበት ባሕርዩ ጸንቶ ኖረ ። በመለኮቱ ገዢ ሲኾን የተገኘ ባሕርይን ገንዘብ አደረገ ፤ግን የጌትነት ክብር ከእርሱ አልተለየም ፤ አንድ ሲኾን ለብዙዎች ምእመ ናን በኵር ኾነ ፤ (በትንሣኤ ፡ በዕርገት) በአንድነቱም ጸንቶ ኖረ ። ሰው እንደመኾኑ በሥጋ ቢሞት የሚያስደንቅ አይደለም ፤እነሆ ፡ በመለኮቱ የማይሞት ነው ።» (ሃይ አበ ገጽ ፪፻፶፩—፶፭)

«ሥጋን በመልበስ ሰው ባይኾንና በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ባይገለጥ ኖሮ ፍጡራን ሊያዩት ባልቻሉም ነበር ፤ ሊያዩት የሚይችሉም ሰዎች ብቻ አይደሉም ፤ መልካቸው ልዩ ልዩ የሚኾን የሚያመሰግኑ ረቂቃን የሚኾኑ በሰማይ ያሉ መላእክትም በነበረበት ባሕርዩ ያዩት ዘንድ ባልቻሉም ነበር ።» (ሃይ. አበ. ገጽ ፫፻)

ቅዱስ ባስልዮስ ፡ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት፡«ሊቀ መላእክት ገብርኤልም ጸጋን የተመላሽ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ሰው ይኾናልና ደስ ይበልሽ በአላት ጊዜ ቃል በማሕፀኗ እንደ አደረ በማይመረመር ምሥጢርም እንደ ዐይን ጥቅሻ ፈጥኖ ከእሷ ሥጋን ፡ ነፍስን ነሥቶ ሰው እንደኾነ እናምናለን ፤ እርሱ ባወቀም በድንግል ማሕፀን አደረ ፤ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ሰው በመኾኑም የማይከፈል የመለኮት አንድነት አልተከፈለም ።» (ሃይ. አበ. ገጽ ፬፻፷፩)

በእኛ ቦታ ኾኖ እኛን ከሞት ለማዳን ሕማምንና ሞትን በተቀበለ ጊዜ ሞትን ብቻ ሳይኾን እርግማንንም ከእኛ ለማስወገድ ስለኾነ በእ ንጨት ላይ እንዲሰቀል አደረገ ፤ በእንጨት ላይ የተሰቀለ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ። (ዘዳ. ም. ፳፩ ቍ. ፳፫ ፡ ገላ. ም. ፫ ቍ. ፲፫)



ይህንን ትምህርት ለማጠቃለል ምሥጢረ ሥጋዌ ማለት ወልደ እግዚአብሔር ቤዛ በመኾን የሰውን ልጅ ከሞት ፍርድ ለማዳን መለኮ ቱን ሕማምንና ሞትን ሊቀበል ከሚችል እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ከአ ዳም ኀጢአት ከነጻ ከሰውነት ጋር ያዋሐደበት ምሥጢር ነው ።

## ምዕራፍ አምስት

## የመድኀኒታችን መለኮታዊ ክብር

### ሀ. መግቢያ

በዝነኛው ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በ፫፻፳፭ ዓ. ም. በኒቅያ ከተማ በተሰበሰበት ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት የዓለም ኤጲስ ቆጶሳት ውሳኔ መሠረት ከተወገዘው ከአርዮስ ጀምሮ የመድኀኒታችንን የባሕርይ አምላክነትና ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት የሚክዱ የአርዮስ ወገኖች ነበሩ ፤ አሁንም አሉ ። በዚህ ጉዳይ ላይ ቤተ ክርስቲያን ያላትን አቋም ለማስረዳት እንዲያመች ገለጻው በአምስት አርእስት ተከፋፍሎ ቀርቦአል ።

በመጀመሪያው ክፍል የታየው ልዑል እግዚአብሔር ለክብሩ ቀናተኛ በመኾኑ መድኀኒታችን እርሱው ራሱ ከሦስቱ የመለኮት አካሎች አንዱ እግዚአብሔር ወልድ እርሱም የባሕርይ አምላክ ባይኾን ኖሮ ለእርሱ የተሰጠው ክብር ኹሉ እንዲሁ ዝም ተብሎ ሊታለፍ አለመቻሉ ነው ።

በኹለተኛው ክፍል በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ነቢያት ለእኛ ለሰው ልጆች ቤዛ ለመኾን ሲል ከሰው እንደሚወለድ ፤ሕማም እንደ ሚደርስበት ፣ እንደሚገደልና ሞትንም ድል ነሥቶ እንደሚከብር ስለ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድመው ትንቢት የተናገሩ መኾናቸው ተገልጾአል ።

በሦስተኛው ክፍል ለልዑል እግዚአብሔር ብቻ የተወሰኑት ስግደትና መለኮታዊ መጠሪያ እንዴት ለመድኀኒታችን እንደተሰጡ ቅዱሳት መጻሕፍት መመስከራቸው ተጠቅሶአል ።

በአራተኛው ክፍል የታየው ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ የኒቅያ ጉባኤ አባቶች የደነገጉት የሃይማኖት ጸሎት እንዴት ከቅዱሳት



መጻሕፍት ጋር እንደሚስማማና ለጌታችንም መለኮታዊ ክብር እንደ ሚመሰክር ነው ።

በአምስተኛው ክፍል የታየው ደግሞ በክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርይ የማያምኑ ወገኖች የሚያቃርቡአቸው የመከራከሪያ ጥቅሶችና ለክርክሩም የተሰጡ መልሶች ናቸው ።

### ለ. እግዚአብሔር ለክብሩ ቀናተኛ ነው ።

ለእርሱ መስጠት ያለበትን ክብርና ምስጋና መሻማት ፣ ወይም ለሌላ ፍጡር መስጠት ፣ ወይም ደግሞ ትእዛዛቱን ማዛባት ፈጣሪ አምላክን በጣም ያስቈጣዋል ። ለክብሩም ቀናተኛ መኾኑን ከሚገልጹት ጥቅሶች መካከል የሚበተሉ ይገኙባቸዋል ።

«ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኹኑልህ ፤ እኔ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነኝና ።» (ዘፀ. ም. ፳ ቍ. ፫ እና ፭)

«አምላክህ እግዚአብሔር የሚበላ እሳት ቀናተኛ አምላክ ነውና ።» (ዘዳ. ም. ፬ ቍ. ፳፬)

«ኢያሱም ሕዝቡን እርሱ ቅዱስ አምላክ ነውና እርሱም ቀናተኛ አምላክ ነውና እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም ፤ መተላለፋችሁንና ኀጢአታችሁን ይቅር አይልም ፤ እግዚአብሔርን ትታችሁ እንግዶችን አማልክት ብታመልኩ መልካም ካደረገላችሁ በኋላ መልሶ ክፉ ያደርግባችኋል ፤ ያጠፋችሁማል አላቸው።» (ኢያ. ም. ፳፬ ቍ. ፲፱—፳)

ለእግዚአብሔር ተገቢ የኾነውን ክብር አለመስጠትና ሕግጋቱንና ትእዛዛቱን ማዛባት ምን ውጤት እንደሚያመጣ ለመረዳት የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት ።

የመጀመሪያው ምሳሌ በኦሪት ዘኍልቍ ም. ፲፪ ቍ. ፩—፲፯ ብንመለከት ነቢዩ ሙሴ በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያኽል ተወዳጅነት እንደነበረው ለመረዳት እንችላለን ።

ወንድማቸው ሙሴ ኢትዮጵያዊቱን በማግባቱ ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም በሙሴ ላይ ከማጕረምረማቸውም በላይ እነርሱም ቢኾኑ

ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ባለሟልነት ከሙሴ እንደሚያንስ በማመን ተመጻደቁ ። ሙሴን ግን የእግዚአብሔር ቅርብ ወዳጅ በመኾኑ በእርሱ ላይ የተደረገው አድማ የእግዚአብሔርን ቍጣ በማስነሣት በማርያም ላይ ለምጽ እንዲወጣባት አደረገ ። ለምጿምም ኾና ሰባት ቀኖች ከቈየች በኋላ ልትድን የቻለችው በሙሴ አማላጅነት ነው ። በዚሁ ምዕራፍ በቍጥር ፫ ላይ በምድር ካሉ ሰዎች ኹሉ ሙሴ እጅግ ትሑት ሰው እንደነበረ ተገልጾአል ። ከቍጥር ፭ እስከ ፱ ድረስ የሚነበበው ቃለ እግዚአብሔር እንዲህ የሚል ነው ።

«እግዚአብሔር ወዲያው ሙሴ ፡ አሮንና ማርያም ሦስታችሁም ወደ መገናኛው ድንኳን ውጡ ብሎ ተናገረ ፤ ሦስቱም ወጡ ። እግዚአብሔርም በደመናው ዐምድ ወረደ ፤ በድንኳኑም ደጃፍ ቆመ ። አሮንንና ማርያምን ጠርቶአቸው ወጡ ። እርሱም አለ ፤ ቃሌን ስሙ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጽለታለሁ ፤ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ ። ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም ፤ እርሱ በቤቴ ኹሉ የታመነ ነው ፤ እኔ አፍ ለአፍ በግልጽ እናገረዋለሁ ፤ በምሳሌም አይደለም ፤ የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል ። በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም አለ ። እግዚአብሔርም ተቈጥቶባቸው ኼደ ።»

የእግዚአብሔር ለክብሩ ቀናተኛነት ግን በጣም ከፍተኛ በመኾኑ የሙሴ ደግነት ፡ የቀሀንትና ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ባለሟልነት ኹናቴውን ሊለውጠው አልቻለም ። ስለዚህም ነው ሙሴና አሮን በመሪባ ውሃ ጉዳይ በሕዝቡ ፊት ለእግዚአብሔር ምስጋና ባለማቅረባቸው ወደ ተስፋ ምድር እንደማይገቡ የእግዚአብሔር ውሳኔ የተነገራቸው ። ቀጥተኛ አባባሉንም ቀጥለን እንመልከት ።

«ሙሴና አሮንም ጉባኤውን በድንጋዩ ፊት ሰበሰበው እናንተ ዐመፀኞች ፡ እንግዲህ ስሙ ከዚህ ድንጋይ ውሃ እናውጣላችሁን ? አሉአቸው ። ሙሴም እጁን ዘርግቶ ድንጋዩን ኹለት ጊዜ በበትሩ መታው ፤ ብዙም ውሃ ወጣ ፤ ማኅበሩም ፡ ከብቶቻቸውም ጠጡ ። እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን በእስራኤል ልጆች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ አላመናችሁብኝምና ስለዚህ ወደ ሰጠኋችሁ ምድር ይህንን ጉባኤ ይዛችሁ አትገቡም አላቸው ።» (ዘኍ. ም. ፳ ቍ. ፲—፲፪)



ወደ ተስፋ ምድር ገብቶ ለማየት እንዲችል ይፈቀድለት ዘንድ ሙሴ በሌላ ጊዜ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ቢለምን ከእግዚአብሔር የተሰጠው መልስ ዳግመኛ ይህንን ጉዳይ እንዳያነሣና ፈስጋ በተባለችው ከፍተኛ ቦታ ተገኝቶ በሩቁ ብቻ ለማየት እንዲችል የተፈቀደለት መኾኑን በኦሪት ዘዳግም ም. ፫ ቍ. ፳፫—፳፱ መመልከት እንችላለን ።



የመሪባ ውሃ (ዘኍ ም. ፳ ቍ. ፯)

እንግዲህ ይህንን ያኽል ደግና የእግዚአብሔር ባለሟል የነበረው ሙሴ ለእግዚአብሔር ሊሰጥ ከሚገባው ክብር ስላስቀረ ለብዙ ዓመቶች በተስፋ ወደደከመለት ወደ ተስፋ ምድር ከመግባት ከተከለከለ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ ኹኔታዎች አምላክነቱንና ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያለውን እኩልነት በይፋ ሲያውጅ ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ እንዲሁም ሰማዕታትና ቅዱሳን ሲመሰክሩለትና ምስክርነታቸውንም ሲቀበል የነበረው መድኃኒታችን እርሱ ራሱ ዘላለማዊ አምላክ በመ

ኾኑ ነው እንጂ ባይኾን ኖሮ ለክብሩ ፣ ለጌትነቱና ለመለኮቱ ቀናተኛ በኾነው አምላክ ዝም ተብሎ ታለፈ ለማለት የማይቻል መኾኑን በዚሁ በሙሴ ምሳሌነት ልንረዳ እንችላለን ።

ኹለተኛው ምሳሌ የእስራኤል ሕዝብ ከምድረ ግብጽ ከወጣ በኋላ መሪዎች የሚኾኑትን ሰዎች በየጊዜው መርጦ የሚሰጠው እግዚአብሔር ነበር እንጂ በሕዝቡ ምርጫ ወይም በትውልድ አልነበረም ። እስራኤላውያን በየጊዜው የአሕዛብን የአኗኗር ዘዴ መከተል ይፈልጉ ስለነበረና በአካባቢአቸው እንደሚኖሩት አሕዛብ በንጉሥ እንዲገዙ ስለጠየቁ ከብንያም ነገድ የነበረው ሳኦል የመጀመሪያው የእስራኤል ሕዝብ ንጉሥ ኾኖ እንዲነግሥ እግዚአብሔር የፈቀደላቸው ከቅሬታ ጋር ነው ። ሳኦልም ከነገሠ በኋላ ብዙ የእስራኤል ጠላቶችን ድል እንዲያደርግ እግዚአብሔር ረድቶታል ።

የእስራኤል ሕዝብ ከምድረ ግብጽ ወጥቶ ተስፋ ወደተሰጠው አገር ለመኼድ በመንገድ ላይ በነበረበት ጊዜ እየተቃወመ ያስቸግሩትን አማሌቃውያንን እንዲበቀል በነቢዩ በሳሙኤል አማካይነት የእግዚአብሔር ትእዛዝ ለሳኦል መጣለት ። በበቀሉም እርምጃ ጊዜ ሰዎችንም ኾነ ከብቶችን አንዳችም ሳያስተርፍ እንዲያጠፋ ታዝዞ ነበር ። ይኹን እንጂ ሳኦልና ወታደሮቹ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና መመሪያ አክብረው ከመጠበቅ ይልቅ ምርጥ ለኾኑት በጎች ፣ በሬዎች ፣ የሰቡ ጥጃዎችና ጠቦቶች ራሩላቸውና ሳያጠፉአቸው ቀሩ ።

ነቢዩ ሳሙኤል ንጉሡን ሳኦልን ለምን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዳፈረሰ በጠየቀው ጊዜ በሰጠው መልስ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ አስቤ ምርጥ የኾኑትን ከማስተረፌ በቀር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አላፈረስኩም ብሏል ። ነቢዩ ግን ትእዛዝ ላፈረሰውና ትእዛዝ ማፍረሱን ግን ላላመነው ለንጉሥ ሳኦል ቀጥሎ ያለውን የማያወላውል መልስ ሰጠው ።

«በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን ? እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል ! ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል . . . . . የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔርም ንጉሥ እንዳትኾን ናቀህ ።» (፩ኛ ሳሙ. ም. ፲፭ ቊ. ፳፪—፳፫)



በትእዛዝ አፍራሽነቱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ራቀ ። ከዚያም በኋላ ከንጉሥነቱ ተሽሮ በእርሱ ምትክ ንጉሥ ዳዊት እንዲቀባ ተደረገ ። በመጨረሻም በጠላቶቹ እጅ ተገደለ ። (፩ኛ ሳሙ ም ፲፭ ቊ. ፱—፳፮ ፡ ም. ፲፮ ቊ. ፲፫—፲፬ ፡ .ም ፴፩ ቊ. ፩—፮)



ነቢዩ ሳሙኤል ዳዊትን ቀብቶ እንዳነገሠው (፩ኛ ሳሙ ም. ፲፮ ቊ. ፲፫)

በዚህም እግዚአብሔር አታድርጉ ብሎ በቀጥታ ያዘዘንን ትእዛዝ ወደ ጐን ትተን ሌላ የራሳችንን ዕቅድ ማውጣት በእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረት የማይደረግለት ኀጢአት መኾኑን ልንገነዘብ እንችላለን ።

ከዐሥሩ የእግዚአብሔር ትእዛዛት መካከል ሰንበትን ማክበር አንዱ ቢኾንም ጌታና ደቀ መዛሙርቱ ለምን ሰንበትን እንደማያከብሩ ፈሪሳውያን በጠየቁት ጊዜ ከሰጣቸው መልስ መካከል እርሱ የሰንበት ጌታ መኾኑን የሚገልጽ ነው ። ይህም ማለት እርሱ በጌትነቱ

የሰጠው ትእዛዝ እንደመኾኑ ስለ ትእዛዛቱ ማንም ሊጠይቀው መብት የለውም ማለት ነው ። ከዚህም ሌላ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፭ ፳፩—፵፰ ስድስቱን ቃላተ ወንጌል በሚደነግግበት ጊዜ ቀድሞ ያልነበሩ ሕጎችን በማከል የሕግን ተፈጻሚነት አብሥሮአል ። ይህም አስቀድሞ በሰጣት ሕግ ላይ ተመርኩዞ የሕግን ተፈጻሚነት በሚያውጅበት ጊዜ በመለኮታዊው ክብሩ መሠረት ያደረገው መኾኑን ያመለክተናል ። ንጉሥ ሳኦል እግዚአብሔር ከሰጠው ትእዛዝ ስላዘነፈ ይቅርታ እንኳን ቢለምን ምሕረት ያልተደረገለት ሲኾን ጌታ ግን የሰንበት ጌታ እርሱ ራሱ መኾኑን በሚገልጽበት ጊዜና እኔ ግን እላችኋለሁ በማለት አዳዲስ የሃይማኖት ሕጎችን በሚደነግግበት ጊዜ አስቀድሞም ቢኾን የሃይማኖት ሕጎችን የሰጠው የባሕርይ አምላክ እርሱ ራሱ ስለኾነ ነው እንጂ ቀናተኛ በኾነው አምላክ ዝም ተብሎ ሊታለፍ የማይቻል መኾኑን በሳኦል ምሳሌነት ልንረዳ እንችላለን ።

ሦስተኛ ምሳሌ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በጥበብና በሀብት ከፍ ያደረገውን እግዚአብሔርን ትቶ እንግዶች አማልክትን በተከተለ ጊዜ የእስራኤል መንግሥት ለኹለት እንደሚከፈል የእግዚአብሔር ውሳኔ ተላለፈ ። በውሳኔውም መሠረት ከሰሎሞን ሞት በኋላ የይሁዳ እና የብንያም ነገዶች ብቻ ኢየሩሳሌም ላይ የሰሎሞንን ልጅ ሮብዓምን በማንገሥ ሲቀሩ የቀሩት ዐሥሩ የእስራኤል ነገዶች ግን የናባጥን ልጅ ኢዮርብዓምን አንግሠው ወደ ሰማርያ ተሰባሰቡ ። ምንም እንኳ ዐሥራ ኹለቱ ነገዶች በኹለት የተለያዩ ግዛቶች ቢከፋፈሉ ጠቅላላው ሕዝብ ግን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ወደ ኢየሩሳሌም የመኼድ ፍላጎት እንዳለው ስለተረዳና ይህም ኹናቴ ስሜታቸውን ያስለውጥና እንዲያምፁብኝ ያደርግ ይኾናል ብሎ ስለፈራ ኢዮርብዓም ኹለት የወርቅ ጥጃዎች ጣዖታትን አሠርቶ አምላኮችህ እነዚህ ናቸውና ስገድላቸው ብሎ ሕዝቡን አሳሳተ ። ይህንኑ የጣዖት ማምለክ በዓል ባከበረበት ጊዜ ነው አንድ የእግዚአብሔር ሰው ከይሁዳ ወደ ቤቴል የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያደርስ የተላከው ። ይህም የእግዚአብሔር ሰው በዚያች አገር እኽል እንዳይበላ ፤ ውሃ እንዳይጠጣና በመጣበት መንገድ እንዳይመለስ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ተሰጥቶት ነበር ። በዚህም መሠረት ኢዮርብዓም እንዲበላና እንዲጠጣ ቢጋብዘው እንቢ ብሎ ኼደ ። በቤቴል የነበረ አንድ ሽማግሌ ነቢይ ግን በእውነት ሳይኾን በውሸት የእግዚአብሔር መልአክ እንዲበላና እንዲጠጣ መልሰው ብሎኛል ብሎ ስላታለለው እውነት መስሎት በመታለል ተመልሶ ወደ ነቢዩ ቤት ገብቶ



እኽል በላ ፤ ውሃም ጠጣ ። በዚህም ምክንያት ያ የእግዚአብሔር ሰው ወደ አገሩ ለመመለስ ገና በመንገድ ላይ እያለ አንበሳ እንዲገድለው ተደረገ ። (፩ኛ ነገ. ም. ፲፩—፲፫)

ይህ ኹናቴ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሰጠንን ቀጥተኛ ትእዛዝ ትተን በሌላ ፍጡር በኩል የሚቀርብልንን ተቃራኒ ሐሳብ በምንቀበልበት ጊዜ ሰይጣን በዚያች ዕድል ተጠቅሞ ከማሰናከል ስለማይመለስ መጠንቀቅ የሚኖርብን ለመኾኑ ትምህርት ይሰጠናል ።

ከላይ እንደተገለጸው ይህ የእግዚአብሔር ሰው የተሳሳተው ዐውቆ ሳይኾን በመታለል መኾኑ ቢነገርም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ብቻ ባለማተኮሩ በሞት የተቀጣ ኾኖ ሳለ ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው ሳያውቅ ሳይኾን ዐውቆ ከዐሥሩ ትእዛዛት አንዱ የኾነው የሰንበት ጌታ እርሱ ራሱ መኾኑን የገለጸውና አዳዲስ የሃይማኖት ሕጎችን የደነገገው ጌታ የሕግጋቱ ባለቤት በመኾኑ ነው እንጂ ያለበለዚያ ግን ቀናተኛው አምላክ በዝምታ ያልፈው እንዳልነበረ በዚሁ በእግዚአብሔር ሰው ምሳሌነትም እንደገና ልንረዳ እንችላለን ።

አራተኛው ምሳሌ ብዙዎቹ የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት በክፉ ሥራቸው እግዚአብሔርን እየበደሉ የኖሩ ሲኾኑ በአንጻሩ ደግሞ አንዳንዶቹ ፈቃዱን በመፈጸም ረገድ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ኾነ ተገኝተዋል ። ከእነዚህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጻሚዎች ከነበሩት ነገሥታት መካከል ዖዝያን የተባለው የይሁዳ ንጉሥ ይገኙባቸዋል ። ዖዝያንም በብዙ መንገድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጻሚ ስለነበረ እግዚአብሔር ረድቶት ከፍ ከፍ ማለት በጀመረ ጊዜ ልቡ ታበየበትና እግዚአብሔርን በደለ ። ለካህናት በቀር ለሌሎች ሰዎች ያልተፈቀደውን ሥልጣን በመዳፈር ወደ መቅደስ ውስጥ ገብቶ በዕጣን መሠዊያው ላይ ዐጠነ ።ካህናቱም ይህ ድፍረቱ ተገቢ የኾነ ሥራ አለመኾኑን ቢገልጹለት እንደደፈሩት ገምቶ ከመቈጣቱ በቀር ጥፋቱን አምኖ አላረመም ። ይህም ድፍረቱ እግዚአብሔርን ስላስቈጣ በግንባሩ ላይ ለምጽ እንዲወጣበት አደረገው ። ለምጻምም በመኾኑ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ከሰው ኹሉ በተለየ ቤት ከኅብረተ ሰቡ ተለይቶ ኖረ እንጂ እንደገና በንጉሥነቱ ለመግዛት ወይም ከኅብረተሰቡ ጋር ለመቀላቀል አልቻለም ። (፪ኛ ዜ. መ. ም. ፳፮)

ምንም እንኳ ንጉሥ ዖዝያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ረገድ ታማኞች ተብለው ከሚታወቁት አንዱ ቢኾን ለካህናት እንጂ ለእርሱ ያልተሰጠውን ሥልጣን በመዳፈሩ አስቸኳይ ቅጣት የተፈጸመ በት ሲኾን መድኀኒታችን ግን «እኔና አብ አንድ ነን ፤ እኔን ያየ አብን አየ ፤ ለአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ነው ፤ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው ።» በሚሉትና በሌሎችም እነዚህን በመሳሰሉ አባባሎች መለኮታዊ ክብ ሩን ሲገልጽና ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት ሲያረጋግጥ አባባሎቹ ትክክል ስለኾኑና እርሱም ዘላለማዊ የባሕርይ አምላክ ስለኾነ ነው እንጂ እንኳን ራስን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከል ቀርቶ ለሌላ ወገን የተሰጠውን ሥልጣን መዳፈርም የሚያስቀጣውና ቀናተኛው አምላክ ዝም ብሎ የማያሳልፍ መኾኑን በዖዝያን ምሳሌነት ልንረዳ እንችላለን።(ማቴ. ም. ፲፪ ቍ. ፰ ፣ ዮሐ. ም. ፲ ቍ. ፴ ፣ ም. ፲፬ ቍ. ፱ ፣ ም. ፲፯ ቍ ፲፭)

ከላይ በቀረቡት ልዩ ልዩ ምሳሌዎች መሠረት እግዚአብሔር ለክብሩ የቱን ያኽል ቀናተኛ መኾኑንና ትእዛዛቱንም በትክክል ግብር ላይ የማያውለውን ሰው ወይም ከእግዚአብሔር ያልተሰጠውን መን ፈሳዊ ሥልጣን የሚዳፈር ሰው ያለምሕረት እንደሚቀጣው ለመረዳት እንችላለን ። ስለዚህም ነው መለኮታዊ ክብሩን እያንጸባረቀ የመጣውን የልዑል እግዚአብሔርን ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ልንገነዘብ የምንችለው ። ነቢያት ፣ ሐዋርያት ፣ ጻድቃንና ሰማዕታት ብቻ ሳይኾኑ ጠላቶቹ አጋንንት እንኳ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ጌትነት መስክ ረዋል ። (ማቴ. ም. ፰.ቍ. ፳፱)

ሐ   የነቢያት ምስክርነት

ስለ መድኀኒታችን ዘላለማዊ ክብር ፣ መለኮታዊ [illegible] ለማዳን ከድንግል ተወልዶ ሰው በመኾን ስለሚደርስበት ሕማምና ሞት የተለያዩ ነቢያት ብዙ ትንቢቶች [illegible]ው ትንቢቶቹም በየጊ ዜአቸው ተፈጽመዋል ።

በቅድሚያ ትንቢቶች ተነግረው በጌታ ጊዜ በትክክል መፈጸማ ቸው ለመድኀኒታችን ማንነት አንድ ትልቅ ማስረጃ መኾኑ ግልጽ ነው ።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከተነገሩት ትንቢቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።



«እነሆ ፣ ድንግል ትፀንሳለች ፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፤ ስሙ ንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ።» (ኢሳ. ም. ፯ ቍ. ፲፬)

«ሕፃን ተወልዶልናልና ፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ፣ አለቅነ ትም በጫንቃው ላይ ይኾናል ፤ ስሙም ድንቅ ፣ መካር ፣ ኀያል አምላክ ፣ የዘላለም አባት ፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ።» (ኢሳ. ም. ፱ ቍ. ፮)

«በእውነት እርሱ ደዌአችንን ተቀበለ ፤ ሕማማችንንም ተሸክሞ አል ፤ እኛ ግን እንደተመታ ፣ በእግዚአብሔር እንደተቀሰፈ ፣ እንደተ ቸገረም ቈጠርነው ፤ እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ ፤ ስለ በደላች ንም ደቀቀ ፤ የደኅንነታችን ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ ፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን ።» (ኢሳ. ም. ፶፫ ቍ. ፬—፭)

«በሌሊት ራእይ አየሁ ፤ እነሆም የሰው ልጅን የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ ፤ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ወደፊቱም አቀረቡት ፤ ወገኖችና አሕዛብ ፣ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ኹሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር ፣ መንግሥትም ተሰጠው ፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው ፤ መንግሥቱም የማይጠፋው ነው ።» (ዳን. ም· ፯ ቍ. ፲፫—፲፬)

«ዐመፃ ይጨረስ ፣ ኀጢአትም ይፈጸም ፣ በደልም ይሰረይ ፤ የዘላ ለም ጽድቅ ይገባ ፣ ራእይና ትንቢት ይታተም ፣ ቅዱስ ቅዱሳኑም ይቀባ ዘንድ ለሕዝብህና ለቅድስት ከተማህ የሰባ ሱባዔ ጊዜ ተወስኗል ።

ትእዛዙ ከሚወጣበት ጊዜ ጀምሮ መሲሑ እስከ ሚመጣበት እስከ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ኹለት ሱባዔ ድረስ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰህ [illegible]ትጠግንና እንድትሠራ ዕወቅ ፣ አስተውል ። መንገዱና [illegible] በሚታደሱበት ጊዜ የጭንቀት ጊዜ ይኾናል ። ከስድሳ ኹለትና ከሰባ ሱባዔ በኋላ መሲ[illegible]ላል ፤ የሚሞተውም ለራሱ አይደለም ። የሚመጣውም አለቃ [illegible]ማይቱንና መቅደሱን ያጠፉሉ ። . . . . እርሱም ከብዙ ሰዎች [illegible] ቃል ኪዳን ለአንድ ሳምንት ያደርጋል ፤ በሳምንቱም እኩሌታ መሥዋዕቱንና ቍርባኑን ያስቀራል ።» (ዳን. ም. ፱ ቍ. ፳፬ — ፳፯)

በትንቢተ ዳንኤል ም. ፱ ቍ. ፳፬—፳፯ ላይ የተሰጠውን ትንቢት በአጭሩ ለመተርጐም ሦስት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን ማስተዋል ያስፈ ልጋል ። እነርሱም ፦

አንደኛ/ ኢየሩሳሌምና ግንቦቿ እንዲታደሱ ትእዛዝ የተሰጠበት ጊዜ ፥

ኹለተኛ/ ሱባዔ የሚለው ቃል ትርጓሜ ፥

ሦስተኛ/ ትእዛዙ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ መሲሑ እስከሚመጣበት ድረስ ያለው የጊዜ አከፋፈል ።

በኦሪት ዘኍልቍ ም. ፲፬ ቍ. ፴፬ እና በትንቢተ ሕዝቅኤል ም ፬ ቍ ፮ መሠረት የትንቢት ቀንን በዓመት በመተርጐም ሰባ ሱባዔ የተባለው አራት መቶ ዘጠና ዓመቶች ናቸው በማለት አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሊቃውንት ይስማማሉ ። 70x7

ትእዛዙ ከተሰጠበት ጀምሮ መሲሑ እስከሚመጣበት ድረስ ያለው ጊዜ በሦስት ክፍል ተከፋፍሎ ቀርቦአል ።

የመጀመሪያው ሰባት ሱባዔ (ሳምንት)

ኹለተኛው ስድሳ ኹለት ሱባዔ (ሳምንት)

ሦስተኛው አንድ ሱባዔ (ሳምንት)

የመጀመሪያው ሰባት ሳምንት ማለት አርባ ዘጠኝ ዓመት ትእዛዙ ከተሰጠበት ጀምሮ ቤተ መቅደሱን ለማደስ የፈጀው ጊዜ ነው ።

ስድሳ ኹለቱ ሳምንት ቤተ መቅደሱ ከታደሰ በኋላ አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱበት ጀምሮ ጌታ የማስተማር ሥራውን እስከጀመረበት ድረስ ያለው ጊዜ ነው ።

አንዱ ሳምንት ማለት ሰባቱ ዓመት ደግሞ የጌታ ያገልግሎት ዘመን ቢኾንም በቍ ፳፯ ላይ በሳምንቱ እኩሌታ በተባለው መሠረት ከሰባቱ በአራተኛው ዓመት ማለት ሦስቱን ዓመት ካሳለፈ በኋላ ሕማምንና ሞትን ድል ነሥቶ ወደ ሰማይ ያረገበት ነው ። ይኸውም ሥራውን የጀመረው በሠላሳ ዓመቱ ሲኾን እስከ ዕርገቱ ድረስ በማስተማር የቈየው ሦስት ዓመት ነው ። (ሉቃ. ም. ፫ ቍ. ፳፫)

በሦስት ክፍል የተከፋፈለውን የአራት መቶ ዘጠና ዓመቱን ትንቢት በሚከተለው የሒሳብ ስሌት እንመልከት ።



| | | | |
|---|---|---|---|
| የቤተ መቅደሱ የዕድሳት ጊዜ | (7X7) | = | 49 |
| ጌታ ፴ ዓመት እስኪኾነው | (62X7) | = | 434 |
| ቀሪው ሰባት ዓመት | (1X7) | = | 7 |
| | | | 490 |

በሌላ በኩል ደግሞ ቤተ መቅደሱ እንዲታደስ ከአርጤክስስ ትእዛዝ የተላለፈው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፬፻፶፯ ዓመት መኾኑ ታውቋል። (የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ በየቤታችን ገጽ ፻፺፱ በእንግሊዝኛ)

(የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች መልስ (በአረብኛ) ገጽ ፻፲፬)

ከ፬፻፺ ላይ ፬፻፶፯ ሲቀነስ ፴፫ በመኾኑ ይኸውም ጌታ እስከ ዕርገቱ ድረስ በዚህ ዓለም ላይ ያሳለፈው ዘመን ነው ።

ቤተ መቅደስ እንዲታደስ ትእዛዝ የተሰጠበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ፬፻፶፬ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ ። እነርሱ ደግሞ ከ፬፻፺ ዓመት ላይ ፬፻፶፬ ሲቀንሱ ፴፮ ስለሚመጣላቸው ከ፴፮ ላይ ሠላሳ ሦስት ተቀንሶ የሚገኘው ፫ ዓመት በሳምንቱ እኩሌታ የሚለውን አባባል ይተረጉማል ይላሉ ። ዘመኑ ፬፻፶፬ ነው የሚሉት ወገኖች አባባል ቀደም ተብሎ ከተዘረዘረው ኹናቴ ጋር ተመሳሳይነት አለው ። ዘመኑ ፬፻፶፯ ነው የሚለው አባባል ግን ከሌላው ትርጓሜ ጋር ስለማይስማማ የስሌት ችግርን ሊፈጥር ይችላል ።

መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል የተባለውን የትንቢት አፈጻጸም ለመረዳት ወደ ዕብራውያን በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፲ ቍ. ፩—፲ ብንመለከት መድኀኒታችን የቀድሞውን የመሥዋዕት ሥነ ሥርዓት ሽሮ በራሱ መሥዋዕትነት የተካው መኾኑን ለመረዳት እንችላለን ።

ሀመፃ ወይም መተላለፍ ፥ ኀጢአትና በደል የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ናቸው ። በዚህም መሠረት ጌታ የሰውን ልጅ ሥጋ ለብሶ ለሰው ልጅ ቤዛ በመኾኑና እኛም አምነንና በትእዛዛቱ ጸንተን ከኖርን ከኀጢአታችን ነጻ ያወጣን መኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፳፱ ፥ ም. ፫ ቍ. ፲፮ ፥ ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው በሐዋርያው የጳውሎስመልእክት ም. ፭ ቍ. ፲፰ ፥ ም. ፰ ቍ. ፥ ፫ በመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ም. ፩ ቍ. ፯ ፥ ም. ፪ ቍ. ፪ ላይ መመልከት እንችላለን ።

በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ም. ፭ ቍ. ፲፱ ላይ እንደተገለጸው በአንድ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደኾኑ እንዲሁም በአንድ ሰው መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይኾናሉ ተብሎአል ። ስለዚህ በክርስቶስ አምኖ በጽድቅ መንገድ ለተጓዘ ኹሉ የዘላለም ጽድቅ ይጠብቀዋል ማለት ነው ።

የራእይና የትንቢት መታተም ተብሎ የተጠቀሰው ደግሞ ብዙዎቹ ነቢያት ራእይ ያዩትና ትንቢት የተናገሩት ስለ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመኾኑና የተነገሩትም ትንቢቶች አምላክ ሰው በኾነ ፣ ሕማምና ሞት ደርሶበት ከሙታን ተለይቶ በመነሣት ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ በመፈጸማቸው የራእይና የትንቢት መታተም የተባለው ስለዚህ ነው ። ለዚህም የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

«እንዲህም አላቸው ፣ ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ በሙሴ ሕግ ፣ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ኹሉ መፈጸም አለበት ብዬ የነገርኋችሁ ቃል ይህ ነው ።» (ሉቃ. ም. ፳፬ ቍ. ፵፬)

«ሙሴም እንዲህ ብሎአል ፣ እግዚአብሔር አምላክ እኔን እንዳስ ነሣኝ እንዲሁ ከወንድሞቻችሁ መካከል ነቢይ ያስነሣላችኋል ፤ እርሱ የሚነግራችሁን ኹሉ ስሙ ፤ ያን ነቢይ የማይሰማ ኹሉ ከሕዝብ ተለ ይቶ ይጥፋ ። ቀጥሎም ከሳሙኤል ጀምሮ የነበሩ ነቢያት ኹሉ ስለዚህ ዘመን እንዲሁ ተናግረዋል ። (የሐ. ሥ. ም. ፫ ቍ. ፳፪—፳፬)

«የዚህን ድኅንነት ነገር ነቢያት በጥንቃቄ ፈልገውና መርምረው ነበር ፤ ስለዚህ እነዚህ ነቢያት እግዚአብሔር ስለሚሰጣችሁ ጸጋ አስ ቀድመው በትንቢት ተናገሩ ። በእነርሱ ውስጥ የነበረውም የክርስቶስ መንፈስ ክርስቶስ ስለሚደርስበት መከራና ከመከራውም በኋላ ስለሚ ያገኘው ክብር አስቀድሞ አመልክቶ ነበር ፤ እነርሱም ይህን ኹሉ በምን ጊዜና በእንዴት ያለ ኹኔታ እንደሚኾን መርምረው ነበር ።» (፩ኛ ጴጥ. ም. ፩ ቍ. ፲—፲፩)

የቅዱሰ ቅዱሳን መቀባት የተባለው የመለኮትና የትስብእት መዋ ሐድ ነው ።

መንገዱና ግንቡ በሚታደሱበት ጊዜ የጭንቀት ጊዜ ይኾናል ለሚለው ትንቢት በመጽሐፈ ዕዝራ ም. ፬ ላይ ብንመለከት ምን ዐይ ነት ችግር እንደደረሰባቸው ለመረዳት ይቻላል ።



የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፉሉ ተብሎ በቍ. ፳፮ ላይ የተነገረው ትንቢት መድኀኒታችን በሉቃስ ወን ጌል ም. ፲፱ ቍ. ፵፩—፵፬ በኢየሩሳሌም ላይ ከተናገረው ትንቢት ጋር ተመሳሳይ ነው ። ይህ ትንቢት እንዴት ተፈጻሚነትን እንዳገኘ ለማ ወቅ የታሪክን ምስክርነት የተመለከትን እንደኾነ ማርቲን ኖት የተባለ የቦን ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ በተሰኘው መጽ ሐፉ በገጽ ፬፻፵፫ ላይ የሮም ወታደሮች እንዴት አድርገው የኢየሩሳሌ ምን ከተማና ቤተ መቅደሱን ለመጨረሻ ጊዜ በሰባ ዓ. ም. እንዳፈ ረሱት ዘርዝሮ በመግለጽ የሚያብራራ ኾኖ እናገኘዋለን ።

የነቢዩን የዳንኤልን ትንቢት አፈጻጸም ትንታኔ በዚሁ እናብቃና ወደቀሩት ወደ ሌሎቹ የትንቢት ጥቅሶች እንመለስ ።

«አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ ፣ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትኾኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ፤ ካንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የኾነ በእስራኤል ላይ ገዢ የሚኾን ይወጣልኛል ።» (ሚክ. ም. ፭ ቍ. ፪)

«የጽዮን ልጅ ሆይ ፣ እነሆ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ ደስም ይበልሽ ይላል እግዚአብሔር ። በዚያም ቀን ብዙ አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር ይጠጋሉ ፤ ሕዝብም ይኾኑኛል ፤ በመካከልሽም እኖራ ለሁ ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ወደ አንቺ እንደላከኝ ታውቂአ ለሽ ።» (ዘካ. ም. ፪ ቍ. ፲—፲፩)

## መ. የእግዚአብሔር መጠሪያዎችና ክብሩ

ለፈጣሪ አምላክ ብቻ መቅረብ ያለባቸው የመለኮት መጠሪያዎች እና አምልኮታዊ ስግደት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የጌታችን ፣ የመድ ኀኒታችን ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘብ ኾነው መቅረባቸው መድኀኒ ታችን እሱው ራሱ ዘላለማዊ አምላክ ለመኾኑ በቂ ማስረጃዎች ናቸው ። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ጥቅሶች ይገኙባቸዋል ።

«በመጀመሪያ ቃል ነበረ ፤ ቃሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፤ ይህም ቃል እግዚአብሔር ነበረ ።» (ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፩)

በዮሐንስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፫ ላይ ኹሉ ነገር በእርሱ እንጂ ያለ
እርሱ ምንም የተፈጠረ ነገር እንደሌለ የተነገረለት መድኀኒታችን
በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፩ ላይ ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በእነርሱ
የሚገኙትን ፍጥረቶች የፈጠረው እግዚአብሔር መባሉን እናስተውል ።

«በገዛ ደሙ የዋጃት የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን» . . . .
(የሐ. ሥ. ም. ፳ ቍ. ፳፰)

«ክርስቶስ በሥጋ የመጣው ከእነርሱ ነው ፤ እርሱም ከኹሉ
በላይ የኾነ የተባረከ አምላክ ነው ።» (ም ፱ ቍ ፭)

«የሃይማኖታችን ምሥጢር ታላቅ ነው ፤ እርሱም እግዚአብሔር
ሰው ኾኖ የተገለጸ ፡ እውነተኛነቱ በመንፈስ የታወቀ ለመላእክት
የታየ ፡ ለሕዝቦች ኹሉ የተሰበከ ፡ በክብር ወደ ሰማይ የወጣ የሚል
ነው ። (፩ኛ ጢሞ. ም. ፫ ቍ. ፲፮)

«ለኢየሱስ ስም ክብር በሰማይና በምድር ፡ ከምድርም በታች
ያሉት ኹሉ በጉልበታቸው ይንበረከካሉ ።» (ፊልጵ. ም. ፪ ቍ. ፲)

«እግዚአብሔር የበኵር ልጁን ልኮ ወደ ዓለም ሲያስገባ የእግዚ
አብሔር መላእክት ኹሉ ይሰግዱለታል ።» (ዕብ. ም. ፩ ቍ. ፮)

«የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣና እውነት የኾነውን እርሱን እን
ድናውቀው አስተዋይ ልቡና እንደሰጠን እናውቃለን ። እኛም በዚህ
እውነት በኾነው በኢየሱስ ክርስቶስ እንኖራለን ፤ እርሱ እውነተኛ
አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው ።» (፩ኛ ዮሐ. ም. ፭ ቍ. ፳)

ሠ. <u>የሃይማኖት ጸሎት</u>

ወልድ ፍጡር ነው በማለት የክሕደት ትምህርት ያስተማረውን
አርዮስን ለማውገዝ በሦስት መቶ ሃያ አምስት ዓ. ም. የተሰበሰቡት
ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት የዓለም ኤጲስ ቆጶሳትና መንፈስ ቅዱስ
ደግሞ ፍጡርና የወልድ አገልጋይ ነው በማለት የክሕደት ትምህርት
ያስተማረውን መቅዶንዮስን ለማውገዝ በሦስት መቶ ሰማንያ አንድ
ዓ. ም. የተሰበሰቡት አንድ መቶ ኀምሳ የዓለም ኤጲስ ቆጶሳት ከሐዲ



ዎቹንና ክሕደታቸውን ካወገዙ በኋላ ለክርስቲያን ሃይማኖት መሠ
ረት የኾነውንና በሃይማኖት ጸሎት ስም የታወቀውን የእምነት ቀኖና
ወስነዋል ። ይህም ቀኖና ስለእምነታችን አጠቃላይ ውሳኔዎችን የያዘ
ከመኾኑም በላይ በተለየ ግን ስለ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ዘላለማዊ ጌትነት ፡ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ መወለዱ ፡ ፍጥረትን
ኹሉ የፈጠረ እርሱ መኾኑ ፡ ምንም እንኳ በመለኮቱ ከአብ ጋር እኩል
ቢኾን የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል ከሰማይ ወርዶ በመንፈስ ቅዱስ ከቅ
ድስት ድንግል ማርያም መወለዱ ፡ ሕማማትን መቀበሉና መሞቱ ፡
ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በክብር ወደ ሰማይ ወጥቶ በአብ በስተ
ቀኝ መቀመጡና ዳግመኛም ወደፊት ለመጨረሻው ፍርድ ወደዚህ
ዓለም ተመልሶ የሚመጣ ለመኾኑ ምስክርነት ተሰጥቶበታል ። አንዳ
ንድ ወገኖች ይህንን የሃይማኖት ቀኖና ግምት የማይሰጡት ከመኾና
ቸውም በላይ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ይመ
ስላቸዋል ።

ጥንታውያኑ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች በየሲኖዶሶቻቸው
አማካይነት እንደ እነዚህ ያሉትን የሃይማኖት ቀኖናዎች በሚያረንግት
በት ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግና በመንፈስ ቅዱስ
በመመራት እንጂ የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ የሚወስኑ አለመኾናቸው
ንና ቀደም ተብሎ በምዕራፍ ሦስት የተገለጸው የሃይማኖት ጸሎትም
እንዴት አድርጎ በቅዱሳት መጻሕፍት የተደገፈ መኾኑን ለመረዳት
የሚቀጥሉትን ዝርዝር ኹናቴዎች እንመልከት ።

<u>ኹሉን በያዘ ፡ ሰማይንና ምድርን ፡ የሚታይና</u>

<u>የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ</u>

<u>በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ።</u>

«ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኹንልህ ።» (ዘፀ. ም. ፳ ቍ. ፫)

«እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን ፡ ባሕርንና በእ
ርሱም ውስጥ የሚገኙትን ፈጠረ ። (ዘፀ. ም. ፳ ቍ. ፲፩)

«እንግዲህ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ ፡ በታችም በምድር አም
ላክ እንደኾነ ሌላም እንደ ሌለ ዛሬ ዕወቅ ፤ በልብህም ያዝ ።» (ዘዳ.
ም. ፬ ቍ. ፴፱)

«እስራኤል ሆይ ፡ ስማ ፡ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው ።» (ዘዳ. ም. ፮ ቍ. ፬)

«የእኛ አምላክ ግን የኹሉ ነገር ፈጣሪ የኾነና እኛም የእርሱ የኾንን አንዱ እግዚአብሔር አብ ብቻ ነው ።» (፩ኛ ቆሮ ም. ፰ ቍ. ፮)

«ደግሞም ከኹሉ በላይ የኾነ ፡ በኹሉም የሚሠራ ፡ በኹሉም የሚኖር ፡ ለኹሉም አባት የኾነ አንድ አምላክ አለ ።» (ኤፌ. ም. ፬ ቍ. ፮)

«ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ በተወለደ ፡
የአብ አንድያ ልጁ በሚኾን በአንድ
ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ።

«እግዚአብሔርም አንተ ልጄ ነህ ፡ እኔ ዛሬ ወለድኩህ አለኝ ።» (መዝ. ፪ ቍ. ፯)

«ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ ።» (መዝ. ፻፲ ቍ. ፫)

«በእርሱ የሚያምን ኹሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና ።» (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፲፮)

«በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፲፮ ቍ. ፴፩)

«ኹሉ ነገር በእርሱ የተፈጠረና እኛም በእርሱ የምንኖር አንዱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ።» (፩ኛ ቆሮ. ም. ፰ ቍ. ፮)

«ለኢየሱስ ስም ክብር በሰማይና በምድር ፡ ከምድርም በታች ያሉት ኹሉ በበጉልበታቸው ይንበረከካሉ ፤ በምላሳቸውም ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ጌታ ነው ብለው በመመስከር ለእግዚአብሔር አብ ክብር ይሰጣሉ ።» (ፊልጵ. ም. ፪ ቍ. ፲—፲፩)



ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፡ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ
እውነተኛ አምላክ ፡ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ ፡
በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል ፡

«ቃል ከኹሉ በፊት ነበረ ፤ ቃሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፤ ይህም ቃል እግዚአብሔር ነበረ ።» (ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፩)

«እኔና አብ አንድ ነን ።» (ዮሐ. ም. ፲ ቍ. ፴)

«እኔን ያየ አብን አይቶአል ።» (ዮሐ. ም. ፲፬ ቍ. ፱)

«የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ነው ።» (ዮሐ. ም. ፲፮ ቍ. ፲፭)

«ከአብ ዘንድ ወደ ዓለም መጥቼአለሁ ፤ እንደገናም ይህንን ዓለም ትቼ ወደ አብ እኼዳለሁ ።» (ዮሐ. ም. ፲፮ ቍ. ፳፰)

«ፍርዱም ይህ ነው ፤ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለኾነ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ ።» (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፲፱)

ኹሉ በእርሱ የኾነ ፡

«ኹሉ ነገር በእርሱ ተፈጠረ ፤ ከተፈጠረው ኹሉ አንድም ነገር ያለ እርሱ የተፈጠረ የለም ።» (ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፫)


«በሰማይና በምድር ያሉት ፡ የሚታዩትና የማይታዩት ፡ የሰማይ ኀይሎችና ገዢዎች ፡ አለቆችና ባለ ሥልጣኖች ኹሉ የተፈጠሩት በእርሱ ነው ።» (ቆላ ም. ፩ ቍ. ፲፮)

ስለ እኛ ስለ ሰዎች ፡ እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ ፡
በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ኾነ ።

«እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ።» (ኢሳ. ም. ፯ ቍ. ፲፬)

«ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ኹኔታ እንዲህ ነው ፤ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳለ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች ።» (ማቴ. ም. ፩ ቍ. ፲፰)

«መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፤ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል ፤ ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ።» (ሉቃ. ም. ፩ ቍ. ፴፭)



ጲላጦስም ካስገረፈው በኋላ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው ።» (ማቴ ም. ፳፯ ቍ. ፳፮)

«ነገር ግን የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከልን ፤ እርሱም ከሴት ተወለደ ፤ ለሕግም ታዛዥ ኾነ ።» (ገላ. ም. ፬ ቍ. ፬)



ሰው ኾኖ በጳንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ ሞተ ፤ ተቀበረ ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ ።

«ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር ማንም ወደ ሰማይ የወጣ የለም ።» (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፲፫)



«በእውነት ደዌአችንን ተቀበለ ሕማማችንንም ተሸከሞአል ፤ ስለመተላለፋችን ቈሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ ፤— በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን ።» (ኢሳ ፶፫ ቍ. ፬—፭)

«ይህ ነገር ሁከት ማስነሣት እንጂ ሌላ ምንም እንደማይጠቅም ባየ ጊዜ ጲላጦስ ውሃ አስመጥቶ እኔ ለዚህ ሰው ሞት ኀላፊ አይደለሁም እናንተ እንደፈለጋችሁ አድርጉ ብሎ እጁን ታጠበ ።» (ማቴ. ም. ፳፯ ቍ. ፳፬)

«በዚያን ጊዜ ጲላጦስ በርባንን ፈትቶ ለቀቀላቸው ፤ ኢየሱስን ግን ካስገረፈው በኋላ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው ።» (ማቴ. ም. ፳፯ ቍ. ፳፮)

«ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾና ነፍሱን ሰጠ ።» (ማቴ. ም. ፳፯ ቍ. ፶)



«ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ ስለ ዐመፀኞች ማለደ ።» (ኢሳ. ም. ፶፫ ቍ. ፲፪)

«ዮሴፍም በንጹሕ በፍታ ሥጋውን ከፈነው ፤ከዐለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው፤በመቃብሩም ደጃፍ ትልቅ ድንጋይ አንከባልሎ ኼደ ።» (ማቴ. ም. ፳፯ ቍ. ፶፱—፷)



«እርሱም ከሞት እነሣለሁ ብሎ እንደተናገረው ተነሥቶአልና እዚህ የለም ።» (ማቴ. ም. ፳፰ ቍ. ፮)

«ሕያውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ ? ተነሥቶአል እንጂ እዚህ የለም ።» (ሉቃ. ም. ፳፬ ቍ. ፭)




«ከስድሳ ሁለትና ከሰባት ሱባዔ በኋላ መሲሕ ይገደላል የሚሞተውም ለራሱ አይደለም ።» (ዳን ም. ፱ ቍ. ፳፭—፳፮)

«ተቀበረ ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ተነሣ ።» (፩ኛ ቆሮ. ም. ፲፭ ቍ. ፬)

«ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣ የእኛም ትምህርት ኸ፣ የእናንተም እምነት ከንቱ መኾኑ ነው ።» (፩ኛ ቆሮ. ም. ፲፭ ቍ. ፲፬)

በክብር ወደ ሰማይ ወጣ ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ።

«ሲባርካቸውም ሳለ ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ሰማይ ወጣ ።» (ሉቃ. ም. ፳፬ ቍ. ፶፩)



የጌታ ትንሣኤ (ማቴ ም. ፳፰ ቍ. ፩—፮)

«ይህንንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰውራ ተቀበለች ው ።» (የሐ. ሥ. ም. ፩ ቍ. ፱)

«እርሱም ሲኼድ ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ኹለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ ፤ ደግሞም የገሊላ ሰዎች ሆይ ፡ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲኼድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው ።» (የሐ. ሥ. ም. ፩ ቍ. ፲—፲፩)



«እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር አየ ። ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየው ።» (የሐ. ሥ. ም. ፯ ቍ. ፶፭)



የጌታ ዕርገት (የሐ. ሥ. ም. ፩ ቍ. ፲—፲፩)

«በሌሊት ራእይ አየሁ ፤ እነሆም የሰው ልጅን የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ ፤ . . . ወገኖችና አሕዛብ ፥ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ኹሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር ፥ መንግሥትም ተሰጠው ፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው ፤ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው» (ዳን ም. ፯ ቍ. ፲፫—፲፬)

«የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ኾኖ ከመላእክቱ ጋር ይመጣል ፤ በዚያን ጊዜም ለያንዳንዱ እንደየሥራው መጠን ዋጋውን ይከፍለዋል ።» (ማቴ. ም. ፲፮ ቍ. ፳፯)

«በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም ።» (ሉቃ. ም. ፩ ቍ. ፴፫)

«የትእዛዝ ድምፅ ፣ የመላእክት አለቃ ድምፅ ፣ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰማል ፤ ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል ።» (፩ኛ ተሰ. ም. ፬ ቍ. ፲፮)

ሕይወትን በሚሰጥ ጌታ ከአብ በሠረጸ ፣ ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለት ፣ በነቢያት አድሮ በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን

«እንግዲህ ኺዱና የዓለምን ሕዝብ አስተምሩ ፤ በአብ ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው ።» (ማቴ. ም. ፳፰. ቍ. ፲፱)

«ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እንዲህ አለ ።» (ማር. ም. ፲፪ ቍ. ፴፮)

«ነገር ግን ከአብ የሚሠርጽና እኔም ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ ፣ የእውነት መንፈስ ሲመጣ እርሱ ለእኔ ይመሰክራል ።» (ዮሐ. ም. ፲፭ ቍ. ፳፮)

«ማንኛውም ትንቢት ከቶ ከሰው ፈቃድ አልመጣም ! ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ተቀብለው የተናገሩት ነው ።» (፪ኛ ጴጥ. ም. ፩ ቍ. ፳፩)

«በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው ፤ እነርሱም አብ ቃልና መንፈስ ቅዱስ ፣ እነዚህም ሦስቱ አንድ ናቸው ።» (፩ኛ ዮሐ. ም. ፭ ቍ. ፯)

ዓለም በቀፋዊትና ሐዋርያዊት በኾነች በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ።

«አንተ ጴጥሮስ ወይም ዐለት ነህ ፤ በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ፣ ይህቺንም ቤተ ክርስቲያን የሲኦል በሮች እንኳ አያሸንፉአትም ።» (ማቴ ም. ፲፮ ቍ. ፲፰)



«እነርሱንም አልሰማ ቢል ለቤተ ክርስቲያን ንገር ፤ ቤተ ክርስቲያንንም የማይሰማ ከኾነ እንደአረመኔና እንደ ኀጢአተኛ ቍጠረው ።» (ማቴ. ም. ፲፰ ቍ. ፲፯)

«ባሎች ሆይ ፣ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደና ራሱን ስለ እርስዋ አሳልፎ እንደሰጠ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ ።» (ኤፌ. ም. ፭ ቍ. ፳፭)

ኀጢአትን ለማስተስረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ፤ የሙታን መነሣትና የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን ፤ ለዘላለሙ አሜን ።

«በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ፣ እኩሌቶቹ ደግሞ ወደ ኀፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቍልና ።» (ዳን. ም. ፲፪ ቍ. ፪)

«ሙታንስ ሲነሡ በሰማይ እንዳሉት መላእክት ይኾናሉ እንጂ አያገቡም ወይም አይጋቡም ። ስለ ሙታን መነሣት የኾነ እንደኾነ ግን እግዚአብሔር ሙሴን በቍጥቋጦው እሳት ውስጥ ምን እንደተናገረው ከሙሴ መጽሐፍ አላነበባችሁምን ? ይኸውም እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ያለው ነው ። ስለዚህ እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም ።» (ማር. ም. ፲፪ ቍ. ፳፭—፳፯)

«ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ በእውነት እልሃለሁ ፤ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ።» (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፭)

«መልካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል ።» (ዮሐ. ም. ፭ ቍ. ፳፱)

«ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው ፣ ንስሓ ግቡ ፤ ኀጢአታችሁም ይቅር እንዲባልላችሁ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ፤

የእግዚአብሔር ስጦታ የኾነውን መንፈስ ቅዱስንም ትቀበላላችሁ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፪ ቁ ፴፰)

«አንድ ጌታ ፡ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ ።» (ኤፌ. ም. ፬ ቁ. ፭)

«የእኛ አገር በሰማይ ነው ፤ ከሰማይም የምንጠባበቀው አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል ፡ እርሱም ይህንን ጐስቋላውን ሰውነታችንን የእርሱን ክቡር ሰውነት እንዲመስል ዓለምን በሚገዛው ከሃሊነቱ ይለውጠዋል ።» (ፊልጵ. ም. ፫ ቁ. ፳—፳፩)

«ጥምቀት የሰውነትን እድፍ ማስወገድ ሳይኾን በመልካም ሕሊና ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ልመና ነው ፤ የሚያድናችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ነው ።» (፩ኛ ጴጥ. ም. ፫ ቁ. ፳፩)

ረ. የመከራከሪያ ጥቅሶችና መልሶቻቸው

የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ባሕርይና በዘላለማዊ አምላክነቱም ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት በመካድ ወይም በመጠራጠር ከሚቀርቡት የመከራከሪያ ጥቅሶች መካከል ጥቂቶቹ ቀጥለው የተዘረዘሩት ሲኾኑ ለእነርሱም ማብራሪያዎችና መልሶች ተሰጥተውባቸዋል ።

(ጥበብ) ከኹሉ በፊት ጌታ ፈጠረኝ (አለች)
(ምሳ. ም. ፰ ቁ. ፳፪)

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው የመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፩ ቁ. ፳፬ ላይ በገለጸው መሠረት ጥበብ የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲኾን እንዴት ጌታ ፈጠረኝ አለ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ።

ያለ እርሱ ፈጣሪነት ምንም የተፈጠረ ነገር የሌለና አብን በመልክ የሚመስለውና በ ብር የሚተካከለው ወልድ የተፈጠረ ነው ማለት ድፍረትም ኀጢአትም ነው ።



ተፈጠረ የተባለው ግን የሰውን ዘር ለማዳን በለበሰው ሥጋ ነው ። በዚህም መሠረት ነው «ጥበብ ለራስዋ ቤት ሠራች» ተብሎ የተገለጸው (ምሳ. ም. ፱ ቁ. ፩) ። የኑሲሱ ቅዱስ ጎርጎርዮስም «ክርስቶስ ማለት ፈጣሪና ፍጡር በአንድ አካልና አንድ ባሕርይ አንድ የኾነ ማለት ነው» ብሏል ። (ሃይ. አበ ፡ ገጽ. ፻፲፱)

ቅዱስ ቄርሎስ የመጽሐፈ ምሳሌን ም. ፰ ቁ. ፳፪ ጥቅስ በተረጐመበት ድርሰቱ እንዲህ ብሏል ።

«ጥበብ ተፈጠረ ይኸውም ቃል ነው ። ከፍጥረቱ አስቀድሞ የነበረ ቃል ሥጋ በመኾኑ ይህ አምላክ ያለ መለወጥ ከንጽሕት ድንግል ከነሣው ሥጋ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ኾኖአልና የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ከጥበብ ተገኝተው በባሕርያቸው ጸንተው ይኖራሉና አሁን ግን ጥበብ ከፍጥረት አስቀድሞ የነበርኩ እኔን ጌታ ፈጠረኝ አለች ። የተገኘ ባሕርይን ገንዘብ ልታደርግ ሰው ኾነች ፤ አብ ፈጠረኝ አላለችም ፤ ጌታ ፈጠረኝ አለች እንጂ ። ወልድ አባቱን ብቻ ለማመልከት በሚናገርበት ጊዜ አባቴ ይለዋል ፤ ተገኘ ባሕርይን ገንዘብ በማድረጉ እርሱ ራሱ ሰው ኾነ ፤ ስለዚህም ጌታ ፈጠረኝ አለ ፤ አባቴ ፈጠረኝ አላለም ።» (ሃይ አበ ፡ ገጽ ፪፻፺፰)

በሌላ በኩል ደግሞ ወልድ የእግዚአብሔር ጥበቡ ሲኾን የእግዚአብሔር ጥበብ ዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር አለ እንጂ የተፈጠረ ሊኾን አይችልም ። በዚህም መሠረት ፈጠረ የተባለው ቃል በሌሎች ደግሞ ወለደ ወይም ገንዘብ አደረገ ተብሎ ተተርጕሟል ።

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ይህንን ጥቅስ ሲተረጕም እንዲህ ብሏል «ጠቢብ ሰሎሞን እግዚአብሔር ቃል ያለ ወንድ ዘር ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ አየ ፤ ወልድ ሰው ከመኾኑ አስቀድሞ አንድ እንደኾነ ሰው ከኾነ በኋላም ከሥጋ ጋር አንድ አካል በመኾን እርሱ አንድ እንዲኾን ባየ ጊዜ ስለዚህ ሰሎሞን ይህ ቅዱስ ሥጋ እንደተናገረ አድርጎ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ አስቀድሞ የነበረ ልኾን አደረገኝ አለ ብሎ ተናገረ ፤ በብዙ አንቀጽ ጥበብ ተብሎ የተነገረለት አካላዊ ቃል የተዋሐደው ይህ ሥጋ ነውና ።» (ሃይ. አበ ፡ ገጽ ፫፻፵፱)

«በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል ፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ ግን በዚህ ዓለምም ኾነ በሚመጣው በደሉ ይቅር አይባልለትም ።» (ማቴ. ም. ፲፪ ቍ. ፴፪)

ይህ አባባል ከሦስቱ የመለኮት አካሎች በአንዱ ላይ ብቻ የስድብ ቃል የሰነዘረ ማለት ሳይኾን መንፈስ ቅዱስ ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ እግዚአብሔር ወይም አምላክ የሚለውን መለኮታዊ መጠሪያ ተክቶ ስለሚገባ ነው ። በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል ማለቱ ተሳዳቢው ሰው የጌታን ዘላለማዊ አምላክነት ሳያውቅ ተራ ሰው መስሎት ከኀጢአተኞች ጋር የሚበላና የሚጠጣ የኀጢአተኞች ወዳጅ ብሎ የሚሳደብ ሰው ስለበደሉ በልቡ እስከተጸጸተ ድረስ ኀጢአቱ ይቅር ይባልለታል ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኀይል በቀር በሰው ኀይል ሊፈጸሙ የማይችሉትን የመንፈስ ቅዱስን ክንዋኔዎች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን እንዳደረጉት የሰይጣን ሥራ አድርጎ ማውራት ወይም የስድብ ቃል መሰንዘር ይቅርታ የማይደረግለት ኀጢአት ነው ። ጌታም ሊል የፈለገው ይህንኑ አባባል ነው ።

ጌታ የሰው ልጅ በሚልበት ጊዜ ስለራሱ መናገሩ እንደመኾኑና የተዋሐደ እንጂ ያልተቀላቀለና ያልተጠፋፋ የመለኮትና የትስብእት ባሕርይ ያለው እንደመኾኑ ከኀጢአት በቀር በዚህ ዓለም በሰዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮች ደርሰውበታል ። ጌታ በዚህ ዓለም እንደማንኛውም ሰው ይኖር በነበረበት ዘመን በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ መለኮታዊ ክብሩ ያልታወቀ በመኾኑ ነው ሕማም አድርሰውበት በሚሰቅሉት ጊዜ እንኳ «አባት ሆይ ፣ የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው» ብሎ የጸለየው ። (ሉቃ. ም. ፳፫ ቍ. ፴፬) ይህንኑ የጌታን አባባል በመመርኰዝ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ መጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፪ ቍ. ፰ ላይ «ዐውቀውትስ ቢኾኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር» ያለው ።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ በሚልበት ጊዜ ስለ ራሱ ማለቱ ሳይኾን ምናልባት ስለማንኛውም ሰው ማለቱ ሊኾን ስለሚችል በእግዚአብሔር ላይ ሳይኾን በሰው ላይ ለተሰነዘረ ስድብ በንስሓ የእግዚአብሔር ይቅርታ ይገኛል ማለቱ ሊኾን ይችላል ።



«ለምን ደግ ትለኛለህ ? ከአንድ ከእግዚአብሔር በቀር ደግ የለም ።» (ማቴ. ም. ፲፱ ቍ. ፲፯ ፣ ማር. ም. ፲ ቍ. ፲፰ ፣ ሉቃ. ም. ፲፰ ቍ. ፲፰—፲፱)

በዚህ አነጋገሩ እግዚአብሔር ሳልኾን እንዴት ለእግዚአብሔር ብቻ መጠሪያ በኾነ ስም ትጠራኛለህ በማለት መለኮታዊ ክብር የሌለው መኾኑን እንደተናገረ አስመስለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሰውን ጥልቅ ሐሳብ የሚያውቅ እንደመኾኑ ደጉ መምህር ሆይ ፣ ባለው ጊዜ በዚያ በተናጋሪው ሰው አስተሳሰብ ጌታን እንደ ተራ ሰው እንጂ እንደአምላክነቱ ያላመነው ኾኖ ሳለ አምላክ ብቻ ሊጠራበት በሚገባ ቅጽል ስም መጥራቱን ስላልፈቀደ ነው እንጂ እኔ ደግ አይደለሁም ወይም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም ለማለት አይደለም ። አንድን ተራ ሰው ለአምላክ ብቻ መጠሪያ በኾነ ስም ጠርቶ ማወደስ እንደሚያስደስተው በመገመት የጌታን መለኮታዊ ክብር ያልተገነዘበው ሰው ጌታን ደጉ መምህር ሆይ ብሎ የጠራው በዚያን ጊዜ በሃይማኖት መሪዎቻቸው ዘንድ በዚህ ስም መጠራት የተለመደ ስለነበረ ነው ።

የጌታ አስተሳሰብ የሰውዬውን አስተሳሰብ ለመቃወምና ቀናውን ትምህርት ለማስተማር እንጂ እርሱ ራሱ ደግ መባልን ለመቃወም አለመኾኑን ለመገንዘብ በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲ ቍ. ፲፩ እና ፲፬ ላይ «እኔ ደጉ እረኛ ነኝ» ብሎ የተናገረ መኾኑን እንመልከት ።

ከናትናኤል ጋር አብሮ ባልነበረበት ጊዜ «ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ኾነህ አየሁህ» ያለውና የሰማርያይቱ ሴት ባል የለኝም ባለችው ጊዜ አምስት ባሎች የነበሩአት መኾኑን የገለጸላት ጌታ በኹሉም ቦታ ሙሉ ኾኖ የሰውን ውሳጣዊ አስተሳሰብ በትክክል የሚያውቅ እንደመኾኑ ደጉ መምህር ሆይ ብሎ ጌታን ያነጋገረው ሰው በጌታ መለኮታዊ ባሕርይ የማያምን መኾኑን ስላወቀ እኔን ደግ ለማለት አንድም በእኔ መለኮታዊ ባሕርይ ማመን አለብህ ያለበለዚያ ግን ደግ ልትለኝ አይገባህም ማለቱ ነው እንጂ እኔ ደግ አይደለሁም ወይም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም ማለቱ አይደለም ። (ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፵፱ ፣ ም. ፬ ቍ. ፲፱)

«በቀኘና በግራዬ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም ።» (ማቴ. ም. ፳ ቍ. ፳፫)

በማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፭ ቍ. ፴—፴፯ ፤ በዮሐንስ ወንጌል ም. ፭ ቍ. ፳፪ ፤ ኹለተኛ ወደ ጢሞቴዎስ በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክትም. ፬ ቍ. ፰ ፤ በዮሐንስ ራእይ ም. ፳፪ ቍ. ፲፪ እና እንዲሁም በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለሰው ኹሉ እንደየሥራው ዋጋውንና ፍርዱን የሚሰጠው ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ በግልጽ ተጠቅሶአል ።

ለሰው ኹሉ እንደየሥራው ዋጋውን የሚሰጠው እርሱ ራሱ ኾኖ ሳለ ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም ያለ ባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ።

የመጀመሪያው ምክንያት የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከድንግል ማርያም ጋር የነበራትን የሥጋ ዝምድና ተገን በማድረግና የጌታን ማንነት ባለመገንዘብ ምድራዊ ገዢ ለመኾን እንደተዘጋጀ ገምታ አንተ በምትነግሥበት ጊዜ ለአንዳቸው በቀኝህ ለአንዳቸው ደግሞ በግራህ የመቀመጥን ሥልጣን ለኹለቱ ልጆቼ ስጥልኝ ብላ በመለመንዋ የምትለምኑትን አታውቁም ብሎ ይጀምርና በዚህ ዓለም ለእርሱ ተዘጋጅቶ የሚጠብቀው በምድራዊ ዙፋን ላይ ተቀምጦ የመንገሥ ምድራዊ ክብር ሳይኾን የመከራ ጽዋና የመከራ ጥምቀት መኾኑን ገለጸላቸው ። የምትለምኑትን አታውቁም ያለው በማቴዎስ ወንጌል ም. ፮ ቍ. ፴፫ ላይ «እናንተ ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ፈልጉ «ብሎ በተናገረው መሠረት መለመን የነበረባችሁ የሰማዩን እንጂ የምድሩን ክብር አልነበረም ሲላቸው ነው ። እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፰ ቍ. ፴፮ ላይ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም» በማለት የፊተኛውን አባባል አጠናክሮአል ።

«በቀኘና በግራዬ መቀመጥ ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም» ማለቱ፡ እናንተ እንዳሰባችሁት የዚህን ዓለም ክብር የምሰጣችሁ ሳይኾን ለወዲያኛው ዓለም ክብር ከኾነ ግን ያ ክብር የሚገኘው ለዚያ ክብር ብቁ በመኾን ነው እንጂ በዝምድናና በደጅ ጥናት አይደለም ብሎ ሲያረጋግጥላቸው ነው ።



ኹለተኛው ምክንያት ደግሞ የሦስቱን የመለኮት አካላት ግብር የሚመለከት ነው ። ቀደም ተብሎ በምሥጢረ ሥላሴ ምዕራፍ ውስጥ እንደተገለጸው አፍአዊ ግብሮች የመለኮታዊ አንድነት ግብሮች ቢኾኑም እነዚህ አፍአዊ ግብሮች በያንዳንዳቸው ስም ለሦስቱም አካላት ይከፋፈላሉ ። ለምሳሌ ከሃሊነትና አዘጋጅነት የአብ ፤ ጥበብ የወልድ ፤ ስጦታ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ግብሮች ናቸው ቢባልም ወልድና ወንፈስ ቅዱስ ከሃሊነት የላቸውም ማለት አይደለም፤አብና መንፈስ ቅዱስ ጥበብ የላቸውም ማለት አይደለም ፤እንዲሁም አብና ወልድ መንፈሳዊ ስጦታን አይሰጡም ማለት አይደለም።ይኹንእንጂ እነዚህ አፍአዊ ግብሮች ለአብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ተከፋፍለው ስለሚገሩና ማዘጋጀት ደግሞ የአብ ግብር ስለኾነ መድኀኒታችን ይህንኑ ለማመልከት ሲል ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም ብሎአቸዋል ። ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ በሚልበት ጊዜ ዝግጅት የአብ ግብር መኾኑን ይጠቍምና በወዲያኛው ዓለም በጌታ ግራና ቀኝ የመቀመጥን ክብር ለመስጠት የግድ መለኮታዊ ውሳኔና ዝግጅት እንደሚያስፈልገው ለመግለጽ ነው ። ዝግጅቱ የአብ ግብር ነው ይባል እንጂ ለሰው ኹሉ ዋጋውን የሚሰጠው እርሱ ራሱ መኾኑን አልካደም ። እንዲያውም በዮሐንስ ወንጌል ም. ፭ ቍ. ፳፪ ላይ «አብ በማንም ላይ አይፈርድም ፤ ፍርድን ኹሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ» በማለት አረጋግጦአል ።

«አባት ሆይ ፥ የሚቻል ከኾነ ይህ የመከራ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ፤ ነገር ግን እንደፈቃድህ እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይኹን ።» (ማቴ. ም. ፳፮ ቍ. ፴፱)

ጌታ ይህንን ጸሎት በመጸለዩ ሕማምና ሞት የደረሰበት በፈቃዱ ሳይኾን ያለፈቃዱ እንደኾነና በዚህም የአብ ክብር ከወልድ ክብር እንደሚበልጥ አድርገው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ።

በስቅለቱ ዋዜማ ጌታ በጌቴሴማኒ ያትክልት ቦታ ያደረጋቸው ድርጊቶች ኹሉ በጭንቀት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባን ለእኛ ትምህርት ሊሰጠን ፈልጎ ብቻ ነው ። ወደ ፈተና አታግባን የሚለውን ጸሎት ባስተማረን መሠረት በተፈጥሮ ደካማነታችን ምክንያት በፍላጎታችን ሕማማትን ለመቀበል እንዳንችል ሊያስተምረን ፈልጎ ነው እንጂ ሕማማቱና የሞቱ ጽዋ እንዲቀርለት ለመጸለይ አይደለም ። ሕማሙን ላለመቀበልና ላለመሞት ቢፈልግ ኖሮ ምንም ባላስቸገረውም ነበር ።

ለምሳሌ ከምኩራብ አስወጥተው ከተማቸው ከተሠራችባት ከተራራው አፋፍ ወደታች ሊጥሉት ሲፈልጉ በመካከላቸው አልፎ የኼደ መኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም. ፰ ቍ. ፶፱ ለመመልከት እንችላለን ። እርሱ በፍላጎቱ ራሱን ሰጠ እንጂ ሊይዙት የመጡት ሰዎች ኢየሱስን እንፈልጋለን ባሉት ጊዜ እኔ ነኝ በማለት መለኮታዊ መልስ ሲሰጣቸው ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ላይ የወደቁ እንደመኾናቸው እርሱ ቢፈልግ ኖሮ ራሱን ለማዳን ባላቃተውም ነበር ። (ዘፀ. ም. ፫ ቍ. ፲፬ ፡ ዮሐ ም. ፲፰. ቍ. ፮)



የጌቴሴማኒ ጸሎት (ሉቃ ም. ፳፪ ቍ. ፵፱)

እንዲያውም ጴጥሮስ ጌታን ሊይዙ ከመጡት ሰዎች መካከል ማልኮስ የተባለውን የሊቀ ካህናቱን አሽከር በሰይፍ ጆሮውን በቈረጠው ጊዜ ሰይፍን የሚመዙ በሰይፍ የሚጠፉ መኾናቸውን ገልጾ ጴጥሮስን ከገሠጸው በኋላ የተቈረጠውን ጆሮ እንደነበረ መልሶለታል ። (ሉቃ.



ም. ፳፪ ቍ. ፶—፶፩ ፡ ዮሐ. ም. ፲፰ ቍ. ፲—፲፩) ይህም ብቻ ሳይኾን የመጻሕፍት አባባል ይፈጸም ዘንድ ሕማም ተቀብሎ ይሞታል እንጂ እርሱ ቢፈልግ ብዙ የመላእክት ሠራዊት አብ ሊልክለት እንደሚችል ገልጾአል ። (ማቴ. ም. ፳፮ ቍ. ፶፪—፶፬ ፡ ሉቃ. ም. ፳፪ ቍ. ፶፩)

በሌላ ጊዜ ደግሞ በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲ ቍ. ፲፯ ላይ «ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ ፈቃደኛ ስለኾንኩ አብ እኔን ይወደኛል ። ሕይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም የለም ፤ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ» ከማለቱም በላይ ይህንን አባባሉን በተግባር ሲገልጸው ነፍሱ ከሥጋው በምትለይበት ጊዜ «አባት ሆይ ፡ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» በማለት በአደራ መልክ አብ ዘንድ እንዲቈይለት ከማድረጉ በቀር ነፍሱን ለማንም አሳልፎ አልሰጠም ። (ሉቃ. ም. ፳፫ ቍ. ፵፮)

ጌቴሴማኒ ኾኖ ባደረገው ጸሎት በኹሉም ነገር እኛን እንደሚመስል ያስተምረናል ። ባይጸልይ ኖሮ እብን ብቻ እንጂ እኛን አይመስለንም ነበር ።

በዚህም መሠረት ፈተና በሚያጋጥመን ጊዜ ኹሉ በጸሎት እንድንተጋ ሊያስተምረን ፈልጎ ነው እንጂ ጽዋው እንዲቀርለት ፈልጎ አይደለም ።

«አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ» (ማቴ. ም. ፳፯ ቍ. ፵፮)

ይህ አባባል የተነገረው በደካማነቱ ምክንያት ወይም መለኮቱ ከእርሱ በመለየቱ እርዳታ ለመጠየቅ ተብሎ ሳይኾን ችግር በሚያጋጥመን ጊዜ የእግዚአብሔርን እርዳታ መለመን እንደሚገባን እኛን ደካማዎቹን ፍጥረቶች ለማስተማር ብሎ ነው ። ስለዚህም ነው በማቴዎስ ወንጌል ም ፲፩ ቍ. ፳፱ ላይ ከእኔ ተማሩ » ያለው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሰው የኾነ አምላክ ማለት ያልተጠፋፋ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ በመኾኑ ሕማም ሊሰማው እንደሚችል ግልጽ ነው ። ለእኛ ለሰው ልጆች ደኅንነት ሲል ሕማም የተቀበለ መኾኑን ለመረዳት በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፶፫ ቍ. ፬-፭ እና በመጀመሪያው የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ም.

፪ ቍ. ፳፩ እንዲሁም በምዕራፍ ፫ ቍ. ፲፰ ላይ ያሉትን ጥቅሶች ለመመልከት እንችላለን ። ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሏል ። እንዲህ መኾኑንማ ካላመንን የደረሰበትን ሕማም ኹሉ በምትሐት መልክ አሳለፈው እንጂ ሌላ ሰው ቢኾን ኖሮ ለሰማው የሚችለው የሕማም ስሜት አልደረሰበትም ብለው የጌታን መሥዋዕትነት ዋጋ ከሚያሳ ፏት መናፍቃን ከነማኒና ከነመርቅያኖስ ጋር አብሮ እንደመሰለፍ ይቈጠርብናል ። በእርግጥ ሕማምና ሞት መቀበልን በፈቃዱ አደረ ገው እንጂ ማንም አላስገደደውም ። ስለዚህ ነው ጌታ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ስለበጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ ይሰጣል» ያለው ። (ዮሐ. ም. ፲ ቍ. ፲፩) — ይህም ማለት ጌታን እስከሞት ድረስ ሊያደርሰው የቻለው የሰውን ልጅ ለማዳን ያለው ፍላጎትና በሰው ልጅ ላይ ያለው ፍቅር ነው እንጂ ማንም አስገድዶት አለመ ኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲ ቍ. ፲፯—፲፰ ገልጾአል ። በምዕራፍ ፪ ቍ. ፲፱-፳፫ ደግሞ «ይህንን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀኖች እሠራዋለሁ በማለት ስለሞቱና ስለትንሣኤው በምሳሌ ተናግሮ አል ። እንዲሁም በሌሎች ጊዜያት ወደፊት ስለሚደርስበት ሕማ ምና ሞት ከዚያም ሞትን ድልን አድርጎ እንደሚነሣ በማቴዎስ ወን ጌል ም. ፳፮ ቍ. ፲፯-፴፫ በማርቆስ ወንጌል ም. ፲፬. ቍ. ፲፯—፳፰ ፤ በሉቃስ ወንጌል ም. ፳፪ ቍ. ፲፬—፳፪ እንደተገለጸው አስቀድሞ መናገሩ ሕማሙንና ሞቱን አስቀድሞ ራሱ የወሰናቸውና በፍላጎቱ የተፈጸሙ ኹናቴዎች ናቸው እንጂ በሕማሙና በሞቱ ጊዜ የተናገራ ቸው አነጋገሮች እኛን ለማስተማር የተነገሩ ከመኾናቸው በቀር እርሱ የማንንም እርዳታ የማይጠይቅ መኾኑን ተረድተን ከመሳሰት እንጠንቀቅ ።

> «ነገር ግን ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም ፤ የሰማይ መላእክትም አያውቁም ፤ ወልድም አያውቅም ።» (ማር. ም. ፲፫ ቍ. ፴፪)

አብ የሚያውቀውን ቀንና ሰዓት ወልድ የማያውቅ ከኾነ የወልድ ክብርና ሥልጣን ከአብ ክብርና ሥልጣን ያንሳል ማለት ነው የሚሉ ወገኖች አሉ ።

በማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፬ ቍ. ፳፱—፴፭ ፤ በማርቆስ ወንጌል ም. ፲፫ ቍ. ፫—፲፫ እና በሉቃስ ወንጌል ም. ፳፩ ቍ. ፳፭—፴፫ ብንመ



ለከት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ስለሚመ ጣበት ጊዜ ኹናቴ ልዩ ልዩ ምልክቶችን በመዘርዘር ያስረዳ መኾኑን ለመመልከት እንችላለን ። በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲ ቍ. ፴ ላይ «እኔና አብ አንድ ነን» ይልና በምዕራፍ ፲፯ ቍ. ፲፭ ላይ ደግሞ «የአብ የኾ ነው ኹሉ የእኔ ነው» በማለት ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት ያረጋግጣ ል ። እንግዲህ በአንድ በኩል ዳግመኛ የሚመጣበትን ጊዜ ከነምልክቱ ዘርዝሮ ያስረዳ በመኾኑና በሌላ በኩል ደግሞ ከአብ ጋር ያለውን እኩ ልነት መላልሶ ያረጋገጠ እንደመኾኑ እርሱው ራሱ ተመልሶ የሚመ ጣበትን ጊዜ የሚያውቀው መኾኑን ሳንጠራጠር ማመን አለብን ።

ከአብ በቀር በሚልበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስም አያውቀውም የሚል ይመስላል ። ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የመጀመሪያው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፪ ቍ. ፲ ብንመለከት «ለእኛ ግን እግዚአብ ሔር በመንፈሱ አማካይነት ምሥጢሩን ገልጾልናል ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንፈስ ጥልቅ የኾነውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንኳ ሳይቀር ኹሉን ነገር ይመረምራል» የሚል እንደመኾኑ መንፈስ ቅዱስ የማያውቀው ነገር እንደሌለ እንገነዘባለን ።

ኹናቴው እንዲህ ከኾነ ለምንድነው ታዲያ ወልድም አያውቀ ውም የተባለው ?

ለዚህ ጥያቄ ሦስት አማራጭ መልሶች አሉ ።

አንደኛ/ ወልድ ቢያውቀውም ይህንን ዕውቀት ለሰው ልጆች አይነግራቸውም ። ይህም የሚኾንበት ምክንያት ተመልሶ የሚመጣ በት ጊዜ ሩቅ መኾኑን ካወቁ ነቅተው ተዘጋጅተው በመጠበቅ ፈንታ ችላ ሊሉ ስለሚችሉና ጊዜው ቅርብ መኾኑን ካወቁ ደግሞ በጣም ከመ ፍራታቸው የተነሣ የጌታን ዳግመኛ መምጣ ጊዜ ብቻ በማሰብ የዚህን ዓለም ኀላፊነታቸውን እንዳይዘነጉ ታስቦ ነው ። ለምሳሌ ለቤተሰባ ችንና ለኅብረተሰቡ ማበርከት ያለብን ግዴታ መኖሩን መርሳት የለ ብንም ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው የመጀመሪያ መል እክቱ ም. ፲፫ ላይ ከማንኛውም ሃይማኖታዊ በጎ ተግባር የእርስ በርሳ ችን መፈቃቀር እንደሚበልጥ ይገልጻል ። ይህንኑ አባባል የሚደግፈው ሐዋርያው ዮሐንስ ደግሞ እንዲህ ብሏል «ማንም እግዚአብሔርን እወ

ዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው ፤ ያየውን ወንድሙን የማ ይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወደው ይችላል ?» (፩ኛ ዮሐ. ም. ፬ ቍ. ፳)

ጊዜው ቅርብ መኾኑን በማወቃችን ደንግጠን በዚህ ዓለም በም ንኖርበት ጊዜ የሚጠበቅብንን ኀላፊነትና ግዴታ ወደ ጐን በመተው ሕይወታችንን ሚዛናዊ ከኾነ የኑሮ ዕቅድ እንዳናገልለውና ጊዜው ሩቅ መኾኑን በማወቃችን ደግሞ ተዝናንተን ከእግዚአብሔር በመራቅ የሰይጣን ማደሪያ እንድንኾን ባለመፍቀዱ ዳግመኛ የሚመጣበትን ጊዜ አይነግረንም ።

ኹለተኛው ትርጒም ደግሞ ወልድም አያውቀውም ማለት በመ ለኮቱ ወይም በትስብእቱ የሚያውቀው መኾኑን ለመካድ ሳይኾን የዕ ውቀቱ ምንጭ ያለመለኮት ትስብእት ብቻ አለመኾኑን ለመግለጽ ነው። ያልተጠፋፋ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ባሕርይ ያለው በመኾኑ ወልድ ስንል ሰው የኾነ አምላክ ማለታችን ነው ። ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመኾኑ አንዳንድ ጊዜ የመለኮት ባሕርይ ብቻ የኾነውን ኹናቴና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የትስብእት ባሕርይ ብቻ የኾነውን ኹናቴ ለጌታ ገንዘቡ እንደኾነ ተደርጎ መነገሩ ባለመጠፋፋትና ባለመለዋወጥ የተፈጸመውን የተዋሕዶ ምሥጢር ስለሚያመለክተን ሊያስገርመን አይገባም ። መለኮት የዕውቀት ኹሉ ምንጭ ሲኾን የሰው ልጅ ግን በኹሉም ነገር ውሱን በመኾኑ በዕውቀቱም ውሱን ነውና ኹሉን ነገር ሊያውቅ አይችልም ። በዚህም መሠረት መድኀኒታችን ውሱን የኾነውን የሰውን ልጅ ሥጋ መልበሱን ለማመልከት ወልድም አያው ቀውም ተባለ እንጂ እርሱ ግን ምንም የማያውቀው ነገር እንደሌለ ማወቅ አለብን ።

ሦስተኛ/ ከምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት እንደተረዳነው የሦስቱ አካሎች አፍአዊ ግብሮች የመለኮታዊ አንድነት ግብሮች ቢኾኑም አንዱ ግብር የአብ ፣ ሌላው ግብር የወልድና ሌላው ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ግብር ተብለው ይታወቃሉ ። በዚህም መሠረት ዕውቀት የመለ ኮታዊ አንድነት ገንዘብ መኾኑ ቢታወቅም ዐዋቂነት የአብ ነው ስለሚ ባል ከአብ በቀር ማንም የሚያውቀው የለም ተባለ እንጂ ወልድና መን ፈስ ቅዱስ አያውቁም ለማለት አይደለም ። የመለኮታዊ አንድነትን ግብር ለማመልከት ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአብ ልብነት ያስባሉ !



አ ብና ሙንፈስ ቅዱስ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ ፤ አብና ወልድ ደግሞ በ መንፈስ ፤ ቅዱስ እስትንፋስነት ይተነፍሳሉ እንላለን ።

«ኢየሱስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የተወደደ ኾኖ በጥበ ብና በቁመት እያደገ ይኼድ ነበር ።» (ሉቃ. ም. ፪ ቍ. ፶፪)

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ሰው መኾን እንዳስፈለገው በሚያስረዳበት ጊዜ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል ። «ልጆች ሥጋና ደም ያላቸው ሰዎች እንደመኾናቸው ኢየሱስም እንደ እነርሱ ሰው ኾነ ። ይህንንም ያደረገው በሞቱ አማካይነት በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን ለመሻር ነው ። እንዲሁም ሞትን በመፍራት ምክንያት ዕድሜ ልካቸውን በባርነት ይገዙ የነበሩትን ለመ ዋጀት ነው ፤ ምክንያቱም የኢየሱስ ፍላጎት መላእክትን ለመርዳት ሳይ ኾን የአብርሃምን ዘር ለመርዳት እስቦ ነው ። ስለዚህ በኹሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው ።» (ዕብ. ም. ፪ ቍ. ፲፬—፲፯)

በም. ፬ ቍ. ፲፭ ላይ ደግሞ «እኛ ያለን ሊቀ ካህናት በድካማችን ሊራራልን የሚችል ነው ፤ ምንም እንኳ እርሱ በኹሉ ነገር የተፈተነ ቢኾን ምንም ኀጢአት አልሠራም» ይላል ።

እነዚህ ኹለቱ ጥቅሶች የሚያመለክቱት መድኀኒታችን የሰውን ልጅ ከሞት ለማዳን ከሰው ከተወለደ በኋላ ከኀጢአት በቀር የሰው ልጅ በሰብአዊ ተፈጥሮው የሚያልፍባቸውን እርምጃዎች ኹሉ ተከትሎ አልፎአል ማለት ነው ። ማንኛውም የሰው ልጅ የቁመትና የጥበብ ዕድ ገቱ ከዕድሜው ጋር አብሮ የሚኼድ እንደመኾኑ መለኮታዊ ተዋሕዶው ባይለየውም እንኳ መድኀኒታችን ከሰው የተለየ ኹናቴ ማሳየት አላስ ፈለገውም እንጂ እርሱ ከፊለገ ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ መገን ዘብ አለብን ።

በኹሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው በተባለውም መሠ ረት መለኮትን በተዋሐደ ትስብእቱ በቁመትና በጥበብ ማደግን ገን ዘብ አደረገ ። ዲያብሎስን በመሻር የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነትና ከሞት ፍርድ ነጻ ለማውጣት ሲል ከሰው ተወልዶ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር ከሰው ልጆች ያልተለየ ኑሮ በመኖሩ ስለ እርሱ በሚነገ ርበት ጊዜ ስለማንኛውም የሰው ልጅ የሚነገረው የንግግር ዐይነት በመ ኾኑ ሊያስገርመን አይገባም ፤ ሰው የኾነ አምላክ ነውና ።

«በዚያን ጊዜ የሚያበረታታው መልአክ ከሰማይ መጥቶ ታየው ። (ሉቃ. ም. ፳፪ ቁ. ፵፫)

መልአክ ሊያበረታታው የሚችለው አንድን ፍጡር እንጂ ፈጣሪን ስለማይኾን ይህ ኹናቴ እርሱ ፍጡር መኾኑን የሚያመለክት በቂ ማስረጃ ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ።

የመላእክት ተፈጥሮ ርኅራኄ የተመላበት በመኾኑና በችግር ላይ የሚያገኙትን ማነኛውንም ሰው ለመርዳት ዝግጁ ኾነው ስለሚገኙ በጌታ ላይ የደረሰ ው ሕማም በፍላጎቱና በፈቃዱ መኾኑን ባለማወቁ ይህ የተጠቀሰው መልአክ የማንም እርዳታ የማያስፈልገውን ጌታን ለመርዳት ብቅ አለ ። ኾኖም ሊያበረታታው ታየ አለ እንጂ አበረታታው አላለም ።

የዚህ መልአክ ጌታን ለማበረታታት መታየት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሰይፉን መዝዞ ማልኮስ የተባለውን የሊቀ ካህናቱን አሽከር ጆሮ ከመቍረጥ ጋር ተመሳሳይ ነው ። ጌታ ግን ለቅዱስ ጴጥሮስ አድራጎት የነበረው አስተሳሰብ እንደሚከተለው ነው ። «ሰይፍን የሚያነሡ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን መልሰህ ወደ ሰገባው ክተት ። ለመኾኑ እኔ አባቴን ብለምን እርሱ በብዙ ሺሕ የሚቈጠሩ የመላእክት ሠራዊት ሊልክልኝ የማይችል ይመስልሃልን ? እንዲህ ከተደረገ ደግሞ መከራ መቀበል አለበት የሚለው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እንዴት ይፈጸማል ?» (ማቴ. ም. ፳፮ ቁ. ፶፪—፶፬) ይህንንም ከተናገረ በኋላ የተቈረጠውን ጆሮ በመፈወስ ቀድሞ እንደነበረ የመለሰለት መኾኑን በሉቃስ ወንጌል ም. ፳፪ ቁ. ፶፩ እንመልከት ።

«ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም ።» (ዮሐ. ም. ፯ ቁ. ፲፮)

ጌታ በዚህ አነጋገሩ ከአብ ከመማሩ በቀር እርሱ ራሱ ምንም ዕውቀት እንዳልነበረውና የዕውቀት ምንጭ አለመኾኑን እንደመሰከረ የሚመስላቸው ወገኖች አሉ ።



ጌታ ይህንን የተናገረው ይህ ሰው ሳይማር እንዴት መጻሕፍትን ሊያውቅ ቻለ ብለው አይሁድ እርስ በርሳቸው ለተጠያየቁት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው ። በአይሁድ ዘንድ አንዳንድ የታወቁ ዝነኞች ምሁራን ነበሩ ። የሰውም ዐዋቂነቱ የሚገመተው በአስተማሪው ዝነኛነት ነበር ። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን ማንነት ሲያስተዋውቅ በገማልያል እግር አጠገብ እንዳደገ ማለት ገማልያል የተባለው ዝነኛ መምህር እንዳስተማረው ይገልጻል ። (የሐ. ሥ. ም. ፳፪ ቁ. ፫)

ጌታ የገለጸላቸው አገላለጽ የእርሱ መምህር ምድራዊ አለመኾኑንና እንደ እነርሱ በምድራዊ መምህር የማይመካ መኾኑን ለማመልከት ነው እንጂ የአብ የኾነው ኹሉ ማለት ሥልጣኑ ፡ ገዢነቱና ዕውቀቱ የእርሱም ገንዘቦች ሳይኾኑ ቀርተው አይደለም ። (ዮሐ. ም. ፲፮ ቁ. ፲፭)

እንደሚታወቀው ጌታ ሰው የኾነ አምላክ በመኾኑና በዚህ ዓለምም እንደሰው በኖረባቸው ዘመናት እኛን መምሰል ስለተገባው አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋቸው የነበሩት ድርጊቶችና ይናገራቸው የነበሩት አነጋገሮች በሰውነቱ ነበር ። (ዕብ. ም. ፪ ቁ. ፲፬—፲፯) — ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክቱም. ፪ ቁ. ፮—፲፩ ላይ ጌታ መለኮታዊ ክብር ያለው ኾኖ ሳለ ራሱን በፈቃዱ ዝቅ አድርጎ እስከሞት ድረስ ታዛዥ በመኾን ራሱን ባዶ አደረገ ያለው ። ስለ መለኮታዊ ክብር በሚናገርበት ጊዜ ያንን ክብር የአብ ክብር ብቻ እንደኾነ አድርጎ መናገሩ ሊያስገርመን አይገባም ። ምክንያቱም እንደዚህ ያለውን አነጋገሩን በሌሎች ጊዜያት ሲያብራራ «እኔና አብ አንድ ነን ።» «የአብ የኾነው ኹሉ የእኔ ነው» በማለት ገልጾታልና ። (ዮሐ. ም. ፲ ቁ. ፴ ፡ ም. ፲፮ ቁ. ፲፭)

«አባቴ ከእኔ ይበልጣል ።» (ዮሐ. ም. ፲፬ ቁ. ፳፰)

በዚህ አነጋገሩ መድኀኒታችን ከአብ ያነሰ ክብር እንዳለው እርሱው ራሱ አረጋገጠ ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ።

አባቴ ከእኔ ይበልጣል ማለቱ በመለኮታዊው ክብር ከአባቱ ጋር እኩል ቢኾንም የፈጠረውን የሰውን ሥጋ ለብሶ በለበሰው ሥጋ ለሕ

ማምና ለሞት የተዳረገ መኾኑን ለመግለጽ ነው እንጂ ከአብ የሚያንስ መኾኑን ለመግለጽ አይደለም ።

አባቴ ከእኔ ይበልጣል ከማለቱ በፊት ብትወዱኝስ ኖሮ ወደ አብ እኼዳለሁ ስላችሁ ደስ ባላችሁ ነበር ብሎአቸዋል ። ይህም ማለት እኔ በዚህ ዓለም ላይ እንደማንኛውም ተራ ሰው ኾኜ ባለሁበት ጊዜ ሕማም ውርደትና ሞት የሚጠብቀኝ ሲኾን ወደ አባቴ በምኼድበት ጊዜ ግን ከአብ ቀኝ የመቀመጥ ክብር ይጠበቀኛል ማለቱ ነው ። ኾኖም ግን ይህንን ሕማም ተቀብሎ በመጨረሻም ለሞት የበቃው በገዛ ፈቃዱ እንጂ ማንም አስገድዶት አይደለም ። (ዮሐ. ም. ፲ ቁ. ፲፯—፲፰)

ለደቀ መዛሙርቱ ወደ አብ እኼዳለሁ ብሎ በነገራቸው ጊዜ ከእነርሱ መለየቱ ስላሳዘናቸው ሊያጽናናቸው ፈልጎ ምንም እንኳ በመለኮታዊ ክብሬ ከአብ ጋር እኩል ብኾን የሰውን ሥጋ በመልበሴና በለበስኩት ሥጋም ሕማምና ሞት የሚደርስብኝ ስለኾነ በዚህ ምክንያት አባቴ ከእኔ ይበልጣልና ከአብ ጋር ባለኝ ዘላለማዊው የክብር ዙፋኔ ላይ ኾኜ ወደምመለክበት ወደ አብ እኼዳለሁ ስላችሁ የምትወዱኝስ ከኾነ ልትደሰቱ እንጂ ልታዝኑ ባልተገባችሁም ነበር ብሎአቸዋል ማለት ነው ።

ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት በተለያዩ ጊዜያት የገለጸ ቢኾንም በተለየ ሕማማትንና ሞትን ለመቀበል ተዘጋጅቶ በነበረበት ዋዜማ «አባት ሆይ ፥ ልጅህ እንዲያከብርህ ልጅህን አክብረው ብሎ የእኩልነት ውል የሚደራደር መኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፯ ቁ. ፩ እንመልከት ።

«እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው ።» (ዮሐ. ም. ፲፭ ቁ. ፩)

አትክልተኛው የወይኑን ግንድ ተክሎና ተንከባክቦ እንደሚያሳድገው አብም ወልድን ፈጥሮና ሥልጣንን ሰጥቶ ከፍ በማድረጉ በአትክልተኛ እና በወይን ግንድ መካከል ባለው የክብር ልዩነት መጠን የአብ ክብር ከወልድ ክብር ይበልጣል ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ።



እዚህ ላይ ጌታ ስለራሱ የወይን ግንድነትና ስለ አባቱ አትክልተኛነት በሚገልጽበት ጊዜ «እኔና አብ አንድ ነን » ያለውን የራሱን አባባል ለመቃረን ሳይኾን ምሳሌነቱ በመዝሙር ፹ ቁ. ፰—፲፮ ላይ እንደተገለጸው እስራኤላውያን ከምድረ ግብጽ ሲወጡ ፍሬ የሚያፈሩ የወይን ግንዶች እንደኾኑ ታስቦ የነበረ መኾኑን የሚመለከት ነው ። ይኹን እንጂ እነዚህ የወይን ግንዶች በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፭ ቁ. ፩—፯ እንደተገለጸው ወይን በማፍራት ፈንታ ሖምጣጣ ፍሬዎችን አፍርተዋል ። ጌታ ግን በዚህ ዓለም ላይ እንደሰው በኖረባቸው ዘመናት ተገቢውን ፍሬ የማፍራት ምሳሌ ስለኾነ «እኔ እውነተኛው የወይን ግንድ ነኝ ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው» ካለ በኋላ በቍጥር ፭ ላይ ደግሞ «እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ» ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ገልጾላቸዋል ። ይህም ቅርንጫፍነት የሚያመለክተው አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ በዛፉ ግንድ ላይ እንዳለ ካልቀጠለ በቀር ሊለመልምና ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችል ኹሉ ማንኛውም ምእመን በጌታችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ካልኾነ በቀር ሃይማኖታዊ ፍሬ ሊያፈራ አለመቻሉን ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ደሙን በወይን አማካይነት ስለሰጠን ራሱን በወይን ግንድ ምሳሌነት ገልጾልናል ።

እንደሚታወቀው አብና ወልድ የሚለያዩት በመለኮታዊ ክብር በመበላለጥ ሳይኾን ወልድ ከሰው በመወለዱና አብ ግን ከሰው ባለመወለዱ ነው ። ወልድ የሰውን ልጅ ከሰይጣን ተገዢነት ነጻ ለማውጣት ሰው መኾን ስለነበረበት መለኮትንና ትስብእትን ባዋሐደ ጊዜ ያልተጠፋፋ ተዋሕዶ በመኾኑ አምላኬ ፥ አባቴ ከእኔ ይበልጣል ፥ አባቴ አትክልተኛ እኔ የወይን ግንድ ነኝ ፥ እኔ የአባቴን ፈቃድ እፈጽማለሁ ብሎ በየጊዜው የተናገራቸው የትኅትና አነጋገሮች ሊያስገርሙን አይገባም ፤ በትስብእቱ ለመለኮት ተገቢውን ክብር መስጠቱ ነውና ። ወደ ዕብራውያን በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፪ ቁ. ፲፩—፲፯ በሚነበበው ቃለ እግዚአብሔር እንደተገለጸው ጌታ ሰው የኾነበት ምክንያት የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት ስለኾነ በኹሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው ተብሏል ።

«የዘላለም ሕይወትም ብቻህን እውነተኛ አምላክ የኾንከውን አን ተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው ፡፡» (ዮሐ. ም. ፲፯ ቁ. ፫)

ብቻህን እውነተኛ አምላክ የኾንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየ ሱስ ክርስቶስን በሚልበት ጊዜ ራሱን ከአምላክነት በማግለል አምላክ ነት የአብ ብቻ መኾኑንና እርሱ ከአብ እንደሚያንስ ማረጋገጡ ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ፡፡

ቀደም ተብሎ በሌሎች አርእስት እንደተመለከተው መድኀኒታ ችን የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት መለኮትንና ትስብ እትን ባዋሐደ ጊዜ ከኀጢአት በቀር የሰው ልጅ በሰብአዊ ተፈጥሮው የሚያልፍባቸውን እርምጃዎች ኹሉ ተከትሎ አልፎአል ፡፡ (ዕብ. ም. ፪ ቁ. ፲፬-፲፯ ፥ም. ፬ ቁ. ፲፭)—እንደሰው ጥቂት በጥቂት አድጓል ፤ እንደ ሰው ተርቧል ፤ እንደ ሰው ተጠምቶአል ፤ እንደ ሰው በልቶአል ፥ ጠጥ ቶአል ፤ እንደ ሰው ተኝቷል ፤ እንደ ሰው ከእንቅልፉ ነቅቶአል ፤ እንደ ሰው ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አቅርቧል ፤ እንደ ሰው ሕማምና ሞት ደርሰውበታል፡፡በዚህ ኹሉ ጊዜ መለኮቱ አልተለየውም ፡፡ ይህም አባባ ላችን መለኮት ታመመ ወይም መለኮት ሞተ ማለታችን አይደለም ፡፡ አባባላችን ግን ግልጽ መኾን ያለበት ወልድ በሰውነቱ ሞተ ማለታችን ሲኾን ኾኖም ግን መለኮት ከትስብእት የተለየበት ጊዜ አለመኖሩን እናምናለን ፡፡

ጌታ እንደ ሰው በሚጸልይበት ጊዜ ሰው ኹሉ የሚጸልየው ለእግ ዚአብሔር እንደመኾኑ እርሱም ለአባቱ አንተ ብቻ እውነተኛ አምላክ ነህ ሲል ጸለየ ፡፡ የዚህም ጸሎት ዋና ዐላማ ጣዖት አምልኮትን ለማው ገዝ ነው ፡፡ እንደ ሰው አምላኬ ወይም እግዚአብሔር ብሎ ካልጸለየ በእርሱ ዘንድ ትስብእት የለም ፤ ወይም መለኮት ትስብእትን ውጦ አጥ ፍቶታል ፤ ወይም መለኮትና ትስብእት ተቀላቅለዋል በሚለው በአ ውጣኬ ክሕደት እንደማመን ይቈጠርብናል ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ክፍሎች አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር አብ ሌላ ጊዜ ለእግዚአብሔር ወልድ ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ የአምላክነት ክብር ተሰጥ ቶ የሚነገርበት ምክንያት በመለኮታዊው ሥልጣን አንድ ስለኾኑ ነው ፡፡



በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፯ ቁ. ፫ እግዚአብሔር አብ ብቻውን እው ነተኛ አምላክ እንደኾነ ተገልጾአል ፡፡ በመልእክተ ይሁዳ ቁ. ፳፭ ላይ እግዚአብሔር ወልድ ብቸኛ አምላክ ነው ተብሏል ፡፡ በማቴዎስ ወን ጌል ም. ፲፪ ቁ. ፴፪ ላይ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተደረገ ስድብ ብቻ ምሕረት እንደማይደረግለት ተገልጾአል ፡፡ ስለዚህ ተመሳሳይ ጥቅ ሶች በሚያጋጥሙን ጊዜ ሊያሰናክሉን አይገባም ፡፡

«ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ፥ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ እወጣለሁ ፡፡» (ዮሐ. ም. ፳ ቁ. ፲፯)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን ጥቅስ በተረጐመበት ድርሳኑ እን ዲህ ብሏል ፤ «ነገር ግን እርሱ በዚህ ክርስቶስ በእውነት ሰው እንደኾነ አስረዳ ፤ ዳግመኛም በተነሣ ጊዜ ከዚህ ከአዳም ባሕርይ ሰው መኾኑን አስረዳ ፤ ፈጽሞ ከእርሱ ወደ አልተለየው ወደ አብም ከማረጉ አስቀ ድሞ ለደቀ መዛሙርቱ አምላኬ ፥ አምላካችሁ አለ ፤ ይህን በሰሙ ጊዜ ይህን የተናገረ ሥጋ ብቻ እንዳይመስላቸው ሰው የኾነ እርሱ እግዚአብ ሔር ቃል አስቀድሞ አባቴ ብሎ ከዚህ በኋላ አምላኬ አለ እንጂ ፡፡ እኔ ሰው የኾንኩ አምላክ ነኝና እኔም አንድ ነኝና ይህንንም ያንንም እኔ እላለሁ ይላል ፤ የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጌአለሁና ፥ ኀጢአት የሌለበት እርሱ እኔ ነፍስን ሥጋን በእውነት ተዋሕጄአለሁና ከእኔ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ላደረግሁት ለሥጋ ሥርዓት እንደሚገባ እንዲህ አባቴን አምላኬ ብዬ ጠራሁት ይላል ፡፡» (ሃይ. አበ. ገጽ ፪፻፵፫)

የጌታችን ልጅነት በመዝሙር ፪ ቁ. ፯ ላይ «እግዚአብሔር አንተ ልጄ ነህ አለኝ» በሚለውና እንዲሁም በዮርዳኖስ ጥምቀትና በደብረ ታቦር መገለጽ ጊዜ ከሰማይ ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ «የምወደው ልጄ ይህ ነውና እርሱን ስሙት» ተብሎ በተሰጠው ምስክርነት መሠ ረት ሲኾን የደቀ መዛሙርቱ ልጅነት ግን ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ «አቤቱ አንተ አባታችን ነህ ፤ እኛ ጭቃ ነን ፤ አንተም ሠሪአችን ነህ ፤ እኛ ኹላችንም የእጅህ ሥራ ነን ተብሎ በተነገረው መሠረት ነው ፡፡ (ኢሳ. ም. ፷፬ ቁ. ፰ ፤ ማቴ. ም. ፫ ቁ. ፲፯ እና ም. ፲፯ ቁ. ፭)

አምላኬ ያለውም መለኮትና ትስብእት ሳይጠፉፉ የተዋሐዱ በመኾናቸው ነው ፡፡ አምላካችሁ ሲል ግን እውነተኛ ፈጣሪያችሁ ማለቱ ነው ፡፡ በእርሱና በእነርሱ መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት

አባታችንና አምላካችን በማለት ፈንታ አባቴና አባታችሁ አምላኬና አምላካችሁ ብሎአቸዋል ፡፡

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ አምላኪ እስከማለት ድረስ ያደረሰውን የትሕትና ምሳሌነት ሲተነትን ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሏል «በዚህ ዐይነት ኢየሱስ ክርስቶስ



የደብረ ታቦር መገለጽ (ማቴ. ም. ፲፯ ቍ. ፩)

ያሳየው የትሕትና ጠባይ በእናንተም ሊኖር ይገባል ። እርሱ የመለኮት ባሕርይ ያለው ኾኖ ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የእኩልነት ሥል ጣን ላለመልቀቅ አልተከራከረም ፤ ይልቁንም ያለውን ሥልጣን ኹሉ በገዛ ፈቃዱ ትቶ እንደ አገልጋይ ኾነ ፤ ሰው ኾኖም በሰው ምሳሌ ተገ ለጸ ።» (ፊልጵ. ም. ፪ ቍ. ፭—፯)



«በኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ፡ አለቅነትንም ኹሉና ሥልጣንን ኹሉ ፡ ኀይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይኾናል ። . . . ኹሉ ነገር ከተገዛለት በኋላ እግዚአብ ሔር ኹሉ በኹሉ ይኾን ዘንድ በዚያን ጊዜ ወልድ ደግሞ ኹሉን ላስገዛለት ተገዢ ይኾናል ።» (፩ኛ ቆሮ. ም. ፲፭ ቍ. ፳፬ እና ፳፰)

ጌታ በትንሣኤው ጊዜ እንደሰውነቱ ሥልጣን ተሰጥቶት እንደነ በረ ገልጾአል ። ይህም ሥልጣን የተሰጠው የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ እንዲያወጣበት ነበር ። በመጨረሻ ግን በዚያ በተሰጠው ሥልጣን ለሰው ልጅ ቤዛ ኾኖ ነፍሳትን ኹሉ የቀደሰ በመኾኑና ከዚያ በኋላ ያ ያማላጅነት ሥልጣን አስፈላጊ ባለመኾኑ ያንን ሥልጣን አስረ ክቦ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው መለኮታዊ ክብሩ ለዘላለም ይኖራል ማለት ነው ። (ማቴ. ም. ፳፰ ቍ. ፲፰)

እግዚአብሔር ኹሉን ነገር በክርስቶስ እግር ሥር ካስገዛለት በኋላ ወልድ ኹሉን ላስገዛለት ተገዢ ይኾናል የተባለው በመለኮታዊ ባሕርዩ ከአብ የሚያንስ ኾኖ ሳይኾን ራሱን ዝቅ አድርጎ በለበሰው የሰው ልጅ ሰውነት ተገዢ ለመኾን ስለፈቀደ ነው ። የሰውን ልጅ ሥጋ ከለበሰ በኋላ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሏል እንደተባለው የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ተገዢ እንደሚኾን ኹሉ ጌታም በለበሰው ሥጋ ተገዢ ኾኗል ።

«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ።» (ኤፌ. ም. ፩ ቍ. ፲፯ ፥ ፩ኛ ጴጥ. ም. ፩ ቍ. ፫)

ይህንን ጥቅስ እንደማስረጃ በማቅረብ አብ ከወልድ በላይ እንደ ኾነና ጌታ ደግሞ መቼም ቢኾን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል አድርጎ እንዳልገመተ በማስመሰል የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ።

ቀደም ተብሎ በሌሎች አርእስት እንደተገለጸው ጌታ የሰውን ሥጋ በለበሰ ጊዜ የመለኮትና የትስብእት ውሕደት ያለመቀላቀል ፥ ያለመጠፋፋትና ያለመለዋወጥ ስለኾነ ስለጌታ በሚነገርበት ጊዜ እንደ ፍጹም አምላክነቱ ወይም እንደ ፍጹም ሰውነቱ ስለሚነገር ሊያ ስገርመንና ሊያስደንግጠን አይገባም ። ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው

መኾኑን መገንዘብ አለብን ። በተመሳሳይ ኹኔታ በሐዋርያት ሥራ ም. ፲ ቍ. ፳፭ ላይ እግዚአብሔር ጌታን ቀባው በሚልበት ጊዜ ትስብእቱን እንጂ መለኮቱን አይደለም ። አንድ ሰው የሹመት ቅባት የሚቀባው አንድ የተወሰነ መንፈሳዊ ወይም ዓለማዊ ክብር ሲሰጠው ነው ። ሟች ፥ ፈራሽና በስባሽ የኾነው የሰው ልጅ ሥጋ ከመለኮት ጋር ተዋሕዶ እንዲያደርግ እግዚአብሔር አክብሮ የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል ስላበቃው ተቀባ ተባለ እንጂ መለኮትማ የክብር ጌታ ነው ።

በሰውነቱ ስለጌታ የሚነገሩ አነጋገሮች ለምሳሌ አባቴ ከእኔ ይበልጣል ፥ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ እኼዳለሁ የተባሉት አባባሎች እንዳሉ ኹሉ አምላካዊ ክብሩን የሚገልጹት ደግሞ የሚከተሉት ጥቅሶችና ማብራሪያዎች ናቸው ።

፩. በሲና ተራራ ላይ የሃይማኖት ሕግጋትን የሰጠው የሕግጋቱ ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ መኾኑ የታወቀ ነው ። (ዘፀ. ም. ፳) በሲና ተራራ ላይ ከተሰጡት ሕግጋት አንዱ ሰንበትን ማክበር ቢኾንም ስለሰንበት መክበርና መሻር ጉዳይ ፈሪሳውያን ጌታን ባነጋገሩት ጊዜ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው የሚል መልስ መስጠቱ ቀድሞውንም ቢኾን ያንን ሕግ የሰጠሁት እኔው ራሴ ነኝ ማለቱ መኾኑ ግልጽ ነው ። (ማቴ. ም. ፲፪ ቍ. ፰)

፪. «በመጀመሪያው ቃል ነበረ ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ። ኹሉ በእርሱ ኾነ ፤ ከኾነውም አንዳች ስንኳ ያለእርሱ የኾነ የለም ።» (ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፩—፫)

፫. አይሁድ ጌታን ሊገድሉት የፈለጉበት ዋነኛው ምክንያት ቅዳሜን በመሻሩ ብቻ ሳይኾን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከል እግዚአብሔርን አባቴ ነው በማለቱ ነው ተብሏል ። (ዮሐ. ም. ፭ ቍ. ፲፰)

፬. ጌታ ከትንሣኤው በኋላ የተቸነከሩ እጆቹንና የተወጋ ጐኑን ባሳየው ጊዜ ሐዋርያው ቶማስ ጌታዬ ፥ አምላኬ ብሎ መልስ ሲሰጠው ለምን አምላኬ ትለኛለህ ብሎ የጠየቀው ሳይኾን እንዲያውም በእኔ አምላክነት የምታምነው ስላየኸኝ ነውን ? ሳያዩኝ በእኔ የሚያምኑ ግን የተመሰገኑ ናቸው በማለት አምላክነቱና አረጋግጦለታል ። (ዮሐ. ም. ፳ ቍ. ፳፰—፳፱)



፭. «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ . . .» (የሐ. ሥ. ም. ፳ ቍ. ፳፰)

ለቤተ ክርስቲያን ደሙን ያፈሰሰላት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲኾን እርሱም እዚህ ጥቅስ ላይ እግዚአብሔር መባሉን እናስተውል ።

፮. «ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ ፤ እርሱም ከኹሉ በላይ ኾኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው ።» (ሮሜ ም. ፱ ቍ. ፭)

፯. «የተባረከውን ተስፋ እርሱም የታላቁን የአምላካችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን ።» (ቲቶ. ም. ፪ ቍ. ፲፫)

፰. «የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣና እውነት የኾነውን እርሱን እንድናውቅ አስተዋይ ልቡና እንደሰጠን እናውቃለን ፤ እኛም በዚህ እውነት በኾነው በኢየሱስ ክርስቶስ እንኖራለን ። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው ።» (፩ኛ ዮሐ. ም. ፭ ቍ. ፳)

ስለዚህም «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ» የተሰኘው ጥቅስ በአንድ በኩል ስለትስብእቱ የሚናገር ሲኾን በሌላ በኩል ደግሞ ቀድሞ ሳናውቀው ኖረን አሁን ጌታ እንድናውቀው ያደረገን ማለት ነውና የጌታን አምላክነት የሚቃረን አይደለም ። (ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፲፬—፲፰)

> «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም ፤ ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ ፥ በሰውም ምሳሌ ኾኖ ራሱን ባዶ አደረገ ።» (ፊልጵ. ም. ፪ ቍ. ፮—፯)

ከእግዚአብሔር አብ ጋር በመለኮታዊ ባሕርዩ እኩል ነው እንጂ በመቀማት የሚያገኘው አይደለም ። ኾኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጎ ሰው በመኾን ሕማምና ሞት እንዲደርስበት ስለፈቀደ ራሱን ባዶ አደረገ አሰኝቶታል ። ሕማምና ሞት የማይደርስበት አምላክ በለበሰው ሥጋ ሕማምና ሞት ደርሰውበታል ። ይህንንም ያደረገው እርሱ ምንም የሚያስፈልገው ነገር ኖሮት አይደለም ። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው

እርሱ ሀብታም ሲኾን እኛ በእርሱ ድኽነት ባለጠጎች እንኾን ዘንድ ስለ እኛ ድኻ ኾነ ። (፪ኛ ቆሮ. ም. ፰ ቊ. ፱)

## የቅዱሳን አባቶች ትርጓሜ ፡

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ «በምንም በምን ሕማም የሌለበት እውነተኛ የባሕርይ አምላክ ፡ እውነተኛ ብርሃን ፡ የእግዚአብሔር አብ ኀይሉ የሚኾን ለሕማም ፡ ለሞት የማይደፈር እርሱን መናፍቃን በክሕደታቸው እንደ ሰው በግድ ታመመ ፤ ደከመ ፤ ሞተ እንደምን ይሉታል ? ለሞቱ ሰዎች ሕይወትን የሰጠውን ፡ ሙታንን ያስነሣውን ፡ ያልነበሩበትን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ያስገኛቸውን ታመመ ፤ ሞተ እንደምን ይሉታል ? . . . ከባሕርዩ ሳይለወጥ ከእመቤታችን ነፍስን ሥጋን ነሥቶ ሰው የኾነ እርሱ እንደ እኛ በላ ፤ ጠጣ ፤ ከእኛ በነሣው በሰው ባሕርይ ሰው ኾኖ ታመመ ፤ ተሰቀለ ፤ ሞተ እንጂ እርሱ የባሕርይ አምላክ ሲኾን ሰው ኾነ ። ከባሕርዩ ከተለወጠማ ወደ ገነት መግባትን በስተቀኙ ለተሰቀለው ወንበዴ እንደ ምን በአበሠረው ነበር ? በመለኮቱ ፡ በሥራውም ኹሉ የሚታመም የሚሞት ከኾነ ሥጋውን ከሙታን ለይቶ እንደምን አስነሣ ?» (ሃይ አበ ፡ ገጽ ፸፯)

ቅዱስ ቴዎዶጦስ ፡ የዕንቈራ ኤጲስ ቆጶስ «የሥጋን ሕማም ለመለኮት ገንዘብ በአደረገ ጊዜ የእግዚአብሔር አካል በባሕርዩ በግድ ሕማምን አልተቀበለም ፤ ሕማም በሚስማማው ባሕርዩ ኀይልን እንጂ ፤ ሞትም በሥጋ ለእግዚአብሔር ቃል ገንዘብ በኾነ ጊዜ ሞትን አጠፋ ፤ ከሞትም በኋላ ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አጠፋ ።» (ሃይ አበ ፡ ገጽ ፻፸፰)

ቅዱስ ቄርሎስ ፡ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት «የወለደው አብን በመልክ የሚመስለው ፡ በባሕርይ የሚተካከለው እርሱ ነው ፤ ሽቶ ቀምቶ ከእግዚአብሔር ጋር የተካከለ አይደለም ፤ ራሱን አዋርዶ ከድንግል ማርያም የአዳምን ባሕርይ ነሥቶ በሰው ባሕርይ ተገኘ ፤ በሰውም መልክ ተገለጠ እንጂ ፤ እርሱ ብቻ ተዋርዶ እስከ መሞት ደርሶ እሺ በጀ አለ ፤ ሞቱም በመስቀል የኾነው ነው ። ከፍጹም ክብሩ ለኹሉ የሚሰጥ እርሱ እስከዚህ ሰው እስከ መኾን ድርሶ ተዋረደ ፤ ማንም ማን ግድ ሳይለው እርሱ ብቻ ወረደ በባሕርዩ መገዛት የሌለበት እርሱ ብቻ እኛን ለማዳን የአዳምን ባሕርይ በፈቃዱ ተዋሐደ ፤ ከፍጥረት ኹሉ የራቀ እርሱ በእኛ ባሕርይ ተገኘ ፤ ኹሉን የሚያድን እርሱ በሞት ከተያዙ ጋር ተቈጠረ ፤ ከሰማይ የወረደ ፡ ለዓለም ሕይወትን የሚሰጥ የሕይወት ምግብ እርሱ ነው ።» (ሃይ. አበ ፡ ገጽ ፻፻፺፫)



«ክርስቶስ ለማይታየው እግዚአብሔር እውነተኛ ምሳሌ ነው ። እርሱ ኹሉ ነገር ከመፈጠሩ በፊት የነበረ የፍጥረት ኹሉ በኵር ነው ።» (ቆላ. ም. ፩ ቊ. ፲፭)

ይህንን ጥቅስ መሠረት በማድረግ አንዳንድ ወገኖች ወልድን ፍ ጡር ነው የማለት ድፍረት የተመላበት ክርክር ያቀርባሉ ። በኵር ማለት ግን በመጀመሪያ የተወለደ እንጂ በመጀመሪያ የተፈጠረ ማለት አይደለም ። በቅዱሱ መጽሐፍ በግልጽ እንደተነገረው እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው ሰማይንና ምድርን ነው ። (ዘፍ. ም. ፩ ቊ. ፩)

በዮሐንስ ወንጌል ም. ፩ ቊ. ፫ መሠረት ኹሉን ነገር የፈጠረ ቃል ነው ተብሏል ። ይህም ኹሉን ነገር የፈጠረው በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፩ ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ነው ። ታዲያ ኹሉን ነገር የፈጠረውን እግዚአብሔርን በኵር በመባሉ ብቻ እንዴት ከፈጣሪ አምላክነት ወደ ፍጡርነት ሊያዛውሩት በቁ ? ችግራቸው በኵር የሚለው ቃል በጥቅሱ ውስጥ እንዴት ሊገባ ቻለ የሚል ከኾነ እዚህ ላይ በኵር ማለት ከተፈጠረው ፍጥረት ኹሉ በፊት የነበረ መኾኑን የሚያመለክት ነው እንጂ ፍጡር መኾኑን የሚያመለክት አይደለም ።

ወደ ቆላስይስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፩ ቊ. ፲፭ ላይ እንደተገለጸው መድኀኒታችን ለማይታየው እግዚአብሔር እውነተኛ ምሳሌ ነው የተባለው ሊታይ የማይቻል መለኮት የሰውን ልጅ ሥጋ ለብሶ ሊታይ በመቻሉ ነው ።

ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ያለ እናት ከአብ ስለተወለደ በኵር ተባለ። ይህም መውለድና መወለድ እኛ ውሱኖቹ መርምረን ልንደርስበት የማንችል ከሥሉስ ቅዱስ ውሳጣዊ ግብሮች ጋር የሚቈጠር ነው ።

በእነዚህም ከላይ በቀረቡትና በሌሎችም ሊቀርቡ በሚችሉ ማስረጃዎች መሠረት በኵር የተባለው ቃል በመጀመሪያ የተወለደ እንጂ በመጀመሪያ የተፈጠረ ማለት አለመኾኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

# ምዕራፍ ስድስት

## ምሥጢረ ተዋሕዶ
## (የተዋሕዶ ባሕርይ ምሥጢር)

### ሀ. መግቢያ

ባሕርይ ማለት ምን ማለት ነው ? ባሕርይ ማለት የአንድን ነገር ትክክለኛ ምንነት የሚገልጽ ቃል ነው ።

ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎችና የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን አባቶችን ትምህርት መሠረት በማድረግ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትና ትስብእት አንድ አካልና አንድ ባሕርይ ለመኾን የተዋሐደው መለኮት ከሙሉ መለኮታዊ ባሕርዩና ጠባዩ ጋር ሲኾን ፡ እንዲሁም ትስብእት ከኀጢአት በቀር ከሙሉ ሰብአዊ ባሕርዩና ጠባዩ ጋር እንዳለ ኾኖ ነው እንጂ በተዋሕዶው ምክንያት መቀላቀል ፡ መጠፋፋት ፡ መለያየትና መለዋወጥ እንዳለ የማታምን ከመኾንዋም በላይ መለኮት እና ትስብእት ተቀላቅለው ትስብእት በመለኮት ተውጦ ጠፍቷል የሚለው የአውጣኬ ክሕደት የተወገዘ መኾኑን ታረጋግጣለች ።

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ አንድ አካል ፡ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ እንዲኖረው ያስፈለገው የሰውን ልጅ ለማዳን የግድ መለኮትና ትስብእት አብረው መኾን ስላለባቸው ነው ። ትስብእት መኖር ያስፈለገው በሰው ልጅ ምትክ መሞት ስላለበት ነው ። መለኮት መኖር ያስፈለገው ደግሞ ውክልና የማይገኝለት በመኾኑ ነው ።

### ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት

ቤተ ክርስቲያን የመለኮትንና የትስብእትን ተዋሕዶ ብታምንና ብታስተምርም የተዋሕዶው ኹናቴ እንደዚህ ነው ወይም በዚህ ዐይነት



ነው ተብሎ ሊገለጽበት የሚቻል በሰው ልጅ ቋንቋ ውስጥ ቃላት የማይገኙለት ምሥጢር መኾኑንና ምሥጢርነቱም የሰው ልጅ አስተሳሰብ ሊረዳው ከሚችለው በላይ መኾኑን ታውቃለች ። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ «እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጸበት የአምልኮ ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው» ሲል የምሥጢረ ተዋሕዶን ረቂቅነት ያረጋገጠው ። (፩ኛ ጢሞ. ም. ፫ ቁ. ፲፮)

መለኮትና ትስብእትም ከተዋሐዱ በኋላ አንድ አካል ፡ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ እንላለን እንጂ ወደ ኋላ ተመልሰን ኹለት አንልም ። መለኮት የመለኮትን ትስብእት ደግሞ የትስብእትን ሥራ ብቻ ይሠራሉ ካልን የትስብእት አዳኝነት በቂ ሊኾን የማይችል ከመኾኑም በላይ በዚህ አባባላችን የእግዚአብሔርን ውለታ ዋጋ ማሳጣት ይኾንብናል ። እንዲሁም ይህ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ካልታመነበት አምላክ ሰው መኾን ባላስፈለገውም ነበር ፤ የአምላክ ሰው መኾን እምነታችንም ከንቱ መኾኑ ነው ። መለኮትና ትስብእት በመዋሐዳቸው የትስብእት ባሕርይ ከውሕደት በፊት ያልነበረውን መለኮታዊ ባሕርይ በመገናዘብ ሥራውም የእግዚአብሔር ልጅ ሥራ ለመባል በቃ ።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ባለመጠፋፋት በመኾኑ ወልድ በሥጋው ሞተ እንላለን ። ይህንኑም በሚከተሉት ጥቅሶች እንመልከት ።

«ልጁ በሥጋ በመሞቱ ምክንያት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር አስታረቃችሁ ።» (ቆላ. ም. ፩ ቁ. ፳፪)

«ክርስቶስ ራሱ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን ፈልጎ እርሱ ጻድቅ ኾኖ ሳለ በኀጢአታችን ምክንያት በማያዳግም ኹኔታ አንድ ጊዜ ሞቷል ! እርሱ በሥጋ ሞተ ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ኾነ ።» (፩ኛ ጴጥ. ም. ፫ ቁ. ፲፰)

«ክርስቶስ በሥጋው ስለ እኛ መከራን ተቀበለ ።» (፩ኛ ጴጥ. ም. ፬ ቁ. ፩)

በሰው ልጅ ላይ የሚነገር ሰብአዊ ስሜት ለምሳሌ እንደ መደሰት ፣ ማዘን ፣ ማፍቀር ፣ መጥላት ፣ መራብ ፣ መጠማት ፣ መታመምና እነዚህንም የመሳሰሉት ስሜቶች ሊደርሱ የሚችሉት የሰው ልጅ ሥጋውና ነፍሱ አብረው ባሉበት ጊዜ መኾኑ ግልጽ ነው ። ሥጋውና ነፍሱ ከተለያዩ በኋላ ማለት ከሞተ በኋላ እነዚህ ስሜቶች አይኖሩም ። ሰው ሲሞት ደግሞ ሥጋው እንጂ ነፍሱ አትሞትም ። የሰውነታችን እንቅስቃሴ ፣ እስትንፋሳችንና በአጠቃላይም ሕይወታችን ነፍሳችን እንደ መኾኑ ነፍሳችን ከሥጋችን በሚለይበት ጊዜ ሥጋችን በድን ይኾናል ። ነፍሱ ከሥጋው የተለየ ሰው ደግሞ ሰው መባሉ ቀርቶ ሬሳ የሚባል ስም ይሰጠዋል ። ኾኖም አንድ ሰው ሲሞት በሥጋው ሞተ አይባልም ፤ ምክንያቱም ሰው ሊባል የሚችለው ነፍስ ሲኖረው ብቻ ነውና ። እንግዲህ የሰው ነፍስ ሞት የማይደርስበት ከኾነ ነፍስን ለሰው ልጅ የሰጠው መለኮት ሕማምና ሞት የማይደርስበት መኾኑ ግልጽ ነው ።

ምንም እንኳ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ያለ መቀላቀልና ያለ መጠፋፋት መኾኑ የታመነ ቢኾን አምላክ በትስብእቱ ሕማምን ተቀብሎ ሞተ እንላለን ። ይህም ማለት ለቅጽበተ ዐይን ያኽል ጊዜ እንኳ መለኮት ከትስብእት ያልተለየ መኾኑን ለማመልከት ነው ። ለዚህም የሚቀጥሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች እንመልከት ።

«ሕፃን ተወልዶልናልና ፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ፣ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይኾናል ፤ ስሙም ድንቅ ፣ መካር ፣ ኀያል አምላክ ፤ የዘላለም አባት ፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ።» (ኢሳ. ም. ፱ ቍ. ፮)

ሕፃን ኾኖ መወለድ የትስብእት ባሕርይ መኾኑ ቢታወቅም በመለኮትና በትስብእት ተዋሕዶ ምክንያት ያ የተወለደው ሕፃን ኀያል አምላክና የዘላለም አባት መባሉን እናስተውል ።

«እነሆ ፣ ድንግል ትፀንሳለች ፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፤ ስሙም ዐማኑኤል ተብሎ ይጠራል ። ዐማኑኤል ማለትም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው ።» (ማቴ. ም. ፩ ቍ. ፳፫)



እዚህም እንደ ፊተኛው ጥቅስ ተፀንሶ መወለድ የትስብእት ባሕርይ መኾኑ ባይካድም ዐማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው የተባለው የመለኮትንና የትስብእትን ተዋሕዶ ሲያመለክተን ነው ።

«እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታል ።» (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፲፮)

የእግዚአብሔር አንድያ ልጅነት በመለኮቱ ቢኾንም ዓለምን ለማዳን ለሕማምና ለሞት ታልፎ ተሰጠ የተባለው መለኮቱ መቼም ቢኾን ከትስብእቱ ያልተለየ በመኾኑ ነው ።

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፳ ቍ. ፳፰)

ቤተ ክርስቲያንን ለመዋጀት ደሙን ያፈሰሰው እግዚአብሔር መባሉን እናስተውል ።

«ዐውቀውትስ ቢኾኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር ።» (፩ኛ ቆሮ. ም. ፪ ቍ. ፰)

የክብር ጌታ የተባለው ፈጣሪ አምላካችን ሲኾን ተሰቀለ መባሉም መለኮትና ትስብእት መቼም ቢኾን ያልተለያዩ መኾናቸውን ሲያመለክተን ነው ።

«የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ ፤ ሞቼ ነበር ፣ ነገር ግን ለዘላለም ሕያው ነኝ ።» (ራ. ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፲፯ — ፲፰)

የመጀመሪያውና የመጨረሻው የሚለው የአምላክ ብቻ መጠሪያ ሲኾን ሞቼ ነበር ያለውም በትስብእቱ ሲሞት መለኮት ያልተለየው መኾኑን ያመለክተናል ።

## ሐ. የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ፡- «ለመወለዱ ጥንት በሌለው አስቀድሞ ዓለም ሳይፈጠር በመለኮቱ ከአብ በተወለደ ፥ ዳግመኛም እኛን ለማዳን በኋላ ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደ በእግዚአብሔር ልጅ እናምናለን ፤ የቀኑ ቀጠሮ ሲደርስ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ፤ ከድንግል ተወለደ ያለው ብፁዕ ሐዋርያ እንዳስተማረን ። ይህ አንዱ አምላክ ነው ፤ በመለኮት የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ የአዳም ነው ፤ የእግዚአብሔር ፥ የአዳም ልጅ ስለኾነም ፡ ለወልድ ዋሕድ ለአንዱ የምንሰግድለት ፡ ለአንዱ የማንሰግድለት ኹለት አካል ኹለት ባሕርይ አለው የምንል አይደለም ፤ ሰው የኾነ የእግዚአብሔር አካሉ ባሕርዩ አንድ ነው እንጂ ፤ ከሥጋው ሳንለይ አንድ አድርገን አንዲት ስግደትን እንሰግድለታለን እንጂ ።» (ሃይ. አበ ፡ ገጽ ፷፰)

ቅዱስ አቡሊዲስ ፡ የሮም ሊቀ ጳጳሳት ፡- «ኹለት አካል፡ኹለት ባሕርይ ብለው የሚያምኑ ለአንዱ እንዲሰግዱ ለአንዱ እንዳይሰግዱ ፡ በመለኮት ባሕርይ እንዲጠመቁ በሥጋ ባሕርይም እንዳይጠመቁ ግድ ይኾን ባቸዋል ። . . . እኛ ግን ስለ መለኮት ስንናገር ወልድ ከሰማይ እንደ ወረደ እንናገራለን ፤ አንዱ አካል ኹለት መኾኑን እናውቅም ። ሰማያዊ መለኮትን ከምድራዊ ሥጋ ፥ ምድራዊ ሥጋንም ከሰማያዊ መለኮት አንለየውም ፤ መክፈል ክሕደት ነውና፤ኹለት አካል ፥ ኹለት ባሕርይ ለሚሉ ሰዎች ምክንያት አንሰጣቸው ። ሥጋም ሥጋ ነው ፤ በገንዘቡ ብቻ ነዋሪ አይደለም ፤ በገንዘቡ ባሕርይ ብቻ የዳነ አይደለም ፤ ከሚያድን ከቃልም ተለይቶ በገንዘቡ ብቻ ሊኖር አይችልም ። ቃልም ሰው ከመኾኑ አስቀድሞ እንደነበረ ኹሉ በመለኮታዊ ባሕርዩ ከሥጋ አይለ ይም ፤ ለብቻውም አንድ ወገን ኾኖ አይኖርም ። . . . . ያልተፈጠረ ቃል ያለ ሥጋ ሰው ኾኖ አልታየምና ማንም ማን ያልተፈጠረ መለኮትን ከሥጋ ልዩ ነው እንዳይል እርስ በርሳቸው አንድ ስለኾኑበት አንድነት በነፍስ በሥጋ አምሳልም ስለተዋሐዱበት ተዋሕዶ ኹለቱ በተዋሕዶ አንድ ኾነዋልና አሁንም በተዋሕዶ አንድ ለኾኑ ለኹለቱ አንድ ስም ይገባል ።» (ሃይ. አበ ፡ ገጽ ፻፴፩)



«የእግዚአብሔር ልጅ ወልድ ዋሕድ ነፍስን ሥጋን ነሥቶ ሰው ኾነ ባልን ጊዜም ስለዚህም ነገር ቢኾን እነዚያ እንደሚያምኑ መቀላቀል የለበትም ፤ የቃል ባሕርይ የሥጋን ባሕርይ ወደመኾን ፥ የሥጋ ባሕርይም የቃል ባሕርይን ወደ መኾን አልተለወጠም ፤ ኹለቱ ባሕርያት ያለመለዋወጥ ባለመቀላቀል ጸንተው ይኖራሉ እንጂ ።» (ሃይ. አበ. ገጽ ፻፵፯)

ቅዱስ ቄርሎስ ፡ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ፡- «በእግዚአብሔር ቃል በረቂቅ ባሕርይ የኾነውን ተዋሕዶ አንክድ ፤ ብረት ከእሳት በተዋሐደ ጊ ዜ ፥ ከእሳትም በመዋሐዱ የእሳትን ባሕርይ ገንዘብ እንዲያደርግ ፥ ብ ረት በመዶሻ በተመታ ጊዜ ከእሳት ጋር በአንድነት እንደሚመታ ፥ ግን ከመዶሻው የተነሣ የእሳት ባሕርይ በምንም በምን እንዳይጐዳ ፥ ሰው የኾነ አምላክ ቃል በመለኮቱ ሕማም ሳይኖርበት በሥጋ እንደታመመ እንዲህ እናስተውል ።

ፈቃድ ሥጋን እንድዋሐድ አደረገኝ የኀጢአትን ፍዳ አጠፋ ዘንድ ስለ መከራም በሥጋዬ ተቀበልኩ ፤ የኹሉን ኀጢአት አጠፋ ዘንድ ስለ እነርሱ ሰው ኾኛለሁና ኹለተኛ አዳም ኾኜ ሞትኩ ። መለኮቴ አልሞ ተም ፤ ሲኦልን በዘበዝኩ እንጂ ፤ በገዛ ሥልጣኔም ተነሣሁ እንጂ በገነት በነበረ ሰው በአዳም በንፍሐት መንፈስ ቅዱስን ያሳደርኹ ፈጣሪ እኔ መኾኔን አስረዳ ዘንድ በደቀ መዛሙርቴ ፊት እፍ ብዬ መንፈስ ቅዱስን አሳደርኩ አለ ።» (ሃይ. አበ. ገጽ ፻፪፻፪)

ቅዱስ ሳዊርስ፡ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት፡-«ከሐዲያን መናፍቃን እንደሚሉት ከኾነ ቢዛችን ኾኖ ፤ ርስቶስ የሞተው ሞት የመለኮት ከሥጋ መለየት ነው እንጂ የነፍስ ከሥጋ መለየት አይደለም ፤ እንደነሱ አነጋገር የእኛን ሞት ካልሞተማ ቤዛችን በኾነ በመድኀኒታችን ሞት እንደምን እንመካለን ? የእኛ ባይደለ በሌላ ሞት ዲያብሎስ ድል ከተነሣ ቃል ከእኛ ባሕርይ ጋር አንድ አልኾነማ ። ነገር ግን እርሱ ቤዛችን ኾኖ እንደ እኛ ሞት ያለ ሞትን እንደ ሞተ ነገሩ የታወቀ ነው ፤ ይኸውም የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው ፤ ነፍሱን በሲኦል አልተወም ፤ ሥጋውም

እንዲፈርስ እንዲበስብስ አላደረገም ፤ ነቢይ እንደተናገረ ፤ ነገር ግን ነፍሱ ከሥጋው በተለየች ጊዜ እግዚአብሔር ቃል በፈቃዱ ይህንን ሠራ ፤ ከተለያዩ ከኹለቱ ከነፍስና ከሥጋ አልተለየም ፤ አንድ አካል በመኾን ከነፍስ ከሥጋ ጋር ተዋሕዶ ይኖራል እንጂ ።» (ሃይ. አበ. ገጽ ፫፻፳፰)

«አሁንም አንዱ የእግዚአብሔር ቃል ባሕርይ ሳይለወጥ ሳይና ወጥ ሰው እንደኾነ ነገሩ የታወቀ የተረዳ ነው ፤ እርሱ አንድ ባሕርይ ፤ አንድ አካል እንደኾነ እናውቃለን ፤ ይህ አንዱ እርሱ የአምላክነትን ሥራ ይሠራል ፤ ወዲህም እርሱ መለወጥ የሌለበት ሰው ነው ፤ እርሱ ወልድ ነው ፤ እርሱ እግዚአብሔር ነውና በቅድምና የነበረ የእግዚአብ ሔር አብ ልጅ ነውና በፍጹም ቸርነቱ ከዳዊት ፣ ከአብርሃም ወገን ተወ ልዶ የሰው ልጅ ሊኾን ወደደ ። እንደ አይሁድ ኹለቱን ባሕርያት እርስ በርሳቸው ለያይቶ ተአምራትን ያደረገ የመለኮት ባሕርይ ነው ፤ መከ ራን የተቀበለ የሥጋ ባሕርይ ነው እንደሚል እንደ ክሑዱ ንስጥሮስ እነጋገር ከተዋሕዶ በኋላ አንዱ ወደ ኹለትነት ሊከፈል አይቻልም ።» (ሃይ. አበ ፣ ገጽ ፫፻፴፱)

ቅዱስ ባስልዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት፡-«ዐማኑኤል ተባለ ትርጓሜውም እግዚአብሔር አምላካችን ከእኛ ባሕርይ ጋር አንድ ኾነ ማለት ነው ፤ ያለመቀላቀል ያለ መለወጥ ሰው የኾነው አንድ ገጽ ፣ አንድ አካል ፣ አንድ ባሕርይ ነው ፤ ከመለኮትና ከትስብእት የኾነ ተዋሕዶ የማይነገር የማይመረመር ነው ፤ በውነት መቀላቀል የሚገባቸውስ ርጐበት ያላ ቸው ሥጋት ናቸው ፤ እነዚህም ግዘፍ ከሌለው ባሕርይ የተለዩ ናቸው ። ከተዋሕዶ በኋላ ወደ ኹለት ባሕርይ አይከፈልም ፤ ተዋሕዶ መንታን ትን አጥፍቷልና ተዋሕዶም ከኹለት የተገኘ ኹለት መባል አለበት የሚለውን ፍርድ ይለውጣል ፤ ይህ ተዋሕዶ የማይከፈል አካላዊ ነውና ፍጡር ያይደለ እግዚአብሔር ቃል ሥጋ ወደ መኾን ይለወጣል ፤ በባ ሕርይ የሚመስለን ፣ ከንጽሕት ድንግል የተገኘ ሥጋም ከባሕርዩ የመ ለኮት ባሕርይ ወደ መኾን ተለወጠ ብሎ መናገር እውነተኛ ነገር እንደ ኾነ የሚያስብ ማነው ? የሙሴ በትር ተለውጣ የምድር እባብ እንደኾ ነች ፤ የፈሳሽ ውሃም ተለውጦ ደም እንደኾነ ፣ የግብጽ ብርሃንም ተለ ውጦ ጨለማ እንደኾነ እንዲሁ የእግዚአብሔር ቃልም የሰው ባሕርይን ወደ መኾን የተለወጠ አይደለም ፤ እነርሱ የተፈጠሩ ናቸውና ፣ በመ ፈጠርም የታወቁ ናቸውና ፣ ከዘመንም በኋላ የተገኙ ናቸውና ፣ ስለዚ ህም መለወጥ አገኛቸው ፤ የመለኮት ባሕርይ ግን መለወጥ የለበትም ፤



ፍጻሜ ሳይኖረውም ኹል ጊዜ ይኖራል ፤ አይወሰንም ፤ መለወጥ መና ወጥ የለበትም ።» (ሃይ. አበ. ፣ ገጽ ፬፻፳፪)

## መ. የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል

የአውጣኪን ክሕደት ለማረም ወይም ከሐዲውን ለማውገዝ የእስክንድርያው በ፬፻፴፩ ዓ. ም. በኤፌሶን የተሰበሰበው ጉባኤ ሰብሳቢ የእስክንድርያው ቤተ ክርስቲያን መሪ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ነበር ። ስብሰባውን በሊቀ መንበርነት እንዲመራ ለቅዱስ ዲዮስቆሮስ ጥሪ የላከለት ትንሹ ቴዎዶ ስዮስ ነው ። በዚህም መሠረት ጉባኤው ተካኺዶ አውጣኪ እምነቱን እንዲያብራራ በተጠየቀ ጊዜ የእርሱ እምነት ከኒቅያ ጉባኤ አባቶችና ከቅዱስ ቄርሎስ ትምህርት የተለየ አለመኾኑን ስለገለጸ ከውግዘቱ ተፈትቶ ወደ ሥራው እንዲመለስ ጉባኤው ወሰነለት ። በዚሁ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ፍላጥያኖስና ሌሎችም በንስጥሮሳዊ እምነታቸው ተወግዘዋል ። በዚህ ጊዜ እነፍላጥያኖስና ሌሎችም ንስጥሮሳውያን ከሮማው ቤተ ክርስቲያን መሪ ከልዮን ጋር በዲዮስቆሮስ ላይ የበቀል እርምጃ የሚወስዱበት ግንባር በመፍጠር ለማመቻቸት ከረዱአቸው ን ዘዴ ይፈልጉ ጀመሩ ። ይህንን ዕቅዳቸውን ለማመቻቸት ከረዱአቸው ኹናቴዎች አንዱ የአውጣኪ ወደ ቀድሞ የክሕደት ትምህርቱ ተመልሶ መገኘቱ ነው ። ኾኖም በዲዮስቆሮስ ሰብሳቢነት የተካኼደውን ጉባኤ ትክክለኛነት የሚመለከት ሌላ ጉባኤ እንዲሰበሰብ በማለት ደጋግመው የጠየቁትን ጥያቄ ንጉሥ ቴዎዶስዮስ ውሳኔው ትክክል ስለኾነ ሌላ ጉባኤ መሰብሰብ አስፈላጊ አይደለም በማለት በሕይወት ዘመኑ ኹሉ ጥያቄአቸውን ውድቅ ሲያደርግባቸው ኖሮአል ። በ፬፻፵፱ ዓ. ም. ንጉሡ ቴዎዶስዮስ ያለ ልጅ ወራሽ ከዚህ ዓለም በሞት በተለየ ጊዜ እኅቱ ብርክ ልያ ከጦር መሪዎች አንዱ መርቅያኖስን አግብታ ዙፋኑን ወረሱ ። ባልና ሚስትም ንስጥሮሳውያን ስለነበሩ ለዲዮስቆሮስ ተቃዋሚዎች አመቺ ጊዜ ተፈጠረላቸው ። በዚህም መሠረት በ፬፻፶፩ ዓ. ም. በኬልቄዶን በተሰበሰበው አብዛኛዎቹ አባላት ንስጥሮሳውያን በነበሩበት ጉባኤ ፊት ዲዮስቆሮስ የአውጣኪ ክሕደት ተከታይ ነው የሚል ክስ ተመሥ ርቶበት ታላቅ ክርክር ተነሣ ። ይህ ክስ እንደ ዋነኛው ክስ ተደርጎ ከመቅረቡ በቀር ሌሎችም ልዩ ልዩ ክሶች ቀርበውበት ነበር ። ከመጀ ከመገመቱ በቀር ሌሎችም ልዩ ልዩ ክሶች ቀርበውበት ነበር ። መሪያውም ቢኾን የስብሰባው ዋና ዓላማ በዲዮስቆሮስ ላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ስለነበረ ከሃይማኖት ሰዎች በማይጠበቅ ተንኰል በአንድ በኩል ከቤቱ እንዳይወጣ በዘበኛ አስጠብቀው ፣ በሌላ በኩል

ደግሞ ብንጠራው ሳይመጣ ቀረ ለማለት ጥሪ አስተላልፈውለት ዲዮስቆሮስ በሌለበት እና ከዳኞችም ተደብቀው የፈለጉትን ውሳኔ በዲዮስቆሮስ ላይ አሳለፉ ። ውሳኔአቸውን ከአመቻቹ በኋላ ግን ዲዮስቆሮስ በስብሰባው እንዲገኝ ፈልገው ነበር ። እርሱ ግን ተመልካች ዳኞች በሌሉበት በስብሰባው ለመገኘት ፈቃደኛ አልኾነም ። ከዚያም ንጉሡን በውሳኔአቸው አሳምነው ዲዮስቆሮስን ጋግራ ወደ ተባለች ደሴት እንዲጋዝ አስደረገዋል ። እስከ ዕለተ ሞቱም ድረስ ቀሪ የሕይወት ዘመኑን ያሳለፈው በዚያው በጋግራ ደሴት ግዞት ነው ። ‹‹ኬልቄዶኑን ጉባኤ ሕገ ወጥ ውሳኔ ካልተቀበሉት መካከል የግብጽ ፣ የኢየሩሳሌም ፣ የሶርያና የአርመን አብያተ ክርስቲያናት ይገኙባቸዋል ። በዚህም የምሥራቅና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ወገናዊነትን በተከተለ ስያሜ ዓለም ዐቀፋዊነትዋ ቀርቶ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለኹለት ተከፈለች ።

የምዕራቦቹ ወገኖች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ ብቻ አለው ብሎ ማመን የአውጣኬን ክሕደት መከተል ነው በሚል ምክንያት በኹለት ባሕርይና በኹለት ፈቃድ እምነት ላይ ሲጸኑ ፣ የምሥራቆቹ ወገኖች ደግሞ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኹለት ባሕርይና ኹለት ፈቃድ አለው ብሎ ማመን የንስጥሮስን ክሕደት መቀበል ነው በማለት በአንድ ባሕርይ በአንድ ፈቃድና በአንድ አካል እምነት ላይ ጸንተዋል ።

ኹለቱም ወገኖች እምነታቸውን ለማብራራት ብለው በየበኩላቸው የሚያቀርቡአቸው የመከራከሪያ ሐሳቦች የሚከተሉት ናቸው ።

የምዕራቦቹ ወገኖች ኹለት ባሕርይና ኹለት ፈቃድ የሚሉበትን ምክንያት ሲያብራሩ ምንም እንኳ መለኮትና ትስብእት የተዋሐዱ መኾናቸው ቢታመንበት ይህ ተዋሕዶ ግን ያለ መቀላቀልና ያለ መጠፋፋት እስከኾነ ድረስ ኹለት ባሕርይና ኹለት ፈቃድ እንላለን እንጂ አንድ ባሕርይ ብቻ ልንል አይገባንም ፤ ያለበለዚያማ አውጣኪ ለምን ተወገዘ ብለው ይጠይቃሉ ።

የምሥራቆቹ ወገኖች ደግሞ አውጣኪ የተወገዘው አንድ ባሕርይ ፣ አንድ ፈቃድና አንድ አካል በሚለው እምነት ላይ በመጽናቱ ሳይኾን ትስብእት በመቀላቀልና በመዋጥ ጠፍቶ የመለኮት ባሕርይ ብቻ ቀርቶ



አል በማለቱ ነው ሲሉ ማብራሪያቸውን ይቀጥሉና መለኮትና ትስብእት ተዋሕደዋል ከተባለ ከተዋሕዶ በኋላ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ እንጂ ኹለት ማለት አግባብ አይደለም ። ያለበለዚያማ ንስጥሮስ ለምን ተወገዘ ብለው ይጠይቃሉ ።

የምዕራቦቹ ወገኖች የእኛ ሃይማኖት ዓለም ዐቀፋዊ ነው ለማለት ካቶሊክ ፣ የምሥራቆቹ ወገኖች ደግሞ ትክክለኛው የእኛ ሃይማኖት ነው ለማለት ኦርቶዶክስ የሚባሉትን ስያሜዎች መርጠው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ኹለቱ ወገኖች ሲለያዩ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ንስጥሮሳዊ ብላ አውግዛለች ፤ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የኦርቶዶክስን ቤተ ክርስቲያን የአውጣኪ እምነት ተከታይ ብላ አውግዛለች ። እነዚህም አባባሎች እንደ እውነት ተቈጥረውና ታምኖባቸው በኹለቱም አብያተ ክርስቲያናት የኖሩ ታሪኮች ናቸው ።

የኬልቄዶኑ ጉባኤ ቅንነትና መንፈሳዊነት የጐደለው ከመኾኑ የተነሣ ከዚያ በኋላ አንዳንድ ቅን አስተሳሰብ የነበራቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለችግሩ በውይይትና በመግባባት መፍትሔ ተፈልጎለት የቀድሞው የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲመለስ ሙከራ ቢያደርጉም ሐሳባቸውን የሚደግፍ ሰው ሳይገኝ ቀርቶ ጥላቻ እና በቀል ፣ መናናቅና መነቃቀፍ መቀጠሉ የክርስትናን መሠረታዊ ዐላማ የሚቃረን ድርጊት ነው ። ጌታ በዚህ ዓለም እንደ ሰው ኖሮ እንደ ሰው ጸሎት በጸለየ ጊዜ ስለ ምእመናን ማለት ስለቤተ ክርስቲያን አንድነት መጸለዩን በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፯ ቍ. ፳—፳፫ መመልከት እንችላለን ። ታዲያ ያንጋገር ወይም ያቀራረብ ልዩነት ካልኾነ በቀር ከአንድ ማንቲም ኹለት ገጽታ ያነሰ ልዩነት ባላቸው ኹለት ወገኖች መካከል አንድነት የሚመለስበትን ኹናቴ ከማመቻቸት ይልቅ ብዛትና ኀይል የነበራቸው የክርስቲያን ወገኖች እንደ እነርሱ የሕዝብ ብዛት ባልነበራቸው የክርስቲያን ወገኖች ላይ ባደረጉት ማሳደድ ምክንያት እንዚያ የተሳደዱት ወገኖች ሕይወታቸውን ለማዳን ሲሉ ክርስትና ሃይማኖታቸው ያልኾነ መንግሥታትን እስከ መጋበዝና አገራቸውንም ክርስቲያን ያልኾነ መንግሥታት እንዲገዛት እስከ ማድረግ ተገድደዋል። ይህም በክርስቲያን ሃይማኖት ላይ አንድ የማይረሳ ጥቁር ነጥብ እንደኾነ ይኖራል ።

እንደ እውነቱ ከኾነ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የአውጣኪን እምነት ተከታይ አይደለችም ፤ የካቶሊክም ቤተ ክርስቲያን የንስጥሮ

ስን እምነት ተከታይ አይደለችም ። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የንስጥሮስን ክሕደት እንደምታወግዝ የአውጣኪንም ክሕደት ታወግዛለች ። የካቶሊክም ቤተ ክርስቲያን የአውጣኪን ክሕደት እንደምታወግዝ የንስጥሮስንም ክሕደት ታወግዛለች ። ስለዚህ ኹሉም በቅን አስተሳሰብ ተንግሥቶ ሙከራ ቢያደርግ ኖሮ ጥንታዊው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንድነት በተመለሰ ነበር ።



# ምዕራፍ ሰባት

## ሥነ ፍጥረት

### ሀ. መግቢያ

ልዑል እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፤ እንዲሁም በእነርሱ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ኹሉ ከምንም ወይም ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣበትን ማለት የፈጠረበትን ያፈጣጠር ታሪክ በዝርዝር የሚያስረዳው ክፍል ሥነ ፍጥረት ይባላል ።

የፍጥረቱ ዝርዝር በጣም ብዙ ከመኾኑ የተነሣ ኹሉንም ለመዘርዘር የማይቻል ቢኾንም በአጠቃላይ መልኩ በሚቀርብበት ጊዜ ግን የሚቀጥለውን ይመስላል ።

እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቀን ሰማይን ፤ ምድርንና ብርሃንን ፈጠረ ።

በኹለተኛው ቀን ከበላይና ከበታች ያለውን ውሃ የሚለይ ጠፈርን ፈጠረ ! ጠፈሩንም ሰማይ ብሎ ጠራው ።

በሦስተኛው ቀን ከሰማይ በታች ያለው ውሃ ተከማችቶ ባሕር እንዲባልና ውሃው አንድ ቦታ ሲከማች የተገለጸው ደረቅ ቦታ ደግሞ ምድር እንዲባል ወስኖ ዘርና ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችና ሳሮች በምድር ላይ እንዲበቅሉ አዘዘ ። እንዲሁም ኾነ ።

በአራተኛው ቀን ዕለታትን ፤ ሳምንቶችን ፤ ወሮችንና ዓመቶችን እንዲለዩ ተብሎ ፀሐይ ፤ ጨረቃና ከዋክብት ተፈጠሩ ።

በአምስተኛው ቀን አዕዋፍና የባሕር ውስጥ ተንቀሳቃሾች ፤ እንዲሁም ዓሣዎች ተፈጠሩ ።

በስድስተኛው ቀን አራዊት ፥ እንስሳትና ሰው ተፈጠሩ ።

የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረቶች ኹሉ እግዚአብሔር በቃሉ እንደፈጠራቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ ። አፈጣጠሩም ከምንም ነው እንጂ የሰው ልጆች አንድን ነገር ለመፈልሰፍ አንዱን ንጥረ ነገር በማሻሻል ወይም አንዱን ከሌላው ጋር በማቀላቀል የሚያከናውኑት ዐይነት ሥራ አይደለም ። ስለዚህ ነው ነቢዩ ዳዊት «በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተፈጠሩ ፤ የሰማይ ሠራዊትም ኹሉ በአፉ እስትንፋስ . . . እርሱ ስለተናገረ ኾነዋል ፤ እርሱም ስላዘዘ ጸንተዋልና» ያለው ። (መዝ. ፴፫ ቊ. ፮ እና ፱)

እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን በላከው መልእክቱ ም. ፲፩ ቊ. ፫ ላይ «ዓለም በእግዚአብሔር አንድ ቃል እንደተፈጠረ የምናውቀው በእምነት ነው ፤ የምናየው ነገር ኹሉ ከምንም እንደ ተገኘ በእምነት እናስተውላለን» ብሏል ።

እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሲፈጥር ለእርሱ ምንም የሚያስፈልገው ነገር ኖሮት አይደለም ። ቀደም ተብሎ በእግዚአብሔር ደግነት ርእስ ሥር እንደተገለጸው በመለኮታዊ ክብሩ ብቻውን መኖር ሲችል የደግነት ባሕርዩ ስለገፋፋው ብቻ ኹሉን ፈጠረ ።

ኹሉን የፈጠረበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ክብሩ እንዲገለጽና እንዲመሰገን ነው ። ይህም ለመኾኑ በራእየ ዮሐንስ ም. ፬ ቊ. ፲፩ ላይ «ጌታችንና አምላካችን ሆይ ፥ ኹሉን ነገር ስለፈጠርኸ ፥ ኹሉም ነገር የተፈጠረውና ከዋኒነትን ያገኘው በአንተ ፈቃድ ስለኾነ ክብርና ምስጋና ለመቀበል የተገባህ ነህ» ተብሎ የተጠቀሰውን እናስተውል ።

እንዲሁም ነቢዩ ኢሳይያስ ምድር የተፈጠረችበትን ምክንያት ሲያብራራ «የሰማይ ፈጣሪ እግዚአብሔር ምድርን የፈጠራት መኖሪያ እንድትኾን ነው እንጂ ለከንቱ አይደለም» ብሏል ። (ኢ.ሳ. ም. ፵፭ ቊ. ፲፰)

ለ. የስድስቱ ቀን አፈጣጠር

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ለስድስቱ ቀኖች አፈጣጠር ትርጉም በሚሰጡበት ጊዜ በሦስት ዐይነት አስተያየቶች ይለያያሉ ።



የመጀመሪያዎቹ ወገኖች ፥ «እግዚአብሔር የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረቶች ኹሉ የፈጠረው በአንድ ቀንና በአንድ ጊዜ ኾኖ ሳለ ሙሴ ስድስት ቀኖችን የዘረዘረበት ምክንያት የእግዚአብሔርን ጥበብ ፥ አስደናቂ ዝግጅቱንና ሥነ ሥርዐቱን ለማሳየት ብሎ ነው ይላሉ ። በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፪ ቊ. ፬ ላይ «እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን ባደረገ ቀን በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው» የሚለው አባባል ፍጥረቶች ኹሉ በአንድ ቀን ለመፈጠራቸው ግልጽ ማስረጃ ነው ይላሉ ። እንደ እነርሱ አባባል የቀንና የሌሊት መለያ የኾነው ብርሃን ተፈጠረ የተባለው በአራተኛው ቀን ከኾነ ከዚያ በፊት ለነበሩት ሦስት ቀኖች ምንም ዐይነት የትርጓሜ ችግር የማይኖርባቸው ፍጥረቶች ኹሉ የተፈጠሩት በአንድ ጊዜና በአንድ ቀን የኾነ እንደኾነ ብቻ ነው ።

ኹለተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፍጥረቶችን ንጥረ ነገሮች ከፈጠረ በኋላ በሚቀጥሉት ቀኖች ሥነ ሥርዐትን እንዲይዙ አደረገ የሚሉ ናቸው ። «እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» በሚልበት ጊዜ ለፍጥረቱ ኹሉ ንጥረ ነገሮችን አዘጋጀ ማለቱ ነው ይላሉ ።

የሦስተኛዎቹ ወገኖች ትርጓሜ በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ስድስት ቀኖች በመደበኛ ኻያ አራት ሰዓቶች የተከፋፈሉ ቀኖች ናቸው እንጂ ከዚህ የተለየ ሊኾን አይችልም ይላሉ ። እነርሱም በኦሪት ዘፀአት ም. ፳ ቊ. ፲፩ ላይ «እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን ፥ ባሕርንም ፥ በእነርሱም ውስጥ የሚገኘውን ኹሉ ፈጠረ» የሚለውን በማስረጃነት ያቀርቡታል ።

በኦሪት ዘፍጥረት መጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የተዘረዘረው የፍጥረት ታሪክ የዘመኑ ሳይንስ መርምሮ ከደረሰበት ዕውቀት ጋር የማይመሳሰል ነው በማለት የሚከራከሩ ሰዎች አሉ ። በዚህም ምክንያት የፍጥረትን ታሪክ በጥርጣሬ መልክ ይመለከቱታል ። ዘመናዊው ሳይንስ መርምሮ ሊደርስበት ቻለ የተባለውና በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ አፈጣጠር የተጻፈው ጽሑፍ የተለያዩ የሚመስለን ቃለ እግዚአብሔርን የመረዳት አቅማችን ውሱን በመኾኑ ነው ። የጂኦሎጂ ሊቃውንት መቼም ቢኾን መርምረው አገኙት የተባለው ውጤት በምናልባትነት ነው እንጂ በማረጋገጥ የቀረበ አይደለም ። የምርመራ ውጤታቸውንም

የሚያወዳድሩት በአሁኑ ጊዜ ካለ ኹናቴ ጋር በመኾኑ በግምት እንጂ በማረጋገጥ ሊኾን አይችልም ። ቅዱሳት መጻሕፍትም የተጻፉት በአ ጠቃላይ ለሰው ልጆች የነፍስ ደኅንነት ነው እንጂ በተለየ የጂኦሎጂ ትምህርት ለተማሩ ሰዎች አይደለም ።

ፍጥረቶችን ኹሉ የፈጠረው ለቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችም እስትንፋሱን ያበረከተ እንደመኾኑ የፍጥረቱ ምርምር ውጤትና ቃለ እግዚአብሔር ልዩነት ሊኖራቸው አይችልም ። ምናልባት ልዩነት ለመገኘቱ እርግጠኞች የኾንን ከመሰለን ይህ ሊኾን የሚችለው አንድም እውነትን የመረዳት አቅማችን ውሱን ከመኾኑ የተነሣ ወይም ደግሞ ያ ተገኘ የተባለው የሳይንስ ምርምር ውጤት ለእኛ ትክክል ቢመስለ ንም ምን አልባት ትክክል ላይኾን ስለሚችል ነው ። የምርምሩ ውጤት የተገኘው ውሱን ከኾነ አስተሳሰብ እንደመኾኑና ተቀባዩም ውሱን በመ ኾኑ ውሱንነት ከሌለው ከእግዚአብሔር ከመነጨው ከሥነ ፍጥረት ታሪክ ጋር ሊወዳደር አይችልም ። ይህም በመኾኑ በእኛ በውሱኖቹ ፍጡራን አስተሳሰብ ልዩነት የተፈጠረ ይመስለናል ።

በሳይንስና በሥነ ፍጥረት ታሪክ መካከል አለ የተባለው ታላቁ ችግር ፍጥረቶች የተፈጠሩበት የጊዜ ርዝመት ነው ። እንደ ሳይንሱ አባባል መሬት የፈላ ውሃ የነበረችና በኋላ በርዳ ወደ የብስነት በመለ ወጥ ሕይወት በላይዋ እንዲታይበት የኾነች ነች ። እንደዚህም ለመኾን በሺሕ የሚቈጠሩ ዘመናት ፈጅቶባታል ። በመጀመሪያ በምድር ላይ ፍጥረቶች ከተገኙበት ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ዱካ እስከታየበት ጊዜ ድረስ ያለው ዘመን ረጅም መኾኑን ሳይንስ ሲናገር መጽሐፍ ቅዱስ ግን ፍጥረቶች ኹሉ የተፈጠሩት በስድስት ቀኖች መኾኑን ይገልጻል ። ይህንኑ መሠረት በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስና ሳይንስ የማይታረቅ ቅራኔ አላቸው ይላሉ ።

በሥነ ፍጥረት ታሪክ ውስጥ ቀን የሚለው ቃል ኻያ አራት ሰዓት ብቻ አለመኾኑንና እኛ ልናውቀው ያልቻልነው አንድ የጊዜ ርዝመት መኾኑን ስንረዳ ግን ከላይ የተጠቀሰው ልዩነት እንደማይኖር ግልጽ ነው ። ቀን የሚለው ቃል ኻያ አራት ሰዓት ብቻ አለመኾኑን መጽሐፍ ቅዱስ በየጊዜው አመልክቶታል ። ለምሳሌ «እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርስ ባደረገ ቀን ፣ በተፈጠሩ ጊዜ ፣ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው» ብሏል ። (ዘፍ. ም. ፪ ቍ. ፬)



እዚህ ላይ ቀን የተባለው ቃል ኻያ አራት ሰዓት ብቻ አለመኾኑ ግልጽ ነው ። የሰማይና የምድር ፍጥረቶች ኹሉ የተፈጠሩት በስድስት ቀኖች መኾኑ ከተገለጸ በኋላ አሁን በዚህ አባባል በአንድ ቀን ተፈጠሩ የሚል ይመስላል ። በተመሳሳይ አነጋገር ደግሞ በመዝሙር ፪ ቍ. ፯ ላይ «አንተ ልጄ ነህ ፤ እኔ ዛሬ ወለድኩህ» ብሏል ። እዚህም ዛሬ የተ ባለው ቃል የኻያ አራት ሰዓት ጊዜ ብቻ አለመኾኑን እናስተውል ።

ስለዚህ ቀን የሚለው ቃል አንድ የተወሰነ የጊዜ ርዝመት ማለትም በመቶና በሺሕ ዓመቶች ለሚቈጠሩ ዓመቶች የተሰጠ ቃል ሊኾን ስለ ሚችል በዚህ ረገድ መጽሐፍ ቅዱስና የጂኦሎጂ ትምህርት ልዩነት አይኖራቸውም ማለት ነው ።

## ሐ. የመላእክት አፈጣጠር

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ በሚልበት ጊዜ ሰማይ ከምድር በፊት መጠቀሱ ሰማይና በሰማይ የሚገኙ መናፍ ስት ከምድር በፊት ስለተፈጠሩ ነው ። ይህንን አባባል ሲያጠናክር ነቢዩ ዳዊት «በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተፈጠሩ ! የሰማይ ሠራዊ ትም ኹሉ በአፉ እስትንፋስ» ብሏል ። (መዝ. ፴፫ ቍ. ፮)

መላእክት የተፈጠሩት በመጀመሪያው ቀን መኾኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ቢስማሙበትም በኦሪት ዘፍጥረት ላይ የተዘረዘረው የፍጥረት ታሪክ ግን መላእክት የተፈጠሩበትን ቀን በግልጽ አልተና ገረውም ። ኾኖም በመጽሐፈ ኩፋሌ ም. ፪ ቍ. ፯—፰ እንደተገለጸው መላእክት የተፈጠሩት በመጀመሪያው ቀን ነው ተብሏል ።

መላእክትም መናፍስት ናቸው ። እነዚህም መናፍስት በኹለት ክፍል ይከፈላሉ ። የመጀመሪያዎቹ ክፍሎች ቅዱሳን ፣ ኹለተኛዎቹ ክፍሎች ደግሞ ርኩሳን የሚል ቅጽል ስም አላቸው ።

ስለ ቅዱሳን መናፍስት ወይም መላእክት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጹት ልዩ ልዩ ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፫ ቍ. ፳፬ ላይ አዳም ከኤደን ገነት እንዲ ወጣ ከተደረገ በኋላ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ እንዲጠ ብቅ እግዚአብሔር ኪሩቤልን ማስቀመጡ ተገልጿል ።

በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፲፮ ቍ. ፯ እና ም. ፳፩ ቍ. ፲፯ ላይ የእግዚአብሔር መልአክ ለአጋር የተገለጸላት መኾኑ ተነግሮአል ።

በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፲፱ ቍ. ፩ ላይ ኹለት መላእክት ወደ ሰዶም መጥተው ሎጥ በእንግድነት እንደተቀበላቸው ተገልጾአል ።

በኦሪት ዘኍልቍ ም. ፳፪ ቍ. ፳፪ እና ቍ. ፴፩ ላይ የእግዚአብሔር መልአክ ለበለዓለምና ለአህያው የታያቸው መኾኑ ተገልጾአል ።

የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ለኢያሱ የተገለጸለት መኾኑን በመጽሐፈ ኢያሱ ም. ፭ ቍ. ፲፫ እንመልከት ።

በመጽሐፈ መሳፍንት ም. ፮ ቍ. ፲፩ ላይ የእግዚአብሔር መልአክ ለጌዴዎን የተገለጸለት መኾኑ ተገልጾአል ።

ማኑሄ ለሚባል ሰውና ለሚስቱ የእግዚአብሔር መልአክ የተገለጸላቸው መኾኑን በመጽሐፈ መሳፍንት ም. ፲፫ እንመልከት ።

በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ም. ፲፱ ቍ. ፭—፯የእግዚአብሔር መልአክ ነቢዩን ኤልያስን ያነጋገረው መኾኑ ተገልጾአል ።

በትንቢተ ዳንኤል ም. ፰ ቍ. ፲፮ እና ም. ፱ ቍ. ፳፩ ላይ መልአኩ ገብርኤል ለነቢዩ ለዳንኤል እንደተገለጸለት ተነግሮአል ።

በትንቢተ ዘካርያስ ም. ፩ ቍ. ፱—፲፪ እንደተገለጸው ለነቢዩ የተገለጸለት መልአክ ስለ ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ይቅርታ ይለምን የነበረው ነው ።

ለጦቢትና ለልጁ ለጦብያ መልአኩ ሩፋኤል የተገለጸላቸው መኾኑን በመጽሐፈ ጦቢት ም. ፲፪ ቍ. ፲፭ እንመልከት ።

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር ፰ ቍ. ፭ ላይ መላእክት ከሰው ልጅ የበለጠ ክብር እንዳላቸው ገልጾአል ።

በማቴዎስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፳ ላይ የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም እንደታየ ተገልጿል ።



በሉቃስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፲፩ ላይ የእግዚአብሔር መልአክ ለካህኑ ለዘካርያስ የተገለጸለት መኾኑ ተነግሮአል ።

በሉቃስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፳፮ ላይ መልአኩ ገብርኤል እመቤታችንን ድንግል ማርያምን እንዳበሠራት ተገልጾአል ።

ጌታ በተወለደ ጊዜ የእግዚአብሔር መላእክት ለእረኞች ተገልጸዋል ። (ሉቃ. ም. ፪ ቍ. ፱—፲፫)

ከዲያብሎስ ፈተና በኋላ መላእክት መጥተው ጌታን አገለገሉት ። (ማቴ. ም. ፬ ቍ. ፲፩)

በጌታ መቃብር አጠገብ መላእክት ለሴቶች ተገልጸዋል ። (ማቴ. ም. ፳፰ ቍ. ፪ ፤ ሉቃ. ም. ፳፬ ቍ. ፬ ፤ ዮሐ. ም. ፳ ቍ. ፲፪)

በጌታ ዕርገት ጊዜ ኹለት መላእክት ለሐዋርያት ተገልጸዋል ። (የሐ. ሥ. ም. ፩ ቍ. ፲)

የጌታ መልአክ ጴጥሮስን አስነሣው (የሐ. ሥ. ም. ፲፪ ቍ. ፯)

«የጌታ መልአክ ፊልጶስን ወደ ጋዛ ወደሚወስደው መንገድ ኺድ አለው ።» (የሐ. ሥ. ም. ፰ ቍ. ፳፮)

ቆርኔሌዎስ የእግዚአብሔርን መልአክ በራእይ አየ ። (የሐ. ሥ. ም. ፲ ቍ. ፫)

ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ ም. ፭ ቍ. ፲፩ ላይ ስለ መላእክት ብዛት ሲገልጽ እንዲህ ብሏል «ስመለከትም በዙፋኑና በእንስሶቹ በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ ፤ ብዛታቸውም በብዙ ሺሕና በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠር ነበር ።»

<u>ሊቀ መላእክት</u> (የመላእክት አለቃ)

የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ አብዛኞቹ የትምህርት መለኮት ምሁራን መላእክት አንድ አለቃ እንዳላቸ

ውና እርሱም መልአኩ ሚካኤል መኾኑን በማመን ይስማማሉ ። ለዚህ እምነት መሠረት የኾኑት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው ።

«በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል ።» (ዳን. ም. ፲፪ ቁ. ፩)

«ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ ።» (ዳን. ም. ፲ ቁ. ፲፫)

«የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም ።» (ይሁ. ቁ. ፱)

«በሰማይ ጦርነት ተነሣ ፤ ሚካኤልና የእርሱ መላእክት ከዘንዶው ና ከመላእክቱ ጋር ተዋጉ ።» (ራ. ዮሐ. ም. ፲፪ ቁ. ፯)

ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ የሚለውን ጥቅስ መሠረት በማድረግ ሌሎችም አለቆች አሉ እንጂ ሚካኤል ብቻውን የመላእክት አለቃ አይደለም የሚሉ ወገኖች አሉ ።

ሌሎች እልቅና ያላቸው መላእክት ቢኖሩም የሚካኤል እልቅና በመላእክት ኹሉ ላይ አጠቃላይ ሲኾን የሌሎቹ እልቅና ግን ውሱን ነው ። ለምሳሌ በአንድ የጦር አዛዥ ጄኔራልና በዝቅተኞች የጦር መኰንኖች መካከል ያለውን ልዩነት ይመስላል ። ለምሳሌ መልአኩ ሩፋኤል ለጦቢትና ለጦብያ ራሱን በገለጸላቸው ጊዜ «የቅዱሳንን ጸሎት ከሚያሳርጉ ፤ ወደ ክበረ ፤ ወደ ገነነ ወደ እግዚአብሔር ጌትነትም ከሚያገቡ ከክበሩ ከሰባት አለቆች አንዱ አለቃ እኔ ሩፋኤል ነኝ» ብሏቸዋል ። (ጦቢ. ም. ፲፪ ቁ. ፲፭)

በድርሳነ ሩፋኤል እንደተገለጸው ሰባት ሊቃነ መላእክት ቢኖሩም የበላይ አለቃቸው ግን ሚካኤል መኾኑ ተረጋግጦአል ። በዚሁ ድርሳን እንደተገለጸውም መልአኩ ገብርኤል ከሊቃነ መላእክቱ አንዱ ሲሆን



ደረጃውም ከሚካኤል ቀጥሎ ነው ተብሏል ። መልአኩ ገብርኤል ሊቀ መላእክት ኾኖ ሳለ በትንቢተ ዳንኤል ም. ፲ ቁ. ፲፫ እና ፳፩ ላይ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ሊረዳው የመጣ መኾኑንና ከሚካኤልም በቀር ሌላ የሚረዳው የሌለ መኾኑን የገለጸው ሊቀ መላእክት ሚካኤል ከሌሎቹ መላእክት ኹሉ የበለጠ ሥልጣን ያለው በመኾኑ ነው ።

ሌሎች ወገኖች ደግሞ ይህ የመላእክት አለቃ የተባለው ሚካኤል ወልደ እግዚአብሔር ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይላሉ ።

ይህ አባባል ትክክል አለመኾኑን የምናረጋግጠው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው ።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ወልድ ከሦስቱ መለኮታዊ አካሎች አንዱ ነው እንጂ ከመላእክት እንደ አንዱ ሊቈጠር ስለማይችል ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ የተባለው ሚካኤል እግዚአብሔር ወልድ ነው ለማለት አይቻልም ።

ኹለተኛው ምክንያት አንድ ፍጡር ፈጣሪውን ቅር ከማሰኘቱ በቀር በአንድ ጉዳይ ላይ የንግግር ቃላት በመለዋወጥ የመከራከር መብት አይኖረውም ። ይህ ከኾነ ደግሞ እንዴት ተደርጎ ነው ከዲያብሎስ ጋር ስለ ሙሴ ሥጋ የተከራከረው እግዚአብሔር ወልድ ነው ለማለት የተደፈረው ? እግዚአብሔር ወልድ ደግሞ የእኛን ሥጋ ከለበሰ በኋላ ነው እንጂ ሰው ከመኾኑ በፊት ጌታና አምላክ የሚሉትን የሰው ልጆች ቋንቋዎች አልተጠቀመባቸውም ። ታዲያ ከጌታ ልደት ብዙ ዘመን በፊት የሞተውን ወይም የተሰወረውን የሙሴን ሥጋ በሚመለከት ጌታ ይገሥጽህ ያለው ሚካኤል እግዚአብሔር ወልድ ነው ማለት የወልድን ማንነት አለማወቅ ነው ። እርሱ ራሱ ጌታ ኾኖ ሳለ ማንን ነው ጌታ የሚለው ?

ሦስተኛ ደግሞ ሚካኤልና የእርሱ መላእክት ከዘንዶውና ከመላእክቱ ጋር ተዋጉ በሚልበት ጊዜ እዚህ ላይ ሚካኤል የተባለው እግዚአብሔር ወልድ ነው ብሎ ማመን ፈጣሪን ወደ ፍጡርነት ደረጃ ዝቅ ማድረግ ነው ። ሰይጣንም ሥራው ክፉ ከመኾኑ በቀር በእግዚአብሔር እንደሚያምንና በፍርሃት እንደሚንቀጠቀጥ ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ም. ፪ ቁ. ፲፱ ላይ ገልጾታል ። ጦርነት ደግሞ የሚካኼደው ጎይ

ላቸውን በሚተማመኑ ወገኖች መካከል ነው እንጂ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ሊኾን አይችልም ። ፈጣሪ ከፈለገ በማንኛውም ጊዜ የፈጠረውን ፍጥረት ሊያጠፋው ይችላል ። ይህንንም ለማድረግ ጦርነትም ኾነ የሌላ እርዳታ አያስፈልገውም ። በቃሉ ይኹን ብሎ እንደፈጠረው እንዲሁም በቃሉ ተቃራኒውን ለማድረግ እንደሚችል የጥፋት ውሃንና የሰዶም ጥፋትን ምሳሌነት እናስታውስ ። (ዘፍ. ም. ፩ ፥ ም. ፲፱ ቍ. ፳፫—፳፱)

ስለዚህ የተጠቀሰው ጦርነት በፍጡርና በፍጡር መካከል እንጂ በፈጣሪና በፍጡር መካከል አለመኾኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

ቀጥለን ስለ ርኩሳን መናፍስት ማለት ሰይጣናት ወይም ስለ አጋንንት እንነጋገራለን ።

የሰይጣን አፈጣጠር ከመላእክት እንደ አንዱ የነበረ ቢኾንም በትዕቢት ኀጢአት በመውደቁ ከክብሩ የተዋረደ መኾኑን ሲያመለክት ኢሳይያስ በትንቢቱ እንዲህ ብሎ ገልጾታል ።

«አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ ? አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ ? አንተም . . . . . በልብህ . . . . ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ ፤ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ ፤ ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ ፤ በልዑልም እመሰላለሁ አልኽ ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጉድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ ።» (ኢሳ. ም. ፲፬ ቍ. ፲፪—፲፭

ስለ ርኩሳን መናፍስት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

በእባብ ውስጥ ኾኖ የመጀመሪያይቱን የሰው ልጆች እናት በማሳሳት አዳምና ሔዋን በኀጢአት እንዲወድቁ አድርጓል ። (ዘፍ. ም. ፫ ቍ. ፩—፮)

ሰይጣን በእስራኤል ላይ ተነሥቶ ሕዝቡን ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው ። (፩ኛ ዜ. መ. ም. ፳፩ ቍ. ፩)



በኢዮብ ላይ ብዙ ፈተናና ችግር እንዲደርስበት ምክንያት የኾነው ሰይጣን ነው ። (ኢዮ. ም. ፩ ቍ. ፯)

ሐሰተኞች ነቢያትን በማስነሣት ንጉሥ አክዓብን አሳስቶታል ። (፩ኛ ነገ. ም. ፳፪ ቍ. ፲፱—፳፪)

ታላቁን ካህን ኢያሱን ይከስሰው ዘንድ ሰይጣን በስተቀኙ ቆሞ ነበር ። (ዘካ. ም. ፫ ቍ. ፩)

ሰይጣን ጌታን ለመፈታተን ሞክሮ አቅቶታል ። (ማቴ. ም. ፬ ቍ. ፩ እና ፲፩)

በጥሩ ዘር መኻል እንክርዳዱን የዘራው ጠላት ዲያብሎስ ነው ። (ማቴ. ም. ፲፫ ቍ. ፴፱)

የዘላለም እሳት ለሰይጣንና ለመላእክቱ ተዘጋጅቶላቸዋል ። (ማቴ. ም. ፳፭ ቍ. ፵፩)

ሰይጣን በይሁዳ ልብ ገባ ። (ሉቃ. ም. ፳፪ ቍ. ፫)

ሰይጣን በሐናንያ ልብ ውስጥ ሞላ ። (የሐ. ሥ. ም. ፭ ቍ. ፫)

ስለ ዲያብሎስ ማንነት ጌታ የሰጠውን ማብራሪያ ቀጥለን እንመልከት ። «እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ ፤ ፍላጎታችሁም የአባታችሁን ምኞት መፈጸም ነው ፤ እርሱ ከመጀመሪያ አንሥቶ ነፍስ ገዳይ ነበረ ፤ እውነት በእርሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ፤ እርሱ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ስለኾነ ሐሰት በሚናገርበት ጊዜ ከገዛ ራሱ አውጥቶ ይናገራል ።» (ዮሐ. ም. ፰ ቍ. ፵፬)

በቅዱሳንና በርኩሳን መናፍስት መካከል በሰማይ የተካኼደውን ጦርነት በሚመለከት ሐዋርያው ዮሐንስ ያደረገውን ገለጻ እንመልከት ።

«በሰማይ ጦርነት ተነሣ ፤ ሚካኤልና የእርሱ መላእክት ከዘንዶውና ከመላእክቱ ጋር ተዋጉ ፤ ነገር ግን ዘንዶውና መላእክቱ ተሸነፉ ፤ ከዚያም በኋላ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም ፤ ታላቁም ዘንዶ ወደ ታች ተጣለ ፤ እርሱ ሰዎችን ኹሉ የሚያስተው ዲያብሎስ ወይም ሰይ

ጣን ተብሎ የሚጠራው የቀድሞው እባብ ነው ፤ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ ፤ የእርሱም መላእክት ከእርሱ ጋር አብረው ተጣሉ ።» (ራ. የሐ. ም. ፲፪ ' . ፯—፱)



የሰይጣን አወዳቅ (ኢሳ. ም. ፲፬. ቍ. ፲፪ - ፲፭)

መ. <u>የሰው አፈጣጠር</u>

እግዚአብሔር አምላክ ለሰው አስፈላጊ የኾኑትን ነገሮች ኹሉ ፈጥሮ ካዘጋጀለት በኋላ በመጨረሻ በስድስተኛው ቀን «ሰውን በመልካችንና እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» አለ ። (ዘፍ. ም. ፩ . ፳፮

የሰው አፈጣጠር ከሌላው ፍጥረት ኹሉ የተለየ የኾነው በእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ ግምት ስለተሰጠው ነው ። እግዚአብሔር ፍጥረቱን ኹሉ በፈጠረ ጊዜ ይኹን ብሎ በቃሉ እያዘዘ ከመኾናቸው ማለት ከመፈጠራቸው በቀር ሌላ የተለየ አድራጎትን አላደረገም ። ሰውን ከመፍጠሩ በፊት ግን ከላይ እንደተገለጸው በምን ዐይነት እንደሚፈጥረው መለኮታዊ ዕቅድ ከማውጣቱም በላይ በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፪ ቍ. ፯ ላይ ለሰው ልጅ የማትሞት ነፍስን በመስጠት እንዳከበረው ተነግሮናል ። እንዲሁም እግዚአብሔር አምላክ ከቀድሞ ጀምሮ ለሰው ልጅ የሚበጀውን ነገር ኹሉ በማዘጋጀት ኑሮውን ያመቻችለት የነበረ በመኾኑ ሰው ብቻውን ይኾን ዘንድ መልካም አይደለምና አብሮት የሚኖር ረዳት እንፍጠርለት ብሎ ከጐኑ አጥንት በመውሰድ ሔዋንን ፈጠረለት ። (ዘፍ. ም. ፪ ቍ. ፲፰—፳፭)

አዳምም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ የተባለው በጽድቅ ፣ በቅድስናና በሕያውነት ነበር ። በትእዛዝ አፍራሽነቱ ግን ሕያው ከመኾን ሟች ኾኗል ፤ ጽድቅና ቅድስናውንም በኀጢአተኛነቱ ምክንያት እንዲያጣቸው ተደርጓል ።

«ከገነት ዛፍ ኹሉ ትበላለህ ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» ተብሎ የተሰጠውን ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ አፍርሶ በተገኘ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል የማይለወጥ በመኾኑ የሞቱ ፍርድ ቢጸናበትም በኋላ ዘመን እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ ለብሶ የተቤዠው ከሌላው ፍጥረት ኹሉ ሰውን የበለጠ ስለወደደው ነው ። (ዘፍ. ም. ፪ ቍ. ፲፯)

በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፩ ቍ. ፳፭ ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ኹሉንም ፍጥረት በየዐይነቱ ፈጥሮ መልካም መኾኑን አየ እንጂ ጥቃቅን ሕዋሳት ለከፍተኛ እንስሳት መገኛ እንዲኾኑና ዝንጀሮች ደግሞ ወደ ፊት ተለውጠው ሰው እንዲኾኑ የተፈጠሩ አለመኾናቸውን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

## ምዕራፍ ስምንት

### የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት

ሀ— <u>መ ግ ቢ ያ ፤</u>

በኹሉም ነገር ውሱን የኾነው የሰው ልጅ ውሱንነት የሌለውን እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ባሕርይ ጠንቅቆ ለማወቅ የማይችል መኾኑ ቀደም ተብሎ በምዕራፍ ፩ ተመላልሶ ተገልጾአል ። የሰው ልጅ ስለ እግዚአብሔር ማንነት ለማወቅ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚገልጹለትን ያኽል ካልኾነ በቀር አስቦና ተመራምሮ የሚደርስበት አይደለም ። የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችም ውሱኖች እንደመኾናቸው ለሃይማኖት መመሪያችን እንዲኾነን ሕገ እግዚአብሔርን በሚያዘጋጁበት ጊዜ የእግዚአብሔርን እርዳታ ካላገኙ በቀር ከስሕተት ሊጠበቁ አይችሉም ። ስለዚህም ነው እግዚአብሔር አምላክ እስትንፋሱን ማለት የመንፈሱን መሪነት ለቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች ያበረከተው ። ይህም የእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት በመጀመሪያ ከአዳም እስከ ሙሴ ባሉት ዘመናት በቃል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሲኾን ከሙሴ በኋላ ቃለ እግዚአብሔር በጽሑፍ መመዝገብ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ግን ጸሐፊዎቹን ከስሕተት ለመጠበቅ አል ተለያቸውም ።

ቅዱሳት መጻሕፍት ሲጻፉ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያስፈለገ ገባቸው ምክንያቶች ፤—

አንደኛ/ የሰው ልጅ አስተሳሰብ ሊደርስበት የማይችለውን ለማሳወቅ ፤

ኹለተኛ/ የእግዚአብሔርን ደግነትና ጥበቡን ሊገልጽልን ስለ ፈቀደ ፤



ሦስተኛ/ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ሥርዐቶችን አዘጋጅቶ ሊሰጠን ስለፈቀደ ነው ።

ጸሐፊዎቹም በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመሩ የጻፉአቸው ስለኾኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት የሌለባቸው መኾናቸውን ቤተ ክርስቲያን ታምናለች ፤ ይህንኑም ታስተምራለች ።

የእግዚአብሔር መንፈስ የቅዱሳት መጻሕፍትን ጸሐፊዎች ከሚጠብቅባቸው ዘዴዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

የመጀመሪያው ዘዴ እግዚአብሔር ሙሴን ቃል በቃል እንዳነጋገረው ያለ ነው ።

«ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም እርሱ በቤቴ ኹሉ የታመነ ነው ፤ እኔ አፍ ለአፍ በግልጽ እናገረዋለሁ ፤ በምሳሌም አይደለም ።» (ዘኍ ፡ ም ፡ ፲፪ ቍ. ፯—፰)

ኹለተኛው ዘዴ ለዮሴፍ እንደተሰጠው ያለ በሕልም የሚገለጽ ትንቢት ነው ።

«ዮሴፍም ሕልምን ዐለመ ፤ ለወንድሞቹ ም ነገራቸው ፤ እነርሱም እንደገና አስበልጠው ጠሉት ።» (ዘፍ፡ ም፡ ፴፯ ቍ. ፭)

ሦስተኛው ዘዴ ደግሞ እግዚአብሔር ለነቢያት በራእይ ተገልጾ ወደፊት የሚኾነውን ጉዳይ እንደገለጸላቸው ያለው ነው ።

«በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ በራእይ እገለጽለታለሁ ።» (ዘኍ. ም. ፲፪ ቍ. ፮)

በራእየ ዮሐንስ ም ፩ ቍ. ፲—፲፩ ሐዋርያው ዮሐንስ የተገለጸለትን ራእይ በጽሑፍ እንዲያሰፍረው መታዘዙን እናነባለን ።

አራተኛው ዘዴ እግዚአብሔር እንዲጽፉ የሚፈልጋቸውን ጉዳዮች ሳይጽፉ እንዳይቀሩና የማይፈልጋቸውን ጉዳዮች ደግሞ እንዳይጽፉ አንዱን ጉዳይ የመምረጥና ሌላውን ጉዳይ የመተው ችሎታ እንዲኖራቸው መንፈስ ቅዱስ እንቀሳቅሶ ሕሊናቸውን አብርቶላቸው የጻፉ መኾናቸው ነው ።

የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችን የእግዚአብሔር መንፈስ የሚ ጠብቃቸው መኾኑ ቢታወቅም በራሳቸው አስተሳሰብ ምንም ለማድ ረግ የማይችሉና እንደ ፋብሪካ መሣሪያ የሚመሩ አይደሉም ። እነርሱ ግን ተናጋሪና ሕያው የኾነ ነጻ ፍላጎት ያላቸው በእግዚአብሔር ፈቃድና በፍላጎቱ መሠረት የሚሠሩ መኾናቸውን የሚያውቁ ናቸው ። ይህም ማለት የመንፈስ ቅዱስ መሪነት የጸሐፊውን የአጻጻፍ ዘዴ አይለው ጠውም ማለት ነው ። ስሕተት እንዳያደርጉ ጥበቃ የሚያደርግላቸው መኾኑ ቢታወቅም እያንዳንዱ ጸሐፊ የራሱ በኾነ የአጻጻፍ ዘይቤ ጻፈ እንጂ የኹሉም አጻጻፍ አንድ ዐይነት አይደለም ። ለምሳሌ እንደ ነቢዩ ሙሴ ያለ የምሁር አጻጻፍ ፤ እንደ ኤርምያስና እንደ ዮሐንስ ያለ ርኅራኄና ረቂቅነት ያለው አጻጻፍ ፤ አስተሳሰባቸው በጣም ልቆ የሚገኘው የኢሳይያስና የጳውሎስ አጻጻፍና እንዲሁም ሌሎች የራሳ ቸው የኾነ የአጻጻፍ ዘዴ አላቸው ።

ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር እስትንፋስ አማካይነት ተጽ ፈው ስሕተት የሌለባቸው ለመኾናቸው በማስረጃነት ከሚቀርቡት አርእስት መካከል የትንቢቶች መፈጸም ፤ የተቃዋሚዎች አለማስተ ባበል ፤ የተቃዋሚዎች ምስክርነት ለሥነ ምግባር ተፈላጊ መኾኑ ፤ ተቃዋሚዎቹን ድል ማድረጉና የመሬት ቁፋሮ ቅርስ ይገኙባቸዋል ።

ለ— የትንቢቶች ተፈጻሚነት ፤

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ትንቢቶች ተነግ ረው እነዚያም የተነገሩት ጉዳዮች ጊዜያቸው ሲደርስ ተፈጽመዋል ። ለምሳሌም ያኽል የመድኀኒታችን መለኮታዊ ክብር በሚለው ምዕራፍ ሥር የነቢያት ምስክርት የሚለውን ክፍል ብንመለከት ትንቢቶቹ እን ዴት ተፈጻሚነትን እንዳገኙ ለመገንዘብ እንችላለን ።

ወደፊት የሚኾነውን ኹናቴ አስቀድመው በትክክል ለመናገር የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ የእግዚአብሔር ነቢያት ናቸው እንጂ ማነኛውም የሰው ልጅ ምንም ያኽል ዕውቀት ቢኖረው ወደፊት የሚኾነውን ነገር አስቀድሞ ሊያውቅ አይችልም ። ይህም ኹናቴ ለቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጻፍ ዋና ማስረጃ ነው ። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ «ማነኛውም ትንቢት ከቶ ከሰው ፈቃድ አልመጣም ፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ



ሰዎች ከእግዚአብሔር ተቀብለው የተናገሩት ነው እንጂ ፤» ሲል ያረ ጋገጠው ። (፪ኛ ጴጥ. ም. ፩ ቁ. ፳፩)

ነቢያት አብዛኛውን ጊዜ ወደፊት የሚኾነውን ኹናቴ አስቀድ ድመው ሊናገሩ የሚችሉት አምላክ በራእይ ፤ የገለጸላቸውን ጉዳይ እንደመኾኑ አንዳንድ ጊዜ እንዳረጋገጡት የተገለጸላቸው ራእይ እነርሱ ራሳቸው እንኳ ቢኾኑ እንዳልገባቸው የገለጹበት ጊዜ አለ ።

«አዳመጥሁ ነገር ግን አልገባኝም ። ጌታ ሆይ ፤ ከዚያ በኋላስ ምን ይኾናል? ብዬ ጠየቅሁ ። ዳንኤል ፤ ኺድ እነዚህ ቃላት እስከ መጨረሻው ጊዜ የታሸጉ ምሥጢር ኾነው ይቈያሉ አለኝ ።» (ዳን ም ፲፪ ቁ. ፰—፱)

«እንደገና ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረውን መልአክ በማነጋገር እነዚህ ነገሮች ምን ማለት ናቸው ብዬ ጠየቅሁት ፤ ያነጋግረኝ የነበረ ውም መልአክ መልሶ እነዚህ ነገሮች ምን ማለት እንደኾኑ አታውቅ ምን አለኝ ። እኔም አላውቅም ጌታዬ አልሁት ።» (ዘካ. ም. ፬ ቁ. ፬—፭)

በነዚህም ጥቅሶች መሠረት በራእይ በነቢያት አማካይነት መንፈስ ቅዱስ ለዓለም የሚገልጻቸው የትንቢት ድርጊቶች ለሌላ ቀርቶ ትንቢቱን ለሚናገሩት ለነቢያት ለራሳቸው እንኳ ድብቅ ምሥ ጢር የሚኾኑበት ጊዜ መኖሩን ለመገንዘብ ይቻላል ። ይህም ኹናቴ ቅዱሳት መጻሕፍት በተጻፉበት ጊዜ ምን ያኽል የእግዚአብሔር መ ንፈስ መሪነትና ጥበቃ የነበረ መኾኑን ያመለክተናል ።

ሐ— የተቃዋሚዎች አለማስተባበል ፤

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገሩት የእስራኤል ሕዝብ በቀይ ባሕር መካከል ማለፍ በግብጽ ሕዝብ ላይ የደረሰው መቅሰፍት፥የጌታ ችን የኢየሱስ ክርስቶስ እና የደቀ መዛሙርቱ ታምራት በእውነት የደረሱ ድርጊቶች ባይኾኑ ኖሮ ብዙ ተቃዋሚዎችና አስተባባዮች በተነሡ ነበር ። ለምሳሌ የአይሁድ ሕዝብ ብዙ ምሁራን የነበሩት ቢኾንም ከእነርሱ አንዱ እንኳ የጌታንና የደቀ መዛሙርቱን ታምራት ያስተባበለ የለም ። እንዲያውም ጌታ ከዐረገ በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ በ ጌታ ስም አስደናቂ ታምራትን በማድረጋቸው በአይሁድ ሸንጎ ፊት

ባቀረቡአቸው ጊዜና አይሁድም እንጴጥሮስን የሚወነጅሉበት ምክንያት ባጡ ጊዜም ምን እንዳደረጉ የሚገልጸውን የሚቀጥለውን ጥቅስ እንመልከት ።

ስለዚህ ከሸንጎው ወዲያ ገለል አደረጉአቸውና በቈይታ እንዲህ ሲሉ ተማከሩ ። እንግዲህ በእነዚህ ሰዎች ላይ ምን እናድርግ? ይህ ታላቅ ታምር በእነርሱ እጅ መደረጉ በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ኹሉ ታውቋል ፤ ስለዚህ ልንክደው አንችልም ።» (የሐ ሥ ም. ፬ ቍ ፲፭ –፲፮)

ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ማንም የሃይማኖት ጠላት የኾነ ሰው በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተነገሩትን ጉዳዮች ሊያስተባብል አለመቻሉንና በዚህም የቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛነት መረጋገጡን ነው ።

መ— <u>የተቃዋሚዎች ምስክርነት ፤</u>

ብዙ አረማውያን ፈላስፎችና ታሪክ ጸሐፊዎች እንዲሁም የተልሙድ ጽሑፎች ስለጌታችን የገለጹት አገላለጽ በወንጌል ውስጥ ከተነገሩት አባባሎች ልዩነት የላቸውም ። በጽሑፎቻቸው በይሁዳ አገር አንድ ኢየሱስ የሚባል የዮሴፍ ልጅ የነበረ ሰው ተነሥቶ ብዙ አስገራሚ የኾኑ ታምራትን ይሠራ ነበር » በማለት መስክረዋል ። ይኹን እንጂ በአረማውያኑ ፈላስፎች አስተሳሰብ የጌታ ድንቅ ታምራት የተፈጸሙት በጥንቈላ መልክ እንደ ኾነ ተገልጿአ ።

በተልሙድ ሰዎች ማለት በአሁዳውያን ዘንድ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ም ፬ ቍ ፲፭—፲፮ መሠረት የዐይን ምስክሮች በመኾናቸው ሊክዱ የማይችሉት ጉዳይ ኾኖ ባገኙት ጊዜ በብዔል ዜቡል ማለት በሰይጣን አማካይነት እንደኾነ ተደርጎ ተነግሮአል ።

«ፈሪሳውያን ግን ሰምተው ፡— በብኤልዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልኾነ በቀር አጋንንትን አያወጣም ብለዋል ። » (ማቴ ም ፲፪ ቍ ፳፬)

ሠ— <u>በተቃዋሚዎቹ ላይ ያገኘው ድል ፤</u>

ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት ከሚቀርቡት ማስረጃዎች መካከል ዋነኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው በየጊዜውና በልዩ ልዩ ቦታዎች የሃይማኖት ጠላቶችና አላማኒዎች በኾኑ ወገኖች አማካይነት በየጊዜው የደረሱበትን ችግሮች እንደየአመጣጣቸው ድል ማድረጉ ነው ።



ወደ ዘመነ ኦሪት መለስ ብለን ብንመለከት የእስራኤል ሕዝብ በፈጣሪው ትእዛዝ ጸንቶ በቈየ ጊዜ ኹሉ እንዴት አድርጎ የሃይማኖት ጠላቶቹን ለማሸነፍ እግዚአብሔር ይረዳው እንደነበረ ለመገንዘብ እንችላለን ።

ለምሳሌ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሥረቻ የኾነው የአርባ ዓመቱ የእስራኤል ልጆች ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ፈርዖን የናንተን እግዚአብሔር አላውቅም ፤ ትእዛዙንም አልቀበልም ባለ ጊዜ በግብጽ ሕዝብ ላይ ያን ኹሉ መቅሰፍት ካወረደበት በኋላ ነው ሳይወድ በግድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያከበረው ። (ዘፀ. ም. ፯—፲፪)



«አንተ ሰይፍ ፡ ጦርና ጋሻ ይዘህ ትመጣብኛለህ ፡ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርከው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ ።» (፩ኛ ሳሙ ም. ፲፯ ቍ. ፵፭)

ለአባቶቻቸውና ለእነርሱ በተሰጠው ተስፋ መሠረት ምድረ ከነዓንን ወርሰው በቅዱሱ መጽሐፍ መሠረት እግዚአብሔር የሚመለከበት መንግሥት ለማቋቋም የታቀደውን ዐላማ እሥራ ላይ ለማዋል ይረዳ ዘንድ በእግዚአብሔር እርዳታና በኢያሱ መሪነት የኢያሪኮን ከተማ እንዴት ድል እንዳደረጉ በመጽሐፈ ኢያሱ ም. ፮ ቍ. ፳ እንመልከት ።

በእግዚአብሔር ትእዛዝና በፈጣሪው እርዳታ የተማመነው ወጣቱ ዳዊት ነው ኀይለኛውንና ግዙፉን ባለጕራዴ ጎልያድን በወንጭፍ የጣለው ። (፩ኛ ሳሙ ም. ፲፯ ቁ. ፵፱—፶፩)

ክርስቲያንነት በዓለም መሠራጨት በጀመረ ጊዜ ስንቶች ተሰደው ና ስንቶች ተሠውተው ነው አሁን ወደ አለበት ደረጃ የደረሰው!



በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን መንግሥት በክርስቲያኖች ላይ ይደርሱ ከነበሩት የግፍ ዐይነቶች መካከል ለአንበሳ ተሰጥተው ሲበሚጨቁ ማየት ነበር ።

ብዙዎቹ የሃይማኖት ጠላቶች መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥፋትና አማኞችንም ለመደምሰስ ሞክረው አልኾነላቸውም ። ለምሳሌ የመቄዶንያው ታላቁ እስክንድር ከሞተ በኋላ መንግሥቱን ተከፋፍለው ከወረሱት መካከል አንጥያኮስ አራተኛ (ኤጲፋኖስ) ለተባለው ሰው የሶርያና የፍልስጥኤም ግዛት ደርሶት ነበር ። እርሱም በነገሠባቸው አገሮች ኹሉ ከግሪክ ባህልና ሃይማኖት በቀር ሌላ ባህልና ሃይማኖት እንዳይኖር ለማስገደድ በነበረው ዐላማ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ በማርከስ ለጣዖት መሥዋዕት እንዲቀርብበትና ሕዝቡም የአይሁድን ሃይማኖት ትቶ ጣዖትን እንዲያመልክ ከማስገደዱም በላይ ያገኛቸውን ቅዱሳት



መጻሕፍት ኹሉ እንዲቃጠሉ አድርጎ ነበር ። ይኹን እንጂ ያ እርሱ የነበረው ምድራዊ ኀይል ቃለ እግዚአብሔርንና ምእመናንን ሊደመስስ ባለመቻሉ መቃብያን የተባሉ የአንድ ቤተ ሰብ አባሎችና ጥቂት ተከታዮቻቸው ብቻ የአንጥያኮስን ታላቅ ምድራዊ ኀይል ሊቋቋሙት ችለዋል ። ቃለ እግዚአብሔርም በእርሱ ፍላጎትና በእርሱ ሥራ አልጠፋም ። (፩ኛ መቃ ፡ የመጽሐፍ ቅ. መዝገበ ቃላት ገጽ ፬፻፯)



የነቢዩ ኤልያስ መስዋዕት ተቀባይነት ሲያገኝናት የበዐል ጣዖት ካህናት መሥዋዕት ተቀባይ ሲያጣ (፩ኛ ነገ ም. ፲፰ ቁ. ፲፱—፵፩)

አስተሳሰባችን ውሱን ከመኾኑ የተነሣ ስደትና ጭቈና ቅዱሳት መጻሕፍትንና እምነትን ያዳከም ይመስለናል ። ለምሳሌ አምልኮተ እግዚአብሔርን በመከልከል ለጣዖት እንዲሰገድ ትእዛዝ ያስተላለፉትን ንጉሥ አክዓብንና ሚስቱን ኤልዛቤልን በመፍራት ወደ ምድረ

በዳ ሸሽቶ የነበረው ኤልያስ «እዚህ ምን ታደርጋለህ» ብሎ እግዚአብሔር በጠየቀው ጊዜ በሰጠው መልስ «ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር በጣም ቀናተኛ ኾንኩኝ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋል መሠዊያህን አፍርሰዋል ነቢያትህንም ገድለዋል ፤ ከነቢያት እኔ ብቻ የቀረሁ ስኾን የእኔንም ሕይወት ሊያጠፉ ይፈልጋሉ » ብሎ ቢናገር እግዚአብሔር ደግሞ በሰጠው መልስ «ከዚህ ሕዝብ መካከል ለበዓል ጣዖት ያልተንበረከኩ ለእኔ ሰባት ሺሕ ሰዎች አስቀርቼ አለሁ» ማለቱ ቃለ እግዚአብሔርና እግዚአብሔርን አምላኪዎች መቼም ቢኾን የሚያሸንፉ እንጂ የማይጠፉ መኾናቸውን ያመለክተናል ። (፩ኛ ነገ ም. ፲፱ ቊ. ፲፫—፲፰)

ነቢዩ ኤልያስ ወደ ምድረ በዳ ከመሸሹ በፊት የእርሱን መሥዋዕት በሕዝቡ ፊት እግዚአብሔር ሲቀበለው አራት መቶ ኀምሳ የነበሩት የበዓል ጣዖት ካህናት ለጣዖታቸው ጸልየው መሥዋዕታቸውን ለማሳረግ ባለመቻላቸው ኹሉም እንዲገደሉ አስደርጓል ። የጣዖት ካህናትን በማስገደሉ ኤልዛቤል ስለዛተችበት ነቢዩ ኤልያስ ወደ በረኻ የሸሸው ለሕይወቱ ፈርቶ ነው ። (፩ኛ. ነገ. ም. ፲፰ ቊ. ፲፱—፵ ፥ ም. ፲፱ ቊ. ፩—፪)

በቤተ ክርስቲያን መመሥረቻ ዘመን እስጢፋኖስና ያዕቆብ በሰማዕትነት ተገድለው ሌሎቹ ደግሞ እስራትና ዛቻ ቢደርስባቸውም የወንጌል ትምህርት ችግርን እየተቋቋመ ቀጠለ እንጂ በተሸናፊነት ወደ ኋላ አልቀረም ። ስለዚህም ነው ጌታ የተመሠረተችውን ቤተ ክርስቲያን የሲኦል ኀይል እንኳ አያሸንፋትም ያለው ። (ማቴ. ም. ፲፮ ቊ. ፲፰)

ለጊዜው በዚሁ እናብቃ እንጂ በዚህ ርእስ ሥር ብዙ ምሳሌዎችን ለማቅረብ በተቻለ ነበር ።

ረ— <u>የጥንታዊ ቅርስ ማስረጃነት</u> ፤

እንደ ነነዌ እንደ ባቢሎንና እንደ ግብጽ በመሳሰሉ አገሮች ውስጥ በሚገኙት የጥንት ከተሞች በየጊዜው የሚደረጉት የቍፋሮ ምርምር ውጤቶች የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነተኛነት ያረጋግጣሉ ።



እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. በሙት ባሕር አካባቢ በአንድ እረኛ አማካይነት ምልክት በማግኘት ምርምሮች ከተካኼዱ በኋላ የተገኙት የጥንት የብራና ጽሑፍ ግኝቶች የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት በመመስከር ረገድ ማስረጃነታቸው ከፍ ያለውን ቦታ ይዞ ይገኛል ።

ሰ— <u>ለሥነ ምግባር ተፈላጊነቱ</u> ፤

ግብረገባዊ ኑሮ ለመኖር ለሚፈልግ ሰው ኹሉ መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ጠቃሚ ነው ። ለምሳሌ ጠላትን መውደድ ፤ ራስን መካድ ፤ ከግል ጥቅም ይልቅ ለኅብረተሰብ ደኅንነትና ክብር የበለጠ ግምት መስጠት ፤ ከጊዜያዊው ይልቅ ዘላለማዊውን መምረጥ ፤ መላ ሰውነት ለእግዚአብሔር ሰጥቶ ለትእዛዛቱ ታማኝ መኾን ፤ ማለት የተፈጥሮ ስሜቶችን ሥርዐት ማስያዝ ነው ።

አረማውያን በሃይማኖት ሳይኾን በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ ሕግ ተገፋፍተው የሚፈልጉት እና የሚመኙት ግብረ ገባዊ ሥነ ሥርዐት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሰፊው ተተንትኖ ስለሚገኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚነት ለአማንያን ብቻ ሳይኾን ሃይማኖት ለሌላቸው ወገኖች እንኳ የተረጋገጠ ነው ።

በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስን በሃይማኖታዊ ስሜት ለሚመለከተው ሰው በትምህርቱ እውነተኛ የአምልኮ መንፈስንና የተቀደሰ ኀይልን የሚያገኝበት ሲኾን ለአዘነ ልብ ደግሞ መጽናናትን ይሰጠዋል።

<u>ተከራካሪዎች ያልተቀበሉአቸው መጻሕፍት</u> ፤

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል ከሌሎቹ መጻሕፍት ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ኾነው መቈጠር የለባቸውም ብለው አንዳንድ ተከራካሪዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚያስወጡአቸው መጻሕፍት መጽሐፈ ጦቢት ፤ መጽሐፈ ዮዲት ፤ ጥበበ ሰሎሞን ፤ መጽሐፈ ሢራክ ፤ አንደኛና ኹለተኛ መቃብያን ፤ መጽሐፈ ባሮክ ፤ እንዲሁም ተረፈ ዳንኤልና ተረፈ አስቴር ናቸው ።

ተከራካሪዎቹ እነዚህን መጻሕፍት ላለመቀበላቸው የሚያቀርቡአቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ።

አንደኛ/ የአይሁድ ሕዝብ እነዚህን መጻሕፍት ያልተቀበላቸው በመኾኑና እኛም ብለይ ኪዳንን የተረከብነው ከአይሁድ ሕዝብ ስለኾነ መቀበልም የሚገባን እነርሱ አምነውበት ለእኛ ያስተላለፉልንን ብቻ ነው ።

ኹለተኛ/ ታዋቂዎቻቸው ቢኾኑ ኖሮ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከእነዚህ መጻሕፍት አንዳንድ ጥቅሶችን በጠቀሱ ነበር ፤ ነገር ግን ምንም የተጠቀሰ ጥቅስ የለም ።

ሦስተኛ/ በመጀመሪያዎቹ የመቶ ዓመቶች ዘመናት ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ መጻሕፍት ከሌሎቹ መጻሕፍት ጋር እኩል የኾነ ግምት አልሰጠቻቸውም ።

<u>ለክርክሩ የተሰጠ መልስ ፤</u>

ምንም እንኳ አይሁዶች እነዚያን መጻሕፍት ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር አብረው ያልያዙአቸው ቢኾኑ በዚያ ጊዜና ከዚያ በኋላ መጻሕፍቱ በአይሁድ ምሁራን ዘንድ የታመነባቸውና የተከበሩ መጻሕፍት ነበሩ ።

ከክርስቶስ ልደት አምስት መቶ ሦሳሳ አራት ዓመት በፊት ዕዝራና አብረውት የነበሩት ነቢያት ቅዱሳት መጻሕፍትን ባሰባሰቡ ጊዜ እስከዚያ ድረስ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉትን መጻሕፍት እንጂ በሌላ ቋንቋ የተጻፉትን መጻሕፍት ሳያሰባስቡ ስላለፉአቸው ቀደም ብለው ከዕብራይስጥ በተለየ ቋንቋ ተጽፈው የነበሩት መጻሕፍት ሳይሰባሰቡ ቀርተዋል ። ከዕዝራ በኋላ በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ በዕዝራ ዘመንና ከዕዝራ በፊት እንደነበረው ያለፈውን ነቢይ የሚተካ ሌላ ነቢይ ባለመነሣቱና የቀሩትን መጻሕፍት በማሰባሰብ ረገድ ተረካቢ የሚኾን ነቢይ ባለመገኘቱ፡ ከዕብራይስጥ በተለየ ቋንቋ የተጻፉትና በዕብራይስጥም ቋንቋ ቢኾን ከዕዝራ በኋላ የተጻፉ መጻሕፍት ከሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር አልተሰባሰቡም እንጂ በአይሁድ ሊቃውንት ዘንድ ግን ክብር የተነፈጋቸው መጻሕፍት አልነበሩም ። ለምሳሌ ከክርስቶስ ልደት ኹለት መቶ ስማንያ ኹለት ዓመት በፊት በኹለተኛው በጥሊሞስ ዘመነ መንግሥት መጽሐፍ ቅዱስን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ እንዲተረጉሙ የተደረጉት ሰባ ኹለት የአይሁድ ሊቃውንት የተረጐሙት መጽሐፍ ቅዱስ ተከራካሪዎቹ ያልተቀበሉአቸውን መጻሕፍት ማጠቃለሉ እነዚያ መጻሕፍት በአይሁድ ሊቃውንት ዘንድ ምን ያኽል ግምት ይሰጣቸው የነበረ መኾኑን ያመለክተናል ።



በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ከእነዚህ መጻሕፍት መካከል በማስረጃነት የተጠቀሰ ጥቅስ የለም የሚለው ኹለተኛው ክርክር ደግሞ መጻሕፍቱን ካለማንበብ የተነሣ የቀረበ ክርክር ይመስላል ። በመሠረቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ኹሉ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የግድ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ መጠቀስ አለባቸው የሚል የሃይማኖት ሕግ አልተደነገገም ። እንደዚህማ ቢኾን ኖሮ ከመጽሐፈ አስቴር ከመጽሐፈ መክብብ ከመኃልየ መኃልይ ከመጽሐፈ ሩት ፡ ከመጽሐፈ መሳፍንትና ከአንደኛ ዜና መዋዕል በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ምንም የተጠቀሰ ጥቅስ ባለመኖሩ ተቀባይነት የሌላቸው መጻሕፍት ናቸው በተባሉ ነበር ነገር ግን ማንም እንደዚህ ያለ የለም ።

በሌላ በኩል ደግሞ ተቀባይነት የላቸውም ብለው ተከራካሪዎቹካስወጡአቸው መጻሕፍት መካከል በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት ጥቅሶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ለመኖራቸው የሚከተሉትን የተዛማጅ ጥቅሶች ማስረጃዎች እንመልከት ።

<u>ከመጽሐፈ ጦቢት ፤</u>

«ምጽዋት በመስጠትህ ለችግር ቀን የሚኾን ማከማቸትህ ነው ። (ጦቢ. ም. ፬ ቍ. ፱)

«በዚህ ዓለም ውስጥ ሀብት አታከማቹ ምክንያቱም በዚህ ምድር ላይ ብልና ዝገት ያጠፉዋል ፤ ሌቦችም ሰብረው ይሰርቁታልና ፥

ይልቅስ ለራሳችሁ በሰማይ ሀብት አከማቹ ።» (ማቴ. ም. ፮ ቍ. ፲፱—፳)

«በራስህ ላይ ሊደረግብህ የማትፈልገውን በማንም ላይ አታድርግ ።» (ጦቢ. ም. ፬ ቍ. ፲፭)

«ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ኹሉ እንዲሁ እናንተም አድርጉላቸው ።» (ማቴ. ም. ፯ ቍ. ፲፪)

ከመጽሐፈ ዮዲት ፤

«እግዚአብሔርን ትፈትን ዘንድ አንተ ማነህ?» (ዮዲ. ም. ፰ ቍ. ፲፪)

«እግዚአብሔርን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎአል አለው ።» (ማቴ. ም. ፬ ቍ. ፯)

ከመጽሐፈ መቃብያን ፤

በመጀመሪያው መጽሐፈ መቃብያን ም. ፬ ቍ. ፶፱ ላይ ይሁዳና ወንድሞቹ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ተሰብስበው የወሰኑት በየዓመቱ መከበር ያለበት የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል እስራኤላውያን ኹሉ በጥንቃቄ የሚጠብቁትና የሚያከብሩት ሲኾን ስለዚህ በዓል ጉዳይ ከመጽሐፈ መቃብያን በቀር በብሉይ ኪዳን ውስጥ በየትም በሌላ ቦታ አልተገለጸም ። ይኸው በዓል ነው በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲ ቍ. ፳፪ ላይ የተጠቀሰው ። ይህ ኹናቴ የሚያመለክተው እነዚያ መጻሕፍት በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ የተን ያኽል የተከበሩ እንደነበሩ ነው ።

ከጥበበ ሰሎሞን ፤

በመጽሐፈ ጥበብ ም. ፪ ቍ. ፮—፱ እና ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በመጀመሪያ በላከው በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፲፭ ቍ. ፴፪ ላይ «ነገ ስለምንሞት ዛሬ እንብላ ፤ እንጠጣ» በሚሉት ወገኖች ላይ የተረበው ወቀሳ ተመሳሳይ ነው ።



«ጌታ ሆይ ፤ ተወዳጅ ልጆችህ ይማሩ ዘንድ የሰውን ልጅ የሚመግበው ልዩ ልዩ እኽል ሳይኾን በአንተ ላይ የሚተማመኑትን ኹሉ የሚጠብቀው ቃልህ ነው ።» (ጥበ ም. ፲፮ ቍ. ፳፮)

«ሰው የሚኖረው እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ኹሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይደለም ተብሎ ተጽፎአል አለው ።» (ማቴ. ም. ፬ ቍ. ፬)

ከመጽሐፈ ሲራክ ፤

«አሁን ዕረፍት አገኘኹአለሁና በሀብቴ እደሰታለሁ የሚል ሰው ያለውን ሀብት ኹሉ ለሌሎች ትቶ መቼ እንደሚሞት አያውቅም ።» (ሲራ. ም. ፲፩ ቍ. ፲፰—፲፱)

«ራሴን ብላ ፤ ጠጣ ፤ ደስ ይበልህ እለዋለሁ ። እግዚአብሔር ግን አንተ ሞኝ ዛሬ በዚህች ሌሊት ነፍስህ ካንተ ትወሰዳለች ። ታዲያ ይህ ያከማቸኸው ሀብት ኹሉ ለማን ይኾናል አለው ።» (ሉቃ. ም. ፲፪ ቍ. ፲፱—፳)

«በምትጸልይበት ጊዜ ኀጢአትህ ይቅር ይባልልህ ዘንድ ጐረቤትህ የበደለህን በደል ይቅር በል ።» (ሲራ. ም. ፳፰ ቍ. ፪)

«በሰማይ ያለው አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ እናንተም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ በሰው ላይ የያዛችሁትን ቂም ይቅር በሉ ።» (ማር. ም. ፲፩ ቍ. ፳፭ ፤ ሉቃ ም. ፮ ቍ. ፴፯)

ሦስተኛው ተቃውሞ ደግሞ በመጀመሪያዎቹ የመቶ ዓመቶች ዘመናት እነዚያ የተጠቀሱት መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት አልነበራቸውም የሚለው አባባል ነው ። ይህ አባባል ግን ከእውነት የራቀ ነው ።

መጽሐፈ ዮዲትን ከሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እኩል ግምት ከሰጡት ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል በመጀመሪያው መቶኛ ዓመት የነበረው ሮማዊው ቅዱስ ቀሌምንጦስ እስክንድርያዊው ቅዱስ ቀሌምንጦስ በሦስተኛው መቶ ዓመት ተርቱሊያኖስና

በአምስተኛው መቶ ዓመት ደግሞ ቅዱስ አገስቲኖስ ይገኙባቸዋል ። (የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መለኮት አንደኛ መጽሐፍ በቄስ ሚካኤል ሚና ፡ ገጽ ፲፯) ።

መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ሢራክን ከሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ያልተለየ ግምት ሰጥተውካቀረቡት ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል የእስክንድርያው ቅዱስ ቀሌምንጦስ ፡ ቅዱስ አትናቴ ዎስ ቅዱስ ባስልዮስ ፡ ቅዱስ ኤፍሬምና ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ይገኙባቸዋል ። (ከላይ የተጠቀሰው ገጽ)

መጽሐፈ ጥበብን ካቀረቡት አባቶች መካከል የእስክንድርያው ቅዱስ ቀሌምንጦስ ፡ የቂሳርያው አውሳብዮስ ፡ ባስልዮስና ኤጲፋንዮስ ይገኙባቸዋል ። (ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍና ገጽ) ።

መጽሐፈ ጦቢትን ካቀረቡት አባቶች መካከል የእስክንድርያው ቀሌምንጦስ ፡ ባስልዮስና አገስቲኖስ ይገኙባቸዋል ። (የላይኛው ጥቅስ)

መጽሐፈ ባሮክን ያቀረቡት የቂሳርያው አውሳብዮስ ፡ አትናቴ ዎስ ፡ ባስልዮስ ፡ የኢየሩሳሌሙ ቄርሎስና ዮሐንስ አፈወርቅ ናቸው ። (ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍና ገጽ)

መጽሐፈ መቃብያንን ካቀረቡት መካከል የእስክንድርያው ቀሌ ምንጦስ ፡ አርጌኖስና አገስጢኖስ ይገኙባቸዋል ። (ያው መጽሐፍና ገጽ) ።

ከዚህም ሌላ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በሕግማት ሳምንት በቤተ ክርስቲያን ከሚነበቡት የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች መካከል ተከራካሪዎቹ ያልተቀበሉአቸው መጻሕፍትም ስለሚገኙባቸው በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ከሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ከጥንት ጀምሮ እኩል ተቀባይ ነት ያላቸው ለመኾናቸው በቂ ማስረጃ ነው ።

ሌላው ተጨማሪ ማስረጃ ደግሞ የሚከተለው ምክንያታዊነት ነው ።



ከክርስቶስ ልደት ኹለት መቶ ሰማንያ ኹለት ዓመት በፊት ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ ከተረጎሙት ሰባ ኹለት የአ ይሁድ ሊቃውንት መካከል ስምዖን የተባለ ሰው ነበረበት ። ለዚህም ስምዖን ለተባለ ሰው ትንቢተ ኢሳይያስን እንዲተረጕም ደርሶት ነበር ። መጽሐፉን በሚተረጕምበት ጊዜ በምዕራፍ ፯ ቁ. ፲፬ ላይ «ስለዚህም እግዚአብሔር ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል ፡ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፡ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ወደሚለው የትንቢት ክፍል ሲደርስ በአንድ በኩል ይህ ነገር ሊኾን የሚችል ነው ወይ ብሎ እርሱው ራሱ በመጠራጠር ፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሚተረጕመውን መጽሐፍ የሚመለከቱ አሕዛብ በአይሁድ መጽሐፍ ውስጥ ሊኾን የማይችል ጉዳይ ተጽፎአል ብለው መሳለቂያ ያደርጉታል ብሎ በመፍራት ሳይተረጕመው ሊያልፍ ፈለገ ። በዚህ ጊዜ የስምዖንን ዝንባሌ የተመለከተው መንፈስ ቅዱስ ያንን የትንቢት ክፍል ሳይተረጕመው እንዳያልፍና እርሱ ደግሞ የዚህን ትንቢት ተፈጻ ሚነት ሳያይ እንደ ማይሞት ለስምዖን ነገረው ።

በሉቃስ ወንጌል ም. ፪ ቁ. ፳፭—፴፪ በሚነበበው ቃለ እግ አብሔር ሕፃን ጌታ ኢየሱስን ዐቅፎ ማዳንህን እንዳይ የሰጠኸኝ ተስፋ አሁን ስለተፈጸመ ከእንግዲህ ወዲያስ ባሪያህን አሰናብተው ብሎ የጸለየው ሰው ይህ ከላይ የተጠቀሰው ስምዖን መኾኑን ቤተ ክር ስቲያን የምታምንበትና የምታስተምረው ትምህርት ነው ።

ሰባ ኹለቱ የአይሁድ ሊቃውንት የተረጐሙት ብሉይ ኪዳን በአሁኑ ጊዜ ተከራካሪዎች ያልተቀበሉአቸውንም መጻሕፍት የሚያ ጠቃልል ነው ።

በዚህም መሠረት መተርጐም ያለበት ክፍል ሳይተረጐም እንዳይ ቃለፍ የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከነበረ በዚያን ጊዜ በተከናወነው አጠ ቃላይ የትርጉም ሥራ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ነበር ማለት ነው ። እንዲተረጐም የተፈለገው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሳይተረጐም እን ዳይቃለፍ የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከነበረበት እንዳይተረጐም የሚፈ ልግም ክፍል ቢኖር ኖሮ መንፈስ ቅዱስ እንዳይተረጐም በከለከለ ነበር ። ይህም ማለት ተከራካሪዎች ያልተቀበሉአቸው መጻሕፍት ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ኾነው አብ ረው እንዳይተረጐሙ የመንፈስ ቅዱስ ፍላጎት ቢኾን ኖሮ አብረው እንዳይተረጐሙ በከለከለ ነበር ማለት ነው ።

ስለዚህም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር አብረው መተርጐማቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ መኾን የማይገባቸው መኾናቸውን ስለምታምን ቤተ ክርስቲያን ምንጊዜም ቢኾን ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለይታ አታያቸውም ።

## በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የቀረቡ ተቃውሞዎችና ለተቃውሞዎቹም የተሰጡ መልሶች ፤

በመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት ላይ የተነሡ ተከራካሪዎች ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር እስትንፋስ መሪነት የተጻፉ አለመኾናቸውን የሚያመለክቱ ኹናቴዎች ይታዩባቸዋል በማለት ከሚያቀርቡአቸው የመከራከሪያ ሐሳቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

አንደኛ/ መጻሕፍቱን በጻፉ ጊዜ በራሳቸው አስተሳሰብ እንጂ በእግዚአብሔር እስትንፋስ አለመኾኑን ለማመልከት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በኹለተኛ መልእክቱ ም. ፲፩ ቊ. ፲፯ ላይ «ይህ የምናገረው በራሴ ሞኝነት እንጂ ጌታ ያዘዘኝን አይደለም» ብሎ አረጋግጦአል ይላሉ ።

የጥቅሱን አመጣጥና አካኼድ ትክ ብለን የተመለከትን እንደኾነ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለራሱ በሚጽፍላቸው ጊዜ የትምክሕት አነጋገር ያኾንብኛል ብሎ ስለሰጋ ራሴን በማመስገንበት ጊዜ ራሳችሁን በማዋረድና ራሳችሁን በመካድ ትሑቶች ኹኑ የሚለውን የጌታን ቃል በመቃረኔ ራሴ ያደረግሁት እንጂ እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ አይደለም ከማለቱ በቀር ጽሑፎቼ ኹሉ ያለእግዚአብሔር እስትንፋስ የተጻፉ ናቸው ማለቱ አይደለም ። የተከራካሪዎቹ ሐሳብ ትክክል አለመኾኑን ለመረዳት ለጢሞቴዎስ በላከው ኹለተኛ መልእክቱ ም. ፫ ቊ. ፲፮ ላይ «ቅዱሳት መጻሕፍት ኹሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ ናቸው ።» የሚለውን ማረጋገጫ መመልከት እንችላለን ።

ኹለተኛ/ በአጻጻፋቸው የመወላወልና የመጠራጠር ኹናቴን ስለሚያመለክቱ ይህ ኹናቴ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ላለመጻፋቸው ማስረጃ ነው ይላሉ ። ለዚህም አባባል ማስረጃ ናቸው ተብለው ከሚቀርቡት ጥቅሶች መካከል በሉቃስ ወንጌል ም. ፫ ቊ. ፳፫ ላይ የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸው እንደነበረ የሚለውና በዮሐንስ ወንጌል



ም. ፪ ቊ. ፮ ላይ «እያንዳንዳቸው ኹለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር ።» የሚለው ይገኙበታል ። መጻሕፍቱ የተጻፉት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቢኾን ኖሮ በትክክል ስለተፈጸመው ድርጊት ይነገር ነበር እንጂ የመወላወል ወይም የመጠራጠር ገለጻ ባልተደረገም ነበር በማለት ይከራከራሉ ።

በእነዚህ ጥቅሶች አገላለጽ የመወላወል ኹናቴ የታየ ሳይኾን በአንድ በኩል የሕዝቡ የአነጋገር ልማድ በመኾኑና ቃለ እግዚአብሔር ደግሞ መቅረብ ያለበት በሕዝቡ ልማድና የአነጋገር ዘይቤ መሠረት ነው እንጂ የተለየ ስለማይኾን ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸው እንደነበረ የሚለው አባባል በወንጌል ውስጥ በልዩ ልዩ ጊዜያት እንደተገለጸው በጊዜው የነበሩ ሰዎች ዮሴፍ የጌታችን ወላጅ አባት ይመስላቸው ነበር ። የወንጌላዊው እምነት ግን ከእነርሱ እምነት የተለየ በመኾኑ የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸው እንደነበረ ሲል ገልጾታል ።

ኹለተኛው የመከራከሪያ ጥቅስ ደግሞ ኹለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር ተብለው የተጠቀሱት ጋኖች ጉዳይ ነው ። ጋን ሠራተኛው እያንዳንዱን ጋን በትክክል ስፍሮና ለክቶ የሚሠራበት ዘዴ ስለሌለው የሚሠራቸው ጋኖች ኹሉ አንድ ዐይነት ይዘት ሊኖራቸው አይችልም ። ይህም ብቻ ሳይኾን የተለያዩ ጋኖች በሚሰባሰቡበት ጊዜ እነዚያ የተሰባሰቡት ጋኖች የተሠሩት በተለያዩ ሠሪዎች ስለሚኾን አንዳቸው ከሌላው የተለየ መጠንና ይዘት ያለው ጋን ይሠራል እንጂ ኹሉም እኩል የኾኑ ጋኖችን የመሥሪያ ዘዴ የላቸውም ። በዚህም መሠረት በዚያን ጊዜ ውሃ የተሞላባቸው ጋኖች በኹለትና በሦስት እንስራዎች መካከል ስለነበሩ ኹለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር ተብሏል ።

ሦስተኛ/ በጽሑፋቸው ውስጥ የጥንተ ንጥር አስተሳሰብ አማኞችን እምነት ስለሚጠቅሱ በእግዚአብሔር እስትንፋስ ለመጻፋቸው አጠራጣሪ ነው ይላሉ ። ለዚህ አባባል በመከራከሪያነት የሚቀርበው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ጥቅስ ነው ።

«የሰው ልጆችና የእንሰሳ ዕድል ፈንታ አንድ ነው ፤ ድርሻቸውም ትክክል ነው ፤ አንዱ እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል የኹሉም እስትንፋስ አንድ ነው ፤ ኹሉም ከንቱ ነውና ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም ። ኹሉ ወደ አንድ ቦታ ይኼዳል ኹሉ ከአፈር ነው

ኹሉም ወደ አፈር ይመለሳል ። የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምት ወጣ  እና የእንስሳት ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንድምትወርድ የሚያውቅ ማነው? ያም ዕድልፈንታው ነውና ሰው በሥራው ደስ ከሚለው በቀር ሌላ መልካም ነገር እንደሌለው አየሁ ፤ ከእርሱ በኋላስ የሚኾነውን ያይ ዘንድ የሚያመጣው ማነው?» (መክ ም. ፫ ቍ. ፲፱—፳፪)

በተቃዋሚዎች አስተሳሰብ ይህ ጥቅስ ትንሣኤ ሙታንንና ከሞት በኋላ ያለውን ዘላለማዊ ሕይወት የሚቃረን እንደመኾኑ መጻሕፍቱም በዚሁ አንጻር በእግዚአብሔር እስትንፋስ መሪነት ያልተጻፉ ናቸው ይላሉ ።

በምዕራፍ ፫ ቍ. ፲፱—፳፪ ከተዘረዘረው አባባል በፊት ከቍጥር ፲፮ ጀምረን የተመለከትን እንደኾነ «እኔ ግን አሁን የማስተውለው ከፀሐይ በታች በሕግ ቦታ ወንጀል በጸድቅ ቦታ ኀጢአተኛ አለ ። የሰው ልጆችም እንዲህ የሚያደርጉት እግዚአብሔር ምንነታቸውን ሊያሳያቸውና አንዱ በሌላው ላይ የሚፈጽመው አድራጎት ከአውሬ ያልተሻለ መኾኑን ሊገልጽላቸው እንደኾነ አሰብሁ» የሚል በመኾኑ ከቍጥር ፀሥራ ዘጠኝ እስከ ኻያ ኹለት ድረስ የተዘረዘረው ጥቅስ የሚያመለክተው የሰው ልጆች በሚፈጽሙአቸው ክፉ ድርጊቶች ከ አውሬ የማይሻሉ መኾናቸውን ለመግለጽ ነው እንጂ የመጽሐፉ መክብብ ጸሐፊ በኦሪት ዘፍጥረት ም ፪ ቍ. ፯ መሠረት እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር የሕይወት እስትንፋስ እፍ ያለበት መኾኑንና የእንስሳት ነፍሳቸው ግን ደማቸው መኾኑ በኦሪት ዘሌዋውያን ም. ፲፯ ቍ. ፲—፲፭ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች የማያውቅ ኾኖ አይደለም ። ይህንን የሚ ያውቅ በመኾኑ ነው ሥጋችን ወደ ተፈጠረበት ወደ ምድር እንደሚ መለስና ነፍሳችን ደግሞ ወደሰጠው ወደ እግዚአብሔር እንደሚመለስ በም. ፲፪ ቍ. ፯ ላይ የገለጸው ። ሥጋችንን አፈር ያለበትን ምክን ያት ለመረዳት ወደ ኦሪት ዘፍጥረት ም. ፪ ቍ. ፯ እና ም. ፫ ቍ. ፲፱ የተመለከትን እንደኾነ እግዚአብሔር ሰውን ከምድር አፈር አበጅቶ የሕይወት እስትንፋስ እፍ በማለት ካከበረው በኋላ ኀጢአት በመሥራቱ ሲረግመው አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ የሚል ኾኖ እናገኘ ዋለን ።

ሰው ከሞተ በኋላ በሥጋው ላይ የሚደርሰው መፍረስና መበስበስ ከእንስሳት ሥጋ ጋር ተመሳሳይ ስለኾነ ሊያወዳድረው ችሏል ። በም



ዕራፍ ፫ ቍ. ፳፩ ላይ «የሰው ልጆች ነፍስ ወደላይ እንደምት ወጣ ፤ የእንስሳም ነፍስ ወደታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማን ነው» የሚለው ይህን ኹናቴ የሚያውቁ ብዙ አይደሉም ለማለት ነው ። በተመሳሳይ አነጋገር ነቢዩ ኢሳይያስ የሰማነውን ነገር ማን አመነን? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?» ብሏል ። (ኢሳ. ም. ፶፫ ቍ. ፩)

ሰው ከሞተ በኋላ ዳግመኛ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ እንደቀድሞው የማይኖር መኾኑ ሌላው ከእንስሳት ጋር የተመሳሰለበት ጉዳይ ነው ።

አራተኛ/ በቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ክፍሎች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አባባሎች ስለሚገኙባቸውና መጻሕፍቱ ደግሞ እርስ በርሳ ቸው እስከ ተቃረኑ ድረስ በእግዚአብሔር እስትንፋስ መሪነት ያልተ ጻፉ ለመኾናቸው ማስረጃ ነው ይላሉ ።

እርስ በርሳቸው ይቃረናሉ ተብለው ከሚቀርቡት ጥቅሶች መካ ከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

፩—በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፯ ቍ. ፱ ላይ ኖኅ ፤ በሉቃስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፯ ላይ ደግሞ ዘካርያስና ኤልሣቤጥ ጻድቃን የተባሉ ሲኾኑ በመዝሙር ፲፬ ቍ. ፩ እና ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው በሐዋርያው በጳውሎስ መልእክት ም. ፫ ቍ. ፲፪ ደግሞ ማንም ጻድቅ የሌለ መኾኑ ተገልጾአል ። በዚህም ምክንያት እነዚህ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው ይቃረናሉ ይላሉ ።

ኖኅ ፤ ዘካርያስና ኤልሣቤጥ በጊዜአቸው ከነበሩት ሰዎች ተሽ ለው በመገኘታቸው ጻድቃን ተባሉ እንጂ ከእግዚአብሔር ፍጹምነት ጋር ሲነጻጸር አሁንም ቢኾን ማንም ጻድቅ የለም ። ለምሳሌ ሙሴን የመሰለ ታላቅ ነቢይና የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ በመሪባ ውሃ ጉዳይ መበደሉ ይታወሳል ። (ዘኍ. ም. ፳ ቍ. ፲—፲፫)

በምሳሌነት የሚጠቀሰው ታላቁ ንጉሥ ዳዊት በኦርዮ ላይ ባደረ ሰው ግፍ ምክንያት ተግሣጽና ቅጣት የደረሰበት መኾኑን በኹለተኛው ሳሙኤል ም. ፲፪ ቍ. ፩—፳፫ እንመለከት ። ይኸው ዳዊት ነው «ከልቤ የምወደውን ፈቃዴንም የሚፈጽመውን የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘ ሁ» ተብሎ በእግዚአብሔር የተመሰከረለት ። (የሐ. ሥ. ም. ፲፫ ቍ. ፳፪)

ይህ አባባል የሚያመለክተው ማነኛውም ሰው ቢኾን ጻድቅ የሚል ቅጽል ስም የሚሰጠው በዘመንና በቦታ ከሚገኙ ከሌሎች ሰዎች ጋር በማነጻጸር ነው እንጂ ፍጹም የኾነ ጻድቅ ሰው አለ ለማለት አለመ ኾኑን ነው ።

፮—በትንቢተ ኤርምያስ ም. ፳፫ ቍ. ፳፫ እና ፳፬ «እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም ። ሰው በስውር ቢሸሸግ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር «ተብሎ በነቢዩ ጽሑፍ የተገለጸ ሲኾን በማቴ ዎስ ወንጌል ም. ፲፰ ቍ. ፳ ላይ «ኹለት ወይም ሦስት ኾነው በስሜ በሚሰበሰቡበት ስፍራ እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ » በማለቱ እነዚህ ኹለቱ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ ።

እግዚአብሔር በኹሉም ቦታ የሚገኝ ሙሉ እንጂ በአንድ ቦታ ብቻ የተወሰነ አምላክ አለመኾኑን ከሚገልጹት ልዩ ልዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋ ።

«በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም ፤ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ ።»
(፩ኛ ነገ. ም. ፰ ቍ. ፳፯)

«ከመንፈስህ ወዴት እኼዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር በዚያ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ትይዘኛለች ።» (መዝ ፻፴፱ ቍ. ፯—፲)

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፡— ሰማይ ዙፋኔ ነው ፤ ምድ ርም የእግሬ መረገጫ ናት ፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዐይነት ቤት ነው ? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድር ነው?» (ኢሳ. ም. ፷፮ ቍ. ፩.)

በእነዚህ ከላይ በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት እግዚአብሔር ውሱን ያልኾነና በኹሉም ቦታ የሚገኝ መኾኑ ከተገለጸ «ኹለት ወይም ሦስት ኾነው በስሜ በተሰበሰቡበት ቦታ እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ» የሚለው የጌታ አባባል እንዴት ይተረጐማል?



ቀደም ተብሎ በቀረበው በንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት እግዚአብሔር በተሠራው ቤተ መቅደስ የማይወሰን መኾኑን ከገለጸ በኋላ ነገር ግን በዚህ ቤተ መቅደስ ተሰባስበን የምናደርገው ጸሎት ተቀባይነት ያግኝ ብሎ ለጸለየው ጸሎት እግዚአብሔር መልስ ሲሰጠው የእስራኤል ልጆች ሕግጋቱን የሚጠብቁ እስከኾነ ድረስ ቤተ መቅደሱን እንደ ሚቀድሰውና ስሙም ለዘላለም በዚያ እንደሚኖር ገልጾለታል ። ስለዚህ በእግዚአብሔር ስም በቤተ መቅደስ ሲሰባሰቡ በቅድስናውና በበረ ከቱ በመካከላቸው ይገኛል ማለት ነው ። (፩ኛ ነገ ም. ፱.)

በትንቢተ ኢሳይያስ በተጠቀሰው ጥቅስ ላይ እግዚአብሔር በሰ ማይም ኾነ በምድር ውሱን አለመኾኑን ከገለጸ በኋላ «ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት ፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ ፥ በቃሉም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ» ብሏል ። (ኢሳ. ም. ፷፮ ቍ. ፪)

ይህ ጥቅስ እንደሚያመለክተው ምንም እንኳ እግዚአብሔር በኹሉም ቦታ ሙሉ ቢኾን በማነኛውም ቦታ ለሚገኝ ማኅበር ወይም ግለሰብ በረከት የሚገባው ኾኖ ሲገኝ በጸጋውና በበረከቱ የማይለየው መኾኑን ነው ።

በማቴዎስ ወንጌል የተገለጸው በመካከላቸው መገኘት ኀይሉን ክብሩንና ምሕረቱን ያድላል ማለት ነው እንጂ እርሱ የሌለበት ቦታ አለ ለማለት አለመኾኑን ዐውቀን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ኹለት ተቃውሞዎችና መልሶቻቸው ለዐይነት ያኽል ቀረቡ እንጂ ተከራካሪዎች የሚያቀርቡአቸው ተመሳ ሳይ የመከራከሪያ ሐሳቦች ግን ራሱን ከቻለ አንድ መጽሐፍ የማያንሱ በመኾናቸው ይህን ትምህርት ለሌላ ራሱን ለቻለ መጽሐፍ እንተወው ።

ስለዚህ ከላይ የተገለጹትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ቅዱ ሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ ለመኾና ቸው እርግጠኞች እንኹን ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ቤተ ክርስቲያን

ሀ— መግቢያ ፡

ቤተ ክርስቲያን ሲባል ሦስት ትርጕሞችን ያመለክተናል ።

አንደኛ/ ለአምልኮተ እግዚአብሔር የተሰበሰቡ ምእመናንን የሚያመለክት ለመኾኑ ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ካህናት ምን እንዳላቸው እንመልከት ።

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ኹሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ።» (የሐ. ሥ. ም ፳ ቊ. ፳፰ ም. ፲፩ ቊ. ፳፫ ፤ ፩ኛ ቆሮ. ም. ፲፭ ቊ. ፲፱)

ኹለተኛ/ ካህናት ማለት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ማለት ለመኾኑ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን እንዳለ እንመልከት ።

«እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገር ።» (ማቴ. ም. ፲፰ ቊ. ፲፯)

ሦስተኛ/ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ተሰብስበን ጸሎታችንንና ምስጋናችንን ለእግዚአብሔር የምናቀርብበት ቦታ ማለት ለዚሁ ዐላማ የታቀደው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እግዚአብሔር መባሉ ለማንም እንግዳ ነገር አይደለም ። እንደዚህ ላለው ቦታ ደግሞ እግዚአብሔር የተለየ ግምት የሚሰጠው መኾኑን ለመረዳት ወደመጀመሪያው መጽሐፈ ነገሥት ምዕራፍ ስምንትና ዘጠኝ የተመለከትን እንደኾነ የሚከተለውን ኹናቴ እናገኛለን ። ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሠርቶ በጨረሰ ጊዜ ለእግዚአብሔር ባቀረበው ጸሎት በቤተ መቅደስ



ተገኝቶ የሚደረገው ጸሎት ኹሉ ተሰሚነትን እንዲያገኝ ብሎ ለለመነው ልመና እግዚአብሔር መልስ ሲሰጠው «በፊቴ የጸለይኸውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቼ አለሁ ፤ ለዘላለም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሼአለሁ ፤ ዐይኖቼና ልቤም በዘመኑ ኹሉ በዚያ ይኾናሉ ።» (፩ኛ ነገ. ም ፱ ቊ፣ ፫)



የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሕንጻ ሥራ ተጠናቅቆ በተመረቀበት ቀን የንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት (፩ኛ ነገ ም. ፰ ቊ. ፳፪—፶፫)

ቤተ ክርስቲያን አራት ቅጽል ስሞች አሏት ። እነርሱም ፡ አንዲት ፡ ቅድስት ፡ ዓለም ዐቀፋዊት ፡ ሐዋርያዊት ናቸው ።

## ለ— ለምን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንኼዳለን?

«ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንኺድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ ።» (መዝ ፻፳፪ ቁ. ፩)

በዚህ ጥቅስ መሠረት ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንኼድ የምንደሰት ከኾነ የምንደሰትበት ምክንያት ምን ይኾን?

የሚያውቁንና የምናውቃቸው ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን የምን ኼድ መኾናችንን አይተው እንዲያመሰግኑንና ለሌላም ሰው ነግረው እንዲያስመሰግኑን በመመኘት ይኾን?

ከልጅነታችን ጊዜ ጀምረን ከቤተሰባችን ጋር በየሳምንቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመኼድ ልምድ ስለነበረንና ከልምዱ በቀር ያለሌላ ምክንያት ይኾን?

ወይስ ደግሞ በዜማ የሚፈጸመው ጸሎት እና ምስጋና ጣዕመ ዜማው ስለሚያስደስተንና እኛም አብረን በማዜም ስሜታችንን ለማር ካት ፈልገን ይኾን ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንኼደው?

ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንኼድባቸው ምክንያቶች እነዚህ ከኾኑ ኹሉም ዐላማውን የሳቱ ናቸው ።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ከምንኼድባቸውና በመኼዳችንም ደስ ሊለን ከሚገባባቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

ከተፈጥሮ ደካማነታችን የተነሣ የምንሠራው ኀጢአት የመንፈስ ጭንቀት ስለሚፈጥርብንና ለዚህም መድኀኒቱ የእግዚአብሔር እርዳ ታ ብቻ በመኾኑ ይህንኑ የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት ስንል ወደ ቤተ ክርስቲያን እንኼዳለን ። የመንፈስ ጭንቀት ሲደርስብን ደግሞ ሕይወታችን ሰላም አይኖረውም ። የሰላምን ጌታ ሰላሙን እንዲሰጠን ብንለምነው ፍላጎታችን ሕገወጥ እስካልኾነ ድረስ ልመናችንን ሰምቶ ፍላጎታችንን ኹሉ እንደሚያሟላልን ስለምናምን ወደ ቤተ ክርስቲያን መኼድ ሊያስደስተን ይገባል ።



በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዐይን በሚታይና በጆሮ በሚሰማ የአምልኮተ እግዚአብሔር አገልግሎት አማካይነት በዐይን የማይታይና በእጅ የማይዳሰስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመሳተፍ ስለምንበቃ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንኼድ ደስ ይለናል ።

ኹለት ወይም ሦስት ኹነው በስሜ በሚሰበሰቡበት ቦታ እኔ በመካከላቸው እገኛለሁ ብሎ በማረጋገጡ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ ወደ ቤተ ክርስቲያን መኼድ ሊያስደስተን ይገባል ።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ ኾነው ምእመናን የሚያቀርቡት ጸሎት ተቀባይነትን እንዲያገኝ የአምላክ ፈቃዱ ስለኾነና እኛም በቤተ ክርስቲያን ተገኝተን ለምናቀርበው ጸሎት ኹሉ ከፈጣሪአችን መልስ እንደምናገኝ ስለምናምን ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንኼድ ደስ ይለናል ።

## ሐ— የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዐት ፤

አብዛኛውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ስንል በክርስቶስ የሚያምኑ ወገኖች ለጸሎት የሚሰበሰቡበት ፤ እግዚአብሔር የቀደሰው ቤት ማለ ታችን እንደመኾኑ ፤ እግዚአብሔር በጸሎተኞቹ መካከል ያለ መኾኑን ማወቅ አለብን ። ጌታም በቃሉ ታማኝ ስለኾነ በመካከላችን እንደሚገኝ እርግጠኞች እንኹን ። (ማቴ ም፡ ፲፰ ቁ. ፳)

ኹናቴው እንዲህ ከኾነ እግዚአብሔር ወደቀደሰውና በጸሎተኞ ቹም መካከል ወደሚገኝበት ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንገባው እንዴት ነው? ገብተንስ ምን ማድረግ አለብን?

ለምሳሌ አንድ ሰው አንድን ርእሰ ብሔር ለመገናኘት ምክንያት ያጋጠመው እንደኾነ ይሽቈጠቈጣል ። ከአክብሮቱ ከፍተኛነት የተ ነሣ ሰውነቱ ይሸማቀቃል ። ርእሰ ብሔሩ የሚገኝበትን አካባቢ በጣም ከማክበሩ የተነሣ አካኼዱና አረማመዱ እንኳ ይለወጣል ።

በመጽሐፈ ሢራክ ም፡ ፲ ቁ. ፲፪ ላይ «ዛሬ ንጉሥ ነገ ሬሳ» ተብሎ በተነገረው መሠረት ዛሬ በሕይወቱ በክብሩና በማዕረጉ ላይ ቢኾንም ነገ በሞት ወይም በሽረት ክብር የሚያጣውን ምድራዊ ገዢና እርሱ

የሚገኝበትንም አካባቢ እንደዚያ የምናከብር ከኾነ ዘላለማዊው ፈጣሪ የሚገኝበትንና አምልኮት እንዲቀርብበት የቀደሰውን ቤተ ክርስቲያን ምንኛ ማክበር እንደሚገባን እንገምት ።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ደርሰን የአክብሮት ስግደት ካደረግን በኋላ በቤተ ክርስቲያን ቀስ ብለን ቦታችንን እንይዛለን ። በዚህ ጊዜ እኛ ልንሳተፍበት የሚገባ የኅብረት ጸሎት ከሌለ የግል ጸሎታችንን ልንጸልይ እንችላለን ። የኅብረት ጸሎት በሚካኼድበት ጊዜ ግን በግል ጸሎት መያዝ አግባብ አይደለም ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ከምንኼድባቸው ምክንያቶች ዋነኛው ምክንያት በኅብረት ጸሎት ለመሳተፍ እንደመኾኑ በኅብረት ጸሎት ጊዜ የግል ጸሎት ማካኼድ የለብንም ። ቤተ ክርስቲያንም ጸሎቱንና ምስጋናውን ሕዝብ በሚሰማው ማለት ሕዝብ በሚያውቀው ቋንቋ ስታቀርበው በሕዝብ ዘንድ ሙሉ ተሳትፎ ማግኘት ይቻላል ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለጸሎት ተሰብስበን በምንገኝበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ኅብረት እንጂ አስተሳሰባችንን ወደ ዓለማዊ ጉዳይ ማባከን ተገቢ አይደለም ። ስለ ዓለማዊው ጉዳይ ለማሰብ ከቤተ ክርስቲያን ከወጣን በኋላ በቂ ጊዜ ይኖረናል ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ጠብቆ በተመስጦ ኾኖ በሚጸልይበት እና ምስጋናውን ለእግዚአብሔር በሚያቀርብበት ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኾናቸውን ባለማጤን የግል ጉዳያቸውን ሲወያዩ ይሰማሉ ። ይህን በሚያደርጉ በት ጊዜ በአንድ በኩል አጠገባቸው ኾኖ በተመስጦ የሚጸልየውን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ይበታትኑበታል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለግል ጉዳያቸው ሌላ በቂ ጊዜ ያላቸው ኾኖ ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረጊያ የኾነችውን ያቺን ጥቂት ጊዜ በማባከን አግባብ ባልኾነ መንገድ ለልዑል እግዚአብሔር መስጠት ከሚገባቸው ክብር ላይ ይቀንሳሉ ።

ቤተ ክርስቲያንን የመሰለ እግዚአብሔር የቀደሰውና ክብሩን የሚገልጽበት ቦታ ብቻ ሳይኾን በጊዜያዊነት እንኳ ለአንዳንድ ቅን ታዛዦቹ የሚገለጽባቸው ቦታዎች ክብር የሚገባቸው መኾናቸውን ሲያመለክተን በኦሪት ዘፀአት ም. ፫ ቁ. ፭ ላይ ለሙሴ በመጽሐፈ ኢያሱ ም. ፭ ቁ. ፲፭ ደግሞ ለኢያሱ እነዚያ እነርሱ የቆሙባቸው ቦታዎች የተቀደሱ ስለኾኑ ጫማቸውን እንዲያወልቁ ተነግሮአቸዋል ።



ስለዚህ ፈጣሪ አምላክ የቀደሰውንና አምልኮተ እግዚአብሔር የሚከናወንበትን ቤተ ክርስቲያን ማክበር ያለብን መኾኑን እናስታውል

መ— ማማተብና ትርጉሙ ፤

ወደ ቤተ ክርስቲያን ደርሰን የአክብሮት ስግደት ከማድረጋችን በፊት በዘፈቀደ እጃችንን ሥርዐት በሌለው ኹናቴ ማወዛወዝ ሳይኾን በመኻል ጣታችንና በአመልካች ጣታችን መስቀለኛ በመሥራት ወይም እነዚሁን ኹለት ጣቶች ከአውራ ጣታችን ጋር በማጣመር ማለት በሦስቱ ጣቶቻችን በአብ ስም ስንል ወደላይ ወደ ግንባራችን በወልድ ስም ስንል ወደታች ወደ ደረታችን ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም ስንል ደግሞ ከግራ ወደ ቀኝ ደረታችን እናማትብና አንድ አምላክ አሜን እንለለን ። የምናማትበውም ወደቤተ ክርስቲያን ስንገባ ብቻ አይደለም ። ጸሎት ስንጀምርና ስንጨርስ ፥ ከምግብ በፊት ፡ በጧት ፥ በመኝታ ጊዜ ፡ ከቤት ስንወጣና ወደ ቤትም ስንገባ ፡ እንዲሁም በሥራችን ኹሉ እናማትባለን ።

ከላይ ወደታችና ከግራ ወደ ቀኝ በምናማትብበት ጊዜ በአንድ በኩል የክርስቶስ መስቀል ኀይላችን ፤ ብርታታችንና የነፍሳችን መድኀኒት መኾኑን ለማመልከት ሲኾን በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ወልድ ከአብ ዘንድ ከወደላይ እኛን ለማዳን ወደዚህ ዓለም የመጣ ለመኾኑ እና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከግራ ወደ ቀኝ ማለት ከክፋ ሥራ ወደ ደግ ሥራ ወይም ከሰይጣናዊ ወደ መንፈሳዊ ዝንባሌ የሚመራንና የሚረዳን ለመኾኑ ምሳሌነት አለው ።

ጌታ በመስቀሉ ሞትን ድል ስለነሣና ዲያብሎስም መስቀልን ፈርቶ እንደሚሸሽ ስለምናምን ማነኛውም ከሰይጣን የኾነ አስተሳሰብና ሰይጣናዊ ትርኢት ባጋጠመን ጊዜ ኹሉ የክፉ ነገር ምንጭ የኾነውን ሰይጣንን ለማባረር እናማትባለን ። በምናማትብበትም ጊዜ የክርስቶስን መስቀል ከክፉ ነገር መከላከያ መሣሪያ ማድረጋችን በመኾኑ እንኰራበታለን ፤ እንመካበታለንም ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የጌታን መስቀል በሚመለከት ካቀረባቸው መግለጫዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«የመስቀሉ ዜና በሚጠፉት ሰዎች ዘንድ ሞኝነት ሲኾን ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው ። «(፩ኛ ቆሮ ም. ፩ ቊ. ፲፰)

«በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር በሌላ መመካት ከእኔ ይራቅ ።» (ገላ ም. ፮ ቊ. ፲፬)

«ይከሰንና ይቃወመን የነበረውን የዕዳ ጽሑፍ ደመሰሰ ። በመስቀል ላይ ቸንክሮም ከእኛ ወዲያ አስወገደው ። አለቆችንና ባለሥልጣኖችን በመስቀሉ ድል ነሥቶ ትጥቃቸውን ካስፈታ በኋላ ምርኮኞች ኾነው በይፋ እንዲታዩ አደረጋቸው ።» (ቈላ ም. ፪ ቊ. ፲፬—፲፭)

በነዚህም ማስረጃዎች መሠረት የክርስቶስ መስቀል ኀይልን ፥ ብርታትን ፥ ድኅነትንና በክፉ ኀይል ላይ ደግሞ ድልን እንደሚሰጠን ስለምናምን በየኹናቴው እናማትባለን ።

ሡ— <u>የኅብረት ጸሎት ሥነ ሥርዐት</u> ፤

ጸሎት በአጠቃላይ በኹለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል ። እነርሱም የግልና የኅብረት ጸሎት ናቸው ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከናወነው የኅብረት ጸሎት በዜማ ወይም ያለዜማ ሊኾን ይችላል ። ያለዜማ በሚደረገው የኅብረት ጸሎት ጊዜ ሳይለያዩ በአንድነት መጸለይ እንጂ አንዱ ሲፈጥን ሌላው ዝግ የሚል ከኾነ የጸሎቱ ስሜት ተመስጦነትን ያጣል ። አንዱ ፈጣን ሌላውም ዝግተኛ በሚኾንበት ጊዜ ተገቢ በኾነው ማዕከላዊ ፍጥነት የሚጸልየው ሰው ግራ ይጋባል ።

በዜማ የሚደረገው የኅብረት ጸሎትና ምስጋና የመንፈሳዊነት ተመስጦ ሊፈጥር የሚችለው ኹሉም በኅብረት ሲያዜመው ነው እንጂ በረጅምና በአጭር ዜማ መለያየት ግን የመንፈሳዊነቱን ስሜት ያሰናክላል ። ታዲያ አንዳንዱ ሰው በረጅሙ የሚያዜም ከኾነና ሌላው ደግሞ የሚያሳጥረው ከኾነ የማንን ድምፅ ተከትሎ ማዜም ይሻላል ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ። በተለየ በቅዳሴ ጸሎት ጊዜ ጸሎቱ የሚመራው በቀዳስያኑ እንደመኾኑ የቀዳስያኑን መሪነት ተከትሎ ማዜም ማለት ሲፈጥኑ መፍጠን ሲያረዝሙ ደግሞ ማርዘም የተሻለ መፍትሔ ኾኖ ይመረጣል ።



በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከናወነው አምልኮተ እግዚአብሔር መስገድ ፥ መቆም ፥ ራስን ዝቅ ማድረግ ፥ እርስ በርስ እጅ መነሣሣትና ሌሎችም ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች አሉት እንጂ በጸሎትና በምስጋና ብቻ የተወሰነ አይደለም ። የአምልኮተ እግዚአብሔር እንቅስቃሴ መፈጸም ያለበት በትእዛዙና በሥነ ሥርዐቱ መሠረት ብቻ ነው ።

ረ— <u>ዕጣን መቅደስና መጋረጃ</u> ፤

የጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን ወገኖች ኹሉ በየአብያተ ክርስቲያናቸው ውስጥ መሠዊያ ወይም መቅደስ አለ ፤ ካህናቱ ዕጣን ያጥናሉ መቅደሱን እና ሌሎቹን የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች የሚለይ መጋረጃ አለ ።

በሐዲስ ኪዳን ሥርዐት መቅደስ ፥ ዕጣንና መጋረጃ አይኖሩም ብለው አንዳንድ ተከራካሪዎች ይከራከራሉ ። ለመከራከሪያ ከሚያቀርቡአቸው ሐሳቦችም መካከል ጌታ በተሰቀለበት ቀን የቤተ መቅደስ መጋረጃ እንዲቀደድ ማድረጉ የመቅደስንና (መሰዊያ) የመጋረጃን ሥርዐት ለመሻሩ ማስረጃ ነው ይላሉ ።

በዚያች ቀንና በዚያች ሰዓት የሰማይና የምድር ጌታ ነፍሱን ሲሰጥ የፀሐይ ብርሃን መጋረድ የምድር መናወጥ ፥ የዐለቶች መሰንጠቅና የመቃብሮች መከፈት ከመሳሰሉት ልዩ ልዩ ታምራት መካከል የቤተ መቅደሱ መጋረጃ መቀደድም አንዱ ነው እንጂ ለዚያ ብቻ የተለየ ትርጕም የሚሰጥበት ምክንያት የለም የኦሪቱን የመሥዋዕት ሥነ ሥርዐት በራሱ መሥዋዕትነት ተክቶ የሻረው መኾኑ ባይካድም የመጋረጃው መቀደድ ግን መቅደስንና መጋረጃን የመሻር ምልክት ኾኖ መቈጠር የለበትም ። የቀድሞውና የአሁኑ ልዩነት ግን ቀድሞ የነበረ ቅድስተ ቅዱሳን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሊቀ ካህናቱ ይገባበት የነበረ ሲኾን የቤተ ክርስቲያን መቅደስ ግን ዘወትር የምሥጢረ ቍርባን ሥርዐት የሚከናወንበት ቦታ ነው ። የቀድሞው እንስሳት በመሥዋዕትነት የሚቀርቡበት ሲኾን የአሁኑ ግን በጸሎት አማካይነት ወደ ፍጹም የጌታ ሥጋንትና ደምነት እንደሚለወጥ የምናምነው የኅብስትና የወይን መሥዋዕት የሚቀርብበት ቦታ ነው ። ይህንኑ ሥርዐት ለማከናወን ከዲያቆናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛው የሃይማኖት መሪ ድረስ በመቅደስ ውስጥ መገኘት ይችላሉ እንጂ እንደ ኦሪቱ ሥርዐት በዓመት አንድ ጊዜ ያውም ለአንድ ሰው ብቻ የተወሰነ አይደለም ።

የቤተ ክርስቲያን መጋረጃ ደግሞ መቅደሱንና ሌሎቹን የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች የሚለይ የሥን ሥርዐት አጠባበቅ ነው ።

መሠዊያው ወይም በእኛ አጠራር መቅደሱ ለክርስቲያን ሃይማኖት ሥነ ሥርዐት መኾኑን ሲያመለክት ነቢዩ ኢሳይያስ በዚያን ቀን በግብጽ ምድር መካከል ለእግዚአብሔር መሠዊያ ይኾናል» ብሏል ። (ኢሳ. ም. ፲፱ ቊ. ፲፱)

በቊጥር ፳፩ ላይ ደግሞ በዚያም ቀን እግዚአብሔር በግብጽ የታወቀ ይኾናል ፤ ግብጻውያንም እግዚአብሔርን ያውቃሉ ፤ በመሥዋዕትና በቁርባን ያመልካሉ ፤ ስለት ይሳላሉ ፤ ይፈጽሙትማል» ብሏል ። ግብጾች ምንጊዜም ቢኾን ወደ አይሁድ ሃይማኖት የገቡበት ጊዜ ባለመኖሩና ከክርስትና በፊት አረማውያን የነበሩ በመኾናቸው በትንቢቱ የተነገረው መሠዊያ ፤ መሥዋዕትና ቁርባን የክርስቲያኑ መቅደስና ሥጋ ወደሙ መኾኑን ያመለክተናል ። እንዲሁም በማቴዎስ ወንጌል ም. ፭ ቊ. ፳፫ ላይ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌልን ሥርዐት በመሠረተ ጊዜ «መሥዋዕትህን በመሠዊያው ላይ በምታቀርብበት ጊዜ» የሚለው አባባል መሠዊያ ወይም መቅደስ በሐዲስ ኪዳን ያልተሻረ ለመኾኑ ማስረጃ ነው ።

ዕጣንን በሚመለከት የነቢዩን የሚልክያስን ትንቢት እንመልከት።

«ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይኾናልና በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ ።» (ሚል. ም. ፩ ቊ. ፲፩)

እግዚአብሔር በነቢዩ አንደበት ይህን ትንቢት ያናገረው የአይሁድ ካህናት የሚያቀርቡትን መሥዋዕት የማይቀበል መኾኑን ከገለጸ በኋላ በመኾኑ ዕጣንን ያጥናሉ ተብሎ የተነገረላቸው የክርስትናን ሃይማኖት ለተቀበሉት ልዩ ልዩ የዓለም ሕዝቦች መኾኑን ያመለክተናል ። በሌላ በኩል ደግሞ በኦሪቱ ሕግ የዕጣን ማጠን ልዩ ሥርዐት በጣም ጥብቅ የነበረ በመኾኑና ማጠንም የተፈቀደላቸው ከሌዊ ነገድ ለነበሩት ካህናት ብቻ የነበረ በመኾኑ ከሥርዐቱ ውጪ የሚሠራውን ሰው ኹሉ የሚቀጣው መኾኑን ለመረዳት በኦሪት ዘኁልቊ ም. ፲፮ ቊ. ፴፭—፵፰ እና በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም. ፳፮ እንመልከት ።



በመጀመሪያው ጥቅስ ቆሬና ጓደኞቹ የዕጣንን ሥርዐት በተላለፉ ጊዜ እነርሱና ለእነርሱ የኾነው ኹሉ እሳትና የተከፈተ መሬት እንዲውጣቸው የተደረገ ሲኾን በኹለተኛው ጥቅስ ደግሞ ንጉሥ ዖዝያን ለካህናት በቀር ለእርሱ ያልተፈቀደውን የማጠን አገልግሎት በተዳፈረ ጊዜ በለምጽ በሽታ መቀጣቱ ተገልጾአል ።

በዚህም መሠረት በየቦታው ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ የተባሉት አይሁዶች ሊኾኑ አይችሉም ። ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ በአሕዛብ ዘንድ የተስፋፋው ሃይማኖት ደግሞ ክርስቲያንነት እንጂ የአይሁድ ሃይማኖት አለመኾኑንና ትንቢቱ የተነገረውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚከናወነው የዕጣን ማጠን ሥነ ሥርዐት መኾኑን እንገነዘባለን ።

የዕጣን ጢስም የምስጋናና የጸሎት ተቀባይነት ምሳሌ መኾኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ ።

«አቤቱ ጸሎቴን በፊትህ እንደ ዕጣን ተቀበልልኝ ።» (መዝ ፻፵፩ ቊ. ፩—፪)

«መጽሐፉን በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ኻያ አራቱ ሽማግሌዎች በግንባራቸው ተደፉ ፤ እያንዳንዳቸው በገና ይዘው ነበር ፤ እንዲሁም የቅዱሳን ጸሎት የኾነው ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ሙዳይ ይዘው ነበር ።» (ራዕ ዮሐ. ም ፭ ቊ. ፰)

«የወርቅ ጥና የያዘ ሌላ መልአክ መጣና በመሠዊያው አጠገብ ቆመ ፤ በዙፋኑ ፊት ባለው የወርቅ መሠዊያ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር የሚያቀርበው ብዙ ዕጣን ተሰጠው ። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ ወደ እግዚአብሔር ፊት ወጣ ።» (ራእ ዮሐ. ም. ፰ ቊ. ፫—፭)

ከላይ በተዘረዘሩት ማስረጃዎች መሠረት ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን የኦሪቱ መሥዋዕት ቀርቶ ለኀጢአታችን ስርየትና ለዘላለም ሕይወት እንታደል ዘንድ የሰጠንን ሥጋውንና ደሙን የምናቀርብበት መሠዊያ ቦታ ወይም መቅደስ ሊኖረን እንደሚገባ አምና የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዋንም በምትሠራበት ጊዜ ለመቅደሱ ተገቢውን ቦታ የምትሰጠው እንጂ ችላ የምትለው አይደለችም ። እንዲሁም ለመልካም መዐዛና ለጸሎት ተቀባይነት ዕጣንን ከማጠን አትቦዝንም ።

# ምዕራፍ ዐሥር

## ሰባቱ ሚስጢራተ ቤተ ክርስቲያን

### ሀ. መግቢያ

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ከሰው ልጅ አስተሳሰብ በላይ ስለ ኾኑ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍቱ አማካይነት ሊገልጽልን የሚፈቅደውን ያኽል ብቻ ካልኾነ በቀር በእኛ በውሱኖቹ የማወቅ ችሎታ ሊታወቁ ስለማይችሉ ምሥጢር የሚባል ቅጽል ስም ተሰጥቶ አቸዋል ።

የእግዚአብሔርን ድርጊቶች የማወቅ ችሎታችን ውሱን ቢኾንም ፈጣሪ አምላክ በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት ሊገልጽልን የሚፈቅ ደውን ያኽል ለማወቅ መሞከር አለብን እንጂ ምንም የማናውቅ መኾን የለብንም ። የአሰጣጡ መንገድ ምሥጢር ቢኾንብንም የሚሰጠንን ዐውቀን ስለስጦታው ምስጋናችንን ማቅረብ ይኖርብናል ። ያለበለዚ ያማ የእግዚአብሔርን ደግነትና ፍቅር እንዴት ልንገነዘብ እንችላለን ?

በጥንታውያኑ ቤተ ክርስቲያኖች ኹሉ የታወቁ ፥ የታመነባቸውና የሚሠራባቸው ሰባት የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት አሉ ። ምሥጢራ ትም የተባሉበት ምክንያት በዐይናችን ልናያቸው ፥ በጆሮአችን ልንሰ ማቸውና በእጃችን ልንዳስሳቸው የማንችል ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በእነዚያ በሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት አማካይነት ስለሚሰጠን ነው ።

በጥምቀት አማካይነት ከአዳም ከተወረሰው ኀጢአት ነጻ እንኾ ናለን ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን በመንፈስ ቅዱስ እንወለዳለን ስንል ቅዱሳት መጻሕፍት ስለነገሩን እናምንበታለን እንጂ ከአዳም ኀጢአት እንዴት ነጻ እንደምንኾንና እንደገና እንዴት እንደምንወለድ በዐይናችን ልናይ የማንችላቸው ምሥጢሮች ናቸው ።



በሜሮን ቅባት አማካይነት መንፈስ ቅዱስን የምንሞላ መኾኑን ብናምንም እንዴት እንደምንሞላ ግን በሕዋሳታችን አማካይነት ልን ረዳው የማንችለው ምሥጢር ነው ።

ኅብስቱና ወይኑ ወደጌታ ሥጋና ደም ተለውጠውልን ከእግዚአ ብሔር ጋር ኅብረትንና የኀጢአት ስርየትን እንደምናገኝባቸው አምነን ብንቀበለውም አለዋወጡም ኾነ ለእኛ የሚሰጠን ስጦታ እንዴት እን ደኾነ እኛ ልናውቀው የማንችለው ምሥጢር ነው ።

የማሰርና የመፍታት ሥልጣን በተሰጣቸው ካህናት አማካይነት በንስሓ የኀጢአት ስርየት የምናገኝ መኾኑን ብናምንም የካህናቱም ሥልጣን ኾነ የኀጢአቱ ስርየት በዐይን ሊታይ የማይቻል ምሥጢር ነው ።

በሥርዐተ ተክሊል ጸሎት አማካይነት የባልና የሚስት አንድነት የሚመሠረት መኾኑን ብናምንም የአንድነቱ ጸጋ እንዴት እንደሚሰጥ በዐይናችን ልናይ የማንችለው ምሥጢር ነው ።

በቀንዲሉ ጸሎት አማካይነት ለሥጋ ሕመምተኛ የኀጢአት ስር የት የሚሰጥ መኾኑን ብናምንም ስርየቱ ግን በዐይናችን ልናየው የማን ችለው ምሥጢር ነው ።

ከዚህ ቀጥሎ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዳቸው ይተነተናሉ ።

### ለ. ምሥጢረ ጥምቀት

በተጸለየበት ውሃ ውስጥ በአብ ፥ በወልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሦስት ጊዜ ተነክረን የመውጣቱ ሥነ ሥርዐት ምሥጢረ ጥምቀት ይባላል ።

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ራሱ ቀድሞ በመጠመቅ የጥምቀትን ሥርዐት ከመሠረተ በኋላ ያለ ጥምቀት ክርስቲ ያን ወይም የክርስቶስ ቤተ ሰብ ለመኾን የማይቻል መኾኑን የገለጸው በሚከተለው ኹናቴ ነው ።

«እውነት እውነት እልሃለሁ ፤ ሰው እንደገና ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም ኒቆዲሞስም ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል ? እንደገና ወደ እናቱ ማሕፀን ገብቶ መወለድ ይችላልን ? ሲል ጠየቀ ። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ ! እውነት እውነት እልሃለሁ ፤ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ፤ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ



የጌታ ጥምቀት (ሉቃ ም. ፫ ቍ. ፳፩—፳፪)

ነው ፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው ። ስለዚህ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋችኋል ስላልኩህ አትደነቅ ፤ ነፋስ ወደ ፈለገው አቅጣጫ ይነፍሳል ፤ ድምፁንም ትሰማለህ ፤ ነገር ግን ከየት እንደሚመጣና ወደየትም



እንደሚኼድ አታውቅም ፤ ከመንፈስ የተወለደ ኹሉ እንዲሁ ነው ።» (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፫—፰)

ቀደም ብሎ ለኒቆዲሞስ የሰጠውን ትምህርት ማለት ያለ ጥምቀት ድኅነት አለመኖሩን እንደገና ለደቀ መዛሙርቱ ሲያረጋግጥላቸው እን



የጌታና የኒቆዲሞስ ውይይት (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፫—፭)

ዲህ ብሏል «ወደ ዓለም ኹሉ ኺዱና ወንጌልን ለፍጥረቱ ኹሉ ስበኩ ፤ አምኖ የሚጠመቅ ኹሉ ይድናል ፤ የማያምን ግን ይፈረድበታል ።» (ማር. ም. ፲፮ ቍ. ፲፭—፲፮)

እንዲሁም ከትንሣኤው በኋላ ከዕርገቱ በፊት ደቀ መዛሙርቱን ያዘዛቸው «ሒዱና የዓለምን ሕዝብ ኹሉ አስተምሩ ፤ በአብ ፡ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው» ብሎ ነው ። (ማቴ. ም. ፳፰ ቍ. ፲፱)

የጥምቀቱ ሥነ ሥርዐት የሚከናወነው በጌታ ትእዛዝ መሠረት በአብ ፡ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው እንጂ በወልድ ስም ብቻ አለመኾኑን ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውና የምትሠራ በት ነው ። በሐዋርያት ሥራ ም. ፪ ቍ. ፴፰ ፡ ም. ፰ ቍ. ፲፮ ፡ ም. ፲ ቍ. ፵፰ ፡ ም. ፲፱ ቍ. ፭ እና እንዲሁም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማጥመቅ ተብሎ የተጠቀሰው በአንድ በኩል የኢየሱስ ክርስቶስ ስምና የክርስቲያን ሃይማኖት ገና ሐዋርያት የጀመሩት አዲስ ስምና አዲስ ሃይማኖት በመኾኑ እና የእኛን ሥጋ ለብሶ በሰዎች መካከል ሰው ኾኖ የተገኘውን የእግዚአብሔር ወልድን አምላ ክነት ማመን ደግሞ ለክርስቲያን ሃይማኖት አማራጭ የሌለው ግዴታ መኾኑን ለማመልከት ነው እንጂ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ስም ሳይጠራ ተጠመቁ ለማለት አይደለም ። ስለዚህ ነው ጌታ ቀጥሎ ያለውን ማረጋ ገጫ የሰጠው «በእርሱ የሚያምን ኹሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር ዓለምን እንዲሁ በነጻ በመውደዱ አንድ ልጁን ለሰዎች ኹሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ ። ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም የላከው ሰዎችን ኹሉ በልጁ አማካይነት ሊያ ድናቸው እንጂ ሊፈርድባቸው አይደለም ። በልጁ የሚያምን አይፈረድ በትም ፤ በልጁ የማያምን ግን በአንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል ።» (ዮሐ. ም. ፫ ቍ. ፲፮—፲፰)

እንዲሁም በምዕራፍ ፮ ቍ. ፵፯ ላይ «እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው» ብሎአል ። ስለዚህ በጊዜው የነበረው የሥራ ጥድፊያ እግዚአብሔር ወልድ በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጎ የእርሱ ፍጥረት ከኾነው ከሰው በመወለድ ሰው ኾኖ ሕማምን ተቀብሎ በመሞትና ሞትንም ድል ነሥቶ በመነሣት ለሰው ልጅ ቤዛ ከኾነ በኋላ ወደሰማያዊ ዙፋኑ የወጣ መኾኑን ማስተማርና ይህም እግ ዚአብሔር ወልድ ሕዝቡ ኢየሱስ በሚል ስም የሚያውቀው እንጂ ሌላ አለመኾኑን ማሳወቅ ስለነበረ ይህንኑ ትምህርት ለማጠናከር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ተባለ እንጂ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ስም ሳይጠራ መጠመቅ ማለት አይደለም ። ጌታ ራሱ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ብሎ ያዘዛቸው እንደመኾኑ ደቀ መዛ



ሙርቱ የጌታቸውን ትእዛዝ እንደሚያከብሩ እርግጠኞች እንኾን ፤ ምክ ንያቱም «ብትወዱኝስ ትእዛዜን ፤ ጠብቁ» ብሎአቸዋልና ። (ዮሐ. ም. ፲፬ ቍ. ፲፭)

በሌላ በኩል ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ የተባለው ከዮሐንስ ጥምቀት የተለየ መኾኑን ለመግለጽ ታስቦ ነው ። ዮሐንስ መጥምቁም የርሱ ጥምቀት ከጌታ ጥምቀት የተለየ መኾኑን ሲያመለክት «እኔስ ለንስሐ በውሃ አጠምቃችኋለሁ ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማ ይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ የበረታ ነው ፤ እርሱ በመ ንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል» ብሏል ። (ማቴ. ም. ፫ ቍ. ፲፩) እንዲሁም በኤፌሶን የተገኙ አማኞች የዮሐንስን ጥምቀት ተጠምቀው እንደነበረና በኋላ ግን በጌታ አምነው እንዲጠመቁ የተደረገ መኾኑን በሐዋርያት ሥራ ም. ፲፱ ቍ. ፩—፯ ማንበብ እንችላለን ። የጌታ ጥም ቀትና የዮሐንስ ጥምቀት ልዩነትም የጌታ ጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ ኾኖ የኀጢአት ስርየትንና ልጅነት ን የሚያድል ሲኾን የዮሐንስ ጥም ቀት ግን ለንስሓ በውሃ ነው ።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ የሚሉትን ጥቅሶች በማሰባሰብ እነዚያን በየተራ ማስረጃ አድርገው እያቀረቡ መጠመቅ ያለብን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው እንጂ በሥላሴ ስም አይደለም በማለት የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ።

ጌታ ደቀ መዛሙርቱን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ በግልጽ ያዘዛቸው ከመኾኑም በላይ ምንም እንኳ እርሱ ጥምቀት የማያስፈልገው ቢኾን የእኛን ሥጋ መልበሱን ለማመልከትና ለእኛ አርአያ ለመኾን በተጠመቀ ጊዜ የሥሉስ ቅዱስ በሥነ ሥርዐቱ ላይ መከሠት የጥምቀት ሥርዐት ምን ዐይነት መኾን እንዳለበት የሚያ ሳይ ምልክት ነው ። አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ ሲያ ሰማ ፡ ወልድ በመጠመቅ ላይ ኾኖ ፡ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል መውረዱ በሉቃስ ወንጌል ም. ፫ ቍ. ፳፩—፳፪ ላይ ተገልጾ አለ ። ይህም ክሥተት የሚያመለክተው መጠመቅ ያለብን በሥላሴ ስም መኾኑን ነው ።

ስለ አብ ፡ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሦስት አካልነት ቀደም ተብሎ በምሥጢረ ሥላሴ ምዕራፍ ውስጥ የተተነተነ ስለኾነ እንደገና በዚህ ጉዳይ ብዙ መናገር አስፈላጊ ባይኾንም በኢየሱስ ክርስቶስ

ስም ብቻ መጠመቅ የሚያምኑት ወገኖች ቅዱሳት መጻሕፍትን ትክ ብለው ቢያስተውሉ እንዳቸው ከሌላው የማይበልጥ ወይም የማያንስ ሦስት የመለኮት አካሎች መኖራቸውን ለማስተዋል በቻሉ ነበር ። ምንም እንኳ አብ ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ማለት የተለመደ አነጋገር ቢኾን አንዳቸው ከሌላው ተቀዳሚነትና ተከታይነት የሌላቸው መኾናቸውን ለማመልከት ሲሉ ቅዱሳት መጻሕፍት የስማቸውን ቅደም ተከተል ለዋውጠው የሚያቀርቡበት ጊዜ አለ ። ለምሳሌ በሉቃስ ወንጌል ም. ቍ. ፩ ፴፭ ላይ መልአኩ ገብርኤል ለእመቤታችን ጥያቄ መልስ ሲሰጥ «መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል ፤ የእግዚአብሔር ኀይልም ይጸልልሻል ፤ ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» ብሏታል ። እንዲሁም የወልድን ስም በማስቀደም ሐዋርያው ጳውሎስ በሚከተለው ኹናቴ አቅርቦታል «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፥ የእግዚአብሔርም ፍቅር ፥ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከኹላችሁም ጋር ይኹን ።» (፪ኛ ቆሮ. ም. ፲፫ ቍ. ፲፬)

<u>በጥምቀት አማካይነት የምንታደላቸው ጸጋዎች</u>

አንደኛ/ <u>ከጥንቱ የአዳም ኀጢአት ነጻ መኾንና ቅድስና</u>

«ታዲያ አሁን ለምን ትዘገያለህ ? ተነሥና የእርሱን ስም በመጥራት ተጠመቅ ፥ ከኀጢአትህም ታጠብ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፳፪ ቍ. ፲፮)

«ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ለመተባበር በተጠመቅን ጊዜ የሞቱም ተካፋዮች ለመኾን መጠመቃችንን አታውቁምን ? በጥምቀት ከእርሱ ጋር በተቀበርን ጊዜ የእርሱ ሞት ተካፋዮች ኾነናል ። ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደተነሣ እኛም በአዲስ ሕይወት እንኖራለን ።» (ሮሜ. ም. ፮ ቍ. ፫—፬)

«እንግዲህ በእናንተም ኀጢአት ሥልጣን እንደሌለውና በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለእግዚአብሔር በሕይወት እንደምትኖሩ አስቡ ።» (ቍ. ፲፩)

«ከእናንተም አንዳንዶቻችሁ እንደ እነዚህ ነበራችሁ ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ከኀጢአት ታጥባችኋል ፤ ተቀድሳችኋል ፤ ጸድቃችኋልም ።» (፩ኛ ቆሮ. ም. ፮ ቍ. ፲፩)



ኹለተኛ/ <u>ከኀጢአት ይቅር መባል</u>

«ኀጢአታችሁ ይቅር እንዲባልላችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፪ ቍ. ፴፰)

ሦስተኛ/ <u>ዳግመኛ መወለድ ማለት የመንፈስ ልደት</u>

«እኛ በሠራነው የጽድቅ ሥራ ሳይኾን በምሕረቱ አዳነን ። ያዳነንም በአዲስ ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በተገኘው መታደስ ነው ።» (ቲቶ ም. ፫ ቍ. ፭)

«ዳግመኛ የተወለዳችሁት ሕያው በኾነውና ለዘላለም ጸንቶ በሚኖረው በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ ከሚጠፋ ዘር አይደለም ።» (፩ኛ ጴጥ. ም. ፩ ቍ. ፳፫)

አራተኛ/ <u>የእግዚአብሔር ልጅ መኾን</u>

«ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ባላችሁ ኅብረት በእምነት አማካይነት ኹላችሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ። ምክንያቱም በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ የኾናችሁ ኹሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል ።» (ገላ. ም. ፫ ቍ. ፳፮—፳፯)

ጥምቀትም ወጣት ፥ ሽማግሌ ፥ ወይም ሕፃን ሳይለይ የክርስቲያን ቤተሰብ ኹሉ ሊታደለው የሚገባ ጸጋ ነው እንጂ ዕድሜ የሚለይበት ስጦታ አይደለም ። ቀደም ተብሎ በተጠቀሰው ጥቅስ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል የተባለው ዐዋቂ ሰው ካልኾነ በቀር ከመጠመቅ በፊት እምነት መቅደም አለበት ለማለት አይደለም ።

ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ዓለም በላከ ጊዜ እነርሱ በሚሰብኩት የክርስትና ሃይማኖት የሚያምን እንደሚያድንና የማያምን ግን እንደሚፈረድበት ለማመልከት ሲኾን ጥምቀት እዚህ ላይ የተጠቀሰው የክርስቶስ ቤተሰብ ለመኾን በቅድሚያ ጥምቀት አስፈላጊ በመኾኑ ነው እንጂ ለሌላ አይደለም ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፪ ቍ. ፲፩—፲፪ ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ መኾኑን ሲገልጽ «ከእርሱም ጋር አንድ በመኾን ተገርዛችኋል ፤ ይህም መገረዛችሁ ኀ ጢአተኛውን ሥጋ ለማስወገድ በክርስቶስ የተደረገ ነው እንጂ ሰው ሠራሽ መገረዝ አይደለም ፤ ምክንያቱም በተጠመቃችሁ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ተቀበ ራችሁ ብሏል ። እንግዲህ ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ከኾነ በወላጆች ኀላፊነት ብቻ ሕፃናት ይገረዙ እንደነበረ በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፲፯ ቍ. ፲፪ እና ፳፫ ፤ ም. ፳፩ ቍ. ፬ ፤ ዘፀ. ም. ፬ ቍ. ፳፬—፳፮ እንመልከት ።

በመጀመሪያ ቤት ክርስቲያን ስትመሠረት የሕፃናት ጥምቀት አከራካሪ አልነበረም ። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ ም. ፲ ቍ. ፵፰ ላይ ቆርኔሌዎስ ከነቤተሰቡ መጠመቁ ፤ በም. ፲፮ ቍ. ፲፭ ላይ ሊድያ ከነ ቤተሰብዋ መጠመቅዋና በመጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፩ ቍ. ፲፮ ላይ የእስጢፋኖስ ቤተ ሰብ የተጠመቀ መኾኑ ስለተገለጸ ሐዋርያት ያጠምቁ የነበሩት ቤተሰ ብን በመላ እንጂ ሕፃናትን አስቀርተው እንዳልነበረ ያመለክተናል ። በእነዚህም ምክንያቶች የሕፃናት ጥምቀት አከራካሪ መኾን የለበትም ።

ሐ. ምሥጢረ ሜሮን

ከጥምቀት በኋላ በእምነታችን እንድንጸና የሚረዳንን መንፈስ ቅዱስ በተቀደሰ ቅባት አማካይነት የምንቀበልበት ሥርዓት ምሥጢረ ሜሮን ይባላል ። የዚህም ምሥጢር ሥርዐት መፈጸም ያለበት ወዲያው የምሥጢረ ጥምቀት ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ ነው ። ይህም ለመኾኑ ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ይገኛሉ ። ለምሳሌ በበዐለ ኀምሳ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልዩ ልዩ ቋንቋዎች መናገር በጀመሩ ጊዜ ይሰሙ የነበሩት ሰዎች ተገርመው ምን እናድርግ ብለው ቢጠይቁ ቅዱስ ጴጥሮስ በሰጣቸው መልስ «ንስሐ ግቡ ፤ ኀጢ ኣታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» ብሎአቸዋል ። (የሐ. ሥ. ም. ፪ ቍ. ፴፰) ይህም ማለት መጀመሪያ ተጠመቁ ከዚያ ቀጥሎ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ይሰጣችኋል ማለት ነው ። እንዲሁም «በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ስደዱላቸው ። እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው ፤ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበር ። በዚያን ጊዜ



እጃቸውን ጫኑባቸው ፤ መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፰ ቍ. ፲፬—፲፯)

«ይህንንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው ።» (የሐ. ሥ. ም. ፲፱ ቍ. ፭—፯)

በሐዋርያት ዘመን አብዛኛውን ጊዜ አዲስ አማኝ ከጥምቀት በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል የሚደረገው በእጅ መጫን አማካይነት የነበረ ቢኾንም በመቀባትም መንፈስ ቅዱስን መቀበል የነበረ ለመ ኾኑ ማስረጃዎች ይገኛሉ ።

«እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብታችኋል ።» (፩ኛ ዮሐ. ም. ፪ ቍ. ፳)

«በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው ፤ ደግሞም ያተመን ፤ የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው ።» (፪ኛ ቆሮ. ም. ፩ ቍ. ፳፩—፳፪)

በእጅ በመጫን ፈንታ በሜሮን መቀባት እንዲተካ ያስፈለገበት ምክንያት ወደ ክርስትና የሚመለሱት አማኞች እየበዙ በመኼዳቸውና በእጅ መጫን አማካይነት የሚደረገው ሥነ ሥርዐት ደግሞ የበለጠ ጊዜ የሚወስድ ኾኖ በመገኘቱ ነው ።

ቤተ ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ መቀበያ ሜሮንን የመረጠችው ያለምክንያት አይደለም ። አንድ ነቢይ ፤ ወይም አንድ ሐዋርያ ፤ ወይም ደግሞ ሌላ አንድ የእግዚአብሔር ሰው የወሰነው ውሳኔ ሳይኾን ልዑል እግዚአብሔር ራሱ አሠራሩንና አጠቃቀሙን በመዘርዘር ለነቢዩ ሙሴ የገለጸለት መኾኑን በኦሪት ዘፀአት ም. ፴ ቍ. ፳፪—፴፰ እንመልከት ። በዚህም በተቀደሰ ቅባት የሚቀቡት ካህናትና የቅድስት ቅዱሳኑ ዕቃ ዎች የእግዚአብሔር መንፈስ አድሮባቸው የተቀደሱ ይኾኑ እንደነበረ ተገልጾአል ።

በእጅ በመጫን ወይም በቅብዐ ቅዱስ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ የሚደረገው ከጥምቀት በኋላ መኾን እንዳለበት ቤተ ክርስ

ቲያን የምታስተምረውና የምትሠራበት ነው ። ይኹን እንጂ በሐዋርያት ሥራ ም. ፲ ቊ. ፵፬ ላይ እንደተገለጸው በቆርኔሌዎስና አብረውት በነበሩት ኹሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ የወረደው ከመጠመቃቸው በፊት ኾኖ እናገኘዋለን ። ይህ ሊኾን የቻለው የጥምቀትንና የሜሮንን ሥርዐት ቅደም ተከተል መለዋወጥ ይቻላል ለማለት ሳይኾን የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ እምነትና ዝንባሌ አሁንም ቢኾን የክርስትናው ዕድል ሊሰጣቸታው የሚገባው ለአይሁድ ወገኖች ብቻ መኾን አለበት የሚል ስለነበረና የእርሱን አስተሳሰብ መለወጥ የአምላክ ፍላጎት ስለነበረ ነው ። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ ሊያሳይ የፈለገው አይሁድ ስላልኾኑ ብቻ ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ እንዳልኾኑ የሚገምታቸው ሰዎች ከጥምቀት በፊት እንኳ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እስከመቀበል ድረስ ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ መኾናቸውን ነው ። ይህም በመኾኑ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ቀድሞ የነበረውን አስተሳሰብ በመለወጥ «እነዚህ ሰዎች እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል ፤ ታዲያ በውሃ እንዳይጠመቁ ማን ይከለክላቸዋል» ብሎ እንዲጠመቁ አዘዘ ። (የሐ. ሥ. ም. ፲ ቊ. ፵፯—፵፰)

ቀደም ተብሎ እንደተዘረዘረው በጥምቀት አዲስ ልደት እርሱም የመንፈስ ልደት የምንወለድ መኾኑ ተገልጿአል ። የሰው ልጅ በሥጋዊ ልደት ተወልዶ በዚህ ዓለም ውስጥ ሲገኝ ሕይወቱን ለማቈየት ፡ ለማሳደግና ሰውነቱን ለማጠንከር ምግብ ፣ ውሃና አየር እንደሚያስፈልገው እንዲሁም ከመንፈሳዊ ልደቱ ማለት ከጥምቀቱ በኋላ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ጥንካሬና ለክርስትያናዊ ዕድገቱ ቅብዐ ሜሮን በዚያም አማካይነት እምነትና በጎ ተግባሩን የሚያሳድግለትና የሚጠብቀው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያስፈልገዋል ።

«እናንተስ መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበላችሁና የእርሱም ቅባት በእናንተ ስለሚኖር ሌላ አስተማሪ አያስፈልጋችሁም ። መንፈስ ቅዱስ እውነትን እንጂ ሐሰትን ስለማይናገር እርሱ ራሱ ኹሉንም ያስተምራችኋል ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በገለጸላችሁ መሠረት በእርሱ ኑሩ ።» (፩ኛ የሐ. ም. ፪ ቊ. ፳፯)

## መ. ምሥጢረ ቊርባን

በቅዳሴ ጸሎትና በቃሉ አማካይነት ኅብስትና ወይኑ ወደ ጌታ ሥጋነትና ደምነት ተለውጠው ሥጋውን በልተንና ደሙን ጠጥተን



ለኀጢአታችን ስርየትና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረን ለማድረግ የሚከናወነው ሥነ ሥርዐት ምሥጢረ ቊርባን ወይም ምሥጢረ ሥጋ ወደሙ ይባላል ። የተቀደሰ ኅብረት ብለው የሰየሙትም ወገኖች አሉ ። ይህም አባባል በሥጋውና በደሙ አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን ኅብረት የሚያመለክት ነው ።

ምሥጢረ ቊርባንን የመሠረተው ጌታ ራሱ በስቅለቱ ዋዜማ ማለት በዕለተ ሐሙስ ነው ።

«ራት ሲበሉም ኢየሱስ ዳቦ አንሥቶ የምስጋና ጸሎት አደረገ ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ እንካችሁ ብሎ ፡ ይህ ሥጋዬ ነው ብሎ ሰጣቸው ። ጽዋውንም አንሥቶ የምስጋና ጸሎት ካደረገ በኋላ እንዲህ ሲል ሰጣቸው ። ኹላችሁም ከዚህ ጽዋ ጠጡ ፤ ይህ ስለብዙዎች ለኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው ።» (ማቴ. ም. ፳፮ ቊ. ፳፮—፳፰ ፤ ማር. ም. ፲፬ ቊ. ፳፪—፳፬ ፤ ሉቃ. ም. ፳፪ ቊ. ፲፱—፳)

የምሥጢረ ቊርባንን መሠረት ከመጣሉ በፊት ስለዚህ ጉዳይ ጌታ ቀደም ብሎ ለደቀ መዛሙርቱና ለሌሎችም ዘርዝሮ አስረድቶ አለ ።

«ከሰማይ የወረደው ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ። ከዚህ እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል ። ለዓለም ሕይወት እንዲኾን እኔ የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው ። በዚህ ጊዜ አይሁዳውያን ይህ ሰው ሥጋውን እንድንበላ እንዴት ሊሰጠን ይችላል ? በማለት እርስ በርሳቸው ተከራከሩ ። ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ ፤ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ሕይወት የላችሁም ። ሥጋዬን የሚበላና ደሜንም የሚጠጣ ኹሉ የዘላለም ሕይወት አለው ፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ። ምክንያቱም ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ፤ ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ ኹሉ በእኔ ይኖራል ፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ ። ሕያው አብ እንደላከኝና እኔም በእርሱ ሕያው እንደኾንኩ እንዲሁም ሥጋዬን የሚበላ ኹሉ በእኔ ሕያው ይኾናል ።» (ዮሐ. ም. ፮ ቊ. ፶፩—፶፯)

በዚህ አነጋገሩ ብዙዎች ስለተሰናከሉ ማለትም ማመን ስላቃታቸው ከዚያን ጊዜ ጀምረው ወደኋላ ያፈገፈጉና ዳግመኛ ከእርሱ ጋር ያልኼዱ መኾናቸውን በዚሁ ምዕራፍ በቊጥር ፷፮ ላይ ለመረዳት እን

ችላለን ። አንዳንዶቹ ቢያጉረመርሙና ሌሎች ደግሞ ከተከታይነታቸው ቢቀሩም መድኀኒታችን ስለ ሥጋውና ስለደሙ ያደርግ የነበረውን ገለጻ ምንም ሳይለውጥ አነጋገሩን በዚያው ዐይነት መቀጠሉ የምሥጢረ ቁርባንን ትክክለኛነት ሊያረጋግጥልን ስለፈለገ ነው ።

ኅብስቱና ወይኑ ወደጌታ ሥጋነትና ደምነት መለወጥ የማይኾን ጉዳይ ነው ብለው የጥርጣሬ ሐሳብ የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ ። የኅብስቱና የወይኑ በምሥጢራዊ ኹናቴ ወደ ጌታ ሥጋና ደም መለወጥ ሊያስገርመን አይገባም ። ከተፈጥሮ ኹናቴአቸው በእግዚአብሔር ኀይል የተለወጡ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል ። ለምሳሌ የሎጥ ሚስት




የምሥጢረቍርባን ምሥረታ (ማቴ. ም. ፳፮ ቍ. ፳፮—፳፱)

ወደጨው ድንጋይነት አልተለወጠችምን ? የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ አገር ከመውጣቱ በፊት ከተደረጉት ታምራት መካከል የአሮን በትር ወደ እባብነት ፥ የወንዙ ውሃ ደግሞ ወደ ደምነት አልተለወጡምን ?



እንዲሁም በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ ውሃ ወደ ወይንነት አልተለወጠምን? (ዘፍ. ም. ፲፱ ቍ. ፲፯ እና ፳፮ ፥ ዘፀ. ም. ፯ ቍ. ፲ እና ፳ ፥ ዮሐ. ም. ፪ ቍ. ፩—፲፩)



ጌታ ውሃውን ወደ ወይንነት የለወጠበት ታምር (ዮሐ. ም. ፪ ቍ. ፩—፲፩)

እነዚህንና ሌሎችንም ተመሳሳይ ኹኔታዎችን ከተፈጥሮ ጠባያቸው ወደሌላ ንጥረ ነገር የለወጠውና ለመለወጥም ከሃሊ የኾነው አምላክ በማይመረመረው ምሥጢሩ ኅብስትንና ወይንን ወደጌታ ሥጋነትና ደምነት እንደሚለውጣቸው ሳንጠራጠር ማመን አለብን ።

በምሥጢረ ቍርባን ላይ ከሚቀርቡ ተቃውሞዎች መካከል ቀጥለው የተዘረዘሩት የሚገኙባቸው ሲኾኑ ለእነርሱም መልሶች ተሰጥተውባቸዋል ።

የመጀመሪያው ተቃውሞ ጌታ ኅብስቱን ሥጋዬ ነው ፤ ወይኑን ደግሞ ደሜ ነው ማለቱ «እኔ የበጎች በር ነኝ ፤ እኔ መንገድ ነኝ» እንዲ

ሁም ሄሮድስን ቀበሮ ፡ ዮሐንስን ኤልያስ እንዳለው ያለ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ ቃል በቃል መወሰድ ያለበት አይደለም ይላሉ ። (ማቴ. ም. ፲፮ ቍ. ፲፬ ፡ ሉቃ. ም. ፲፫ ቍ. ፴፪ ፡ ዮሐ. ም. ፲ ቍ. ፱ ፡ ም. ፲፬ ቍ. ፯)

በምሳሌነት የሚነገር ቃልና ዋናው ሐሳብ ኹለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው እንጂ ዋናውን ሐሳብ ምሳሌ አድርጎ መናገር የተለመደ አይደለም ።



የሎጥ ሚስት ወደ ጨው ድንጋይነት መለወጥ (ዘፍ. ም. ፲፱ ቍ. ፲፯—፳፮)

ጌታ በምሳሌ በሚናገርበት ጊዜ ሰዎች የሚሰናከሉ ኾነው ካገኛቸው ወይም ያልገባቸው ኾነው ሲያገኛቸው እንደገና ተንትኖ ገለጻ በማድረግ ያስረዳቸው ነበር እንጂ እንዲሁ አይተዋቸውም ነበር ። ለምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲፮ ቍ. ፮ ላይ እንደተገለጸው ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ እንዲጠነቀቁ በነገራቸው ጊዜ ከነበሩበት ሰፈር ወደሌላ ሲኼዱ ምግብ ይዘው ባለመኼዳ



ቸው ይህን ማስጠንቀቂያ እንደነገራቸው ስለገመቱ የልባቸውን ሐሳብ ዐውቆ ከስሕተት እንዲታረሙ ገለጸላቸው ።

እንደሚታወቀው እርሾ ማለት አዲስን ሊጥ ለማቡካት የሚረዳ አሮጌ ሊጥ ነው ። እንግዲህ የጌታ አባባል በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን አሮጌ ልማድ ተጠምዳችሁ አዲሱን የወንጌል ትምህርት ወደኋላ አትጐትቱ ማለቱ እንጂ እነርሱ እንዳሰቡት አለመኾኑን ገለጸላቸው ። እን



የአሮን በትር ወደ እባብነት መለወጥ (ዘፀ ም. ፯ ቍ. ፲—፲፫)

ዲሁም ደግሞ ጌታ ለኒቆዲሞስ ዳግመኛ ስለመወለድ ገለጻ ያደርግለት በነበረ ጊዜ ገለጻውን በምሳሌ ከጀመረ በኋላ ኒቆዲሞስ ግን ምሳሌው ስላልገባው ወደ ቀጥተኛ አገባል የተዛወረ መኾኑን በዮሐንስ ወንጌል ም. ፫ ቍ. ፩—፳፩ እንመልከት ።

ስለ ሥጋውና ስለደሙ እውነተኛ ምግብነትና መጠጥነት ጉዳይ ይናገር በነበረ ጊዜ ግን ከሰሚዎቹ አንዳንዶቹ ቢያጉረመርሙና ሌሎች ደግሞ ከተከታይነታቸው ወደኋላ ቢያፈገፍጉም ንግግሩን በበለጠ በማረጋገጥ ገለጻውን ከመቀጠሉ በቀር ምንም አባባሉን አልለወጠም ።

ስለሥጋውና ስለደሙ ያደርግ የነበረው ገለጻ ምሳሌያዊ አነጋገር ቢኾን ኖሮ ለሰሚዎቹ በሚገባ አነጋገር አባባሉን በለወጠ ነበር ። ነገር ግን ምንም ያኽል የሰሚዎቹ እምነት ሊቀበለው ያልቻለ መኾኑ ቢገለጥ አነጋገሩን አለመለወጡ የምሥጢረ ቊርባንን ትክክለኛነትና የእርሱም ገለጻ ቀጥተኛ እንጂ ምሳሌያዊ አነጋገር አለመኾኑን ሊገልጽልን ስለ ፈለገ ነው ።

ሄሮድስን ቀበሮ ማለቱ እንደ ቀበሮ ተንኰለኛ ነው ማለቱ ነው ። ዮሐንስን ኤልያስ ያለበት የመጀመሪያው ምክንያት በትንቢተ ሚልክያስ ም. ፬ ቊ. ፭ ላይ በነቢዩ በኤልያስ ስም ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ትንቢት ተነግሮ የነበረ በመኾኑ ሲኾን ኹለተኛው ምክንያት ለእውነት በመመስከርና ኀጢአተኛውን በመገሠጽ ረገድ ማንኛውንም ምድራዊ ባለሥልጣን ባለመፍራት ኤልያስና ዮሐንስ ይመሳሰሉ ስለነበረ ነው ። እኔ መንገድ ነኝ ያለውንና እኔ በር ነኝ ያለውን ግን ራሱ ተርጕሞታል ። እኔ በር ነኝ ካለ በኋላ በእኔ በበሩ በኩል የሚገባ ይድናል ብሏል ። (ዮሐ. ም. ፲ ቊ. ፱) እኔ መንገድ ነኝ ካለ በኋላ ደግሞ በእኔ በኩል ማለት በእኔ መንገድነት በኩል ካላለፈ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ብሏል ። (ዮሐ. ም. ፲፬ ቊ. ፮) ኅብስትና ወይኑ ግን ቤተ ክርስቲያን እንደምታስተምረው በመለወጥ ነው እንጂ ምሳሌያዊ አነጋገር አይደለም ።

ሌላው ተቃውሞ ደግሞ በሉቃስ ወንጌል ም. ፳፪ ቊ. ፲፱ ላይ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት ስላለ ይህ ኅብስትና ወይን ለጌታ መታሰቢያ ነው እንጂ የተለወጠ ሥጋና ደም አይደለም ይላሉ ።

መታሰቢያ መኾኑ ግን ወደጌታ ሥጋነትና ደምነት መለወጥን አይከለክልም ። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ስለሰው ልጆች የሚደረጉድንቅ ድርጊቶች እንዲታወሱ ይፈልጋል ። ለምሳሌ በኦሪት ዘፀአት ም. ፲፮ ቊ. ፴፪ ላይ መና በመባል የታወቀ ውንና ከሰማይ ይወርድ የነበረውን ምግብ በመታሰቢያነት ለወደፊት ትውልድ እንዲያስቀምጥ እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው ይላል ። እንዲሁም ታምራት የተሠሩባት የአሮን በትር ለመታሰቢያነት እንድትቀመጥ የተደረገ መኾኑን በኦሪት ዘኍልቍ. ም. ፲፯ ቊ. ፲ እንመልከት ። እነዚህ በመታሰቢያነት ይቀመጡ የተባሉት መና እና የአሮን በትር በምሳሌነት ሳይኾን እነርሱው ራሳቸው ናቸው ። በዚሁም ዐይነት ለመታሰቢያዬ አድርጉት ያለው ሥጋውን በበላንና ደሙን በጠጣን ጊዜ ኹሉ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያለውን ፍቅር ፤ ለእኛ ሲል የፍጡሩን ሥጋ መልበሱን ሕማማትን



መቀበሉንና መሞቱን ማስታወስ አለብን ለማለት ነው እንጂ ኅብስቱና ወይኑ ወደጌታ ሥጋነትና ደምነት አይለወጡም ለማለት አይደለም ። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፲፩ ቊ. ፳፮—፳፯ እንደገለጸው «ይህንን ዳቦ በምትበሉበት ጊዜና ይህንን ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ኹሉ ጌታ ኢየሱስ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ» ብሏል ። ስለዚህ በእነዚህ መግለጫዎች መሠረት ቤተ ክርስቲያን የኅብስቱና የወይኑ ወደጌታ ሥጋነትና ደምነት መለወጥ ታምናለች ! ይህንኑም ታስተምራለች ።

ማንም ሰው ከኀጢአት ነጻ አለመኾኑን በመገንዘብ የቤተ ክርስቲያን አባል የኾነ ሰው ኹሉ ኀጢአቱን ለካህን ተናዝዞ መቊረብ አለበት እንጂ ለሥጋውና ለደሙ ብቁ አይደለሁም በሚል ምክንያት ሕይወቱን በሙሉ ለኀጢአታችን ይቅርታና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ፤ እንዲሁም ዘላለማዊ ሕይወትን ከሚያድለን ከጌታ ሥጋና ደም ርቆ መኖር የለበትም ።

መንፈሳዊ ሰውነታችን በየጊዜው መውደቅና መነሣት የሚፈራረቁበት መኾኑን ማሳወቅ የካህናትና የሰባክያን ፈንታ ነውና ንስሐ ገብቶ ሥጋውንና ደሙን መቀበል እንዳለበት ክርስቲያን ለኾነ ሰው ኹሉ ማስተማር አለባቸው እንጂ ኀላፊነታቸውን መርሳት የለባቸውም። በዚህ ጉዳይ ላይ መድኀኒታችን መላልሶ ያረጋገጠውን ማስጠንቀቂያ እንመልከት ።

«እውነት እውነት እላችኋለሁ ፤ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ፤ ሥጋዬን የሚበላ ፤ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው ፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ፤ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ፤ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ፤ ሥጋዬን የሚበላ ፤ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል ፤ እኔም በርሱ እኖራለሁ ።» (ዮሐ. ም. ፮ ቊ. ፶፫—፶፮)

ማንኛውም ሰው የዘላለም ሕይወት ሊኖረው የሚችለው የጌታን ሥጋና ደም በመቀበል ብቻ ከኾነ ማንም ይህ ዕድል እንዳያመልጠው ማድረግ የኹሉም ኀላፊነት ነው ። በተለየ ግን ካህናትና ሰባክያን የበለጠ ኀላፊነት አለባቸው ።

በየትኛውም ክፍለ ዓለም ፡ በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ከሥጋ ውና ከደሙ ርቆ የሚኖር ክርስቲያን በፍጹም አይገኝም ። ይህን በጣም አስፈላጊ የሃይማኖት ትምህርት ሳናስተምርና መመሪያ ሳንሰጥ ቀርተን ያልተማረው ሰው ባለማወቁ ከዘላለማዊው ሕይወት ቢታገድ ወይም እንደጥፋተኛ ቢቈጠር በኀላፊነት የምንጠየቅ ለመኾኑ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት ።

«እኔ ኀጢአተኛውን በእርግጥ ትሞታለህ ባልኩት ጊዜ ከክፉ መንገዱ ተመልሶ ነፍሱ ትድን ዘንድ አንተ ባታስጠነቅቀው ያ ኀጢአተኛ በኀጢአቱ ቢሞትም ደሙን ግን ከእጅህ እፈልገዋለሁ ።» (ሕዝ. ም. ፫ ቁ. ፲፰)

ስለዚህ ማንኛውም ክርስቲያን ሥጋውንና ደሙን ባለመቀበሉ የዘላለምን ሕይወት ከሚያጣና እኛም እንዲቈርብ ባለማስተማራችን ከሚፈረድብን ይልቅ ተግተን ማስተማር ግዴታችን መኾኑን እንርሳ ።

ሠ. <u>ምሥጢረ ክህነት</u>

የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ለማከናወን ፡ ምእመናንን ለማስተማር ፡ የንስሐ ኑዛዜን በመስማት ተገቢውን እርማትና ምክር ለመስጠት ፡ እንዲሁም ኀጢአትን ይቅር ለማለት የሚያስችለውን ጸጋ መቀበል ምሥጢረ ክህነት ይባላል ።

ይህ ምሥጢር የተመሠረተው መድኀኒታችን ዐሥራ ኹለቱን ሐዋርያት በመረጠ ጊዜ ነው ። ከዚያ በኋላ ሐዋርያት ከእነርሱ ቀጥለው ለተነሡት የሃይማኖት መሪዎች ፡ እነዚያ ደግሞ ለተተኪዎቻቸው እያስተላለፉ እስከ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ጸጋ እግዚአብሔር ነው ።

ዐሥራ ኹለቱን ሐዋርያት ከመምረጡ በፊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተራራ ወጥቶ ሲጸልይ ማደሩን በሉቃስ ወንጌል ም. ፮ ቁ. ፲፪—፲፫ እንመልከት ። ለእነዚህ ለዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያትም ርኩሳን መናፍስትን እንዲያስወጡ ፡ በሽታንና ደዌን ኹሉ እንዲፈውሱ ሙታንን እንዲያስነሡና አጋንንትን እንዲያስወጡ ሥልጣን ሰጣቸው ። (ማቴ. ም. ፲ ቁ. ፩—፰) ቀጥሎም ሰባ ሰዎችን መርጦ ለማስተማር መላኩን በሉቃስ ወንጌል ም. ፲ ቁ. ፩—፱ እንመልከት ። ሐዋርያትን



ከመምረጡ በፊት ሲጸልይ ማደሩ ምሥጢረ ክህነት ምን ያኽል ክብር እንዳለው ሊያስተምረን ስለፈለገ ነው ።

መድኀኒታችን የክህነትን ጸጋ እንዴት አድርጎ ለደቀ መዛሙርቱ እንደሰጠና ይህም ምሥጢረ ክህነት በእነርሱ ብቻ ተወስኖ የማይቀርና የሚቀጥል መኾኑን የገለጠበትን ኹናቴ እንመልከት ።

«ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንደገና ሰላም ለእናንተ ይኹን ፡ አብ እኔን እንደላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ አላቸው ። ይህንን ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ። እናንተ የሰዎችን ኀጢአት ይቅር ብትሉ ይቅር ይባልላቸዋል ፤ እናንተ የሰዎችን ኀጢአት ይቅር ባትሉ ግን ይቅር አይባልላቸውም አላቸው ።» (ዮሐ. ም. ፳ ቁ. ፳፩—፳፫)

«እነሆ ፡ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ኹልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ።» (ማቴ. ም. ፳፰ ቁ. ፳)

ከሐዋርያት መካከል እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በዚህ ዓለም ይኖራል ፡ ወይም እስከዛሬ ድረስ ኖሮአል ተብሎ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተመሰከረለት አንድም ሰው የለም ። እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ኹልጊዜ ከእናተ ጋር ነኝ ያለው ግን ከሐዋርያት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ለሚቀጥለው ሥልጣነ ክህነት ነው ።

የክህነት ደረጃዎች ጵጵስና ወይም ኤጲስ ቆጶስነት ፡ ቅስናና ዲቁና ናቸው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የኤጲስ ቆጶስን ግዴታ ሲያመለክት «ኤጲስ ቆጶስ የእግዚአብሔርን ሥራ በአደራ የተቀበለ ስለኾነ ነቀፌታ የሌለበት መኾን አለበት ።» ይላል ። (ቲቶ. ም. ፩ ቁ. ፯)

ካህናት እንዴት እንደተሾሙ በሐዋርያት ሥራ ም. ፲፬ ቁ. ፳፫ ላይ ስንመለከት «የቤተ ክርስቲያንንም ሽማግሌዎች ሾሙላቸው ፤ ከጾሙና ከጸለዩም በኋላ ላመኑበት ጌታ አደራ ሰጡአቸው» የተባለ ኾኖ እናገኘዋለን ።

ቅዱስ ጳውሎስ ለቲቶ በላከው መልእክቱ ም. ፩ ቍ. ፭—፯ ላይ «አንተን በቀርጤስ የተውኩበት ምክንያት የጐደለውን በማሟላት እንድታደራጅና ባዘዝኩህም መሠረት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን በየከተማው እንድትሾም ነው ። የቤት ክርስቲያን ሽማግሌ የማይነቀፍና የአንዲት ሚስት ባል በመኾንና ባለመታዘዝ ምክንያት የማይወቀሱ አማኞች ልጆች ያሉት ሰው መኾን ይገባዋል» ይላል ። ስለዲያቆናት ደግሞ ሲጽፍ «እንዲሁም ዲያቆናት የተከበሩና በቃላቸው የሚታመኑ ፣ የወይን ጠጅ የማይጠጡ ፣ ለገንዘብ የማይስገበገቡ መኾን አለባቸው» ብሏል ። (፩ኛ ጢሞ. ም. ፫ ቍ. ፰)

በመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት ም. ፪ ቍ. ፭ እና ፱ ላይ «በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ለማቅረብ ቅዱሳን ካህናት ትኾናላችሁ ፤ . . . የንጉሥ ካህናት እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ» ስለሚል በብሉይ ኪዳን ሥርዓት ነው እንጂ በሐዲስ ኪዳን ግን አማኞች በሙሉ የክህነትን ሥራ ለማከናወን መብት አላቸው እንጂ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተሰጠ መብት አይደለም ብለው የሚከራከሩ ሰዎች አሉ ።

የክህነት ሥልጣን ለተወሰኑ ሰዎች እንጂ ለምእመናን ኹሉ ያልተሰጠ ለመኾኑ ብዙ ማስረጃዎች ያሉ ሲኾን ከነዚህም ጥቂቶቹ ቀጥለው የቀረቡት ናቸው ።

አንደኛ/ ተከራካሪዎቹ እንደሚሉት ቢኾን ኖሮ ጌታ በመጀመሪያ ዐሥራ ኹለቱን ሐዋርያት ቀጥሎም ሰባ ኹለቱን አርድእት ባልመረጠም ነበር ። መምረጥ ብቻ ሳይኾን በተለየም ለዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት ልዩ ልዩ ሥልጣን የሰጣቸው መኾኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል ። ይህም የመመረጥ ዕድል የተሰጣቸው ። ለተወሰኑና ለተመረጡ ሰዎች ነው እንጂ ለአማንያን ኹሉ አይደለም ።

ኹለተኛ/ ሐዋርያው ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ወንጌልን አስተምረው ብዙዎችን በጌታ እንዲያምኑ ካደረጉ በኋላ ከአንጾኪያ ተነሥተው ወደ ሌላ አገር ከመኼዳቸው በፊት የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች ማለት ካህናትን እንደሾሙላቸው በሐዋርያት ሥራ ም. ፲፬ ቍ. ፳፫ ላይ ማንበብ እንችላለን ። ተከራካሪዎቹ እንደሚሉት አማንያን ኹሉ የክህነት ሥልጣን ቢኖራቸው ኖሮ ካህናት መሾም ባላስፈለጋቸውም ነበር ።



ሦስተኛ/ ሐዋርያው ጳውሎስ የቀርጤስ ኤጲስ ቆጶስ የነበረውን ቲቶን በየከተማው ካህናትን እንዲሾም አዝዞታል ። (ቲቶ. ም. ፩ ቍ. ፭) አማንያን ኹሉ የክህነት ሥልጣን ካላቸው ለምን ታዲያ ካህናት መሾም አስፈለጋቸው ?

አራተኛ/ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቲቶ በላከው መልእክቱ ም. ፩ እና ወደ ጢሞቴዎስ በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፫ ላይ ኤጲስ ወጾሳት ፣ ካህናትና ዲያቆናት ምን ዐይነት ጠባይ ሊኖራቸው እንደሚገባ ዘርዝሮ በሚያስረዳበት ጊዜ ለእነርሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የተለየ ጸጋ ስላላቸው ነው እንጂ እነርሱን ከሌሎቹ አማንያን ለይቶ ባልጠቀሳቸውም ነበር ። እንዲያውም ለቲቶ በላከው መልእክቱ ም. ፩ ቍ. ፯ ላይ ኤጲስ ቆጶስ የእግዚአብሔርን ሥራ በአደራ የተቀበለ ነው በማለት ከሌሎች አማኞች የተለየ ሥልጣን እንዳለው በግልጽ ያሳያል ። የክህነትም ሹመት ለማንም የማይሰጥና የተለየ ክብር ያለው መኾኑን ሲያመለክት ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፭ ቍ. ፳፪ ላይ «እጆችህን በመጫን ማንንም ለመሾም አትቸኵል ፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር በኀጢአት አትተባበር ፤ ራስህን በንጽሕና ጠብቅ» ብሎ አስጠንቅቆታል ።

አምስተኛ/ ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ም. ፭ ቍ. ፲፬ ላይ የታመመ ሰው ቢኖር ከሕመሙና ከኀጢአቱ በጸሎታቸው እንዲያድኑት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ማለት ካህናትን እንዲጠሩ ማስተማሩ ለካህናት የተለየ ጸጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸው መኾኑን ሲያመለክትን ነው እንጂ ማንኛውም ምእመን ይጸልይለት ብሎ በተናገረ ነበር ። ካህናት ትኾናላችሁ ወይም የንጉሥ ካህናት ትኾናላችሁ የሚለው ግን ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ በቀጥታ የሚወሰድ አይደለም ። ካህናት ትኾናላችሁ ከማለቱ በፊት ድንጋዮች ትኾናላችሁ ብሏል ። ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ ቃል በቃል ድንጋይ መኾን አይደለም ። እንዲሁም ኹሉም ካህን ፣ ኹሉም የንጉሥ ካህን ይኾናል ማለት አይደለም ። እያንዳንዱ ክርስቲያን በሃይማኖት ውስጥ የተለያየ የሥራ ድርሻ አለው እንጂ ኹሉም ካህን ሊኾን አይችልም ። ይህንኑ በሚመለከት ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፲፪ ቍ. ፳፰—፴ ላይ እያንዳንዱ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያየ የሥራ ድርሻ አለው እንጂ ኹሉም የሐዋርያነት ፣ ኹሉም የመምህርነት ፣ ኹሉም ታምራት አድራጊ ፣ ኹሉም የመፈወስ ኹሉም ያስተዳዳሪነት ስጦታ የላቸውም ብሏል ። በዚህም አባባሉ

ምእመናን ኹሉ የክህነትን ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ ለሚሉት ሰዎች መልስ ለመስጠት የፈለገ ይመስላል ።

ረ. <u>ምሥጢረ ንስሓ</u>

ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት መሠረት በማድረግ ሰው ኹሉ ከአዳም በተወረሰ ኀጢአት ተወልዶ የኀጢአት ዝንባሌ እንደሚኖረው ታምናለች ። ስለተፈጥሮአችን ክፉ ዝንባሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፯ ቍ. ፲፬ ፡ ፳ ፡ ፳፬ ላይ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል ፡ «ሕግ መንፈሳዊ መኾኑን ዐውቃለሁ ፤ እኔ ግን የኀጢአት ባሪያ ለመኾን የተሸጥሁ ሥጋዊ ነኝ ፤ ማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር የማድረግ ከኾንኩ ይህን የሚያደርገው በእኔ ውስጥ ያለው ኀጢአት ነው እንጂ እኔ አይደለሁም ማለት ነው ። እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ ? ወደ ሞት ከሚወስደኝ ከዚህ ሰውነትስ ማን ያድነኛል ?»

በጥምቀት እንደገና ተወልደን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ከተቀበልን በኋላ በተፈጥሮ ክፉ ዝንባሌያችን ለምናደርሰው በደልና ለምንሠራው ኀጢአት መድኀኒቱ ንስሓ ነው ። ችግሩን ሰምተው የሚረዱን ኀጢአቱን ይቅር ያላችሁለት ይቅር ይባልለታል ተብሎ ኀጢአትን የማስተስረይ ሥልጣን የተሰጣቸው ካህናት ናቸው ። (ዮሐ. ም. ፳ ቍ. ፳፫)

ምሥጢርነቱም ለካህናት በተሰጣቸው በዐይን በማይታየው ሥልጣን አማካይነት በንስሓ ተመላሾቹ የሚያገኙት በዐይን የማይታየው የኀጢአት ስርየት ነው ።

ንስሓ መግባት ማለትም በተሠራው ኀጢአት መጸጸትና ዳግመኛ ወደፊት ያንን ኀጢአት መልሶ ላለመሥራት መወሰን መኾኑን በሚቀጥሉት ማስረጃዎች እንመልከት ።

«የእስራኤል ቤት ሆይ ፡ እንደመንገዱ በየሰው ኹሉ ላይ እፈርድባችኋለሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ፤ ንስሓ ግቡ ፤ ኀጢአትም እንቅፋት እንዳይኾንባችሁ ከኀጢአታችሁ ተመለሱ ።» (ሕዝ. ም. ፲፰ ቍ. ፴)



«በደማስቆስ ላሉት ፡ በኢየሩሳሌምና በይሁዳም አገር ኹሉ ፡ ለአሕዛብም ንስሓ ይገቡ ዘንድና ለንስሓ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፳፮ ቍ. ፳)

የምሥጢረ ንስሓ አፈጻጸም እንዴት ነው ? ቤተ ክርስቲያን የምታምንበትና የምታስተምረው ንስሓ ማለት አንድ ከኀጢአተኛነቱ ተመልሶ በጽድቅ ሥራ ለመኖር የሚፈልግ ሰው ስለሠራው ኀጢአት በመጸጸት ወደፊት ያንን ኀጢአት መልሶ እንዳይሠራ መወሰን ብቻ ሳይኾን ይህንኑ ችግር ለመስማት ሥልጣን ለተሰጠው ካህን መናዘዝ ነው ። ስለኑዛዜ የቅዱሳት መጻሕፍትን ምስክርነት እንመልከት ።

«ከእነዚህ ነገሮች በአንዲቱ በደለኛ ሲኾን የሠራውን ኀጢአት ይናዘዝ ።» (ዘሌ. ም. ፭ ቍ. ፭)

«ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም ፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል ።» (ምሳ. ም. ፳፰ ቍ. ፲፫)

«እንድትፈወሱ ኀጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ ፤ እያንዳንዱም ለሌላው ይጸልይ ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት ብዙ ውጤት የሚያስገኝ ታላቅ ኀይል አለው ።» (ያዕ. ም. ፭ ቍ. ፲፮)

«ለኀጢአት ኑዛዜ ብናደርግ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን ፡ ከዐመፃም ኹሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው ።» (፩ኛ ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፱)

ሰ. <u>ምሥጢረ ተክሊል</u>

አንድነት ለመፍጠርና የጋብቻቸውንም ግዴታ ለማክበር በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ቃል ለሚገቡ ሙሽራና ሙሽሪት ካህኑ የሚያከናውነው የጸሎትና የ ሚሰጠው ም የቡራኬ ሥነ ሥርዐት ምሥጢረ ተክሊል ወይም ሥርዐተ ተክሊል ይባላል ።

ጋብቻም ምሥጢር መኾኑን ቅዱሳት መጻሕፍት አረጋግጠዋል ።

«ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፤ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸው አላነበባችሁምን ? ደግሞም በእዚህ ምክንያት ሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበ

ራል ፤ ኹለቱም አንድ ይኾናሉ ያለውን አላነበባችሁምን ? ስለዚህ እነርሱ ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ናቸው እንጂ ኹለት አይኾኑም ፤ እግዚአብሔር አጣምሮ አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም ።» (ማቴ. ም. ፲፱ ቍ. ፬—፮)

«ባሎች ራሳቸውን እንደሚወዱ ሚስቶቻቸውን መውደድ ይገባቸዋል ፤ ሚስቱን የሚወድድ ራሱን ይወድዳል ፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ የለምና ። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል ፤ ኹለቱም አንድ ይኾናሉ ። ይህ ምሥጢር ትልቅ ነው ።» (ኤፌ. ም. ፭ ቍ. ፳፰—፴፪)

እግዚአብሔር የጋብቻን ምሥጢር የመሠረተው ገና የሰው ልጅ በኤደን ገነት በነበረ ጊዜ ነው ።

«እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ፤ እግዚአብሔርም ባረካቸው ፤ እንዲህ ም አላቸው ፡ ብዙ ፤ ተባዙ ፤ ምድርንም ሙሉአት ፤ ግዙአትም ። . . . እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ፤ ወደ አዳምም አመጣት ። አዳምም እንዲህ አለ ፤ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት ፤ ሥጋም ከሥጋዬ ናት ፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል ። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ፤ በሚስቱም ይጣበቃል ፤ ኹለቱም አንድ ይኾናሉ ።» (ዘፍ. ም. ፩ ቍ. ፳፯—፳፰ ፡ ም. ፪ ቍ. ፲፰ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬)

ይህንኑ አባባል ነው መድኀኒታችን «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየው» ሲል ያጸደቀው ። (ማቴ. ም. ፲፱ ቍ. ፮)

ጌታም የጋብቻን ውሕደት በቃሉ ብቻ ያስተማረው ሳይኾን በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ ተገኝቶ ባርኮታል ፤ ቀድሶታል ። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ «ጋብቻ በኹሉም ዘንድ ክቡርና መኝታውም ንጹሕ ይኹን» ያለው ። (ዕብ. ም. ፲፫ ቍ. ፬)

በክርስቲያን ሃይማኖት ከአንድ ሚስት ወይም ከአንድ ባል በላይ ማግባት በፍጹም የተከለከለ ነው ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ብቻ መፍጠሩ የጋብቻ ሥነ ሥርዐት አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ፡ አንዲት ሴት ደግሞ ለአንድ



ወንድ ብቻ መኾኑን ሲያመለክተን ነው ። ቅዱሳት መጻሕፍትም ስለ ባልና ሚስት በሚናገሩበት ጊዜ የሚያስለክቱት ስለአንድ ባ ል ወይም ስለአንዲት ሚስት እንጂ ከዚያ አስበልጠው አለመኾኑን በሚከተሉት ጥቅሶች እንመልከት ።

በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፪ ቍ. ፳፬ ላይ «ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ፤ በሚስቱም ይጣበቃል» አለ እንጂ በሚስቶቹም አላለም ።

በሉቃስ ወንጌል ም. ፲፬ ቍ. ፳፮ ላይ «ማንም አባቱንና እናቱን እንዲሁም ሚስቱን ትቶ ባይከተለኝ» አለ እንጂ ሚስቶቹን አላለም ።

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፯ ቍ. ፪ ላይ «በዝሙት ኀጢአት ላለማውደቅ እያንዳንዱ ወንድ የራሱ ሚስት ትኑረው እያንዳንዱዋም ሴት የራስዋ ባል ይኑራት አለ እንጂ የራሱ ሚስቶች ወይም የራስዋ ባሎች አላለም ።

በእግዚአብሔር ፈቃድ አንድ አካል የኾኑት ባልና ሚስት በዝሙት ምክንያት ካልኾነ በቀር መፋታት እንደማይገባቸው የቤተ ክርስቲያን እምነትና አሠራር ነው ። ይህን እምነትና ትምህርት የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ተናግሮአል ። «እኔ ግን እላችኋለሁ ፡ ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ኹሉ አመንዝራ ያደርጋታል ፡ የተፈታችውንም የሚያገባ ኹሉ ያመነዝራል» (ማቴ. ም. ፭ ቍ. ፴፪)

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን በላከው መልእክቱ ም. ፲፫ ቍ. ፬ ላይ ስለጋብቻ ክቡርነት ሲገልጽ «ጋብቻ በኹሉም ዘንድ ክቡርና መኝታውም ንጹሕ ይኹን» በማለት ብቻ አላቆመም ፤ መፋታት የማይገባ መኾኑን ሲገልጽ ደግሞ ፤ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፯ ቍ. ፩—፫ «ወንድሞች ሆይ ፡ ሰው ባለበት ዘመን ኹሉ ሕግ እንደሚገዛው አታውቁምን ? ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለች ፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከታሰረች በት ሕግ ነጻ ናት ። ስለዚህ ባልዋ በሕይወት እያለ ከሌላ ወንድ ጋር ብትጋባ አመንዝራ ትባላለች ፤ ባልዋ ከሞተ ግን ከእርሱ ጋር ከታሰረችበት ሕግ ነጻ ትወጣለች» ብሏል ።

ከላይ በተገለጹት ማስረጃዎች መሠረት ለጋብቻ መፍረስ ሕጋዊ ምክንያቶች ሊኾኑ የሚችሉት ዝሙት ወይም ሞት ብቻ መኾናቸውን ቤተ ክርስቲያን ታምናለች ፤ ይህንኑም ታስተምራለች ።

## ሸ. ምስጢረ ቀንዲል

በካህናት ጸሎት አማካይነት አንድን ሕመምተኛ ከሰውነቱ ክፍሎች ሦስት ቦታ በተቀደሰ ዘይት በመቀባት የሚፈጸመው ሥነ ሥርዐት ምሥጢረ ቀንዲል ይባላል ። ይህ ምሥጢር ግን ከሌሎቹ ምሥጢራት በኹለት ኹናቴዎች ይለያል ። የመጀመሪያው መለያ የዚህ ምሥጢር ግልጋሎት የሚፈጸመው በተለይ ለታመሙ ሰዎች ብቻ መኾኑ ነው ። ኹለተኛው መለያ ደግሞ የዚህ ምሥጢር ግልጋሎት ውጤት ኹለት መኾኑ ነው ። ይህም ማለት ሕመምተኛው የሥጋ ሕመም ፈውስና የኀጢአት ስርየት ያገኛል ማለት ነው ።

የተቀደሰው ዘይትም የሚቀባው አንደኛ ግንባሩ ላይ እርሱም የአምስቱ ሕዋሳት ማእከልና የማሰብ ኀይል የሚገኝበት በመኾኑ ፣ ኹለተኛ ደረቱ ላይ ፣ እርሱም የልብ ማረፊያ በመኾኑ ፣ ሦስተኛ እጆቹ ላይ እነርሱም ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት የሚንቀሳቀሱ በመኾናቸው ነው ። በእነዚህም በሦስቱ የአካል ክፍሎች የተቀደሰው ዘይት መቀባት ያስፈለገው ሰውነታችንን የሚበክል የርኩሰት ቍስል ከእነርሱ ሊፈልቅ ስለሚችል ይህንኑ ቍስል ለማጽዳት ታስቦ ነው ።

አሠራሩ በግልጽ ባይነገርም እንኳ የዚህ ምሥጢር መሥራች መድኀኒታችን መኾኑን ለመገመት አያዳግትም ። በማርቆስ ወንጌል ም. ፮ ቍ. ፯ ላይ ዐሥራ ኹለቱን ወደርሱ ጠርቶ ኹለት ኹለት አድርጎ ላካቸው ፤ በርኩሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሰጣቸው» ካለ በኋላ በቍጥር ፲፪ እና ፲፫ ላይ ደግሞ «እነርሱም ከዚያ ወጥተው ሰዎች ኹሉ ንስሓ እንዲገቡ አስተማሩ ፣ ብዙ አጋንንትንም አስወጡ ፤ ብዙ ሰዎችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱ» በማለት የምሥጢረ ቀንዲልን አጀማመር ያመለክታል ።

ምንም እንኳ ወንጌላዊው ማርቆስ የምሥጢረ ቀንዲልን አጀማመር ፍንጭ ቢሰጥ አሠራሩን በዝርዝር አላሳየውም ነበር ። በአንድ ቦታ ያልተሟላ መስሎ የሚታየው በሌላ ቦታ ተሟልቶ መገኘት በእግ



ዚአብሔር መንፈስ እየተመሩ የተጻፉት የቅዱሳት መጻሕፍት አሠራር በመኾኑ የምሥጢረ ቀንዲልን አሠራር በዝርዝር ሲያስረዳ ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ብሏል ። «ከእናንተ መካከል የታመመ ሰው ቢኖር የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደርሱ ይጥራ ፤ እነርሱም በሽተኛውን በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት ። እንዲህ ዐይነቱ በእምነት የተመሠረተ ጸሎት በሽተኛውን ያድነዋል ፤ ጌታም ከበሽታው ይፈውሰዋል ፤ የሠራው ኀጢአትም ቢኖር ይቅር ይባላልለታል ።» (ያዕ. ም ፭ ቍ. ፲፬—፲፭)

…ን የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር የማያምኑና የማይቀበሉ ወገኖች ከሚያ…ርቡአቸው ተቃውሞዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

አንደኛ/ ሐዋርያው ያዕቆብ ያቀረበው የዘይት መቀባት ጉዳይ ምሥጢር ሳይኾን በወንጌል ውስጥ የተነገረ ሕመምተኞችን ዘይት በመቀባት የማዳን ተአምር ነው ይላሉ ።

የአንድ ተአምራዊ ውጤት ልዩ ልዩ ምልክቶችንና የአሠራሮችን ቅደም ተከተል ሕግ በማውጣት የሚፈጸም አይደለም ። በሌላ በኩል ደግሞ ሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት አማካይነት ተአምራዊ ውጤትም አስገኝተው ከኾነ ምንም አያስገርምም ።

ኹለተኛ/ ሐዋርያው ያዕቆብ የጠቀሰው የዘይት መቀባት ጉዳይ የታመመን ሰው ለመፈወሻ የሚኾን አንድ ተራ ቀላል መንገድ ነው እንጂ ምሥጢር አይደለም ይላሉ ።

እነርሱ እንደሚሉት ሐዋርያው ያዕቆብ የጠቀሰው የዘይት መቀባት ጉዳይ አንድ ተራ አሠራር ቢኾን ኖሮ ለምን ታዲያ ካህናት መጠራት አስፈለጋቸው ? ደግሞስ የካህናት ዋና ሥራ የኾነው የኀጢአት ማስተስረይ ጉዳይስ ለምን እዚህ መኖር አስፈለገው ?

ሦስተኛ/ የዘይት መቀባቱ ሥራ እንደቤተ ክርስቲያን ምሥጢር የሚቈጠር ከኾነ ሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ውጤት እንደሚገኝባቸው የሚታመን እንደመኾኑ ለምን ታዲያ በዚህ መልክ ዘይት የተቀባ ሕመምተኛ ኹሉ ከሕመሙ አይፈወስም ብለው ይጠይቃሉ ።

የሕመምተኛው አለመፈወስ ምሥጢርነቱን አይከድም ። ምናልባትም ለኀጢአቱ ስርየት ሲባል የሕመሙ መዳን አስፈላጊ አይኾን ይኾናል ፤ ወይም አዳኙ ጌታ ብቻ የሚያውቀው ሌላ ምክንያት ሊኖር ይችላል ። ለምሳሌ ምሥጢረ ቊርባን ለኀጢአት ስርየትና ለዘላለማዊው ሕይወት የሚያድለን መኾኑ የታመነ ቢኾንም ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፲፩ ቊ. ፴ ላይ ከእናንተ መካከል ብዙዎች የደከሙትና የታመሙት አንዳንዶችም የሞቱት የጌታን ሥጋና ደም በመቀበላቸው ነው ሲል ገልጾላቸዋል ። ይህም የሚያመለክተው እንደየኹናቴው አመጣጥ ጠቃሚው ነገር እንኳ ጒጂ የሚኾንበት ወይም ጥቅሙን የማያስገኝበት ጊዜ መኖሩን ነው ።



# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## የሰው ነፍስና
## ትንሣኤ ሙታን

### ሀ— መ ግ ቢ ያ ፤

በዓለም የሚገኙትን የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ብናስተውል በአጠቃላይ ኹለት ኹናቴዎችን እናገኛለን ። አንዱ የሚንቀሳቀስ የሚመገብ ፥ በመዋለድ የሚበዛና የሚሞት ሲኾን ሌላው ደግሞ እነዚህ ጠባዮች የሌሉት ነው ። የመጀመሪያው ዐይነት ፍጥረት ሕይወት ያለው ወይም ሕያው የሚባል ኾኖ ኹለተኛው ዐይነት ፍጥረት ግን ሕይወት የሌለው ግዑዝ ነው ።

ሕይወት ያለው ወይም ሕያው ከሚባለው ፍጥረት መካከል አሁን የምንነጋገርበት በተለይ ስለሰው ነፍስ ጉዳይ ነው ።

ነፍስ ሲባል እኛ ልንነጋገርበት ካቀድነው ትርጉም ሌላ የእንስሳትን ተፈጥሮ ፥ የሰውን ሕይወት ፥ ስሜትን እና ፈቃድን ያጠቃልላል ። (ዘፍ ም፩ ቊ. ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፳፬ ፡ ፴ ም. ፲፯ ቊ. ፬ ፡ ዘሌ. ም. ፳፬ ቊ. ፲፯-፲፰ ኢያ ም. ፲፩ ቊ. ፲፩ ፡ ሕዝ. ም. ፲፰ ቊ. ፬ ፡ ሉቃ ም. ፩ ቊ. ፵፯፡ የሐ. ሥ. ም. ፫ ቊ. ፳፫፡ ሮሜ ም. ፲፩ ቊ፡ ፫፡ ም. ፲፫ ቊ. ፩ ፡ ፩ኛ ጴጥ. ም ፫ ቊ. ፳)

ከላይ የተጠቀሱትን ትርጓሜዎች ማለት ነፍስ ሲባል የሰውንና የእንስሳትን ተፈጥሮ ፡ የሰውን ሕይወት ፡ ስሜትንና ፈቃድን በማመልከታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነፍስ ለሚለው ቃል የተሰጠውን ትርጓሜ የሚከዱ ወገኖች አሉ ። እንደእነርሱ አባባል ነፍስ ማለት ሕይወት ማለት እንደመኾኑ የሰውና የእንስሳ ነፍስ ተመሳሳይ ነው ።

ለ— የሰው ነፍስ ፤

እግዚአብሔር ሕይወት ያላቸውን ፍጥረቶች ኹሉ ይኹኑ ፥ ይፈጠሩ ብሎ በትእዛዙ መሠረት ፣ ከመኾናቸው በቀር ሌላ የተለየ አድራጎትን አላደረገም ። ሰውን ሲፈጥር ግን በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ካለበት በኋላ ነው ሕያው ነፍስ ያለው ፍጡር የኾነው ። (ዘፍ. ም. ፪ ቍ. ፯)—በምዕራፍ ፩ ቍ. ፳ ላይ ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ የተባለውን አባባል መለኮታዊ የሕይወት እስትንፋስ እፍ ከተባለበት ፍጡር ጋር አንድ አድርጎ መገመት የእግዚአብሔርን ክብር ዝቅ እንደማድረግ ይቈጠራል ።

እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ በፊት ያቀደው ዕቅድ በምድር ያለውን ፍጥረት ኹሉ ይገዛ ዘንድ ሰውን በመልካችንና እንደም ሳሌአችን እንፍጠር በማለት ነው ። (ዘፍ. ም. ፩ ቍ. ፳፮—፳፯)

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጠረ የተባለው (አንደኛ) በምድር ላይ ባለ ፍጥረት ኹሉ ላይ ገዢ እንዲኾን በመደረጉ (ኹለተኛ) ክፉንና ደግን ለመለየት በመቻሉ (ሦስተኛ) ምንም እንኳ እንደ አንበሳ ነብር ዝኆንና ሌሎችም ትላልቅ አራዊት በጉልበታቸው ከሰው የበለጠ ዐቅም ቢኖራቸው እግዚአብሔር ዐዋቂነትን ስለሰጠው የሰው ልጅ በብልኅቱ እነርሱን አሸንፎ በመኖሩና (አራተኛ) ደግሞ የማትሞት የሕይወት እስትንፋስን በአፍንጫው እፍ ብሎበት የሰው ልጅ ሥጋው እንጂ ነፍሱ የማትሞት በመኾንዋ ነው ። ይህም ብቻ ሳይኾን በኋላ ጊዜ በትእዛዝ አፍራሽነቱ በኀጢአት ከመውደቁ በቀር ሰው ሲፈጠር በጽድቅና በቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል ስለ ነበረ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ተፈጠረ ተባለ ። (ዘፍ. ም. ፩ ቍ. ፳፯ ፡ ም. ፱ ቍ. ፯፡ ም. ፲ ቍ. ፳፱ ፡ ሮሜ ም. ፭ ቍ. ፲፪—፳፩ ፡ ፩ኛ ቆሮ ም ፲፭ ቍ. ፵፱ እና ፵፭)

የሰው ልጅም ከእግዚአብሔር እስትንፋስ የተገኘች ነፍስ ስላለችውና ለእግዚአብሔር ቅርብ በመኾኑ ነው በኋላ ዘመን እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ ለብሶ በኀጢአት ባርነት ለወደቀው ለሰው ልጅ ቤዛ የኾነለት ።

ስለማትሞተው ስለሰው ነፍስ በሚነገርበት ጊዜ ነፍስና መንፈስ የሚባሉት ኹለት ቃላት ተመሳሳዮች ኾነው ስለሚቀርቡ ሊያሳስቱን



አይገባም አብዛኛውን ጊዜ መንፈስ ሲባል የማይጨበጥ የማይዳሰስና የማይታይ ረቂቅ ነገር ማለት በመኾኑና ነፍስም እነዚህ ጠባዮች ስላሉት ተመሳሳይ ይኾናሉ ። እግዚአብሔር መንፈስ ነው ፥ መላእክትም መናፍስት ናቸው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ም ፭ ቍ. ፳፫ ላይ ነፍስ መንፈስና ሥጋ ብሎ በሚለያይበት ጊዜ መንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ያለው ሥጋ ዓለማዊውን ኹናቴ ብቻ የሚያመለክት ሲኾን ነፍስ ደግሞ በኹለቱ መካከል የሚገኝ የሕሊና ዳኛ ማለት ደግና ክፉ ነገሮችን የሚያመዛዝነው የሰውነት ክፍል አድርጎ በመቍጠር ሦስቱም ግን ሳይለያዩ በአንድ ሰው ተፈጥሮ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ የአስተሳሰብና የዝንባሌ ክፍሎች እንደ ኾኑ የሚያሳይ ነው ። ይህን ልዩነት በማመልከት በሌላ ጊዜ ያደረገውን ገለጻ እንመልከት ። «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና ፥ የሚሠራም ኹለትም አፍ ካለው ሰይፍ ኹሉ ይልቅ የተሳለ ነው ፤ ነፍስንና መንፈስንም ፥ ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል ፥ የልብንም ስሜትና ሐሳብ ይመረምራል ።» (ዕብ. ም. ፬ ቍ. ፲፪)

ነፍስም የማትሞት ለመኾንዋ ብዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ያሉ ሲኾን ጥቂቶቹ ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው ።

«አፈር ወደነበረበት ምድር ሳይመለስ ፥ ነፍስም ወደሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ ።»(መክ. ም ፲፪ ቍ. ፯)

ይህ አባባል የሚያመለክተው ሰው በሚሞትበት ማለት ሥጋና ነፍሱ በሚለያዩበት ጊዜ ከአፈር የተፈጠረው ሥጋ መሬት ተቈፍሮ የሚቀበር ሲኾን ነፍስ ግን የማትሞት የእግዚአብሔር እስትንፋስ በመኾንዋ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለች ማለት ነው ።

«ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሩ ነፍሳችሁን ግን ለመግደል አይችሉም» በማለት መድኀኒታችን ነፍስ የማትሞት መኾንዋን ገልጾአል ። (ማቴ. ም. ፲ ቍ. ፳፰)

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ም. ፳፫ ቍ. ፵፮ ላይ ነፍሱን ለአብ አደራ መስጠቱና ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ም፯ ቍ. ፶፱ ላይ ነፍሱን ለጌታ ኢየሱስ አደራ መስጠቱ ሥጋ ፥ በሚሞትበት ጊዜ ነፍስ የማትሞት በመኾንዋ ነው ።

ጌታ ተሰቅሎ በነበረ ጊዜ በስተቀኙ ተሰቅሎ ለነበረው ሰው «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖናለህ» ያለው የሰው ነፍስ የትንሣኤ ሙታንን ጊዜ በገነት ወይም በሲኦል ኾና እንደምትጠብቅ እንጂ ከሥጋ ጋር የማትሞት መኾንዋን ያመለክተናል ። (ሉቃ ም. ፳፫ ቁ. ፵፫)

ሐ— ትንሣኤ ሙታን ፤



«የትእዛዝ ድምፅ የመላእክት አለቃ ድምፅ የእግዚአብሔር መለ ከትም ይሰማል፤ ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል ።» (፩ኛ ተሰ. ም. ፬ ቁ. ፲፮)

ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው የሰው ነፍስ በዐይን የማይታይና በእጅ የማይዳሰስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መለኮታዊ እስትንፋስ በመ



ኾኑ የማይሞት ነዋሪ ነው ተብሏል ። ሰው ኹሉ ነፍሱና ሥጋው በመለያየት ጊዜው ሲደርስ የሚሞት መኾኑ ግልጽ ነው ። ይኹን እንጂ እነዚህ የተለያዩት ሥጋና ነፍስ በመጨረሻው ዘመን እንደገና ኅብረት እንዲኖራቸው ዳግመኛ በማይፈርስና በማይበሰብስ ሥጋ የሚነሡ መኾናቸውን የሚገልጸው የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ትንሣኤ ሙታን ይባላል ። ይህም ትምህርት ለሰው አስተሳሰብ ረቂቅ ምሥጢር በመኾኑ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ይባላል ። ስለትንሣኤ ሙታን ማስረጃነት ከሚቀርቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

በትንሣኤ ሙታን የማያምኑት ሰዱቃውያን ጌታን ሊፈትኑት ፈልገው ጥያቄ በጠየቁት ጊዜ መልስ ሲሰጣቸው «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል ካለማወቃችሁ የተነሣ ትስታላችሁ ሙታንስ ሲነሡ በሰማይ እንዳሉት እንደ እግዚአብሔር መላእክት ይኾናሉ እንጂ አያገቡም ፣ አይጋቡም ። ስለሙታን መነሣት የኾነ እንደኾነ ግን እኔ የአብርሃም አምላክ ፣ የይስሐቅ አምላክ ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ያለውን አላነበባችሁምን? ስለዚህ እግዚአብሔር የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም ።» ብሎአቸዋል ። (ማቴ. ም. ፳፪ ቁ. ፳፫—፴፪)

«በዚህ አትደነቁ በመቃብር ያሉ ኹሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣልና ። መልካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል ።» (ዮሐ. ም. ፭. ቁ. ፳፰—፳፱)

«እነርሱ እንደሚያምኑት እኔም የጻድቃንና የኃጥአን ትንሣኤ መኖሩን አምናለሁ ።» (የሐ ሥ. ም. ፳፬ ቁ. ፲፭)

«ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ የሚሰበክ ከኾነ እንዴት ከእናንተ አንዳንዶቹ የሙታን ትንሣኤ የለም ይላሉ? ሙታን ከሞት የማይነሡ ከኾነ ክርስቶስ አልተነሣማ ፣ ክርስቶስ ካልተነሣ ደግሞ የእኛም ትምህርት ኾነ የእናንተም እምነት ከንቱ መኾኑ ነው ።» (፩ኛ ቆሮ. ም፣ ፲፭ ቁ. ፲፪ -፲፬)

ሙታን የሚነሡት እንዴት ነው? በሚነሡበትስ ጊዜ የሚኖራቸው አካል ምን ዐይነት ነው ብሎ የሚጠይቅ ሰው ይኖር ይኾናል ። አንተ ሞኝ የምትዘራው እኽል ካልሞተና አፈር ውስጥ ገብቶ ካልበሰበሰ

በስተቀር ሕይወት ሊኖረውና ሊበቅል አይችልም ። የምትዘራት አንዲት የስንዴ ቅንጣት ወይም የሌላ እኽል ዘር ነው እንጂ ዋናውን የአትክልት አካል አይደለም ። በበቀለና ባደገ ጊዜ ግን አንተ ከዘራኸው ዘር የተለየ መልክና አካል ይኖረዋል ።» (፩ኛ ቆሮ ም ፲፭ ቍ. ፴፭ —፴፯)

በመጽሐፈ መክብብ ም. ፫ ቍ. ፲፱—፳፪ ላይ «በእውነቱ የሰውና የአራዊት ዕድል ፈንታ አንድ ነው ፤ አንዱ እንደሚሞት ሌላውም ይሞታል ኹለቱም አንድ ዐይነት እስትንፋስ አላቸው ፤ ሰው ከእንስሳ አይበልጥም ፤ ኹሉም ከንቱ ነውና ። ኹለቱም ወደ አንድ ቦታ ይኼዳሉ ፤ ኹለቱም የተገኙት ከአፈር ነው ፤ ኹለቱም ወደአፈር ይመለሳሉ ። የሰው ነፍስ ወደላይ እንደምትወጣና ወይም የአራዊት ነፍስ ወደታች ወደመሬት እንደምትወርድ ማን ያውቃል? ይህም ዕድል ፈንታው ስለኾነ ሰው በሥራው ደስ ከሚለው በቀር ሌላ ደስታ እንደሌለው አያለሁ ። ከጊዜው በኋላ የሚኾነውንስ ነገር ያይ ዘንድ ማን ሊያመጣው ይችላል?» ተብሎ የተዘረዘረውን አባባል መሠረት በማድረግ የሰው ነፍስ ከእንስሳ ነፍስ ልዩነት እንደሌላትና በዚህም ምክንያት ትንሣኤ ሙታን የሌለ መኾኑን በማመን ክሕደታቸውን የሚያጠናክሩ ሰዎች አሉ ። ከላይ ከተጠቀሰው ጥቅስ ቀደም ብለን ከቍጥር ፲፯ ጀምረን የተመለከትን እንደኾነ «እኔ ግን አሁን የማስተውለው ከፀሐይ በታች በሕግ ቦታ ወንጀል ፣ በጻድቅ ቦታ ደግሞ ወንጀለኛ አለ ።... የሰው ልጆችም እንዲህ የሚያደርጉት እግዚአብሔር ምንነታቸውን ሊያሳያቸውና አንዱ በሌላው ላይ ያላቸው አድራጎት ከአውሬ ያልተሻለ መኾኑን ሊገልጽላቸው እንደኾነ አስባሁ ።» የሚል ኾኖ እናገኘዋለን ። ስለዚህ ከዚሁ አከታትሎ በቍ ፲፱—፳፪ ያለውን ጥቅስ መዘርዘሩ የሰው ልጆች በሚፈጽሙአቸው ክፉ አድራጎቶች ከአውሬ የማይሻሉ ናቸው ለማለት ነው እንጂ የመጽሐፈ መክብብን ጸሐፊ እምነት ለመረዳት ቀደም ተብሎ በሰው ነፍስ ርእስ ሥር የተጠቀሰውንና በመጽሐፈ መክብብ ም. ፲፪ ቍ. ፯ ላይ የሚገኘውን ጥቅስ እንመልከት ።

«አፈር ወደነበረበት ምድር ሳይመለስ ፣ ነፍስም ወደሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህ ን አስብ ።»

ምንም እንኳ ነፍስ የማትሞት ብትኾን ሥጋ ግን መሟሸሽና ውድቀት እንደሚደርስበት የታወቀ ነው ። ከሞት በኋላ በሰው ልጅ ሥጋ ላይ የሚደርሰው መፍረስና መበስበስ ከእንሰሳ ምንም ልዩነት ስለማይኖረው ሊያወዳድረው በቅቷል ።



የሰውን ልጅ ከእንስሳት የሚለየው የአንጐሉ መጠንና የአስተሳሰቡ ከፍተኛነት ብቻ ሳይኾን ተንቀሳቃሽና ተናጋሪ ነፍሱ ከላይ የመጣችና ወደ ላይ የምትመለስ መኾንዋ ነው ። የእንስሳት ነፍሳቸው ግን ደማቸው መኾኑን በኦሪት ዘሌዋውያን ም. ፲፯ ቍ. ፲፬ ላይ መመልከት እንችላለን ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፲፭ ቍ. ፶፩—፶፪ ላይ «እነሆ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ ፤ ኹላችንም አንሞትም ፤ ነገር ግን ኹላችንም እንለወጣለን ። የምንለወጠውም የመጨረሻው መለከት በሚነፋበት ጊዜ እንደ ዐይን ቅጽበት በአንድ ጊዜ ነው ። መለከቱ ይነፋል ፤ የሞቱትም ሰዎች የማይጠፉ ሕያዋን ኾነው ይነሣሉ ፤ እኛም እንለወጣለን ካለ በኋላ መጀመሪያ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፬ ቍ. ፲፮ ላይ ደግሞ «የትእዛዝ ድምፅ ፣ የመላእክት አለቃ ድምፅ ፣ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰማል ፤ ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል በክርስቶስ አምነው የሞቱትም አስቀድመው ይነሣሉ ፡» በማለት የትንሣኤ ሙታንን ዝርዝር ኹናቴ ገልጾአል ።

መ— <u>ዘላለማዊ ፍርድ</u> ፤

የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ከእግዚአብሔር በቀር ማንኛውም ፍጡር በማያውቀውና እርሱው በወሰነው ቀን ጌታችንና አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግ ለሠራ ሰው ዋጋ መንግሥተ ሰማያትን ሊያድለው ክፉ በሠራ ሰው ላይ ደግሞ ዘላለማዊ ስቃይን ሊፈርድበት የሚመጣበት የመጨረሻ ዘመን እርሱም ዘመን ትንሣኤ ሙታን ወደፊት የሚደርስ መኾኑን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው እውነት ነው ።

ከሦስቱ መለኮታዊ አካሎች ለፍርድ ወደዚህ ዓለም የሚመጣው አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ ሳይኾን ወልድ ብቻ የኾነበት ምክንያት የሰው ልጅ በመኾኑ የመፍረድ ሥልጣን ስለተሰጠው ነው ። (ዮሐ. ም. ፭ ቍ. ፳፯)

የሰው ልጅ መኾኑና የመፍረድ ሥልጣን መስጠቱ ምን ግንኙነት አለው ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ።

ቀደም ተብሎ በሌላ ትምህርት እንደተገለጸው ማንም እግዚአብሔርን ያየውና ሊያየውም የሚችል ሰው አለመኖሩ ተነግሮአል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰው የኾነ አምላክ በመኾኑ ሰዎች ሊያዩት ይችላሉ ። በእነሙሴ ዘመን እንደተደረገው የእግዚአብሔርን ፊት ሳያዩ ድምፁን መስማት ብቻ ሳይኾን በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ማለት በጌታ ዳግመኛ መምጫ ጊዜ ግን «እነሆ በደመና ታጅቦ ይመጣል ፤ የወጉት እንኳ ሳይቀሩ ሰዎች ኹሉ ያዩታል ።» (ራ. ዮሐ. ም. ፩ ቍ. ፯)

ስለዚህ የሚፈረድላቸውም ኾኑ የሚፈረድባቸው ሰዎች ኹሉ ያዩታል ፤ ፍርዱንም ከአንደበቱ ይሰማሉ ።

ስለዘላለማዊው ፍርድ ከቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለትንሣኤ ሙታንና ስለመጨረሻው ፍርድ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል «የሰው ልጅ በመላእክቱ ታጅቦ በክብር ዙፋኑ ላይ ይቀመጣል ሕዝቦች ኹሉ በፊቱ ይሰበሰቡና እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ እርሱም ሕዝቦችን ይለያል ፤ በጎቹን በቀኙ ፍየሎቹን ደግሞ በግራው ያቆማቸዋል ።» (ማቴ. ም. ፳፭ ቍ. ፴፩—፴፫)

«ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ።» (ማቴ ም. ፳፭ ቍ. ፴፬)

«በዚያን ጊዜ በግራው በኩል ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል — እናንተ ርጉማን ፣ ለሰይጣን እና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ኺዱ ።» (ማቴ. ም. ፳፭ ቍ. ፵፩)

ታናናሾችንና ታላላቆችን ሙታን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ ፣ መጻሕፍትም ተከፈቱ ፣ የሕይወት መጽሐፍ የኾነ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ ሙታንም በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው ሥራቸው መሠረት ፍርድ ተቀበሉ ባሕርም በውስጡ ያሉትን ሙታን ሰጠ ፣ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ውስጥ የነበሩትን ሙታን ሰጡ ፤ እያንዳንዱም ሰው በሥራው መሠረት ፍርድ ተቀበለ ።» (ራ ዮሐ፡ ም. ፳ ቍ. ፲፪—፲፫)



ምንም እንኳ በሙታን መነሣት የሚያምኑ ቢኾኑ መንግሥተ ሰማይ ወይም የጻድቃን መኖሪያ እንጂ ገሃነመ እሳት ወይም የኀጢአተኞች መኖሪያ ዘላለማዊ አይደለም በማለት የሚክዱ ወገኖች አሉ ። እንደእነርሱ አባባል አንድ ነገር ወደ እሳት ውስጥ ከተጣለ ተቃጥሎ ያልቃል እንጂ ምንም አይተርፍም ። እንዲሁም በትንቢተ ሕዝቅኤል ም. ፲፰ ቍ. ፬ ላይ «ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ራስዋ ትሞታለች ፣ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲ ቍ. ፳፰ ላይ ደግሞ «ይልቅስ ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ ።» የሚሉትንና ሌሎችንም ተመሳሳይ ጥቅሶችን በመጥቀስ የኀጢአተኛ ነፍስ ከሥጋው ጋር ትሞታለች እንጂ ዘላለማዊ ስቃይ የለም በማለት ይከራከራሉ ።

ከትንሣኤ ሙታን በኋላ ጻድቃንም ኾኑ ኀጢአተኞች እንደየሥራቸው ተፈርዶላቸው ወይም ተፈርዶባቸው እየተደሰቱ ወይም እየተሰቃዩ ለዘላለም ይኖራሉ እንጂ የኀጢአተኛው ነፍስ ከመኖር ወደ አለመኖር ትዛወራለች የሚለው አባባል ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርት አይደለም ።

ገሃነመ እሳት ዘላለማዊ መኾኑን ከሚገልጹት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«ወጥተውም በእኔ ያመፁብኝ ሰዎች ሬሳቸውን ያያሉ ፤ ትላቸው አይሞትምና ፣ እሳታቸውም አይጠፋምና ፤ ለሥጋ ለባሽም ኹሉ አስጸያፊ ነገር ይኾናሉ ።» (ኢሳ ም. ፷፮ ቍ. ፳፬)

«በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹ ደግሞ ወደ ዕፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቍልና ።» (ዳን. ም. ፲፪ ቍ. ፪)

በሉቃስ ወንጌል ም. ፲፮ ቍ. ፲፱—፴፩ ላይ አልአዛር ስለተባለው ድኻና ስለባለጸጋው በተሰጠው ምሳሌ ተኰናኙ ሰው በእሳት ውስጥ እየተቃጠለ ዕረፍት ማጣቱን እንጂ ተቃጥሎ የጠፋ መኾኑን የሚያመለክት አይደለም ።

«ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግንባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል... ቢኖር ...በቅዱሳን መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሰቃያል ። የስቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከዘላለም

ድረስ ይወጣሉ ፤ ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበሉ ኹሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም ። «(ራዮሐ. ም. ፲፬ ቁ. ፱—፲፩)

ሥ— ሺሕ ዓመት ፤

በራእየ ዮሐንስ ም. ፳ ቁ. ፩—፮ ላይ « የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ ። የቀደ መውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው ሺሕ ዓመትም አሰረው ወደጥልቅም ጣለው ፤ አሕዛብንም ወደፊት እንዳያስት ሺሕ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል ዙፋኖችንም አየሁ ፤ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው ስለኢየሱስም ምስክርነትና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት ፤ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግንባራቸውና በእጆቻቸው ላይ ያላደረጉትን አየሁ ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺሕ ዓመት ኖሩና ነገሡ ። የቀሩት ሙታን ግን ይህ ሺሕ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም ። ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው ። በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው ። ኹለተኛው ሞት በእነርሱም ላይ ሥልጣን የለውም ። ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይኾናሉ ። ከእርሱም ጋር ይህን ሺሕ ዓመት ይነግሣሉ ። ሺሑም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል» የሚለውን ጥቅስ መሠረት በማድረግና ይህን አባባል ቃል በቃልም በመውሰድ ጌታ ለመጨረሻው ፍርድ ከሚገለጽበት ቀን በፊት ከቅዱሳኑ ጋር ሺሕ ዓመት በዚህ ዓለም ላይ ሥጋዊ ንግሥ ይነግሣል የሚሉ ወገኖች አሉ ።

በወንጌልና በልዩ ልዩ መልእክቶች ስለ ጌታችን ዳግመኛ መም ጣት በተነገረበት ጊዜ ኹሉ ማንም ሊያውቀው በማይችልበት ጊዜ ለመጨረሻው ፍርድ አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚመጣ እንጂ በቅድሚያ ለሺሕ ዓመት ምድራዊ ንግሥ እንደሚመጣ አልተነገረም ።

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሕማሙና ስለ ሞቱ በሦስተኛው ቀን ከሞት የሚነሣ ስለመኾኑ የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ የሚሰጠው ስለመኾኑ ፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ አላውቀውም ብሎ የሚክድ ስለመኾኑ ፣ ስለኢየሩሳሌም መፍረስ ፣ ከዕርገቱ በኋላ መንፈስ



ቅዱስን የሚልክላቸው ስለመኾኑ ፣ በመጨረሻው ዘመን ለፍርድ ተመ ልሶ የሚመጣ ስለመኾኑና ስለሌሎችም ልዩ ልዩ ጉዳዮች አስቀድሞ በግልጽ የተናገረ መኾኑን በመመስከር ወንጌላውያን መዝግበውታል ። አንዳንዶቹን ጉዳዮች አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሳይኾን ጌታ በየጊዜው መላ ልሶ ተናግሮአቸዋል ። ማንም እንደፈለገ ሊረዳው በማይችለው በራእይ መጽሐፍ ማስረጃነት ተንሥተው ጌታ ለሺሕ ዓመት ምድራዊ ንግሥ ይነግሣል የሚሉት ወገኖች አባባል ትክክል ቢኾን ኖሮ ይህን የሚያ ኽል ታላቅ ሃይማኖታዊ ትንቢት አንድ ጊዜ እንኳ በጌታ ሳይነገር ባልታለፈም ነበር ። ምናልባት እርሱ ተናግሮት ወንጌላውያን ሳያቀ ርቡት ቀሩ እንዳይባል አራታቸውም ረሱት ለማለት የማይመስል አባባል ከመኾኑም በላይ የመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ያልተለያቸው መኾኑንም መዘንጋት የለብንም . (፪ኛ ጢሞ. ም. ፫ ቁ. ፲፮) ይህም ብቻ ሳይኾን ከዐሥራ አራቱ የጳውሎስ መልእክቶች ፤ ከኹለቱ የጴጥሮስ መልእክቶች ከሦስቱ የዮሐንስ መልእክቶች እንዲሁም ከያዕቆብና ከይሁዳ መልእክቶች በአንዳቸው ስንኳ የሺሕ ዓመት ምድራዊ ንግሥ ጉዳይ አልተጠቀሰም ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ የጠቀሰው የሺሕ ዓመት ምድራዊ ንግሥ ጉዳይ ቃል በቃል የሚወሰድ መኾኑን አምኖበት ቢ ቢኾን ኖሮ በወንጌሉ ወይም ከሦስቱ መልእክቶች በአንዳቸው ሳይጠ ቅሰው ባላለፈም ነበር ። እንዲያውም በዮሐንስ ወንጌል ም. ፭ ቁ. ፳፰ እና ፳፱ ላይ «በዚህ ነገር አትደነቁ ምክንያቱም በመቃብር ውስጥ ያሉት ኹሉ የእርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል መልካም የሠሩ ከሞት ተነሥተው በሕይወት ይኖራሉ ፤ ክፉ የሠሩ ግን ከሞት ተነሥተው ይፈረድባቸዋል» ብሎ የጌታን ቃል በሚመዘግብበት ጊዜ አምኖበትና በመንፈስ ቅዱስም ተመርቶ መኾኑ ግልጽ ነው ። የጥቅ ሱን አባባል የተመለከትን እንደኾነ በመቃብር ውስጥ ያሉት ኹሉ አንድ ጊዜ ተነሥተው ጻድቃን እንደጽድቃቸው ኀጢአተኞችም እንደ ኀጢአታቸው ዋጋቸውን ከመቀበላቸው በቀር የተወሰኑ ጻድቃን ቀድም ብለው ተነሥተው ከጌታ ጋር ሺሕ ዓመት ይነግሣሉ አልተባለም ። ይህም አባባል የዮሐንስን ትክክለኛ እምነት ያመለክተናል ።

ጌታም በዚህ ዓለም ላይ ምድራዊ ንግሥ እንደማይነግሥ ለጲላጦስ ሲያረጋግጥለት መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም ብሎታል ። (ዮሐ. ም. ፲፰ ቁ. ፴፮)

በራእየ ዮሐንስ ውስጥ የተመዘገበው ትንቢታዊ ራእይ በመኾኑና ትንቢትን ፡ ራእይንና ሕልምን ደግሞ ማነኛውም ሰው እንደፈለገ ሊተረጒመው ስለማይችል በዚሁ ምክንያት ራእይን የአንድ መሠረታዊ እምነት መነሻ ማድረግ አግባብ አይደለም ፤ ምክንያቱም ራእይና ትንቢት መንፈስ ቅዱስ የገለጸላቸው ሰዎች ካልተረጐሙት በቀር ትንቢቱ የሚፈጸምበት ጊዜ ደርሶ ከመፈጸሙ በፊት ሊታወቅ አይችልምና ። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ የሚከተለውን ማብራሪያ የሰጠው «ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ኹሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጕም አልተፈቀደም ፡ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ፡ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩ ። » (፪ኛ ጴጥ ም. ፩ ቍ. ፳—፳፩)

የትንቢትም ትርጒም በጣም ከባድ ከመኾኑ የተነሣ አንዳንድ ጊዜ ትንቢቱን ለተናገሩት ሰዎች እንኳ ምሥጢር የሚኾንበት ጊዜ መኖሩን ለመገንዘብ በትንቢተ ዳንኤል ም. ፲፪ ቍ. ፰—፱ እና በትንቢተ ዘካርያስ ም. ፩ ቍ. ፬-፮ መመልከት እንችላለን ።

ራእይንና ሕልምን ማንም ሰው ሊተረጒማቸው ባለመቻሉ ነው የፈርዖንን ሕልም ለመተርጐም ጻድቁ ዮሴፍና የናቡከዳነፆርን ሕልም ለመተርጐም ደግሞ ነቢዩ ዳንኤል ያስፈለጉት ። (ዘፍ፡ ም. ፵ ዳን ም. ፪)

በትንቢተ ሚልክያስ ም. ፬ ቍ. ፭—፮ በኤልያስ ስም የተነገረው ትንቢት ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተነገረ መኾኑን ጌታ የገለጸው የትንቢት አባባል ቃል በቃል የሚወሰድ ባለመኾኑ ነው ። (ማቴ. ም. ፲፯ ቍ፡ ፲—፲፪)

አንዳንድ አባቶች እንደተረጐሙት ይህ ሺሕ ዓመት የተባለው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በምእመናን አድሮ ከፍተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የሚፋጠንበትና በዚህም ሰይጣን ድል የሚኾንበት አንድ የተወሰነ የጊዜ ርዝመት በመኾኑና በክርስቲያናዊ እምነት አማካይነት የሰይጣን ተንኰል ድል በመነሣቱ ክርስቶስ በምድር ላይ ነገሠ ተባለ ። ይህም ማለት ፈቃዱ በሰማይ እንደኾነች እንዲሁም በምድር ኾነች ማለት ነው ። ቅዱሳኑም በክርስቶስ ትምህርት ተግባራዊነት ሰይጣንን ድል በመንሣታቸው ከክርስቶስ ጋር ነገሡ ተባለ እንጂ ምድራዊያን ነገሥታት የሚነግሡት ዐይነት ንግሥ ይነግሣሉ ማለት አይደለም ።



ሌሎች ምሁራን ደግሞ በራእየ ዮሐንስ የአንድ ሺሕ ዓመት ንግሥ ምን ማለት እንደኾነ ለማወቅ የሚቻለው ወደፊት ጊዜው ደርሶ ሲፈጸም ነው እንጂ አሁን እኛ በፈቃዳችን እንደዚህ ነው ወይም እንደዚያ ነው ብለን ለመተርጐም አንችልም ብለዋል ።

## ምዕራፍ ዐሥራ ኹለት

### እምነትና ሕግጋት

እምነትና ሥራ ለመዳናችን አስፈላጊ የሚኾኑበት ምክንያት ጻድቅ ወደመኾን ደረጃ የሚያደርሱን ኹለቱም በአንድነት በእኛ ዘንድ የተገኙ እንደኾነ ብቻ መኾኑን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው ነው ። ይኹን እንጂ ለመዳን የሚረዳን እምነታችን ብቻ እንጂ ሕግ ፈጻሚነታችን አይደለም ምክንያቱም ጻድቅ ወደ መኾን ደረጃ ለመድረስ ምክንያት ሊኾን የሚችለው እምነት ብቻ በመኾኑ ነው ፤ ሕግ ፈጻሚነት ግን የእምነት ውጤትና በጽድቅ ምክንያት የሚመጣ እንጂ ራሱ ጽድቅን እና መዳንን የሚያስገኝ አይደለም የሚሉ ወገኖች አሉ ። እነርሱም ለክርክራቸው ማስረጃ አድርገው ከሚያቀርቡአቸው ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን የሚያጸድቀው የሕግን ሥራ በመፈጸሙ ሳይኾን በእምነት መኾኑን እንገነዘባለን ። (ሮሜ. ም. ፫ ቊ. ፳፰)

«አብርሃም በእግዚአብሔር ስላመነ እምነቱ ፤ ጽድቅ ኾኖ ተቈጠረለት ።» (ሮሜ. ም. ፬ ቊ. ፫)

«እንግዲህ እኛ ጽድቅን ያገኘነው በእምነት ስለኾነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን ።» (ሮሜ ም ፭. ቊ. ፩)

ሐዋርያው ጳውሎስ የሕግንና የእምነትን ጉዳይ በማንሣት ብዙ ሊተችባቸው የበቃው አይሁድ ያለ እነርሱ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሊኾን የሚችል ሕዝብ እንደሌለ ያምኑ ስለነበረ በተለየም የሙሴን ሕግጋት በእምነት ሳይኾን በዘልማድና ለሌላ ሰው ጻድቅ ለመምሰል ይፈጽሙት ስለነበረና ይህንንም በማድረጋቸው ሕግ ፈጻሚዎች ነን በማለት ስለሚመኩ ሰው የሚድነው እናንተ በምትመኩበት በሙሴ ሕግ ሳይኾን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተሐድሶ



ነው ብሎ ለማስረዳት አስቦ ነው ። አይሁድ ይመኩበት ከነበረው ሕጋቸው አንዱ ግዝረት ስለነበረና ያልግዘረት ወደ ክርስትና የገቡት አሕዛብ በምንም ከአይሁዳውያን ክርስቲያኖች የማያንሱ መኾናቸውን ሲያመለክት አብርሃም እምነቱ ጽድቅ ኾኖ የተቈጠረለት ከመገረዙ በፊት መኾኑን ቅዱስ ጳውሎስ ወደሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፬ ቊ. ፲ ላይ ገልጾታል ።



ከፈሪሳዊው ይልቅ ቀራጩ ጻድቅ ኾኖ የተመለሰበት ምሳሌ (ሉቃ ም. ፲፰ ቊ. ፲፬)

ስለ እምነትና ስለ ሕግጋት ተመላልሶ የተተቸበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ሕግጋቱን መፈጸም የሚጠበቅብን ግዴታ መኾኑ የታወቀ

ቢኾንም ይህን ግዴታችንን መፈጸም ብቻ ለመንግሥተ ሰማያት ብቁ እንደሚያደርገን በማመን መመካት የማይገባን መኾኑን እንድንገነዘብ ስለተፈለገ ነው ። ይህም ማለት እግዚአብሔር ከሚያደርግልን ምሕረት ጋር የእኛ ሕግ ፈጻሚነት ሊወዳደር አይችልም ማለት ነው ። ለምሳሌ ሕግን በመፈጸሙ የሚመካና የሚመጻደቅ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ እንደሌለው መድኀኒታችን በምሳሌ ሲናገር አንድ ፈሪሳዊና አንድ ቀራጭ ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ ወጥተው ሳለ ፈሪሳዊው ሕግጋቱን እንደሚፈጽም በመዘርዘር በሚመጻደቅበት ጊዜ ቀራጩ ስለ ኀጢአቱ ከእግዚአብሔር ይቅርታ ይለምን እንደነበር ያስረዳና በመጨረሻም ከፈሪሳዊው ይልቅ ቀራጩ እንደጸደቀ ይገልጻል ። (ሉቃ. ም. ፲፰ ቍ. ፱—፲፬)

በሌላ በኩል ደግሞ ብዙዎቹ የሙሴ ሕግጋት ለክርስቲያን ሃይማኖት ግዴታ እንዳልኾኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ገልጸዋል ። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ ም. ፲፭ ቍ. ፳፬—፳፮ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ተሰብስበው ወደ አንጾኪያ በላኩት መልእክት «ያላዘዝናቸው ሰዎች ከእኛ ወጥተው ትገረዙ ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጡአችሁ ስለሰማን ስለጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነፍሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር የተመረጡትን ሰዎች ወደ እናንተ እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ኾነን ፈቀድን» ይላል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፪ ቍ. ፲፬—፲፭ እንዲህ ብሏል ።

«ለያይቶን የነበረውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰና አይሁዳውያንንና አረማውያንን አንድ ያደረገ ሰላማችን ክርስቶስ ነው ። ሰላምንም በማድረግ ከኹለቱ ሕዝቦች ከእርሱ ጋር የሚተባበር አንድ አዲስ ሕዝብ ለመፍጠር የሕግን ትእዛዞችና ደንቦች በሥጋው ሻረ ።»

ወደ ዕብራውያን በላከው መልእክቱ ም. ፯ ላይ ደግሞ የጌታችን ክህንት በመልከጼዴቅ ክህነት የሚመስል መኾኑን ካስረዳ በ[illegible]ላ መልከጼዴቅ በኦሪቱ ሕግ ከተወሰነው ክህነት ከተፈቀደላቸው ከሌዊ ነገድ ውጪ ብቻ ሳይኾን እንዲያውም ሕግ ከተሰጣቸው ከእስራኤል ወገን ያልኾነ ሰው መኾኑንና ይህም ከነበረው ሕግ የተለየ በመኾኑ ሕጉም በዚሁ አንጻር ተሽሮ በአዲስ ሕግ ተለውጦአል ማለት



ነው በማለት ይገልጻል ። በተለየ ግን ሕግንና እምነትን በሚያነጻጽር በት ጊዜ ለክርስቲያን ሃይማኖት አስፈላጊ ያልኾኑትን የሙሴን ሕግጋት ፤ ማለቱ ለመኾኑ ለገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፪ ቍ. ፳፩ ላይ «ሰው የሚጸድቀው የሙሴን ሕግ በመፈጸም ከኾነማ ክርስቶስ የሞተው በከንቱ ነው ማለት ነው» ብሏል ።



የሳሌም ወይም የሰላም ንጉሥ የተባለው መልከጼዴቅ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር እርሱም አብርሃምን ባረከው አብርሃምም ዓሥራት አውጥቶ ሰጠው ። ይህ መልከጼዴቅ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነበር. ። (ዕም. ፯)

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ በሕግና በእምነት ላይ ያለው አስተሳሰብ በዚህ ዐይነት ነው እንጂ ሕግ ቀርቶ እምነት ብቻ ማለቱ አይደለም ።

የምንድነው በእምነት ብቻ ነው የሚሉት ሰዎች ማስታወስ የሚገባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ ።

አንደኛ/ ሰው የሚድነው በእምነት ብቻ ከኾነ የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና ሕግጋት ኹሉ ዋጋ እንደሌላቸው መቍጠራቸው ነው ። ለእግዚአብሔር ትእዛዛትና ሕግጋት ተገዢ መኾን ወይም አለመኾን ምን ውጤት እንደሚያመጣ ለመገንዘብ የሚከተሉትን ጥቅሶች እን መልከት ።

«በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ኹሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም ።» (ማቴ ም. ፯ ቁ. ፳፩)

«ወደ ሕይወት ትገባ ዘንድ ብትፈልግ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ ።» (ማቴ ም፡ ፲፱ ቁ. ፲፯)

«እውነት እውነት እላችኋለሁ ማንም ቃሌን ቢጠብቅ ለዘላለም ሞትን አያይም ።» (ዮሐ . ም. ፰ ቁ. ፶፩)

«ብትወዱኝስ ትእዛዞቼን ጠብቁ ።» (ዮሐ. ም. ፲፬ ቁ. ፲፭)

ኹለተኛ/ በእምነት ብቻ እንጸድቃለን ማለት በተግባራችን መሠረት ዋጋ የሚሰጥበትን የእግዚአብሔርን የፍርድ መመዘኛ እንደ መቃወም ይቈጠራል ። ፍርዳችንን የምንቀበለው እንደየሥራችን መኾኑን ከሚገልጹት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«እግዚአብሔር ለያንዳንዱ እንደየሥራው ይሰጠዋል ።» (ሮሜ. ም. ፪ ቁ. ፮)

«እያንዳንዱ በሥጋው ላደረገው ክፉም ኾነ ደግ ነገር እንደየሥራው ዋጋውን ለመቀበል ኹላችንም በ፡ርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለብን ።» (፪ኛ ቆሮ ም. ፭ ቁ ፲)

«አገልጋይም ኾነ ጌታ እያንዳንዱ በሠራው መልካም ሥራ ከጌታ ኢየሱስ ዋጋውን የሚቀበል ለመኾኑ እርግጠኞች ኹኑ ።» (ኤፌ. ም. ፮ ቁ. ፰)

«እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ። ለያንዳንዱም እንደየሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ ።» (ራ. ዮሐ ም፡ ፳፪. ቁ. ፲፪)



ሦስተኛ/ ሰው ሊጸድቅ የሚችለው በእምነቱ ብቻ ነው እንጂ በበጎ ተግባሩ ወይም ለእግዚአብሔር ሕግጋት ተገዢ በመኾኑ አይደ ለም በሚባልበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያቀረበውን ቃለ እግ ዚአብሔር እንደመቃወም ይቈጠራል ።

ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ም. ፪ ቁ. ፲፬፡፲፯፡፲፱፡፳፩ እና ፳፮ ላይ በማያሻማ ቋንቋ ሲገልጸው እንዲህ ብሏል ።

«ወንድሞቼ ሆይ ፥ ሰው እምነት አለኝ ቢል ነገር ግን እምነቱን በመልካም ሥራ ባይገልጸው ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ከመልካም ሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው ። አንተ አንድ እግዚአብሔር አለ ብለህ ታምናለህ ይህም መልካም ነው ። ማመንማ አጋንንትም ያምናሉ ፥ በፍርሃትም ይንቀጠቀጣሉ ። አባታችን አብር ሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲኾን ባቀረበው ጊዜ በሥራው አልጸደቀምን? ከነፍስ የተለየ እም ነት የሞተ ነው ፤ እንዲሁም ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው ።»

ስለዚህ ከላይ በተዘረዘሩት ማስረጃዎች መሠረት ሰው ሊጸድቅ የሚችለው በእምነት እና በበጎ ተግባር ነው እንጂ በእምነት ብቻ አለ መኾኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ

ሀ— <u>መ ግ ቢ ያ ፤</u>

ነጻ ፈቃድ ማለት አንድ ሰው አንድን ድርጊት ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ያለው የፍላጎት ነጻነት ነው ። የሰው ልጅ ሊያስመሰግን ወይም ሊያስወቅስ ፥ ዋጋ ሊያስጥ ወይም ሊያስቀጣ ፥ ሊጐዳ ወይም ሊጠቅም የሚችለውን አድራጎት ለማድረግም ኾነ ላለማድረግ ነጻ ፈቃድ አለው ። አንድን ድርጊት የሚያደርገው ወይም የማያደርገው ማንም ሳያስገድደው በፍላጎቱ ነው ።

የሰው ልጅ የፈቃድ ነጻነት ባይኖረው ኖሮ የእግዚአብሔር ሕግ ጋትና ፍርድ መኖር ባላስፈለጋቸው ም ነበር ። የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ያለው መኾኑን ከሚያመለክቱት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉትን ኹለት ጥቅሶች እንመልከት ።

አንድ ሰው ወደጌታ ቀርቦ የዘላለም ሕይወት ለመውረስ ምን ላድርግ ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ጌታ በሰጠው መልስ ወደመንግሥተ ሰማይ ለመግባት ከፈለግህ ትእዛዛትን ጠብቅ ብሎታል ። ከፈለግህ የሚለው ቃል ለሰው ልጅ የተሰጠውን የፈቃድ ነጻነት ያመለክተናል ። (ማቴ ም. ፲፱ ቍ. ፲፮—፲፯)

«ነቢያትን የምትገድዪ ፥ ወደ አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ ኢየሩሳሌም ፥ ኢየሩሳሌም ሆይ ዶሮ ጫጩቶቿን በክንፎችዋ ሥር እንደምትሰበስብ እኔም ልጆችሽን ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ ሞከርኩ ፥ አንቺ ግን ፈቃደኛ አልኾንሽም ።» (ማቴ. ም. ፳፫ ቍ. ፴፯)

ፈቃደኛ ላለመኾን ያለውን ነጻ ፈቃድ እናስተውል ።



ለ— <u>የተከራካሪዎች ተቃውሞና ለክርክሩ የተሰጠ መልስ ፤</u>

ፈጣሪ አምላክ ያለሌላ የፍርድ መመዘኛ አስቀድሞ በመምረጥ ሊያጸድቅ የሚፈልገውን ሰው እንደሚያጸድቀውና ሊኰንን የሚፈልገውን ሰው ደግሞ እንደሚኰንነው በማመን ከሚቀርቡት የመከራከሪያ ጥቅሶች መካከል ቀጥለው የተዘረዘሩት ይገኙባቸዋል ።

«እኔ የፈርዖንን ልብ አጸናሁ ።» (ዘፀ ም ፯ ቍ፡ ፫)

«ይቅር የምለውን ይቅር እላለሁ ፤ የምምረውንም እምረዋለሁ ።» (ዘፀ. ም. ፴፫ ቍ. ፲፱)

«ኀጥአን ከማኅፀን ጀምረው ተለዩ ከሆድም ጀምረው ሳቱ ፤ ሐሰትንም ተናገሩ ።» (መዝ ፶፰ ቍ. ፫)

«የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ ፤ በሆድ ሳል ሠራህ አውቄሃለሁ ፤ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ፤ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ ።» (ኤር. ም. ፩ ቍ. ፬—፭)

«አንተ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር ምን መብት አለህ? ሸክላ ሠሪውን ለምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ሊለው ይችላልን? ከአንድ ዐይነት የሸክላ ጭቃ አንዱን ዕቃ ለክብር ሌላውን ዕቃ ደግሞ ለውርደት ለመሥራት መብት የለውምን?» (ሮሜ ም. ፱ ቍ. ፳—፳፩)

«ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን ኾነን በፊቱ እንድንገኝና ልጆቹ እንድንኾን ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን ።» (ኤፌ ም. ፩ ቍ. ፬)

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን ልዩ ልዩ ጥቅሶች ለማስረጃነት በምናቀርባቸው ጊዜ የጉዳዩን አመጣጥና አካኼድ እንደሁም እነዚያ ጥቅሶች የተጠቀሱባቸውን ምክንያቶች ተረድተን እንጂ በነጠላቸው ብቻ የወሰድናቸው እንደኾነ ቤተ ክርስቲያን ያወገዘቻቸው ብዙዎቹ መናፍቃን የደረሰባቸው ክስረት እንዳይደርስብን መጠንቀቅ ይኖርብናል ።

የቅዱሳት መጻሕፍትን ልዩ ልዩ ክፍሎች ትክ ብለን ብናስተውል ስለአንዳንድ ሰዎች የወደፊት ኹናቴ በቅድሚያ የሚነገርበት ምክንያት እነዚያ የተነገረላቸው ወይም የተነገረባቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ረገድ ወደፊት ምን ዐይነት ሰዎች እንደሚኾኑ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለሚታወቁ ነው እንጂ ያለምክንያት አይደለም ።

ለምሳሌ ኤርምያስን በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ብሎታል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፰ ቍ. ፴ ላይ» አስቀድሞ ያወቃቸውን ጠራቸው ።» ብሏል ።

ሐዋርያው ጴጥሮስ «በእግዚአብሔር አብ አስቀድማችሁ ለታወቃችሁትና ለተመረጣችሁት» ብሏል ። (፩ኛ ጴጥ ም ፩ ቍ. ፪)

እኔ የፈርዖንን ልብ አጸናሁ ያለው በመልእክተኞቹ በሙሴና በአሮን አማካይነት የምልክበትን ማስጠንቀቂያ እስካልተቀበለ ድረስ ልቡን እንዳጸና እተወዋለሁ ማለት እርሱ የፈለገውን ግትርነት አልከለከውም ማለቱ ነው እንጂ ለእምቢተኛነቱና ለግትርነቱ ምክንያት እኾነዋለሁ ማለቱ አይደለም ። ፈርዖንም ወደፊት ምን ዐይነት ሰው እንደሚኾን አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ በመኾኑ በቅድሚያ ስለእርሱ ተነግሮአል (ጥበ. ም. ፲፱ ቍ. ፩—፫)

ለምሕረትና ለይቅርታ ተገቢ ኾኖ የሚገኘውን ሰው ኹሉ አምላክ ምሕረትና ይቅርታ ያደርግለታል ። ለምሕረትና ለይቅርታው ላልተዘጋጀ ሰው ግን ይቅርታ አይደረግለትም ። ስለዚህ ነው የምምረውን እምረዋለሁ ይቅር የምለውንም ይቅር እለዋለሁ ያለው ። (ዘፀ. ም. ፴፫ ቍ. ፲፱)

ሐዋርያው ጳውሎስ የሰውን ልጅ በሸክላ ሥራና እግዚአብሔርን ደግሞ በሸክላ ሠሪነት መስሎ የተናገረው የእግዚአብሔርን ኹሉን ቻይነትና የሰውን ልጅ ውሱንነት ሲያነጻጽር ነው እንጂ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ያለምንም የፍርድ መመዘኛ የሚያጸድቀው ወይም የሚኰንነው ኾኖ አይደለም ።



ሐ— <u>ለኹሉም እንደየሥራው ፤</u>

እግዚአብሔር ሰውን በሥራው እንጂ ያለሥራው የማይመርጠውና የማያጸድቀው ወይም የማይኰንነው መኾኑን በግልጽ ለመረዳት የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት ።

«ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና በምድር ከሚኖሩ አሕዛብ ኹሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትኾንለት ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር መረጠህ እግዚአብሔር የወደዳችሁ ከአሕዛብ ኹሉ በቍጥር ስለበዛችሁ አይደለም ። እናንተ ከአሕዛብ ኹሉ በቍጥር ጥቂቶች ነበራችሁና ነገር ግን እግዚአብሔር ስለወደዳችሁ ፤ ለአባቶቻችሁም የማለላቸውን መሐላ ስለጠበቀ ስለዚህ እግዚአብሔር በጽኑ እጅ አወጣችሁ ፤ ከባርነትም ቤት ከፈርዖን እጅ አዳናችሁ ።» (ዘዳ ም. ፯ ቍ. ፮—፰)

በኦሪት ዘፀአት ከምዕራፍ ፯ እስከ ፲፬ ድረስ በሚነበበው ቃለ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ እንዴት ኾኖ ከፈርዖን ጭቆና ነጻ እንዲወጣ የተደረገ መኾኑን እናነባለን ። ከዚያም በኋላ እስራኤላውያን ወደተስፋ ምድር ከመድረሳቸው በፊት በተዋጉአቸው ጦርነቶች በእግዚአብሔር ዕርዳታ ከእነርሱ በሕዝብ ብዛት በልጠው የሚገኙትን አገሮች ያሸነፉ ሲኾኑ በአንጻሩም ደግሞ እግዚአብሔርን ቅር በሚያሰኙበት ጊዜ ኹሉ በጠላቶቻቸው እጅ ይሸነፉ እንደነበረ ተገልጾአል ።

የእስራኤል ሕዝብ ከሌላ ሕዝብ ተለይቶ ተመራጭ የኾነበት ምክንያት ቀደም ተብሎ የተገለጸ ሲኾን ተመራጭ ሕዝብ ኾኖ ለመኖር ከፈለገ ደግሞ ግዴታዎችን ማክበር ያለበት መኾኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ቀጥለን እንመለከት ።

«ነገር ግን ዛሬ እንደኾነ ለአባቶችህ የማለውን ቃል ኪዳን ያጸና ዘንድ ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጕልበት ሰጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ ። አምላክህን እግዚአብሔርን ብትረሳ ሌሎችንም አማልክት ብትከተል ፤ ብታመልካቸውም ፤ ብትሰግድላቸውም ፈጽሞ እንደምትጠፋ እኔ ዛሬውን እመሰክርባችኋለሁ ። የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ስላልሰማችሁ እግዚአብሔር ከፊታችሁ እንደሚያጠ

ፋቸው እንደ አሕዛብ እንዲሁ እናንተም ትጠፋላችሁ ።» (ዘዳ. ም. ፰ ቍ. ፲፱—፳) )

የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቆ በኖረ ጊዜ ኹሉ በሰላም ኖሮአል ፤ ጠላቶቹም ሊቋቋሙት አልቻሉም ነገር ግን



የቅዱስ ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ መመለስ (የሐዋ. ሥ. ም. ፱)

ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ባፈነገጠ ጊዜ ኹሉና በነቢያት አማካይነት የሚቀርብለትን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ባለመቀበል በኀጢአት ጸንቶ በቈየ ጊዜ ኹሉ በጠላቶቹ እጅ ተሸንፈ ፣ ተማረከ ፤ ተበታትኖ ተዋረደ ።



በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ የነበረው ሙሴን የመሰለ ታላቅ ነቢይ በመሪባ ውሃ ጉዳይ እግዚአብሔር ቀጣው እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደና የተመረጠ ስለነበረ አልማረውም

በምሳሌነት የሚጠቀሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ የነበረውን ዳዊትን የመሰለ ታላቅ ንጉሥና ነቢይ በኦርዮ ላይ ባደረሰው ግፍ ምክንያት እግዚአብሔር የልጅ ጠላት አስነሥቶ በማዋረድ ቀጣው እንጂ አንድ ጊዜ ተመርጦአል በማለት አልማረውም ።

ጌታ መርጦአቸው ከነበሩት ዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት መካከል የአስቆሮቱ ይሁዳ በኀጢአቱ ተለየ እንጂ አንድ ጊዜ ተመርጦአልና ምርጥ እንደኾነ ይቀራል አልተባለም ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያንነትን ለማጥፋት ብዙ ጥረት ካደረገ በኋላ እንደገና በተቃራኒው የክርስትናን ሃይማኖት ለማስፋፋት ወስኖ ከአሳዳጅነት በተመለሰ ጊዜ ነው ያለፈው በደሉ ይቅር ተብሎ አንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመኾን የበቃው ።

ብዙዎች ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሳይመለሱ ከኀጢአታቸው የሚሞቱ ሲኾኑ ሐዋርያው ጳውሎስ ግን ከኀጢአቱ እንዲሞት የእግዚአብሔር ፍላጎት ስላልነበረ አምላክ ራሱ በጉዳዩ በቀጥታ በመግባት ከቤተ ክርስቲያን አሳዳጅነት ወደ ሐዋርያነት እንዲመለስ ማድረጉ አስቀድሞ የመረጠው መኾኑን ስለሚያሳይ ይህ ኹናቴ የእግዚአብሔር ምርጫ በፍላጎቱ ነው እንጂ በተመራጩ ተገቢ መኾን አይደለም ብሎ የጥርጣሬ ሐሳብ የሚሰነዝር ይኖር ይኾናል ።

እግዚአብሔር ግን በተለይ ቅዱስ ጳውሎስን ብቻ ሳይኾን ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም ። ማንኛውም ሰው እንዲጠፋ የማይፈልግ በመኾኑ የመዳኛውን መንገድ ያዘጋጅለታል ።

ከዘመን ኦሪት የጀመርን እንደኾነ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከገነት መካከል ያለችውን የዛፍ ፍሬ የበሉ እንደኾነ ስለሚሞቱ እንዳይበሉ አስጠንቅቆአቸው ነበር ። ማስጠንቀቂያውን ችላ ብለው የተከለከለውን ፍሬ በመብላታቸው የሞትን ፍርድ በራሳቸውና በሰው ዘር ኹሉ ላይ አመጡ ። (ሮሜ ም. ፭ ቍ. ፲፪ እና ፲፫)

አቢሜሌክ የተባለው ንጉሥ በአብርሃም ሚስት ላይ ኀጢአት ከሠራ እንደሚፈረድበት እግዚአብሔር ባስጠነቀቀው ጊዜ ማስጠንቀቂያውን ተቀብሎ ኀጢአት ከመሥራት በመገታቱ የእግዚአብሔርን ይቅርታ አግኝቶአል ። (ዘፍ ም. ፳ ቍ. ፯ እና ፲፯)

የነነዌ ከተማ ሰዎች በኀጢአታቸው ምክንያት እንዳይጠፉ ነቢዩን ዮናስን በላከላቸው ጊዜ በንስሓ ተመልሰው የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስለለመኑ ምሕረት አግኝተዋል ። (ዮና. ም. ፫ ቍ. ፲)

በዚህ ጉዳይ ላይ ሌሎችም ብዙ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ይቻላል ።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የሚያውቀው መልኩን ብቻ ሳይኾን ኹለንተናውን መኾኑን የሚያስረዱ ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያሉ ሲኾን ጥቂቶቹን እነሆ ።

«እግዚአብሔር ልብን ኹሉ ይመረምራል ፤ የነፍስንም ሐሳብ ያውቃል ።» (፩ኛ ዜ. መ. ም. ፳፰ ቍ. ፱)

«ሰው ፊትን ያያል ፡ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል ።» (፩ኛ ሳሙ. ም. ፲፮ ቍ. ፯)

«እግዚአብሔር የልብን ምሥጢር ያውቃል ።» (መዝ. ፵፬ ቍ. ፳፩)

«የእናንተስ የራስ ፀጉራችሁ እንኳ የተቈጠረ ነው ።» (ማቴ. ም፲ ቍ. ፴)

በዚህም መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ለኦሪት ሕግ በጣም ታማኝ በመኾን የክርስትናን ሃይማኖት ያሳድድ የነበረው በቅን ልቡና እግዚአብሔርን ያስደሰተ መስሎት ነው እንጂ የክርስትናን ሃይማኖት ትክክለኛነት ዐውቆ ያላደረገው መኾኑን የሰውን ጥልቅ አስተሳሰብ የሚያውቀው ጌታ ስለተመለከተው ለቅዱስ ጳውሎስ ስሕተተኛነቱን ገለጸለት ። እርሱም የተገለጸለትን እውነት በመቀበል ወደጌታ ተመለሰ እንጂ እንደነፈርያን ልቡን አላጸናም ። የተሰጠውንም ማስጠንቀቂያና የተነገረውን እውነት ተቀብሎ ወደጌታ መመለሱ የልቡን ቅንነት



ያመለክታል ። በዚሁ በቅን አስተሳሰቡ ተመረጠ እንጂ ያለምክንያት የተመረጠ አይደለም ።

መ— <u>የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች</u> ፤

የሰው ልጅ የሚመረጠው ወይም የሚጸድቀው ያለዚያም የሚኰነነው በእምነቱና በሥራው ነው እንጂ ሥርዐት በሌለው ኹናቴ አለመኾኑን ከሚገልጹት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

«ጌታ ሆይ ፡ ጌታ ሆይ ፡ የሚለኝ ኹሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት አይገባም ። ወደመንግሥተ ሰማያት የሚገባው ግን በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚፈጽም ነው ።» (ማቴ ም. ፯ ቍ. ፳፩)

«ወደሕይወት መግባት ብትፈልግ ግን ትእዛዞችን ጠብቅ ። (ማቴ. ም፣ ፲፱ ቍ. ፲፯)

«ነገር ግን እናንተ ንስሓ ባለመግባታችሁና እልኸኞች በመኾናችሁ የእግዚአብሔር ቁጣ በሚገለጽበትና ትክክለኛ ፍርዱ በሚሰጥበት ቀን ኀይለኛ ቅጣት ይጠብቃችኋል ። እግዚአብሔር ለኹሉም እንደ የሥራው ይፈርዳል ።» (ሮሜ. ም. ፪ ቍ. ፭—፯)

«እንግዲህ ከእነዚህ ክፉ ነገሮች ተለይቶ መኖር ለተከበረ አገልግሎት የሚውልና ለጌታው የተቀደሰና ጠቃሚ ዕቃ መኾን ማለት ነው ። (፪ኛ ጢሞ. ም. ፪ ቍ. ፳፩)

አንዳንድ ጊዜ ከሚቀርቡ ጥያቄዎች መካከል እግዚአብሔር አምላካችን ኹሉን ቻይ፡ደኅንነትን እንጂ ችግርን ፣ ልማትን እንጂ ጥፋትን የማይወድ እንደመኾኑ ለምን ሰው ኹሉ እንዲድን ወይም እንዲጸድቅ እንጂ እንዳይጠፋ ወይም እንዳይኰነን አላደረገም ብለው የሚጠይቁ ሰዎች አሉ ።

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከፈጠረ በኋላ በዓለም በፈጠረው ፍጥረት ኹሉ ላይ የበላይነትን ሰጥቶታል በኦሪት ዘፍጥረት ም ፫ ቍ. ፳፪ ላይ ደግሞ የሰው ልጅ ጥቅሙንና ጉዳቱን ማለት ደጉንና ክፉውን ለይቶ የማወቅ ችሎታ ያለው መኾኑ ተገልጾአል ።

# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## የቅዱሳን አማላጅነት

አማላጅነት ማለት ከጌታ ጋር በቀጥታ ለመነጋገር ብቁ አይደ ለሁም በሚል የትሕትና አስተሳሰብ በዚህ ረገድ የእግዚአብሔር ጸጋና ክብር በተሰጣቸውና ለማማለድም ብቁዎች በኾኑ መላእክትና ጻድቃን አማካይነት እግዚአብሔርን መለመንና አማላጁም በበኩሉ ስለእኛ የእግዚአብሔርን ይቅርታ መለመን ማለት ነው ።

ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ ፤ ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም ፤ እኔ በር ነኝ ፤ በእኔ በኩል ካልኾነ በቀር ማንም ወደአብ ሊመጣ አይችልም ብሎ መድኀኒታችን በየጊዜውና በልዩ ልዩ ኹናቴ ያረጋግጣቸውን አባባሎች በመመልከት ከአማላጅነት ጋር ተቃራኒ የሚመስላቸው ሰዎች ይኖሩ ይኾናል ። (ማቴ ም. ፱ ቍ. ፲፫ ፤ ም. ፲፩ ቍ. ፳፰ ዮሐ ፤ ም. ፲ ቍ. ፱ ፤ ም. ፲፬ ቍ. ፯)

እነዚህ ጌታ የሰጣቸው መግለጫዎች የሚያመለክቱት የሃይማኖ ታችን መሠረቱ ስለጌታ ሰው መኾን መታመም መሞት ከሙታን ተለይቶ መነሣት ወደሰማይ ወጥቶ በክብር ዙፋኑ ላይ መቀመጥና ዳግመኛ ተመልሶ ለፍርድ ወደዚህ ዓለም የሚመጣ መኾኑን ማመን ለማለት ነው እንጂ ከአማላጅነት ጋር ግንኙነት አለው ለማለት አይደ ለም ።

እንዲሁም በመዝሙር ፻፵፭ ቍ. ፫-፬ ላይ «ማዳን በማይችል በሰው ልጅ አትተማመኑ ፤ ነፍሱ ትወጣለች ወደመሬቱም ይመለሳል ፤ ያን ጊዜ ምክሩ ኹሉ ይጠፋል» የሚለውንና በትንቢተ ኤርምያስ ም. ፲፯ ቍ. ፭ ላይ «በሰው የሚተማመን ርጉም ነው ።» ተብሎ የተጠቀሰውን ከአማላጅነት ጋር ተቃራኒ አስመስሎ ለማቅረብ ይሞከር ይኾናል ። እግዚአብሔርን ትቶ በሰው ልጅ ላይ እምነትን መጣልና በእግዚአብሔርና በአንድ ኀጢአተኛ መካከል ገብቶ አማላጅ እንዲ



ኾን አንዱን ቅዱስ መለመን ኹለት የተለያዩ ኹኔታዎች ናቸው ። አማላጅነት ማለት ደግሞ የእግዚአብሔርን ክብር ለሌላ መስጠት ሳይኾን በበለጠ እግዚአብሔርን ማክበር መኾኑን ልንረዳው ይገባል ።


እኔ በቀጥታ ወደ ጌታ ፊት ለመቅረብ ብቁ አይደለሁም ብሎ እግዚአብሔር ባከበራቸው መላእክትና ቅዱሳን አማካይነት መጸለይ የእግዚአብሔርን ክብር ለፍጡር አሳልፎ መስጠት አይደለም ። ይህም ባለመኾኑ ነው ጌታ «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል ።— ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል ፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ያገኛል» በማለት ያረጋገጠው ። (ማቴ ም. ፲ ቍ. ፵—፵፩)

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደጢሞቴዎስ በላከው በመጀመሪያ መል እክቱ ም. ፪ ቍ. ፭ ላይ «አንድ እግዚአብሔር አለ ፤ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለው ማእከላዊ አገናኝ አንድ ነው ፤ እርሱም ሰው የኾነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ።» የሚለው ጥቅስ ከቅዱስን አማላጅ ነት ጋር ተቃራኒ ሊመስለን አይገባም ። የጌታችን አማላጅነት ከ ጥንቱ የአዳም ኀጢአት ነጻ ለማውጣት የተደረገ ሰውንና እግዚአብ ሔርን ማስታረቅ በመኾኑ ከፍጡር አማላጅነት ጋር ተመሳሳይ አይደ ለም ። ይህም ማንኛውም ፍጡር ሊያከናውነው የማይችል ቤዛነት በመኾኑ ይህን ቤዛነት መላእክትም ኾኑ ቅዱሳን የማይችሉት አማላ ጅነት ነው ።

ቅዱሳን በዚህ ዓለም የሚደርሰውን ኹናቴ ሊያውቁ ስለማይችሉ አማላጅነታቸውን የሚፈልጉ ሰዎች በሚለምኑአቸው ጊዜ እንዴት ሊረዱአቸው ይችላሉ ተብሎ ይጠየቅ ይኾናል ። ቅዱሳን በዚህ ዓለም የሚደርሰውን ኹናቴና የሰውን አስተሳሰብ የሚያውቁት በተፈጥሮ ዕውቀታቸው ሳይኾን በእግዚአብሔር ፈቃድና በመንፈስ ቅዱስ እር ዳታ ነው ። ለምሳሌ ሐናንያና ሰጲራ የተባሉ ባልና ሚስት ቤተ ክርስ ቲያንን ለማታለልና ለመዋሸት በምሥጢር መስማማታቸውን ሐዋር ያው ጴጥሮስ እንዴት ለማወቅ እንደቻለ በሐዋርያት ሥራ ም. ፭ ቍ. ፩—፲፩ እንመልከት ።

በምድር ላሉ ቅዱሳን እንደዚህ አድርጎ ዕውቀትን የሚገልጽላ ቸው ከኾነ በሰማይ ላሉትማ የበለጠ እንደሚገልጽላቸው መገንዘብ ይኖርብናል ። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን አባባል ሲያብራራ እንዲህ

ብሏል ፤ «አሁን በመስታወት እንደምናየው ዐይነት በድንግዝግዝ እናያለን በዚያን ጊዜ ግን እግዚአብሔር እኔን የሚያውቀኝን ያኽል ሙሉ ዕውቀት ይኖረኛል ።» (፩ኛ ቆ ሮ ም. ፲፫ ቍ. ፲፪)



ሐናንያና ሰጲራ የደረሰባቸው የእግዚአብሔር ቅጣት (የሐ ሥ. ፭ ቍ. ፩—፮)

በንጉሥ ሳኦል ላይ የሚደርሰውን ችግር ነቢዩ ሳሙኤል ዘርዝሮ የነገረው ነቢዩ ራሱ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ መኾኑን በ፩ኛ ሳሙ ም. ፳፰ ቍ. ፲፫—፲፱ እንመልከት ። እንዲሁም የሰማይ መላ እክት በምድር ያሉ ኀጢአተኞች በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱ ዐውቀው የሚደሰቱ መኾናቸውን በሉቃስ ወንጌል ም. ፲፭ ቍ. ፲ እንመልከት ።

በእነዚህም ማስረጃዎች መሠረት በምድር ላይ ያለውን ኹናቴና የእኛንም ፍላጎት በሰማይ ያሉ ቅዱሳን እንደሚያውቁ ተገንዝበን አያውቁም የሚለውን ጥርጣሬ ከአስተሳሰባችን ማስወጣት አለብን ።



ስለቅዱሳን አማላጅነት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የሚ ከተሉት ናቸው ።

በኦሪት ዘፀአት ም. ፴፪ ቍ. ፲፩—፲፭ በሚነበበው ቃለ እግዚአብ ሔር ፈጣሪ አምላክ በእስራኤል ላይ ተቈጥቶ ሊያጠፋቸው በነበረ ጊዜ በሙሴ አማላጅነት የዳኑ መኾናቸውን እንመልከት ።

በኦሪት ዘኍልቍ ም. ፲፪ ላይ ማርያም በወንድምዋ በሙሴ ላይ ባመፀች ጊዜ እግዚአብሔር በለምጽ በሽታ ስለቀጣት ሙሴ አማላጅ ኾኖ ከጸለየላት በኋላ መዳንዋ ተገልጾአል ።

ሰሎሞን እግዚአብሔርን በመበደሉ እርሱ ከሞተ በኋላ መንግ ሥቱ ለኹለት እንደሚከፈል እግዚአብሔር ቢነግረውም ለባሪያዬ ለዳዊት ስል ግን ለአንተ አንድ ነገድ አስቀርልሃለሁ ያለው መኾኑን በ፩ኛ ነገሥት ም. ፲፩ ቍ. ፲፪ እንመልከት ።

በ፪ኛው መጽሐፈ ነገሥት ም. ፲፱ ቍ. ፴፩ እና ም. ፳ ቍ. ፮ ላይ ስለባሪያዬ ስለዳዊት ይህችን ከተማ አድናታለሁ ብሎ እግዚአብ ሔር አምላክ የዳዊትን አማላጅነት በገለጸ ጊዜ ዳዊት ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ ብዙ ዘመናት አልፈው ነበር ።

በትንቢተ ዘካርያስ ም. ፩ ቍ. ፲፪ እና ፲፮ ብንመለከት የእግዚአብ ሔር መልአክ ስለኢየሩሳሌም ይቅርታ ለምኖ ልመናውንም እግዚአብ ሔር እንደተቀበለው እናነባለን ።

እነዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የቅዱሳን አማላጅ ነት እንዴት በእግዚአብሔር ዘንድ የተደገፈ መኾኑን ያረጋግጡልናል ።

የቅዱሳን አማላጅነትም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ብቻ ሳይኾን እንዲያውም እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ አማላጅ የመራ በት ጊዜ አለ ።

ለምሳሌ ሦስቱ የኢዮብ ወዳጆች የኢዮብን አማላጅነት እንዲሹ እግዚአብሔር ነግሮአቸዋል ። የባሪያዬን የኢዮብን ጸሎት ስለምቀ በል እንዲጸልይላችሁ ወደ እርሱ ኺዱ ብሎአቸዋል ። (ኢዮ፪ም. ፵፪ ቍ. ፰)

ለአቢሜሌክ እግዚአብሔር ይቅርታ ያደረገለት አብርሃም ዘንድ ኼዶ እንዲጸልይለት እግዚአብሔር ካመለከተውና አብርሃምም ከጸለየለት በኋላ ነው ። (ዘፍ ም. ፳ ቍ. ፯)

ሙሴና ሳሙኤል ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ ከብዙ ዘመን በኋላ «ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም ልቤ ወደዚህ ሕዝብ አያዘነብልም አለኝ» ብሎ ነቢዩ ኤርምያስ በትንቢቱ ም. ፲፭ ቍ. ፩ ላይ መስክሮአል። ይህም የሚያመለክተው ሙሴና ሳሙኤል ለእስራኤል ሕዝብ እያማለዱ የነበሩ መኾናቸውን ነው ።

ይህንኑ እውነት ንጉሥ ሰሎሞን በጥበብ መጽሐፉ በግልጽ ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል ፡ «ጸጋውና ምሕረቱ ከቅዱሳን ጋር እንደኾነና የተመረጡትንም እንደሚያከብራቸው ይህን ሰዎቹ አይተው አልተረዱትም ፡ በአእምሮአቸውም አላኖሩትም ። ስለዚህ የሞተው ጻድቅ ባልሞቱት ኀጢአተኞች ላይ ይፈርዳል ።» (ጥበ. ም ፬ ቍ. ፲፭—፲፮)

ስለዚህ ከላይ በተረዘረዘሩት መግለጫዎችና ማስረጃዎች መሠረት ቤተ ክርስቲያን በመላ እክትና በቅዱሳን አማላጅነት ታምናለች ፤ ይህንኑም ታስተምራለች ።



# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት
# ቅድስት ድንግል ማርያም



ወላዲተ አምላክ

## ሀ— ድንግልናዋ ፤

የእመቤታችን የወላዲተ አምላክ ድንግልና ከጥንት ጀምሮ የታመነበትና እንዲያውም ድንግል የሚለው ቃል ለእርስዋ መጠሪያ መኾኑ የተለመደ ኾኗል ።

ጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው እመቤታችን ጌታን ከመውለድዋ በፊት ፣ በምትወልድበት ጊዜና ከወለደችም በኋላ ድንግል መኾንዋን ነው ። መድኀኒታችን ከማሕፀንዋ ሲወጣ ድንግልናዋ እንደተጠበቀ የቈየው ፀሐይ በመስታወት ውስጥ አልፎ ሲገባ መስታወቱ ምንም ጉዳት የማይደርስበት ከመኾኑ ጋር ተመሳሳይ ነው ። ፀሐይ መስታወቱን አልፎ ይገባል መስታወቱ ግን እንደነበረ ይቀራል እንጂ አይሰበርም ወይም አይሰነጠቅም ። በዚሁም ዐይነት ምንም እንኳን እመቤታችን ጌታን በማሕፀንዋ ፀንሳ የወለደችው መኾንዋ የታወቀ ቢኾን ይህ መፅነስ ግን በእግዚአብሔር ተአምር ያለወንድ ዘር እንደመኾኑ ማኅተመ ድንግልናዋም በመውለድዋ ጊዜም ኾነ ከወለደች በኋላ አልተለወጠም ። ስለዚህም ነው ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ እመቤታችን ዘላቂ ድንግልና ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ትንቢት የተናገረው ።

«ወደ ምሥራቅም ወደ ሚመለከተው በስተውጪ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ። በሩም ተዘግቶ ነበር ። እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ፤ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራ አለኝ ።» (ሕዝ. ም. ፵፬ ቊ. ፩ –፪)

ኾኖም በትንቢተ ኢሳይያስ ም ፯ ቊ. ፲፬ ላይ የተነገረው ትንቢት ድንግልናን አያመለክትም በማለት ፣ የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ተብሎ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፩ ቊ. ፳፭ ላይ በመገለጹ ፣ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲፫ ቊ. ፶፭ - ፶፮ ላይ ጌታ የዮሴፍ ልጅ ፣ የያዕቆብ ፣ የዮሴፍ ፣ የስምዖንና የይሁዳ ወንድም ነው ብለው አይሁድ ፣ በመናገራቸው በአንዳንድ ወገኖች በኩል በጠቅላላው የእመቤታችንን ድንግልና በመካድና በሌሎች ወገኖች በኩል ደግሞ ጌታን ከወለደች በኋላ ማኅተመ ድንግልናዋ ያልተጠበቀና እንዲያውም ዮሴፍን አግብታ ሌሎች ልጆችን እንደወለደች አስመስለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ። የተከራካሪዎቹም የመከራከሪያ ሐሳቦችና ለክርክሮቹም የተሰጡት መልሶች የሚከተሉት ናቸው ።

በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፯ ቊ. ፲፬ ላይ ፣ «ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ፣ ይሰጣችኋል ፣ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፤ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች » ተብሎ ስለጌታ ልደት የተነገረውን ትንቢት የክርስትና ጠላቶች የመድኀኒታችንን



ያለወንድ ዘር መወለድ ታሪክ ዋጋ እንዳይኖረው ለማድረግ ሲሉ የሚያቀርቡት ትችት የሚከተለው ነው ።

በዕብራይስጡ ቋንቋ «አልማ» የሚለው ቃል ወጣት ሴት ልጅ ማለት ስለኾነ ይህች ወጣት ድንግል ልትኾን ወይም ድንግል ላትኾን ማለት ባል ያገባች ወይም ባል ያላገባች ልትኾን ስለምትችል በጥቅሱ ላይ የተመለከተው ድንግልናን አያመለክትም በማለት ይከራከራሉ ።

በጥቅሱ ላይ የተመለከተው ። «አልማ» የሚለው ቃል በመጽሐፈ ምሳሌ ም. ፴ ቊ. ፲፰ እና ፲፱ ላይ ከተነገረው ጋር ተመሳሳይ ነውና ድንግልና ማለት ለመኾኑ ምንም ማስረጃ የለም ይላሉ ።

የመጽሐፈ ምሳሌው አባባልም እንደሚከተለው ነው ፤

«ከአስተሳሰቤ በላይ የኾኑ ሦስት ነገሮች አሉ ፤ በውኑ ላስተውላቸው የማልችል አራት ናቸው ፣ እነርሱም በሰማይ ላይ የንስር መንገድ ፣ በቋጥኝ ላይ የእባብ መንገድ ፣ በውቅያኖስ መካከል የመርከብ መንገድ ፣ ከወጣት ሴት ጋር የወንድ መንገድ ።»

በዕብራይስጡ ቋንቋ «አልማ» የሚለው ቃል ወጣት ሴት ወይም ድንግል ተብሎ ሊተረጐም የሚችል በመኾኑ ብቻ የጉዳዩ አመጣጥ እንኳ ድንግልናን የሚያመለክት ቢኾን ስለድንግል የተነገረውን ባል ስላገባች ሴት እንደተነገረ አድርጎ ማቅረብ አግባብ አይደለም ።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በዕብራይስጡ ቋንቋ «አልማ» የሚለው ቃል የተነገረላቸውና ደናግል ልጃገረዶች የነበሩ ለመኾናቸው የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት ።

በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፳፬ ቊ. ፵፫—፵፬ «እነሆ ፣ እኔ በውሃው ምንጭ አጠገብ ቆሜአለሁ ፤ ውሃ ልትቀዳ ለምትመጣውም ልጃገረድ ጥቂት ውሃ ከእንስራሽ አጠጪኝ ስላት እርስዋም አንተ ጠጣ ደግሞም ለግመሎችህ እቀዳለሁ የምትለኝ እግዚአብሔር ለጌታዬ ልጅ ያዘጋጃት ሚስት እርስዋ ትኹን» በሚለው ጥቅስ ውስጥ ድንግል ተብሎ የተተረጐመው በመጀመሪያው ቋንቋ በዕብራይስጡ በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፯ ቊ. ፲፬ ላይ ድንግል ተብሎ ከተተረጐመው ጋር አንድ

የኾነው «አልማ» የሚለው ቃል ነው ። እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ጉዳይ የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት እንዲፈልግለት የተላከው አንዲት ባል ያላገባች ልጃገረድን እንጂ ባል ያገባች ወ ጣት ሴትን አለመኾኑን ነው

በኦሪት ዘፀአት ም. ፪ ቊ. ፰ ላይ «ብላቴናይቱም ኼ ዳ የሕፃኑን እናት ጠራች ።» ተብሎ ትንሽ ልጅ ስለነበረችው ስለሙሴ እኅት የተ ነገረው የዕብራይስጡ ቃል በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፯ ቊ. ፲፬ ላይ የተጠቀሰው «አልማ» የሚለው ቃል ነው ።

በመዝሙር ፷፰ ቊ. ፳፭ ላይ «ከበሮን በሚመቱ ልጃገረዶች መካከል ። የሚለው ቃል የዕብራይስጡ «አልማ» ነው ።

በመጽሐፈ መኀልይ ም. ፩ ቊ. ፫ ላይ ደናግል የሚለው ቃልና በምዕራፍ ፮ ቊ. ፰ ላይ ወጣቶች ሴቶች ልጆች ተብለው የተተረጐሙት በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፯ ቊ. ፲፬ ላይ ድንግል ተብሎ የተተረጐመው በዕብራይስጡ ቋንቋ «አልማ» የሚለው ቃል ነው ።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ኹሉ ወደልዩ ልዩ ቋንቋ ዎች ሲተረጐሙ አንድ ጊዜ ድንግል ፥ አንድ ጊዜ ወጣት ሴት ልጅ በሌላ ጊዜ ደግሞ ብላቴና ተብለው ተተርጒመዋል እንጂ ባል ያገባች ሴት ልጅ ተብለው የተተረጐሙበት ጊዜ የለም ።

ወንጌላውያን ማቴዎስና ሉቃስም በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት እንዴት ተፈጸሚነትን እንዳገኘ ሲያብራሩ ጌታችን መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለአባት ከእናት ብቻ መወለዱን በዝርዝር ገልጸዋል ። (ማቴ. ም. ፩ ቊ. ፲፰ ፥ ሉቃ. ም. ፩ ቊ. ፴፬—፴፭)

«እኔ ወንድ የማላውቅ ድንግል ስኾን እንዴት ልወልድ እችላ ለሁ «ብላ ድንግል ማርያም መልአኩን ቅዱስ ገብርኤልን በጠየቀችው ጊዜ የሰጣት መልስ ባል ካገባሽ በኋላ ትወልጂአለሽ ብሎ ሳይኾን «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኀይልም ይጸ ልልሻል » ብሎ ነው ። (ሉቃ. ም. ፩ ቊ. ፴፭)

በሌላ በኩል ደግሞ የጥቅሱን አባባል ብንመለከት ጌታ ምል ክት ይሰጣችኋል መባሉ ባል ያገባች ሴት ልጅ የወለደች እንደ



ኾነ እንዴት ምልክት ሊኾን ይችላል? ሴቶች ኹሉ የሚወልዱት ባል ካገቡ በኋላ እንደመኾኑ አንዲት ባል ያገባች ሴት በወንድ ዘር አማካይነት ልጅ የወለደች እንደኾነ ምልክት ሊኾን አይችልም ። ምልክት ተብሎ የተነገረውና ምልክትም ሊኾን የሚችለው ባል ያላገባች ወይም ከወንድ ጋር በግብረ ሥጋ ያልተገናኘች ድንግል ፀንሳ የወለደች እንደኾነ ብቻ ነው ።



ንጉሥ ዳዊት በግእዚአብሔር ታቦት ፊት ሲዘፍንና ሲዘልል ባየችው ጊዜ ንቃው የንቀት ንግግር በመናገርዋ የሳኦል ልጅ ሜልኮል እስከሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም ። (፪ኛ ም. ፮ ቊ. ፲፪—፳፫)

ስለዚህ ከላይ በቀረቡት መግለጫዎችና ማስረጃዎች መሠረት በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፯ ቊ. ፲፬ ላይ የተነገረው በዕብራይስጡ ቋ ንቋ «አልማ» የሚለው ቃል ድንግል እንጂ ባል ያገባች ሴት አለመ ኾንዋን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

በማቴዎስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፳፭ ላይ «የበኵር ልጅዋን እስክት ወልድ ድረስ አላወቃትም በመባሉ ከዚያ በኋላ ዐወቃት ለማለት ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ ።

እስከ የሚለው ቃል ተከራካሪዎቹ እንደሚሉት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል አይደለም ። ለምሳሌ የሳኦል ልጅ ሜልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወደችም ይላል ። (፪ኛ ሳሙ ም. ፮ ቍ. ፳፫) — ይህም ማለት እስከመቼም ድረስ አልወለደችም ለማለት ነው እንጂ ከሞተች በኋላ ወለደች ለማለት አለመኾኑ ግልጽ ነው ።

በመዝሙር ፻፲ ቍ. ፩ ላይ «እግዚአብሔር ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መረጋገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» ሲባል ጠላቶቹን ካሸነፈ በኋላ በቀኝ መቀመጡ ቀረ ማለት አይደለም ። ወደ ቆላስይስ ሰዎች በተላከው በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፪. ቍ. ፲፬—፲፭ ጌታችን በመስቀሉ ድል የነሣ መኾኑ የተነገረ ሲኾን በሐዋርያት ሥራ ም. ፯ ቍ. ፶፭ ላይ ደግሞ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ሰማዕት እስጢፋኖስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከእግዚአብሔር አብ ቀኝ ኾኖ ያየው መኾኑን ተናግሮአል ፤ ይህም የኾነው ጌታ ጠላቶቹን ድል ከነሣ በኋላ በመኾኑ እዚህ ላይ የተጠቀሰው እስከ ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው ።

በማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፰ ቍ. ፳ ላይ «እነሆ ፥ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ኹልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ያለው ከዓለም ፍጻሜ በኋላ ከእነርሱ ይለያል ለማለት አይደለም ።

በእነዚህና በሌሎችም እነዚህን በመሳሰሉ ኹኔታዎች እስከ የሚለው ቃል ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዳለመኾኑ እንዲሁም የእመቤታችን ድንግልና ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው ።

የበኵር ልጅዋን እስከወለደች ድረስ ከተባለ ሌሎች ልጆች ለመ ወለዳቸው ማስረጃ ነው ይላሉ ። በመጀመሪያ የተወለደ ልጅ በኵር ለመባል ሌላ ልጅ መወለድ አያስፈልገውም ። ማሕፀን የሚከፍት ኹሉ በኵር መኾኑንና በኵር ልጅ ሲወለድ ደግሞ የሚደረግ የተለየ ሥነ ሥርዓት መኖሩን በኦሪት ዘፀአት ም. ፲፫ ቍ. ፩—፪ ላይ ተገልጾአል ። ተከራካሪዎቹ እንደሚሉት በኵር ለመባል ሌሎች ልጆች መወለድ



ካለባቸው በእስራኤሎች ዘንድ በቤተ መቅደስ ለበኵር ልጅ ይደረግ የነበረው ሥርዐት ኹሉ ሌላ ልጅ እስኪወለድ ድረስ ማቈየት ነበረባ ቸው ማለት ነው ። እስራኤላውያን ግን ይህን አላደረጉም ። በሌላ በ ኩል ደግሞ «የበኵር ልጅዋን እስከወለደች ድረስ አላወቃትም» ያለው የእመቤታችንን ድንግልናና የጌታችንንም ያለወንድ ዘር መወ ለድ ሊያረጋግጥልን ፈልጎ ነው ። በመጽሐፉም አባባል በኵር ማለት በመጀመሪያ ከእናቱ ማሕፀን የወጣ ማለት ነው እንጂ ሌሎች ልጆች ለመወለዳቸው ማስረጃ አይደለም ። ለምሳሌ ወደዕብራውያን በተላ ከው በሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፩ ቍ. ፮ ላይ እግዚአብሔር ወልድ የእግዚአብሔር አብ የበኵር ልጅ የተባለው ከርሱ ሌላ ልጅ አለ ለማለት አይደለም ።

ስለዚህ ከላይ በተዘረዘሩት መግለጫዎችና ማስረጃዎች መሠረት በኵር ማለት ሌላ ልጅ ተወልዶአል ለማለት ማስረጃ አለመኾኑ ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲፫ ቍ. ፶፭—፶፮ «ይህ የዚያ የአንጨት ጠራቢው ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም አይደለችምን? ወንድሞ ቹስ ያዕቆብ እና ዮሳ ፥ ስምዖንና ይሁዳ አይደሉምን? እኅቶቹስ ኹሉ ከእኛ ጋር አይደሉምን? ያሉት » አጋንንትን የሚያስወጣው ብዔል ዜቡል ከሚባለው ከአጋንንት አለቃ ጋር በመስማማት ነው እንጂ በራሱ ኀይል አይደለም» ብለው በሌላ ጊዜ በመናገር የጌታን ክብር ያቃለሉ የመሰላቸው አይሁድ ናቸው እንጂ ሌሎች ወገኖች አይደሉም ። ስለዚህም ነው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ እንደዚህ ያለ ጽርፈት የሚና ገሩ ኹሉ በዚህ ዓለምም ኾነ በሚመጣው ዓለም ለኀጢአታቸው ይቅ ርታ አያገኙም ብሎ ጌታ ያረጋገጠው ። (ማቴ ም. ፲፪ ቍ. ፴፪—፴፪፥ ማር ም. ፫ ቀ . ፳—፴ ፥ ሉቃ ም. ፲፩ ቍ. ፲፬ —፳፫)

በጣም የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን አንዳንድ የክርስቲያን ወገኖች ከዚያ ከተጠቀሰው አባባል ግማሹን አምነው የሚቀበሉ መኾናቸው ነው ። ጌታ የዮሴፍ ልጅ ነው ተብሎ በአይሁድ የተነገረውን አባባል የማይ ቀበሉ ሲኾኑ እነያዕቆብ የጌታ ወንድሞች ናቸው የሚለውን አባባል ግን እውነት ነው ብለው ይቀበላሉ ።

እመቤታችን ጌታን ከወለደች በኋላ ድንግል እንደኾነች ኖረች እንጂ ሌሎች ወገኖች እንደ ሚሉት ዮሴፍን አግብታ ሌሎች ልጆችን

የወለደች አይደለችም ። ለዚህ አባባል ትክክለኛነት ከሚቀርቡት ማስ ረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

፭— በትንቢተ ኢሳይያስ ም. ፯ ቍ. ፲፬ ላይ «እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» አለ እንጂ ከዚያ በኋላ ባል ታገባለች አላለም ወይም ደግሞ ድንግል የሚለውን ስም አልነፈጋትም ።

፮— በትንቢተ ሕዝቅኤል ም. ፵፬ ቍ. ፩—፪ «ወደ ምሥራቅም ወደ ሚመለከተው በስተውጪ ወዳለው ወደመቅደሱ በር አመጣኝ ። በሩም ተዘግቶ ነበር ። እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም ፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል አለኝ ።» ይህ ትንቢት የድንግል ማርያምን ዘላቂ ድንግልና የሚያመለክት ነው ።

፯— ከምሥራቅ አገር ከመጡት የከዋክብት ተመራማሪዎች በተረዳው ዘመን መሠረት ሄሮድስ በቤተልሔም የሚገኙትን እስከ ኹለት ዓመት ዕድሜ ድረስ ያላቸውን ሕፃናት ማስገደሉ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፪ ቍ. ፲፮ ላይ ተገልጾአል ። ይህም የሚያመለክተው እነዚያ ሰዎች በመጡበት ጊዜ ጌታ ከተወለደ ኹለት ዓመት ኾኖት ነበር ማለት ነው።»እመቤታችን ዳግም ዮሴፍን የምታገባ ብትኾን ኖሮ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ባገባችው ነበር እንጂ ኹለት ዓመት ሙሉ ሳታገባው ባልዘገየችም ነበር ። የከዋክብት ተመራማሪዎች መጥተው እስከ ኼዱበት ጊዜ ድረስና እንዲያውም ከግብጽ ስደት መልስ እስከ ተደረገበት ጊዜ ድረስ ዮሴፍን ያላገባች መኾንዋ በሚከተሉት ጥቅሶች ግልጽ ኾኖ ተነግሮአል ።

«የከዋክብት ተመራማሪዎች ከኼዱ በኋላ የእግዚአብሔር መል አክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ ሄሮድስ ሕፃኑን ለመግደል ስለሚፈልግ ተነሥና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ኺድ ... አለው ። (ማቴ. ም. ፪ ቍ. ፲፫)

«ዮሴፍም በሌሊት ተነሣና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዞ ወደ ግብጽ ኼደ ።» (ማቴ. ም. ፪ ቍ. ፲፬)



«ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ በግብጽ አገር ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ ሕፃኑን ለመግደል የሚፈልጉት ሰዎች ስለ ሞቱ ፤ ተነሥና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ኺድ አለው ። ስለዚህ ዮሴፍ ተነሣና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዞ ወደ እስራኤል አገር ተመለሰ ።» (ማቴ. ም. ፪ ቍ. ፲፱—፳፩)

ዮሴፍ ድንግል ማርያምን እንዲጠብቅ በእግዚአብሔር የታዘዘ እንጂ ለእርስዋ ባል እንዲኾን ያልተወሰነ መኾኑ የሚታየው ሚስቱን ወይም እጮኛውን በማለት ፈንታ ሕፃኑንና እናቱን ማለቱ ነው ። እመቤታችን ጌታን ከመውለድዋ በፊት በማቴዎስ ወንጌል ም፩ ቍ. ፲፰ እና ፳፬ ላይ ፤ እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፳፯ እና ም. ፪ ቍ. ፭ ላይ የዮሴፍ እጮኛ ተብላ ስትጠራ ከቈየች በኋላ አሁን ያ አባ ባል ተለውጦ ሕፃኑና እናቱ መባሉ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዮሴፍ ለእመ ቤታችን ጠባቂዋ ለጌታ ደግሞ ሞግዚትና አሳዳጊው እንዲኾን የተወሰ ነለት መኾኑን ያመለክተናል ። ያለበለዚያ ግን እናቱን ከማለት ይልቅ እጮኛውን ወይም ሚስቱን ማርያምንና ሕፃኑን ኢየሱስን ማለት በቀለለ ነበር ።

፰— መልአኩ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም ተልኮ ልጅ እንደም ትወልድ ባበሠራት ጊዜ እኔ ድንግል ኾኜ ሳለ ይህ እንዴት ሊኾን ይችላል ብላ መጠየቅዋ ባል ላለማግባት የነበራትን ቍርጥ ሐሳብ ያመለክታል ። እንዲዚያ ባይኾን ኖሮ ባል ካገባሁ በኋላ ስለምወልደው ልጅ የተነገረኝ ትንቢት ነው ብላ ትቀበለው ነበር እንጂ ያን ጥያቄ ባልጠየቀችም ነበር ። የመልአኩም ብሥራት በተነገራት ጊዜ የዮሴፍ እጮኛ እንደነበረች ተገልጾአል ። ለእመቤታችን ጥያቄ መልአኩ ገብርኤል መልስ ሲሰጥ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፤ የል ዑልም ኀይል ይጸልልሻል» ከማለቱ በቀር ምነው እጮኛ አለሽ አይ ደለም ወይ አላላትም ። (ሉቃ ም. ፩ ቍ. ፴፭)

መፅነስዋም እንደታወቀ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ተገልጾለት ወደቤቱ እንዲወስዳት ያዘዘው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከሰዎች አሉባልታና ከችግር እንዲጠብቃት ነው እንጂ እንዲያገባት አይደለም ። ነፍሰ ጡር ሴትንም ማግባት የተለመደ አይደለምና ወደቤቱ የወሰዳት ለጥበቃ እንጂ ለጋብቻ አለመኾኑ መታወቅ አለበት ። ይህም በመ ኾኑ ነው ከዚያ በኋላ እጮኛውን ማለቱ ቀርቶ ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ማ ለት የጀመረው ። ጠባቂነቱም በእጮኛ ነት ስም የተደረገበት ምክንያት

ያው የተፈራው የአይሁድ አሉባልታ እንዳይመጣ ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ነው ።

፫— በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፱ ቊ. ፳፮ እና ፳፯ ላይ ጌታ ተሰቅሎ በነበረ ጊዜ እናቱን ለሚወደው ደቀ መዝሙር በአደራ ማስረከብና ደቀ መዝሙሩም ከዚያን ቀን ጀምሮ ወደቤቱ ይዟት መኼዱ የተነገረው ሌሎች ልጆች የሌሏት በመኾኑ ነው እንጂ ልጆች እያሏት ልጅዋ ወዳልኾነ ሰው ቤት ባልኼደችም ነበር ።

፬— ወንድሞች የተባሉት ያዕቆብና ይሁዳ በመልክቶቻቸው መክፈቻ ላይ ።

«የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ከኾነው ከያዕቆብ የተላከ መልእክት ።»

«የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕቆብ ወንድም ከኾነው ከይሁዳ ።»

ብለው ከመጀመር ይልቅ የጌታ ወንድሞች ሳይሉ ባላለፉም ነበር ። በተለየም ይሁዳ በያዕቆብ ወንድምነቱ ኩርቶ ሲናገር የጌታ ወንድምነቱ የበለጠ ባኰራው ነበር ።

ደግሞስ ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክ «አንቺ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ ፥ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ» ብሎ ክብርንና ምስጋናውን ያቀረበላት የአምላክ እናት እንዴት በእግዚአብሔር ከታደለችበት ከፍተኛ ክብር ተነሥታ ባል ወደማግባት ዝቅተኛ ደረጃ የመዛወር ፍላጎት አደረባት ተብሎ ይታመናል?

ስለዚህ እመቤታችን በአምላክ እናትነትዋ፥ ተከብራ የምትኖር ቅድስት እመቤት ነች እንጂ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲፫ ቊ. ፶፭ ላይ በተነገረው የአይሁድ አሉባልታ መሠረት የሲፍን አግብታ ሌሎች ልጆችን ያልወለደች መኾንዋን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ ።

ስለእነዚህ የጌታ ወንድሞችና እኅቶች ስለተባሉት ግን ቤተ ክርስቲያን ኹለት አማራጭ ትርጓሜዎች አሉአት ።



አንደኛ/ ጌታ ተሰቅሎ በነበረ ጊዜ በመስቀሉ አጠገብ ቆመው ነበር ተብሎ ስሞቻቸው ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል የእመቤታችን እኅት ማለት የቀለዮጳ ሚስት ማርያም ነበረችበት ። ይህችውም ማርያም ያዕቆብና ዮሳ የተባሉ ልጆች እንዳልዋት በማርቆስ ወንጌል ም. ፲፭ ቊ. ፵ እና ፵፯ በምዕራፍ ፲፯ ቊ. ፩ እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል ም. ፳፬ ቊ. ፲ ላይ ተጠቅሶአል ። በአይሁድ ልማድ እንዲያውም በብዙ የምሥራቅ አገሮች ልማድ የቅርብ ዘመድ የኾነ ሰው ወንድም ወይም እኅት መባሉ የተለመደ ባህል ነው ። ለምሳሌ ሎጥ የአብርሃም የወንድሙ ልጅ ሲኾን ወንድሙ መባሉን በኦሪት ዘፍጥረት ም. ፲፩ ቊ. ፳፯ እና ም. ፲፬ ቊ. ፲፯ መመልከት እንችላለን ። እንዲሁም ሴዴቅያስ የኢዮአኪን አጐት መኾኑ በኹለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ም. ፳፬ ቊ. ፲፯ የተገለጸ ኾኖ ሳለ በኹለተኛው ዜና መዋዕል ም. ፴፮ ቊ. ፲ ላይ ወንድሙ ተብሎ እናገኘዋለን ።

ኹለተኛ/ ሌሎች ምሁራን እንደሚሉት ደግሞ እነዚያ በጌታ ወንድምነትና እኅትነት የተጠቀሱት ሰዎች ዮሴፍ ከሚችት የቀድሞ ሚስቱ የወለዳቸው ናቸው ።

<u>የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት ፥</u>

<u>ቅዱስ ቴዎዶጦስ ፥ የዕንቄራ ኤጲስ ቆጶስ</u> ፥- «ዛሬ እግዚአብሔር ከቅድስት ድንግል ተወልዶ ታየ ። ድንግልም እንደ ቀድሞዋ በድንግልና ጸንታ ኖረች ። እናትም ተባለች ፤ ሕይወትን የሚለውጥ በድንግል ተፈትሐ ማሕፀንን አላመጣም ። (ሃይ አበ ገጽ. ፻፸፪)

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፥ የእንዚናዙ</u> ፥ ሥጋ የሌለው እርሱ ሥጋዋን ተዋሕዶ እንደ ሰው ኹሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በጌትነቱ ሳለ በማሕፀኗ ተወሰነ ፤ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀንም ከተፈጸመ በኋላ የሚወለድበት ቀን ቢደርስ በማይመረመር ግብር በኅቱም ድንግልና ተወለደ ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ተወለደ እንጂ ።» (ሃይ አበ ፥ ገጽ ፻፻፲፪)

<u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤</u> ከአዳም ጐን የጐድን አጥንት እንደነሣ አዳምንም አካል እንዳልጐደለው ፥ እንዲሁ ከድንግል የምትናገር የምታውቅ ነፍስ ያለችው ሥጋን ነሣ ፤ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም ፥ አዳም የጐድን አጥንት ከእርሱ ከተነሣ በኋላ አካል ሳይጐ

ድለው ፍጹም ኾኖ ኖረ ፡ ድንግልም ሕፃን ክርስቶስ ከእርስዋ ከተወለደ በኋላ እንዲሁም ያለመለወጥ በድንግልና ጸንታ ኖረች ።» (ሃይ አበ ፡ ገጽ ፪፻፵)

**ቅዱስ ሳዊሮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት** ፡ «አምላክን የወለደች ማርያም ለዘላለሙ ድንግል እንደኾነች መውለድዋም የማይመረመር ድንቅ እንደኾነ ከወለደችም በኋላ በድንግልና ጸንታ እንደኖረች አስረዳን ።» (ሃይ አበ ፡ ገጽ ፫፻፸፩)

**ለ— የአምላክ እናትነትዋ ፤**

የእመቤታችንን ድንግልና ብቻ ሳይኾን የአምላክ እናት መኾንዋን የሚክዱ አሉ ። እነርሱም የንስጥሮስና የመሰሎቹ ተከታዮች እንደመኾናቸው ትስብእት እንጂ መለኮት አይወለድም በሚል ምክንያት ይከራከራሉ ።

የአምላክ እናት ለመኾንዋና ከእርስዋ የተወለደውም የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ለመኾኑ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ያሉ ሲኾን ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥለን እንመለከት ።

«ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ።» (ሉቃ. ም. ፩ ቁ. ፴፭)

«ኤልሣቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ በታላቅ ድምፅ እን እንዲህ አለች ፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይኾንልኛል?» (ሉቃ.. ፩ ቁ. ፵፩—፵፫)

«የሃይማኖታችን ምሥጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው ። እርሱም እግዚአብሔር ሰው ኾኖ የተገለጠ ፡ እውነተኛነቱ በመንፈስ የታወቀ ለመላእክት የታየ ለሕዝቦች ኹሉ የተሰበከ ፡ በዓለም ያሉ ሰዎች ያመኑበት ፡ በክብር ወደ ሰማይ የወጣ የሚል ነው ።» (፩ኛ ጢሞ ም. ፫ ቁ. ፲፮)

«ነገር ግን የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከልን ፡ እርሱም ከሴት ተወለደ ለሕግም ታዛዥ ኾነ ።» (ገላ. ም. ፬ ቁ. ፬)



በእነዚህም ከላይ በተዘረዘሩት ማስረጃዎች መሠረት እመቤታችን የአምላክ እናት መኾንዋ የተረጋገጠ ከመኾኑም በላይ ጥንታዊዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ ያረጋገጡት እምነት ነው ።

### የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት ፤

**ቅዱስ ቄርሎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት** ፡— «አምላክን በምታገለግልበት በሹመትህ መናፍቃንን ልታወግዝበት የሚገባውን ነገር እነሆ ከዚች መልእክት በታች ጻፍኩልህ ፤ ዐማኑኤል የባሕርይ አምላክ እንደኾነ ንጽሕት ድንግልም አምላክን የወለደች እንደኾነች ፡ ሰው የኾነ የእግዚአብሔርንም ቃል እንደወለደች የማያምን ሰው ፡ ቢኖር ውጉዝ ይኹን ።» (ሃይ አበ ፡ ገጽ ፪፻፸፯)

«ዳግመኛ በኋላ ዘመን ቅድስት ድንግል እርሱን በሥጋ ወለደችው ፡ ስለ እኛ ሰው የኾነ እግዚአብሔር ቃልን ወለደችው ፡ስለ ዚህም ቅድስት ድንግልን ወላዲተ አምላክ እንላታለን ፤ ሰው ሳይኾን ሰውም ከኾነ በኋላ አንድ ወልድ አንድ ክርስቶስ ነው ፤ ከእግዚአብሔር አብ የተገኘ ቃል ሌላ አይደለም ፤ ከቅድስት ድንግል የተወለደውም ሌላ አይደለም ፤ የምናምንበት ከዓለም አስቀድሞ የነበረ ፡ ከድንግልም በሥጋ የተወለደ ይህ አንድ ወልድ ነው እንጂ ።» (ሃይ. አበ ፡ ገጽ ፫፻፷)

**ቅዱስ ሳዊሮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት** ። «ንጽሕት ድንግል በውነት አምላክን የወለደች እንደኾነች እንናገራለን ፡ እግዚአብሔር ቃል ከእርስዋ ሥጋን ተዋሕዶአልና ፡ ከመለኮትና ከትስብእት ከኹለቱ አንድ ኾኖ እርሷ ፀነሰችው፡ ወለደችው እንደ እውነተኛው ነገር ሥጋን የተዋሐደ ፡ እግዚአብሔር ቃል ተተዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ ገዥ ፡ አንድ ክርስቶስ እንደኾነ በዐማኑኤል እናምናለን ።» (ሃይ አበ ገጽ ፫፻፸፪)

**ሐ— ክብርዋ ፤**

መልአኩ ገብርኤል ያከበራትና ያመሰገናት ፡ በመንፈሱ ቅዱስ የተመላችው ኤልሣቤጥ ያከበረቻትና ያመሰገነቻት መኾኑ በቅዱሱ መጽሐፍ የተገለጸ ቢኾንም አንዳንድ ተከራካሪዎች ለምን ጥንታውያን አብያት ክርስቲያናት ለድንግል ማርያም ይህን ያኽል ክብር ይሰጡአታል ብለው ይከራከራሉ ።

ዓለማዊ ምሳሌ ብንወስድ የአንድን ንጉሥ ቤተሰብ የምናከብር በት ምክንያት የቤተሰቡ አባሎች በሙሉ በዙፋን የተቀመጡ ነገሥታት ስለኾኑ አይደለም ። የንጉሥን እናት የምናከብራት ንጉሡን በማክበ ራችን ነው ፤ የንጉሡን ባለሟሎች የምናከብራቸው ንጉሡን በማክበ ራችን ነው ። ጌታም ስለ እናቱ ክብር የማይገደው አይደለም ። ለደቀ መዛሙርቱ እንኳ «እናንተን የሚቀበል እኔን የተቀበለ ነው ፤ እናንተ ንም የሚንቅ እኔን የናቀ ነው» ብሎአቸዋል ።(ማቴ ም. ፲ ቍ. ፵ እና ሉቃ ም. ፲ ቍ. ፲፮)

ጌታ የሰውን ልጅ ሥጋ ከለበሰ በኋላ ከኀጢአት በቀር በኹሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሏል ። (ዕብ ም. ፪ ቍ. ፲፬—፲፯ ም. ፬ ቍ. ፲፭)

በአንድ በኩል ለሕግ ታዛዥ ኾነ ተብሎ ወደ ገላትያ ሰዎች በተላ ከው በሐዋርያው በጳውሎስ መልእክት ም. ፬ ቍ. ፬ ላይ በተነገረው መሠረት አባትህንና እናትህን አክብር የሚለውን ሕግ በመጠበቅ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰው የኾነ አምላክ በመኾኑና ሰብአዊ ስሜቱ እናቱን ወደመውደድና ወደማክበር ስለሚገፋፋው ኹሉም የእርሱን ፈለግ ቢከተልለት እንደሚመርጥ ለመገመት አያዳግትም ።

ቅዱሳት መጻሕፍት ከተጻፉባቸው ምክንያቶች መካከል በቅዱ ሳንና በደጋግ ሰዎች አማካይነት የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጽበትን ኹናቴ ለማሳየት እንጂ እነዚያን ደጋግ ሰዎች ለማሞገስ አይደለም ። የተከበረችው እመቤትና የአምላክ እናት በጊዜው ወጣትነት የነበራ ቸው ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ያደርጉት እንደነበ ረው የመፋለምና የመሯሯጥ እንቅስቃሴ ባለማድረጓ በየጊዜው ስምዋ አልተነሣም እንጂ ተገቢ የኾነው ክብር አልተነፈጋትም ። ስለ እመቤታችን ክብርና ምስጉንነት በቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና በልዩ ልዩ የቅዱሳን አባቶች ጽሑፎች ውስጥ ለመመልከት ይቻላል ።

ኾኖም በየጊዜው ተመላልሶ አልተደጋገመም ለማለት ካልኾነ በቀር መጽሐፍ ቅዱስ የእመቤታችንን ክብር ሳያመለክተን የቀረ አይደለም ። ለምሳሌ ዘካርያስ ልጅ ይወለድሃል ተብሎ በቅዱስ ገብር ኤል በተነገረው ጊዜ በእሁኑ በሽምግልና ዕድሜዬ ይህ እንዴት ሊኾን ይችላል ብሎ በመጠየቁ ልጁ እስከተወለደበት ጊዜ ድረስ በዱዳነት ተቀጣ ። ይህ በኾነ በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል እመቤታ ችንን ለማብሠር በተላከ ጊዜ እኔ ድንግል ኾኜ ይህ እንዴት ሊኾን



ይችላል ብትለው የሚኾንበትን መንገድ በአክብሮት ከመግለጹ በቀር እርስዋ በጠየቀችው ጥያቄ እንደ ዘካርያስ ያልተወቀሰችው ክብር የሚ ገባት የአምላክ እናት በመኾንዋ ነው ። መልአኩም ሰላም ላንቺ ይ ኹን ብሎ የአክብሮት ሰላምታ ካቀረበላት በኋላ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ ብሏ ታል ። (ሉቃ. ም. ፩)

በዕድሜዋ ትልቅ የነበረችውን ዘመድዋን ኤልሣቤጥን ለመጠየቅ እመቤታችን በኼደች ጊዜ የጠበቃት አቀባበል በዕድሜ ልጅ እግር ለኾነ ዘመድ የሚደረግ ዐይነት አቀባበል አልነበረም ። የእመቤታችንን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ከአክብሮቱ የተነሣ ፅንሱ በኤልሣቤጥ ማሕፀን ውስጥ ዘለለ ። ኤልሣቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ የጌታዬ እናት በማለት አከበረቻት ፤ አመሰገነቻት ።

ከዚያም እመቤታችን እግዚአብሔርን ስታመሰግን እነሆ ፣ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ኹሉ ያመሰግኑኛል ብላ ትንቢት ተናገረለች ።

ተከራካሪዎቹ እንደሚመስላቸው እመቤታችን ጌታን ከወለደች በኋላ የተተወች አይደለችም ። ለምሳሌ ጌታ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ እናቱን ለሚወደው ደቀ መዝሙር አደራ መስጠቱ የሚያስብላትና የሚጠነቀቅላት እንደነበረ ያመለክተናል ። (ዮሐ. ም. ፲፱ ቍ. ፳፭—፳፯)

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለእመቤታችን ተገቢ የኾነ ክብርዋን ትሰጣለች አማላጅነትዋን ታምናለች ፤ ይህንኑም ታስተምራለች ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

## ጾምና ጸሎት

ሀ. <u>መግቢያ</u>

ጾም ማለት ለአንድ ለተወሰነ ጊዜ ከማንኛውም ዐይነት ምግብ መከልከልና ከዚያም ከተወሰነው ጊዜ በኋላ የቅባት ምግብ በተለየም የእንስሳት ውጤቶችን አለመብላትና የሚያሰክር መጠጥ አለመጠጣት ማለት ነው ። (ዳን. ም. ፲ ቍ. ፪—፫)

ጸሎት ሲባል ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግን ፣ ልመናን ፣ ንስሓን ፣ ስእለትንና ምስጋናን ያመለክታል ።

ምንም እንኳ ነጻ ፈቃድ በሚለው ርእስ ሥር በተዘረዘረው መሠረት የሰው ልጅ ፍላጎቱን የመምረጥና የመወሰን ሙሉ ነጻነት ያለው መኾኑ ቢታወቅ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሰውነታችን መካከል ኀይለኛ ትግል የሚካኼድ መኾኑን ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፯ ቍ. ፲፬—፳፭ ዘርዝሮ ገልጾታል ። ይኹን እንጂ ለእግ አብዚሐር ፈቃድ ተገዝቶ ወደ ጽድቅ ጐዳና የመራመዱ ፍላጎት ካለ ሥጋዊውን ፍላጎት ለማሸነፍ እንድንችል በጾምና በጸሎት ኾነን የፈጣሪአችንን እርዳታ ከለመንን ልመናችንን ሰምቶ ፍላጐታችንን እንደ ሚፈጽምልን እርግጠኞች እንኹን ። ጸሎታችን ኹሉ ተቀባይነት የሚ ያገኝ መኾኑን መድኀኒታችን የገለጸው «ለምኑ ይሰጣችኋል ፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል» በማለት ነው ። (ማቴ. ም. ፯ ቍ. ፯)

በጾምና በጸሎት ጊዜ በተገቢው መንገድ የምንጾምና የምንጸልይ እስከኾን ድረስ እግዚአብሔር ከእኛ አይለይም ። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከኾነ ደግሞ ምንም ሊያሸንፈን የሚችል ኀይል አይኖርም ። (ሮሜ ም. ፰ ቍ. ፴፩)



በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን የጾምና የጸሎት ዐይነቶች ለመረዳት የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት ።

«ከጾም ፣ ከምጽዋትና ከጽድቅ ሥራ ጋር ጸሎት ጠቃሚ ነው ። ከጽድቅ ሥራ ጋር የሚጸለየው ትንሽ ጸሎት ያለጽድቅ ሥራ ከሚጸለየው ብዙ ጸሎት የተሻለ ነው ።» (ጦቢ. ም. ፲፪ ቍ. ፰)

«ምንም ላታየው ለምን ጾምን ? ምንም ላትመለከተው ለምን ራሳችንን አዋረድን ብለው ይጠይቃሉ ። እነሆ ፣ በጾማችሁ ቀን ፍላጎታችሁን ታደርጋላችሁ ፤ ሠራተኞቻችሁን ታስጨንቃላችሁ ፤ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ ፤ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ ። ዛሬ እንደምትጾሙት ያለ ጾም ድምፃችሁን ወደላይ አያሰማውም ። እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን ? ሰውስ ነፍሱን የሚያዋርደውና ራሱንም እንደ እንግጫ ዝቅ አድርጎ ማቅንና አመድን በበታቹ የሚያነጥፈው በእንደዚህ ያለ ኹናቴ ነውን ? ይህን ዐይነቱንስ ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን ? እኔ የመረጥሁት ጾም የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ ፣ የቀንበርን ጠፍር ትለቁ ዘንድ ፣ የተጨቈኑትን ነጻ ታወጡ ዘንድ ፣ ቀንበሩን ኹሉ ትሰብሩ ዘንድ ፣ እንጀራህን ከተራበ ሰው ጋር ትካፈል ዘንድ ፣ ቤት ለሌለው ድኻ መጠለያ ትሰጥ ዘንድ ፣ የተራቈተ ሰው ብታይ ታለብሰው ዘንድ ፣ የሥጋ ዘመድህንስ ፊት እንዳትነሣ አይደለምን ? የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደንጋት ያበራል ፤ ቍስልህም ፈጥኖ ይፈወሳል ፤ ጽድቅህም በፊትህ ይኼዳል ፤ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ኾኖ ይጠብቅሃል ፤ የዚያን ጊዜ ትጠራለህ ፤ እግዚአብሔርም ይሰማሃል ፤ ትጮኻለህ ፤ እርሱም እነሆኝ ይላል ።» (ኢሳ. ም. ፶፰ ቍ. ፫—፱)

ለ. <u>የጾምና የጸሎት ውጤት ማስረጃዎች</u>

ጾምና ጸሎትም በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያኽል ተቀባይነት እንዳላቸው ለመረዳት በተለያዩ ኹኔታዎች ሲደርሱ የነበሩ ችግሮች በጾምና በጸሎት አማካይነት ፈጣሪ አምላክ እንዳይደርሱ ያደረገ ለመኾኑ ቀጥለው የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች እንመልከት ።

<u>የመጀመሪያ ማስረጃ</u> ፦ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ረገድ በትክክል ይራመድ የነበረው ሕዝቅያስ የተባለው የይሁዳ ንጉሥ የመሞ

ታቸው ጊዜ የተቃረበ በመኾኑ ቤቱን እንዲያስተካክል በነቢዩ በኢሳይያስ አማካይነት ከእግዚአብሐር ተነገረው ። ንጉሥ ሕዝቅያስም የመሞቻው ጊዜ ሲነገረው ምርር ባለ ለቅሶ ልመናውን ለእግዚአብሔር ስላቀረበ እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቶ በመቀበል ዕድሜው በዐሥራ አምስት ዓመቶች እንዲራዘም ያደረገለት መኾኑን በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ም. ፳ እንመልከት ።

ኹለተኛ ማስረጃ ፦ አርጤክስስ በተባለው በፋርስ ንጉሥ ዘመነ መንግሥት ሐማ ለተባለ ሰው ከፍተኛ ሹመት ተሰጥቶት ነበር ። ለዚህም ሐማ ለተባለ ሰው የቤተ መንግሥቱ አሽከሮች ኹሉ እንዲሰግዱለት የንጉሡ ትእዛዝ ተላለፈ ። ከቤተ መንግሥቱ አሽከሮች መካከል መርዶክዮስ የተባለ አይሁዳዊ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አልሰግድም በሚል የጸና እምነት እንደሌሎቹ የቤተ መንግሥት አሽከሮች የማይሰግድለት መኾኑን ባወቀ ጊዜ ይህ ሐማ የተባለው ባለሥልጣን ንጉሡን አስፈቅዶ በግዛቱ ይገኙ የነበሩት የአይሁድ ወገኖች በሙሉ እንዲገደሉ ትእዛዝ አስተላለፈ ። በዚህም ምክንያት መርዶክዮስና በዚያን ጊዜ ንግሥት ኾና የነበረችው አስቴር የተባለችው የመርዶክዮስ የአጐት ልጅ ለአይሁድ ሕዝብ በመላ ጾምንና ጸሎትን አወጁ ። ሕዝቡም አዋጁን ሰምቶና ተቀብሎ በጾመና በጸለየ ጊዜ ለመርዶክዮስ አዘጋጅቶት በነበረው ግንድ ላይ ሐማ ራሱ እንዲሰቀል ከመደረጉም በላይ መርዶክዮስም ከንጉሡ ቀጥሎ ያለ ከፍተኛ ሹመትና ክብር ተሰጥቶት ሐማ ያስተላለፈው ውሳኔ እንዲሻር ተደረገ ። ኹናቴው በዚህ ብቻ ያቆመ ሳይኾን የሐማ ዐሥር ልጆችና የአይሁድ ሕዝብ ጠላት የኾነ ሰው ኹሉ እንዲገደል የተደረገ መኾኑን በመጽሐፈ አስቴር ከም. ፬ እስከ ፲ እንመልከት ።

ሦስተኛ ማስረጃ ፦ ዝነኛው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በነገሠ በኹለተኛው ዓመት ሕልም ካለመ በኋላ ሕልሙን ማስታወስ ስላቃተው መንፈሱ ታወከበት ። በዚያን ጊዜ የነበሩትን የባቢሎንን ጠቢባን ኹሉ ሰብስቦ ሕልሙን እንዲነግሩት ጠየቃቸው ። እነርሱም ሕልሙን ነግሮአቸው ለመተርጐም ካልኾነ በቀር ምን ሕልም እንዳለመ ሊነግሩት የማይችሉ መኾናቸውን በገለጡለት ጊዜ ኹሉም ተሰብስበው እንዲገደሉ ትእዛዝ አስተላለፈ ። በዚህ ጊዜ ነቢዩ ዳንኤል የንጉሡን ጥያቄ ለመመለስ ጊዜ ይሰጠው ዘንድ ከጠየቀ በኋላ ከጓደኞቹ ከአናንያ ፤ ከሚስኤልና ከአዛርያ ጋር ኾነው በመጸለይ ሕልሙ ከነትርጓሜው



ለዳንኤል ተገልጾለት ለንጉሡ በመናገሩ ለወገኖቹ ለአይሁድ ሕዝብ ዕረፍትን ከማስገኘቱም በላይ የባቢሎን ጠቢባንን ከሞት ፍርድ እንዲድኑ ረድቶአቸዋል ። (ዳን. ም. ፪)

አራተኛው ማስረጃ ፦ የነነዌ ከተማ ሰዎች በክፉ ሥራቸው እግዚአብሔርን ቅር አሰኝተው ስለነበረ በንስሐ የማይመለሱ ከኾነ ከተማቸው ከሦስት ቀኖች በኋላ የምትገለበጥ መኾንዋን የሚገልጽ የእግዚአብሔር ቃል ወደነቢዩ ዮናስ መጣ ። ይህንኑ የእግዚአብሔርን ውሳኔ ነቢዩ ዮናስ ለነነዌ ሰዎች በነገራቸው ጊዜ በንጉሡ አዋጅ መሠረት ሕዝቡ ራሱን ዝቅ አድርጎ በጾምና በጸሎት የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስለለመነ ሊደርስ የነበረው ቅጣት ሳይደርስ ቀርቶአል ። (ዮና. ም. ፫)



«እግዚአብሔርም ዓሣውን አዘዘው ፥ እርሱም ዮናስን በየብስ ላይ ተፋው» (ዮና ም. ፪ ቍ. ፲፩)

አምስተኛ ማስረጃ፦ በዘመነ ሐዋርያት ንጉሥ ሄሮድስ አይሁድን ለማስደሰት ሲል የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን ከገደለው በኋላ ጴጥሮስን ደግሞ ለፍርድ ለማቅረብ አስቦ ወደ እስር ቤት በመላክ በአራት ጠባቂዎች እንዲጠበቅ አደረገው ። በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ስለጴጥሮስ አጥብቃ በመጸለይዋ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ አራት ኾነው

ከሚጠብቁት ጠባቂዎች መካከል ከእስር ቤት ያስወጣው መኾኑን በሐዋርያት ሥራ ም. ፲፪ ቍ. ፩—፲ እንመልከት ።



«እነሆም የጌታ መልአክ ቀረበ ፤ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አንቃውና ፈጥነህ ተነሥ አለው ።» (የሐ. ሥ. ም. ፲፪ ቍ. ፯)

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾምንና የጸሎትን ኀይል ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስረዳ «እንደዚህ ዐይነቱ ርኩስ መንፈስ



በጾምና በጸሎት አማካይነት ካልኾነ በቀር አይወጣም» ብሎአቸዋል ። (ማቴ. ም. ፲፯ ቍ. ፳፩)

ሐ. የተከራካሪዎች ተቃውሞና ለተቃውሞውም የተሰጡ መልሶች

የጾምን ጠቃሚነት በሚመለከት ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራእየ ዮሐንስ ድረስ በሚገኙት ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብዙ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል ። እነዚህንም ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያስረከቡንን የአጽዋማት ቀኖና የምናከብር መኾናችን ግልጽ ነው ። ይኹን እንጂ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ እነርሱ በፈለጉት መንገድ ከመምራታቸው የተነሣ አንዳንድ ተከራካሪዎች በጾም ጠቃሚነት ላይ ከሚያቀርቡአቸው ተቃውሞዎች መካከል ቀጥለው የተዘረዘሩት ይገኙባቸዋል ።

የመጀመሪያው ተቃውሞ ፦ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጾሙ እንደነበረና የጌታ ደቀመዛሙርት ግን የማይጾሙ መኾናቸው በማቴዎስ ወንጌል ም. ፱ ቍ. ፲፬ ላይ በመገለጹ ይህ ሊኾን የቻለው የጾምን ጠቃሚነት ጌታ ስላላመነበት ነው የሚል ሐሳብ የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ ። ይህ አባባል ግን የጥቅሱ አመጣጥና አካኼድ ሳይመረመር የተሰነዘረ በመኾኑ ትክክል አይደለም ። ጌታ አርባ ቀኖችን በመጾም ለእኛ ምሳሌ ከመኾኑም በላይ የጾምንና የጸሎትን ኀይል ያረጋገጠ መኾኑን በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲፯ ቍ. ፳፩ እንመልከት ።

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደጌታ ቀርበው እኛና ፈሪሳውያን የምንጾም ስንኾን የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጾሙት ስምንድነው ብለው በጠየቁት ጊዜ የሰጣቸው መልስ ጾም አስፈላጊ አለመኾኑን ሳይኾን ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሰርገኞች የማይጾሙ መኾናቸውንና ሙሽራው ከእነርሱ ሲወሰድ ግን የሚጾሙ መኾናቸውን ነው ። ሙሽራ የተባለው ጌታ ነው ። ሰርገኞች የተባሉት ደግሞ የጌታ ተከታዮች ናቸው ። እንዲሁም መወሰድ የተባለው ዕርገቱ ነው ። በዚህም መሠረት ከዕርገቱ በኋላ የጌታ ተከታዮች መጾም የጀመሩ መኾናቸውን ለመረዳት የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት ።

«እነርሱም ጌታን ሲያመልኩና ሲጾሙ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ እኔ ለመረጥኋቸው ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ አለ ።» (የሐ. ሥ. ም. ፲፫ ቍ. ፪)

ጌታም ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጥያቄ መልስ መስጠቱን በመቀጠል በአረጀ ልብስ ላይ አዲስ መጣፊያ የሚጥፍና በአረጀ አቁማዳ ደግሞ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር አለመኖሩን የሚገልጽ ምሳሌ የተናገረው የአሪቱ የጾም ሥነ ሥርዐት ከሐዲሱ የጾም ሥነ ሥርዐት የተለየ መኾኑን ሊያስረዳቸው ስለፈለገ ነው ።

አንዳንድ ጊዜ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚቀርበው ጥያቄ ወይም ትችት ሰው ባስፈለገው ጊዜ ብቻ ይጾማል እንጂ በዓመት ወይም በሳምንት የተወሰኑ ጊዜያትንና ቀኖችን ወስኖ መጾም አስፈላጊ አይደለም የሚል ነው ።

ማንኛውም ኅብረተሰብ የግድ የመተዳደሪያ ደንብ ያስፈልገዋል ። ያለመተዳደሪያ ደንብ የሚካኼድ ማኅበራዊ ኑሮ ከቶ ሊኖር አይችልም ። የሚኖርም ከኾነ ከእንስሳት ኑሮ ያልተሻለና የተበላሸ እንጂ ያማረ አይኾንም ።

አንድ መንግሥት አጠቃላይ የኾነ ሕግ ማለት ሕገ መንግሥት ይኖረውና ያንን መሠረት በማድረግ የፍትሐ ብሔር ሕግ ፥ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፥ የንግድ ሕግና ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ ሕጎች ይኖሩታል እንጂ በሕገ መንግሥቱ ብቻ ተወስኖ እንደማይኖር የታወቀ ነው ።

ማንኛውም ሥርዐትን ያልተከተለና ማዕከላዊነት የሌለው አሠራር ውጤቱ የማያምር ከመኾኑም በላይ በእግዚአብሔር ዘንድም የተወደደ አሠራር አይደለም ። እግዚአብሔርም ሥርዐተ ቢስ ከኾነው አሠራር ይልቅ በሥነ ሥርዐት የሚካኼደውን አሠራር የሚመርጥ መኾኑን ለመረዳት የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት ።

ነቢዩ ሙሴ በምድረ በዳ የእስራኤልን ሕዝብ ሥነ ሥርዐት በሌለው ኹናቴ ይመራ በነበረ ጊዜ በሥነ ሥርዓት እንዲሠራ አማቱ ዮቶር የሰጠውን ምክር ተቀብሎ በመሥራቱ ሥራው የተቃናለት ከመኾኑም በላይ በእግዚአብሔርም ዘንድ የድጋፍ እንጂ ምንም የተቃውሞ ምልክት አልታየም ። (ዘፀ. ም. ፲፰ ቁ. ፲፫—፳፮)

በሌላ በኩል ደግሞ ቆሬና አብረውት የነበሩት ኹሉ ሥነ ሥርዐትን በማፍረስ ለአምልኮተ እግዚአብሔር የራሳቸውን መንገድ ስለተከተሉ ነው እግዚአብሔር ተቈጥቶባቸው መሬት ተከፍቶ እንዲውጣቸው ያደረገው ። (ዘኍ. ም. ፲፮)



መጽሐፍ ቅዱስን ለሃይማኖታችን እንደ ሕገ መንግሥት ብንወስደው ሌሎቹን የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥነ ሥርዐቶች እንደ ልዩ ልዩ የመንግሥት ሕጎች ልንቈጥራቸው እንችላለን ። ምንም እንኳ መሠረታዊውን የመጽሐፍ ቅዱስ ድንጋጌ የማይቃረን ኾኖ ቢዘጋጅ በቤተ ክርስቲያን የሚከናወነው አምልኮተ እግዚአብሔር የራሱ የኾነ ደንብና ሥነ ሥርዐት አለው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፲፬ ቁ. ፴፫ እና ፵ ላይ እንደገለጸው «እግዚአብሔር የሰላም እንጂ የሥርዐተ አልባነት አምላክ ስላልኾነ ኹሉ ነገር በአግባብና በሥነ ሥርዐት ይኹን» ይላል ። በዚህም መሠረት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና አምልኮተ እግዚአብሔር በሥርዐት ይኾን ዘንድ የቤተ ክርስቲያን እምነት በመኾኑ መጀመሪያ በሐዋርያት በኋላ ደግሞ በተጨማሪ በዓለም ዐቀፋዊዎቹ ሲኖዶሶች ውሳኔዎች መሠረት ከተደነገጉት ልዩ ልዩ ቀኖናዎችና ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን መካከል የአጽዋማቱ ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው ።

<u>ዐቢይ ጾም</u> ፦ መሠረቱ ጌታ የጾመው ፵ ቀን ኾኖ ከመነሻው በፊት አንድ ሳምንትና ከመጨረሻው በኋላ ደግሞ አንድ ሳምንት አክለንበት ፶፭ ቀኖች የምንጾመው ጾም ዐቢይ ጾም ይባላል ። ከበፊቱ የተጨመረው አንድ ሳምንት የዝግጅትና የመለማመጃ ጊዜ ሲኾን በመጨረሻ የሚጨመረው አንድ ሳምንት ደግሞ የጌታን ሕማማት ሳምንት ለማስታወስ ነው ። የመጀመሪያውን ሳምንት ሕርቃል ከተባለ ንጉሥ ታሪክ ጋር በማያያዝ ጾመ ሕርቃል የሚባል ስም መስጠቱ የተለመደ ነው ።

<u>ጾመ ነቢያት (የልደት ጾም)</u>፦ ይህ ጾም ኅዳር ፲፭ ቀን ይጀምርና ከልደት በዐል አንድ ቀን በፊት ያልቃል ። በተከታታይ ሦስት ዓመቶች ታኅሣሥ ፳፰ አልፎ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ይፈስካል ። በአራተኛው ዓመት ማለት ጳጉሜ ፮ ቀን ኾና በምትውልበት በዘመነ ዮሐንስ ግን ጾሙ የሚያልቀው ታኅሣሥ ፳፯ ቀን ኾኖ የሚፈስከው ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ነው ። ይህም የሚኾንበት ምክንያት እመቤታችን ጌታን የፀነሰችው መጋቢት ፳፱ ቀን መኾኑ ስለሚታመንና አንድ ሴት ፀንሳ ልትወልድ የምትች

ለው ደግሞ በዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን መኾኑ የተለመደ ስለኾነ ከመጋቢት ፳፱ ቀን ጀምሮ በመቍጠር ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ካለቀ በኋላ የሚኾነው ጳጕሜ ፭ ቀን ኾና ስትውል ብቻ ነው ። ጳጕሜ ፮ ቀን ኾና በምትውልበት በዘመነ ዮሐንስ ግን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ለመቍጠር የግድ በዐለ ልደቱ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን መዋል ይኖርበታል ። ይህን ጾም የምንጾመው የሰውን ልጅ ከሰይጣን ተገዢነት ለማላቀቅ መድኀኒታችን ለእኛ ቤዛ ለመኾን ከሰው በመወለዱ በጾምና በጸሎት ኾነን ምስጋናችንን ለማቅረብና በዐለ ልደቱንም ቀድመን በመጾም ለመቀበል ነው ። እዚህ ላይ ቃለ እግዚአብሔርን ማለት የወልደ እግዚአብሔርን ልደት በጾም መቀበላችን ነቢዩ ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃላት ወይም ትእዛዛት ከመቀበሉ በፊት ከመጾሙ ጋር ምሳሌነት አለው ። (ዘፀ. ምዕ. ፴፬ ቍ. ፳፰)

<u>ጾመ ሐዋርያት</u>፡- ይህ ጾም የመንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ መውረድ መታሰቢያ ማለት የጰራቅሊጦስ በዐል በዋለ በሚቀጥለው ሰኞ ይጀምርና ሐምሌ ፬ ቀን ተፈጽሞ ሐምሌ ፭ ቀን ይፈሰካል ። ጾመ ነነዌና በዐለ ትንሣኤ ከሚውሉባቸው ቀኖች መቅደምና መዘግየት የተነሣ ጾመ ሐዋርያት ከ፲፭ እስከ ፵፱ ቀኖች ከፍና ዝቅ ይላል ። ይህ በሐዋርያት ስም የተሰየመው ጾም ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በመቀበላቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ ተብሎ የተደነገገ ነው ።

<u>ጾመ ፍልሰታ</u> ፡- ከነሐሴ ፩ ቀን እስከ ነሐሴ ፲፭ ቀን ድረስ የምንጾመው ጾም የእመቤታችን የድንግል ማርያም ጾም ወይም የፍልሰታ ጾም ይባላል ። በቤተ ክርስቲያን እምነት መሠረት የእመቤታችን ሰውነት መፍረስና መበስበስ ሳይደርስበት ወደ ሰማይ እንዲወሰድ በመደረጉ ስለተሰወረባቸው ኹናቴውን እስኪያውቁ ድረስ ሐዋርያት የጾሙት ጾም ነው ። የሰማይንና የምድርን ጌታ በማሕፀንዋ የተሸከመችውየቅድስትና ቡርክት እመቤት ንጹሕ ሰውነት ወደ ሰማይ እንዲወጣ ቢደረግ ምንም ሊያስገርመን አይገባም ። ሰማይ የጌታ ዙፋን ነው ። (ኢሳ. ምዕ. ፷፮ ቍ. ፩ ፤ የሐ. ሥ. ምዕ. ፯ ቍ. ፵፱) —እመቤታችን ደግሞ የጌታ እናት ነች ። በንጉሥ እናትና በንጉሥ መቀመጫ መካከል ታላቅ ልዩነት አለ ። ስለዚህ እመቤታችን ከሰማይ የበለጠ ክብር ያላት በመኾንዋ ወደ ሰማይ መወሰድዋ ምንም አያስገርምም ። በሌላ በኩል ደግሞ ሔኖክና ኤልያስ ወደ ሰማይ የተወሰዱ ከኾነ የአምላክ እናት ሰውነት ወደ ሰማይ መወሰዱ ሊያስገርመን አይገባም ።



ሌሎች ወገኖች እንደሚሉት ደግሞ ይህን ጾም መጀመሪያ የጾመችው እመቤታችን ነች ። ይህን አባባል በሚሉት ወገኖች ዘንድ የእመቤታችን የድንግል ማርያም ጾም የሚለው ነው እንጂ ጾመ ፍልሰታ



የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመግደል ተሰብስበው ሲመካከሩ ። (ማቴ ምዕ ፳፯ ቍ. ፩—፭ ፤ ማር. ምዕ. ፲፬ ቍ. ፲—፪ ፤ ሉቃ ምዕ. ፳፪ ቍ. ፩—፪ ፤ ዮሐ. ምዕ. ፲፩ ቍ. ፵፭—፶፫)

የሚለው ስም አይታወቅም ። የእመቤታችን ሰውነት ወደ ሰማይ መወሰዱን አምነው የሚቀበሉት ቢኾኑም የጾሙን ምክንያት ግን ከዚያ ጋር አያገናኙትም ።

ጾመ ነነዌ ፡- የነነዌ ከተማ ሰዎች በጾምና በጸሎት ለሦስት ቀኖች ራሳቸውን ባዋረዱ ጊዜ የእግዚአብሔር ምሕረት የወረደላቸው መኾኑን ለማስታወስ የምንጾመው የሦስት ቀኖች ጾም ጾመ ነነዌ ይባላል ።

የረቡዕና የዐርብ ቀኖች ጾም፡- እነዚህ ኹለቱ የሳምንት ቀኖች ከበዐለ ትንሣኤ በኋላ ባሉት በኀምሳዎቹ ቀኖችና የልደት ወይም የጥምቀት በዐል ከኹለቱ በአንዱ ቀን ካልዋለ በቀር ዓመቱን በሙሉ ይጾምባቸዋል ረቡዕ ጌታን ለመግደል የተዶለተበት ቀን ሲኾን ዐርብ ደግሞ የስቅለቱ መታሰቢያ ነው ።

የገሃድ ጾም ፡- በልደት ዋዜማና በጥምቀት ዋዜማ የሚጾመው የያንዳንድ ቀን ጾም የገሃድ ጾም ይባላል ። የገሃድ ጾም የሚጾምባቸው ኹለት ምክንያቶች ይሰጣሉ ። የመጀመሪያው ምክንያት የልደት ወይም የጥምቀት በዐል በረቡዕ ወይም በዐርብ ቀን በሚውልበት ጊዜ ስለማይጾም ለነዚያ ማካካሻ እንዲኾን ታስቦ ነው ። ኹለተኛው ምክንያት ደግሞ ጥምቀትንና ልደትን ለሚያኽሉ ታላላቅ በዓላት መዘጋጀት ስለሚያስፈልግ እነዚህን በዓላት በጾም ተዘጋጅተን ለመቀበል የገሃድን ጾም እንጾማለን የሚል ነው ።

ኹለተኛው ተቃውሞ ፡- ወደጢሞቴዎስ መጀመሪያ በተላከው በሐዋርያው በጳውሎስ መልእክት ም. ፬ ቍ. ፩—፫ «በኋለኛው ዘመን አንዳንድ ሰዎች ጋብቻን ይከለክላሉ ፤ የሚያምኑና እውነትን የሚያውቁ ሰዎች እግዚአብሔርን እያመሰገኑ እንዲይበሉ እግዚአብሔር የፈጠረውን ምግብ አትብሉ እያሉ ይከለክላሉ» ስለሚል በድንግልና መኖርንና መጾምን ማስተማር ስሕተት ነው በማለት በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነቀፌታ ትችት የሚሰነዝሩ ወገኖች አሉ ።

ተከራካሪዎቹ ከኹሉ በፊት ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ በጾም የምታምነዋና ለምእመናንም የጾምን ጠቃሚነት የምታስተምረዋ ቤተ ክርስቲያን የጥንት የመሠረትዋ እንጂ በኋላ ዘመን የተነሣች አለመኾንዋንና የጾም መሠረት የተጣለው ደግሞ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እንጂ በኋላ ዘመን አለመኾኑን ነው ።

በተከራካሪዎቹ የተጠቀሰው ጥቅስ ግን በሦስተኛው መቶ ዓመት ተነሥተው ስለነበሩት ማኒ ፥ መርቅያኖስና ሲሞን ይባል ስለነበሩት



መናፍቃን እንጂ ስለጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን የሚያወሳ አይደለም ። ማኒና ጓደኞቹ የሥጋ ምግብ ፥ መጠጥና ሴት የተፈጠሩት በክፉት አምላክ ስለኾነ ክልክል ናቸው ብለው ያስተምሩ ነበር ።

ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ግን በዓመት ውስጥ በተወሰኑ ጊዜያትና በሳምንት ኹለት ቀኖች የጾምን ቀናና ከመደንገግዋ በቀር ሥጋ መብላት ኀጢአት ነው ብላ አላስተማረችም ። እንዲሁም የጋብቻን ውሕደት ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ መኾኑን አምና ታስተምራለች ። መጾምም ኾነ በድንግልና መኖር የተመሰገኑና የሚመሰገኑ አድራጎቶች ናቸው እንጂ የተወገዙ ወይም የሚወገዙ አድራጎቶች አይደሉም ።

ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ያለዝሙት ምክንያት ማንም ሰው ሚስቱን መፍታት እንደማይገባው በገለጸላቸው ጊዜ እንደዚህስ ከኾነ አለማግባት ይሻላል ቢሉት የሰጣቸው መልስ «ልዩ ችሎታ ለተሰጣቸው ነው እንጂ ይህ ነገር ለኹሉም አይኾንም» ብሎ ነው ። (ማቴ. ም. ፲፱ ቍ. ፱—፲፩)—ይህንኑ የድንግልናን ኑሮ በሚመለከት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱ ም. ፯ ቍ. ፩—፪ እና ቍ. ፯—፱ እንዲህ ብሏል፡- «ስለጻፋችሁልኝ ጥያቄ ሰው ከሴት ጋር በግብረ ሥጋ ባይገናኝ መልካም ነው ። ነገር ግን በዝሙት ኀጢአት ላለመውደቅ እያንዳንዱ ወንድ የራሱ ሚስት ትኑረው እያንዳንድዋም ሴት የራስዋ ባል ይኑራት ። ሰው ኹሉ እንደኔ ሚስት ሳያገባ ቢኖር በወደድሁ ነበር ። ነገር ግን ለያንዳንዱ እግዚአብሔር የተለየ ስጦታ ሰጥቶታል ። አንዱ አንድ ዐይነት ስጦታ ፥ ሌላው ሌላ ዐይነት ስጦታ አለው ። ላላገቡ ፥ እንዲሁም ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች የምለው እንዲህ ነው ። ሳያገቡ እንደኔ ቢኖሩ መልካም ነው ። ነገር ግን ራሳቸውን መቈጣጠር ቢያቅታቸው ያግቡ ፤ ምክንያቱም በሥጋ ምኞት ከመቃጠል ይልቅ ማግባት የተሻለ ነውና ።»

ከምግብና ከጋብቻ ራስን መግታት ደግሞ ለጽድቅ ሲባል የተፈጥሮ ፍላጎትን መካድ ማለት ነው ። ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ «እኔን መከተል የሚፈልግ ራሱን ይካድ» አላቸው እንጂ ራሱን የካደ ኀጢአተኛ ነው አላላቸውም ። (ማቴ. ም. ፲፮ ቍ. ፳፬)

ሦስተኛው ተቃውሞ፡- ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱም. ፲፬ ቍ. ፲፯ ላይ «የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ

ቅዱስ የሚገኝ ጽድቅ ፥ ሰላምና ደስታ እንጂ የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደለም» ባለው መሠረት በጾምና በጸሎት የምታምነዋ ቤተ ክርስቲያን በጾም አማካይነት የእግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚገኝ ማስተማርዋ ስሕተት ነው በማለት የሚከራከሩ ሰዎች አሉ ።

ተከራካሪዎቹ ትክ ብለው አልተመለከቱትም እንጂ ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው የጾምን ቀኖና አይደለም ። የጥቅሱን አመጣጥ ለመረዳት በዚሁ ምዕራፍ ቊ. ፲፬ ብንመለከት አንዱን ዐይነት ምግብ ርኩስ እንደኾነ ለሚገምት ሰው በልቡ ጥርጣሬ ስላለና ያ ምግብ ለእርሱ ርኩስ ስለሚኾንበት ያን ምግብ በመብላቱም ኾነ ባለመብላቱ አትፍረዱበት ብሎ የሚያስተምረን መኾኑን እንገነዘባለን ።

<u>አራተኛው ተቃውሞ፦</u> ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም. ፪ ቊ. ፲፮ ላይ «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ፥ በዓላትን ፥ ወይም የወር መባቻን ፥ ወይም ሰንበትን በማክበር ምክንያት ማንም አይፍረድባችሁ» የሚለው ምግብን ላለመብላት በራሳቸው ላይ የሚፈርዱትን ሰዎች የሚመለከት ነው በማለት የሚተቹ ወገኖች አሉ ። ሐዋርያው ጳውሎስ እዚህ ላይ ሊተችበት የፈለገው ለክርስቲያን ሃይማኖት አስፈላጊ ያልኾኑትን የአይሁድን ሕግጋት ነው እንጂ የቤተ ክርስቲያንን የጾም ቀኖና አለመኾኑን ተከራካሪዎቹ የነገሩን ቅደም ተከተል በትክክል ያልተመለከቱት ይመስላል ። ከአይሁድ ሃይማኖት ወደ ክርስትና የገቡት ወገኖች የአይሁድን ሕግጋት መፈጸም ግዴታ እንደኾነ ያምኑ ስለነበረና ይህንንም እምነትና አድራጎት የማይፈጽመውን ሰው ይፈርዱበት ስለነበረ ይህንኑ ለመቃወም የተጠቀሰ ነው እንጂ የቤተ ክርስቲያንን የጾም ቀኖና የሚመለከት አይደለም ።

<u>አምስተኛው ተቃውሞ፦</u> በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲፭ ቊ. ፲፩ ላይ ጌታ «ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣው ነው እንጂ ወደአፍ የሚገባው አይደለም» በማለቱ በጾም ጊዜ የፍስክ ምግብ መብላት አያረክሰንም ብለው ከጥቅሱ ጋር ግንኙነት የሌለው ክርክር የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ ። ጌታ ግን ይህን የተናገረው ፈሪሳውንና የሙሴ ሕግ መምህራን ደቀ መዛሙርትህ እጃቸውን ሳይታጠቡ በመብላት ለምን የሽማግሌዎችን ወግ ያፈርሳሉ ብለው ለጠየቁት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፈልጎ ነው እንጂ የጾምንና የፍስክን ምግብ በሚመለከት አይደለም ። ጾም ግን ለሰውነታችን ብርታትንና ጥንካሬን ሰጥቶ ወደ ክፉ ዝንባሌና ወደ



ትዕቢት ከሚመራን ከባድ ምግብና ከሚያሰክር መጠጥ መከልከልና የሥጋን ፍላጎት ገትቶ ለፈጣሪ አምላክ መንበርከክና ራስን ማዋረድ ነው እንጂ አንዱ ምግብ ንጹሕ ነው ፤ ሌላው ምግብ ደግሞ ርኩስ ነው ለማለት አይደለም ።

ነቢዩ ዳንኤል እንዴት እንደጾመ ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል ። «በዚያም ወራት እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበርሁ ፤ ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም ፤ ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም ፤ ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይት አልተቀባሁም ።» (ዳን. ም. ፲ ቊ. ፪—፫)

ጌታ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፮ ቊ. ፲፮ ላይ «በምትጾሙበት ጊዜ ግብዞች እንደሚያደርጉት የሐዘን መልክ አታሳዩ» በሚልበት ጊዜ መጾም የሚገባን መኾኑን ሊገልጽልን ፈልጎ ነው እንጂ ያለበለዚያ ግን የጾማችሁ እንደኾነ ወይም ለመጾም የፈለጋችሁ እንደኾነ ባለ ነበር።

<u>ስድስተኛው ተቃውሞ፦</u> ከዐቢይ ጾም በቀር ሌሎቹ አጽዋማት ኹሉ ሰው ሠራሽ በመኾናቸው ልንጾማቸው አስፈላጊ አይደሉም ብለው የሚከራከሩ አሉ ።

መጻሕፍቱን በሚጽፉበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ጥበቃ ያልተለያቸው መኾኑን እናምናለን እንጂ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቤተ ክርስቲያን ቀኖናዎችን ያዘጋጁት ሰዎች መኾናቸውን አንክድም ።

ለምሳሌ ለአይሁድ ሕዝብና ለነነዌ ከተማ ሕዝብ ጾም አውጀው ሕዝቡም በአዋጁ መሠረት ጾሞ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲያገኝ ያስደረጉት አስቴር ፥ መርዶክዮስና የነነዌው ንጉሥ ፥ ሰዎች እንጂ መላእክት አልነበሩም ።

ስለዚህ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያዘጋጁልንን የአጽዋማት ቀኖና አክብረን መቀበልና መታዘዝ እንደሚገባን እናምናለን ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

## መንፈሳውያን በዓላትና የቀን አቈጣጠር

በልዩ ልዩ ጊዜያት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያደላቸውን ጸጋና በረከት ምእመናን ኹሉ በምስጋና እንዲያስታውሱና ፈጣሪ አምላክን እንዲያከብሩባቸው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳውያን በዓላትን የደነገገችው በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ ነው ።

የበዓላትም መከበር የቤተ ክርስቲያን ባህል ብቻ ሳይኾን ወደ ዘመነ ኦሪት መለስ ያልን እንደኾነ እስራኤላውያን ልዩ ልዩ በዓላትን እንዲያከብሩ የታዘዙ መኾናቸውን ለመረዳት የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት ።

«እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፤ መላው የእስራኤል ሕዝብ ለአምልኮ ስለሚሰበሰቡባቸው የሃይማኖት በዓላት አከባበር የተሰጡት የሥርዐት መመሪያዎች እነዚህ ናቸው ።

ሥራ የምትሠሩባቸው ስድስት ቀኖች አሉላችሁ ፤ ሰባተኛው ዕለተ ሰንበት ግን የዕረፍት ቀን መኾኑን አስታውሱ ፤ በዚያን ዕለት ለአምልኮ ተሰብሰቡ እንጂ ምንም ሥራ አትሥሩበት ።» (ዘሌ. ም. ፳፫ ቍ. ፩—፫)

«እግዚአብሔር የሚከበርበት የፋሲካ በዐል የመጀመሪያው ወር በገባ በዐሥራ አራተኛው ቀን ጀንበር ጠልቃ መሸትሸት ሲል ይጀምራል ፤ በዐሥራ አምስተኛው ቀን የቂጣ በዐል ይጀምራል» (ቍ. ፭—፮)

«ከሰባተኛው ሰንበት በኋላ በኀምሳኛው ቀን እንደገና የአዲስ እኽል ቁርባን ለእግዚአብሔር ታቀርባለህ ።» (ቍ. ፲፮)

«በሰባተኛው ወር መጀመሪያ ዕለት ልዩ የዕረፍት ቀን ታከብራላችሁ ፤ የመለከት ድምፅ በምትሰሙበት ጊዜ እግዚአብሔርን ለማምለክ ተሰብሰቡ ። ለእግዚአብሔር የምግብ መባ አቅርቡበት እንጂ በዚያን ቀን ምንም ሥራ አትሥሩበት ።» (ቍ. ፳፫—፳፭)



«ሰባተኛው ወር ከገባ በኋላ ያለው ዐሥረኛው ቀን የሕዝቡን ኀጢአት ለማስወገድ ዓመታዊ ሥርዐት የሚፈጸምበት ዕለት ነው ።» (ቍ. ፳፯)

«የዳስ በዐል ሰባተኛው ወር ከገባ ከዐሥራ አምስተኛው ቀን ጀምሮ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ይከበራል ።» (ቍ. ፴፫—፴፬)

ምንም እንኳ ሐዋርያው ጳውሎስ አንዳንዶቹ የሙሴ ሕግጋት ለክርስቲያን ሃይማኖት አስፈላጊ አለመኾናቸውን ቢጠቊም በሐዋርያት ሥራ ም. ፲፰ ቍ. ፳፩ ላይ እንደተመለከተው «የሚመጣውን በዐል ኢየሩሳሌም ኼጄ ማክበር አለብኝ» ማለቱ የመንፈሳዊ በዓላትን ማክበር አስፈላጊነት ያመነበት መኾኑን ያመለክተናል ።

በዓመት ውስጥ ብዙ ዓለማዊ በዓላትን የምናከብር ከኾነ የእግዚአብሔርን ውለታዎች ማስታወሻና እግዚአብሔር ያከበራቸውን የመላእክትንና የቅዱሳንን በዓላትማ ምንኛ ማክበር እንደሚገባን መገመት እንችላለን ።

የክርስቲያኑ ዓለም ኹለት የተለያዩ የዘመን አቈጣጠሮችን ተከትሎ የሚጓዘው በአራት መቶ ኀምሳ አንድ ዓመተ ምሕረት ለተፈጸመው የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል መፍትሔ ተፈልጎለት ወደ ቀድሞው አንድነት ከመመለስ ይልቅ ልዩነቶቹና የልዩነቶቹ ምክንያቶች እየበዙ እንዲኼዱ በመደረጋቸው ነው ።

የምዕራቡ ዓለም የቀን አቈጣጠር ከክርስቶስ ልደት በፊት የዩልዮስ ቄሳር አቈጣጠር ተብሎ ይጠራ የነበረውን ደንብ ተከትሎ እስከ ፲፭፻፹፪ ዓ. ም. ድረስ ከቈየ በኋላ ጎርጎርዮስ በተባለው የሮማ ቤተ ክርስቲያን መሪ አማካይነት የከዋክብት ሊቃውንት ተሰብስበው የዘመን አቈጣጠሩን እንዲያስተካክሉት የተደረገ ነው ። ስለዚህ ነው የምዕራባውያኑ የቀን አቈጣጠር ጎርጎርዮሳዊ የሚል ቅጽል ስም የተሰጠው ።

የምሥራቃውያኑ የቀን አቈጣጠር ግን ከመቶ ሰማንያ ስምንት እስከ ኹለት መቶ ሠላሳ ዓ. ም. ድረስ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መሪ በነበረው ድሜጥሮስ በተባለው ጻድቅ አማካይነት የተዘጋጀውን ባሕረ ሐሳብ የሚከተል ነው ። ይህንንም ባሕረ ሐሳብ ባዘጋጀበት ጊዜ በጊ

ዜው በነበረ በጥሊሞስ በተባለ የከዋክብት ሊቅ የተረዳ መኾኑ ይነገራል ። (የግብጽ ሕዝብ ታሪክ ፣ ገጽ ፶፩)

ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ የቀረበው በድሜጥሮስ ባሕረ ሐሳብ መሠረት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የበዐላትና የአጽዋማት አቈጣጠር ነው ። በኹሉም ዘንድ መታወቃቸው በጣም አስፈላጊ መኾኑ የታመነባቸው አቈጣጠሮች በአጭሩ ቀረቡ እንጂ በባሕረ ሐሳቡ ውስጥ የሚገኙት ቁም ነገሮች ግን ብዙ ናቸው ።

ለማስረዳትም ኾነ ለመረዳት አመቺ ይኾን ዘንድ በምሳሌነት የቀረበው ዘመን ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. ነው ።

## የቃላት ትርጉም

ጥንተ ቀመር፡- ዕለተ ማክሰኞ ሲኾን እርሱም ቅመራ ወይም ስሌት የተጀመረበት ቀን ነው ።

ሕጸጽ ከመስከረም ጀምሮ በየኹለት ወሩ የሚገኝ አንድ ቀን ማለት ነው ። ለምሳሌ በጥቅምት መጨረሻ አንድ ሕጸጽ አለ ፣ በታኅሣሥ መጨረሻ ኹለት ይኾናል እንዲሁም በየካቲት መጨረሻ ሦስት እያለ ይቀጥላል ።

ሠርቀ መዓልት፡- ከወሩ ቀኖች እያንዳንዱ የሚውልበት ዕለት ነው ። ለምሳሌ የዛሬው ቀን የቃና ዘገሊላ በዐል ቢኾን ሠርቀ መዓልቱ ዐሥራ ኹለት ነው ማለት ነው ።

ሠርቀ ሌሊት፡- ለጸሎት የምንጠቀምበት አቈጣጠር ነው ። እርሱም ሠርቀ መዓልትን ፣ አበቅቴንና ሕጸጽን በመደመር ይገኛል ።

ዓውደ ወርኅ፡- በፀሐይ ፴ ቀኖች፤ በጨረቃ ግን አንድ ጊዜ ፴ አንድ ጊዜ ፳፱ በመኾን ይፈራረቃሉ ። በዚህም መሠረት የዓመቱ ቀኖች በፀሐይ ከጳጒሜን ጋር ፫፻፷፭ በጨረቃ ግን ጳጒሜን ሳይጨመር ፫፻፶፬ ነው ።

ተውሳክ፡- ለተለያዩ አቈጣጠሮች መነሻ ወይም ተጨማሪ በመኾን የሚያገለግል በተለያዩ መንገድ የሚገኝ ቍጥር ነው ። ለምሳሌ የዕለታት ተውሳክ የሚከተሉት ናቸው ።



| | | | |
|---|---|---|---|
| ቅዳሜ | ፰ | እሁድ | ፯ |
| ሰኞ | ፮ | ማክሰኞ | ፭ |
| ረቡዕ | ፬ | ሐሙስ | ፫ |
| ዓርብ | ፪ | | |

መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋር የአጽዋማትና የበዐላት ማውጫ ነው ።

አበቅቴ ከሠርቀ መዓልትና ከሕጸጽ ጋር የሌሊት ማውጫ ነው ።

ዐበይ ቀመር ፭፻፴፪ ዓመት ነው ።
ማዕከላዊ ቀመር ፸፮ ዓመት ነው ።
ንዑስ ቀመር ፲፱ ዓመት ነው ።

መባጃ ሐመር በዐለ መጥቅዕና መጥቅዑ የዋለበት ተውሳክ ተደምረው ጾመ ነነዌን እንዲሁም ሌሎቹን አጽዋማትና በዐላት ለማግኘት የሚያገለግል ቍጥር ነው ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት ዘመን የተቈጠረለት ጊዜ ፭ሺሕ፭፻ ዓመት ነው ።

ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. ነው ።

የእነዚህ የኹለቱ ድምር (፭ሺሕ፭፻ + ፲፱፻፹፪ = ፯ሺሕ፬፻፹፪) ዓመተ ዓለም ይባላል ።

## የበዐላትና የአጽዋማት አቈጣጠር

የዘመን መለወጫ፡- ዓመቶች ኹሉ በያንዳንዳንዱ ወንጌላዊ ስም የሚፈራረቁ ኾነው ቍጥራቸውም እንደ ቅደም ተከተላቸው ነው ።

፩. ማቴዎስ ።　　፪. ማርቆስ ።
፫. ሉቃስ ።　　ባዶ ወይም ፬. ዮሐንስ ።

አንድን ዘመን በማንኛው ወንጌላዊ ስም የሚጠራ መኾኑን ለማወቅ ዓመተ ዓለሙን ለአራት እናካፍለውና ተራፊው አንድ ቢኾን

ዘመነ ማቴዎስ ተራፊው ኹለት ቢኾን ዘመነ ማርቆስ ፡ ተራፊው ሦስት ቢኾን ዘመነ ሉቃስ ፡ ምንም ሳይተርፍ ቢካፈል ደግሞ ዘመነ ዮሐንስ ነው እንላለን ።

ለምሳሌ በ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. በድምር የተገኘውን ዓመተ ዓለም (፭ሺሕ፭፻+፲፱፻፹፪=፯ሺሕ፬፻፹፪) ለአራት ስናካፍለው ፲፰፻፸ ደርሶ ተራፊው ኹለት ስለኾነ ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. ዘመነ ማርቆስ ነው ማለት ነው።ለአራት ሲካፈል የሚደርሰው ድርሻ (፲፰፻፸) ራብኢት ይባላል ። ይህም ተራፊውን (፪) አይጨምርም ።

የዘመን መለወጫ ማለት መስከረም ፩ ቀን ከሳምንቱ ቀኖች በየት ኛው ቀን እንደሚውል ለማወቅ ዓመተ ዓለምንና ራብኢትን ካዳመርን በኋላ የሚገኘውን ውጤት ለሰባት አካፍለን ተራፊውንና ጥንተ ቀመ ርን በማገናዘብ ልናገኘው እንችላለን ።

ለምሳሌ የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. መስከረም ፩ ቀን መቼ እንደሚውል ለማወቅ ዓመተ ዓለሙን ፯ሺሕ፬፻፹፪ ከራብኢት ፲፰፻፸ ጋር አዳምረን የምናገኘውን ፱ሺሕ፫፻፶፪ ውጤት ለሰባት ስናካፍለው ያለምንም ትርፍ ፲፫፻፴፮ ይደርሳል ። ያለምንም ትርፍ ሲካፈል ደግሞ የተካፈለው ለሰ ባት እንደመኾኑ ሰባት እንደተረፈን አድርገን እንቈጥረዋለን ። በዚህም መሠረት ከጥንተ ቀመር ማለት ከማክሰኞ ጀምረን ሰባት ቀኖችን የቈጠ ርን እንደኾነ ሰኞ ላይ ስለሚያርፍ የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. መስከረም ፩ ቀን የሚውለው ሰኞ ዕለት ነው ማለት ነው ።

<u>የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. በዐለ መጥቅዕ፦</u> ዓመተ ዓለሙን ለዐቢይ ቀመር ስናካፍለው ( ፯ሺሕ፬፻፹፪ ÷ ፫፻፺፫ ) = ፲፱ ደርሶ ፲፭ ይተርፋል ። ተራፊውን ፲፭ ደግሞ ለንዑስ ቀመር ስናካፍለው (፲፭ ÷ ፲፱) — አንድ ደርሶ ፲፭ ይተርፋል ። ከዚህ ከተራፊው ላይ አንድ መግደፍ ደንብ ስለኾነ ቀሪው ፲፬ ይኾናል ማለት ነው ። ይህም መጥቅዕንና አበቅቴን ለማስገኘት በማባዣነት የሚጠቅም መደብ የተባለ ቍጥር ነው ።

መደብን በንዑስ ቀመር አባዝተን የተገኘውን ውጤት ለሠላሳ ከአካፈልን በኋላ የሚገኘው ትርፍ የዘመኑ መጥቅዕ ይኾናል ።

ለምሳሌ ፲፬×፲፱=፪፻፷፮÷፴ = ፰ ደርሶ ፳፮ ይተርፋል ። ይህ ተራፊ ፳፮ የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. መጥቀዕ ነው ። ሰኞ ዕለት ከዋለው መስከ



ረም ፩ ቀን ተነሥተን ኻያ ስድስት ቀኖችን የቈጠርን እንደኾነ የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. በዐለ መጥቅዕ ዓርብ መስከረም ፳፮ ቀን የሚውል ኾኖ እናገኘዋለን ።

መጥቅዕ ከአንድ እስከ ዐሥራ ሦስት ቢኾን በዐለ መጥቅው በጥቅ ምት ይኾናል ፤ ከዐሥራ አምስት በላይ ከኾነ ግን በመስከረም ይኾናል ።

የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. አበቅቴ የጨረቃ ዓመት ፫፻፶፬ ቀኖች ከፀሐይ ዓመት ፫፻፷፭ ቀኖች ላይ ቢቀነስ (፫፻፷፭—፫፻፶፬=፲፩) ዐሥራ አንድ ቀን ይተርፋል ። ወይም ደግሞ የዓመቱ ስድስት ሕጸጽና አምስት ጳጉ ሜን ቢደመሩ ዐሥራ አንድ ይኾናሉ ።

ይህን ዐሥራ አንድ ቍጥር ቀደም ብለን በስሌት ባገኘነው መደብ ማለት በዐሥራ አራት አባዝተን የምናገኘውን አንድ መቶ ኀምሳ አራት ውጤት ለሠላሳ ስናካፍል አምስት ደርሶ የሚተርፈው አራት የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. አበቅቴ ነው ።

መጥቅዕና አበቅቴ ተዳምረው ምንጊዜም ቢኾን ፴ መኾን አለ ባቸው ። ለምሳሌ ፳፮+፬ = ፴

<u>መባጃ ሐመር፦</u> ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው መጥቅዕና በዓለ መጥ ቅዑ የዋለበት ዕለት ተውሳክ ተዳምሮ መባጃ ሐመር ይኾናል ።

ለምሳሌ የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. በዐለ መጥቅዕ የዋለው በዓርብ ቀን ስለኾነና የዓርብ ተውሳክ ደግሞ ኹለት ስለኾነ ኹለትና ኻያ ስድስት በመደመር የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. መባጃ ሐመር መስከረም ፳፰ ቀን ይውላል ማለት ነው ።

<u>ጾመ ነነዌ፦</u> ከሳምንቱ ቀኖች መስከረም ፩ ቀን የዋለበት ዕለት ማግስት ጥር ፩ ቀን ይውላል ። የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. መባጃ ሐመር ፳፰ ነው ብለናል ። ጾመ ነነዌ መባጃ ሐመር በዋለበት ዕለት የሚውል እንደ መኾኑ የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. ጾመ ነነዌ ጥር ፳፰ ቀን ይውላል ማለት ነው ።

መባጃ ሐመር ለነነዌ ጾም መሠረት እንደኾነ እንዲሁም የነነዌ ጾም ለአጽዋማትና ለበዐላት አወጣጥ መሠረት ነው ። ጾመ ነነዌ የሚ ጀምረው ኹልጊዜ በሰኞ ቀን ነው ።

ዐቢይ ጾም፦ ከነነዌ ማግስት ጀምሮ ዐቢይ ጾም እስከሚጀመርበት ቀን ድረስ ዐሥራ አራት ቀኖች ናቸው ። የዐቢይ ጾም ተውሳክ ዐሥራ አራት ነው የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው ። ዐሥራ አራቱን ተውሳክና የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. መባጃ ሐመርን ብንደምራቸው ውጤቱ አርባ ኹለት ይኾናል ። ከአርባ ኹለት ላይ ሠላሳን በመቀነስ ቀሪው ዐሥራ ኹለት ስለሚኾን የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. ዐቢይ ጾም መግቢያ የካቲት ፲፪ ቀን ይኾናል ማለት ነው ። ዐቢይ ጾም የሚጀምረው ኹልጊዜ በሰኞ ቀን ነው ።

ደብረ ዘይት ፦ ከነነዌ መግቢያ ማግስት ጀምሮ እስከ ደብረ ዘይት ድረስ አርባ አንድ ቀኖች ናቸው ። ከአርባ አንዱ ላይ ሠላሳ የቀነስን እንደኾነ ዐሥራ አንድ ይተርፋል ። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ ነው የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው ። የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. መባጃ ሐመርን ከዐሥራ አንዱ ተውሳክ ጋር ስንደምረው ሠላሳ ዘጠኝ ስለሚኾን ከውጤቱ ላይ ሠላሳ ቀንሰን ዘጠኝ ይተርፈናል ።

በዚህም የደብረ ዘይት በዐል መጋቢት ዘጠኝ ቀን እንደሚውል እንረዳለን ። እንዲሁም በዐቢይ ጾም መግቢያ ላይ ፳፯ ቢጨመር ደብረ ዘይት ይገኛል ። የደብረ ዘይት በዐል የሚውለው ኹልጊዜ በእሁድ ቀን ነው ።

ሆሣዕና ፦ ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ሆሣዕና ድረስ ስድሳ ኹለት ቀኖች ናቸው ። ከስድሳ ኹለት ላይ ኹለት ሠላሳዎችን ማለት ስድሳ ስንቀንስ ኹለት ይተርፈናል ። ስለዚህም ነው የሆሣዕና ተውሳክ ኹለት ነው የሚባለው ። ኹለት ተውሳክንና ኻያ ስምንት መባጃ ሐመርን ስንደምራቸው ሙሉ ሠላሳ ስለሚኾን የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. የሆሣዕና በዐል የሚውለው በመጋቢት ሠላሳ ቀን ነው ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በደብረ ዘይት ላይ ኻያ አንድ ቢጨመር ሆሣዕና ይገኛል ። ሆሣዕና ኹልጊዜ በእሁድ ቀን ይውላል ።

ስቅለት ፦ ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ስቅለት ድረስ ስድሳ ሰባት ቀኖች ናቸው ። ከስድሳ ሰባት ላይ ኹለት ሠላሳዎችን ቀንሰን የሚተርፈን ሰባት የስቅለት ተውሳክ ነው ። ኻያ ስምንት መባጃ ሐመርንና ሰባት ተውሳክን ስንደምራቸው ሠላሳ አምስት እናገኛለን ። ከሠላሳ አምስት ላይ ሠላሳ ሲቀነስ አምስት ስለሚተርፍ የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. የስቅለት በዐል የሚውለው ሚያዝያ አምስት ቀን ነው ማለት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ በሆሣዕና ላይ አምስት ቢጨምሩ ስቅለት ይገኛል ። የስቅለት በዐል ኹልጊዜ በዓርብ ቀን ይውላል ።



ትንሣኤ ፦ ከነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ትንሣኤ ድረስ ፷፱ ቀኖች አሉ ። ከስድሳ ዘጠኙ ቀኖች ላይ ኹለት ሠላሳዎች ሲቀነሱ ቀሪው ዘጠኝ የትንሣኤ ተውሳክ ነው ። ኻያ ስምንት መባጃ ሐመርንና ዘጠኝ ተውሳክን ስንደምር ሠላሳ ሰባት ይኾናል ። ከሠላሳ ሰባት ላይ ሠላሳ ስንቀንስ የሚተርፈው ሰባት የሚያመለክተው የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. የትንሣኤ በዐል የሚውለው ሚያዝያ ፯ ቀን መኾኑን ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በስቅለት ላይ ኹለት ቢጨመር ትንሣኤ ይገኛል ። የትንሣኤ በዐል ኹልጊዜ በእሁድ ቀን ይውላል ።

ዕርገት ፦ ከነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ዕርገት ድረስ ፻፰ ቀኖች አሉ ። ከመቶ ስምንት ላይ ሦስት ሠላሳዎች ማለት ዘጠና ሲቀነስ የዕርገት ተውሳክ የኾነው ዐሥራ ስምንት ይተርፋል ። መባጃ ሐመሩንና የዕርገትን ተውሳክ ስንደምር አርባ ስድስት ይኾናል ። ከአርባ ስድስት ላይ ሠላሳ ሲቀነስ ዐሥራ ስድስት ስለሚተርፍ የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. የዕርገት በዐል የሚውለው ግንቦት ፲፮ ቀን ነው ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በትንሣኤ ላይ ሠላሳ ዘጠኝ ቀኖች ብንጨምር ዕርገት ይኾናል ። ዕርገት ኹል ጊዜ በሐሙስ ቀን ይውላል ።

ጰራቅሊጦስ ፦ ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ጰራቅሊጦስ ድረስ አንድ መቶ ዐሥራ ስምንት ቀኖች ናቸው ። ከመቶ ዐሥራ ስምንት ላይ ሦስት ሠላሳዎች ሲቀንሱ ኻያ ስምንት ይተርፋል ይህም የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ነው ። መባጃ ሐመሩንና ተውሳኩን ስንደምር የድምሩ ውጤት ኀምሳ ስድስት ስለሚኾን ከውጤቱ ሠላሳ ከቀነስን በኋላ ኻያ ስድስት ይተርፈናል ። ይህም የሚያሳየን የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. የጰራቅሊጦስ በዐል የሚውለው ግንቦት ፳፮ ቀን መኾኑን ነው ። በዕርገት ላይ ዐሥር ቀኖች ቢጨምሩ ጰራቅሊጦስ ይገኛል ። የጰራቅሊጦስ በዐል ኹልጊዜ እሁድ ይውላል ።

ጾመ ሐዋርያት ፦ ከጾመ ነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ጾመ ሐዋርያት መግቢያ ድረስ አንድ መቶ ዐሥራ ዘጠኝ ነው ። ከመቶ ዐሥራ

ዘጠኝ ላይ ሦስት ሠላሳዎች ሲቀነሱ ኻያ ዘጠኝ የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ይገኛል ። መባጃ ሐመሩንና ተውሳኩን ስንደምር ኀምሳ ሰባት ስለሚኾንና ከኀምሳ ሰባት ላይ ሠላሳ ቀን ስን ፳፯ ስለሚተርፈን የ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. ጾመ ሐዋርያት መጀመሪያ ግንቦት ፳፯ ቀን መኾኑን ለማወቅ እንችላለን ። ጾመ ሐዋርያት የሚጀመረው ኹልጊዜ በሰኞ ቀን ነው ። በጰራቅሊጦስ ላይ አንድ ቢጨምሩ ጾመ ሐዋርያት ይገኛል ።

<u>ጾመ ድኅነት</u> ፡- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ጾመ ድኅነት ድረስ አንድ መቶ ኻያ አንድ ቀን ነው ። ከመቶ ኻያ አንዱ ቀን ላይ አራት ሠላሳዎችን ስንቀንስ አንድ ይቀራል ። ስለዚህ ነው የጾመ ድኅነት ተውሳክ አንድ ነው የሚባለው ። መባጃ ሐመሩንና ተውሳኩን በምንደምርበት ጊዜ ኻያ ዘጠኝ ስለሚኾን የ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. ጾመ ድኅነት የሚውለው ግንቦት ፳፱ ቀን ነው ማለት ነው ። በጾመ ሐዋርያት ላይ ኹለት ቢጨምሩ ጾመ ድኅነት ይገኛል ጾመ ድኅነት ኹልጊዜ በረቡዕ ቀን ይውላል ።

## <u>ያለ ተውሳክ የሚገኙ አጽዋማትና በዐላት</u>

<u>ጾመ ነቢያት (የልደት ጾም)</u> ፡- ኅዳር ፲፭ ቀን ይጀምርና ከልደት በዐል አንድ ቀን በፊት ያልቃል ።

በዐለ ልደት ከዘመነ ማቴዎስ እስከ ዘመነ ሉቃስ ባሉት ሦስት ተከታታይ ዓመቶች ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ይከበራል ። በአራተኛው ዓመት ማለት በዘመነ ዮሐንስ ግን ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ይከበራል ።

<u>የጥምቀት በዐል</u> -፡ ኹልጊዜ ጥር ፲፩ ቀን ይከበራል ። በማግስቱ ጥር ፲፪ ቀን ደግሞ የቃና ዘገሊላ በዐል ነው ።

<u>ጾመ ፍልሰታ</u> ፡- በየዓመቱ ነሐሴ ፩ ቀን ይጀምርና ነሐሴ ፲፭ ቀን ያልቃል ።

<u>የገሀድ ጾም</u> ፡- በጥምቀትበዐል ዋዜማ የሚጾም የአንድ ቀን ጾምና እንዲሁም ጾመ ነቢያትን ለማይጾሙ ሰዎች በልደት በዐል ዋዜማ የሚጾም የአንድ ቀን ጾም ናቸው ።



<u>በዐለ ብሥራት</u> ፡- በሉቃስ ወንጌል ም. ፩ ቍ. ፴፩ እንደተገለጸው መላኩ ገብርኤል ለድንግል ማርያም «እነሆ ፡ ትፀንሻለሽ ፤ ወንድ ልጅም ትወልጂአለሽ ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ» ብሎ ባበሠራት ጊዜ በዚሁ ምዕራፍ ቍ. ፴፰ መሠረት «እነሆኝ እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ ፤ እንደቃልህ ይኹንልኝ» ብላ እምነትዋን በእግዚአብሔር ላይ በማሳረፍዋ በዚያኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ጌታን እንደፀነሰችና ይህም የኾነው መጋቢት ፳፱ ቀን መኾኑን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው ነው ።

<u>በዐለ ስምዖን ፡-</u> <u>በሉቃስ ወንጌል ም. ፪ ቍ. ፳፪—፴፱ መሠረት</u> ሕፃን ጌታ ኢየሱስ እንደ አይሁድ ሥርዐት ወደቤተ መቅደስ የተወሰደበት ቀን የካቲት ፰ ቀን እንደሚታሰብ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው ።

<u>ግዝረት</u> ፡- ጥር ፮ ቀን የሚውለው የጌታ ግዝረት መታሰቢያ የሚኾነው በሉቃስ ወንጌል ም. ፪ ቍ. ፳፩ መግለጫ መሠረት ነው ።

<u>ደብረ ታቦር</u> ፡- በማቴዎስ ወንጌል ም. ፲፯ ቍ. ፩—፰ መሠረት ጌታ ለሦስት ደቀ መዛሙርቱ መለኮታዊ ክብሩን የገለጸበት መታሰቢያ በዐል ነሐሴ ፲፫ ቀን ይከበራል ።

<u>ጸሎተ ሐሙስ</u> ፡- በማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፮ ቍ. ፳፮—፴ እና በዮሐንስ ወንጌል ም. ፲፫ መሠረት የምሥጢረ ቍርባን ምሥረታና የኅፅበተ እግር መታሰቢያዎች የሚከበሩት በበዐለ ስቅለት ዋዜማ በዕለተ ሐሙስ ነው ።

በዐለ ቶማስ በዮሐንስ ወንጌል ም. ፳ ቍ. ፳፬—፳፱ መሠረት ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያው ቶማስ በተገኘበት የተገለጸበት መታሰቢያ ቀን ከትንሣኤ በሚቀጥለው እሁድ ይውላል ።

ሠርቀ ወርኀን ማለት ጨረቃ መታየት ከጀመረች ስንት ቀኖች ያለፉ መኾኑን ለማወቅ በሠርቀ ሌሊቱ ላይ አራት ቍጥር እንደምርበታለን ።

## ፲፱፻፹፫ ዓ. ም.

ዓመተ ዓለም — ፲፱፻፹፫+፭ሺሕ፭፻=፯ሺሕ፬፻፹፫

የዘመኑን ወንጌላዊ ለማወቅ ዓመተ ዓለሙን በ፬ ማካፈል ያስፈልጋል ።

፯ሺሕ፬፻፹፫÷፬=፲፰፻፸ ደርሶ ፫ ስለሚተርፍ ዘመኑ ዘመነ ሉቃስ ነው ።

መስከረም ፩ ቀን ከሳምንቱ ቀኖች በየትኛው ቀን እንደሚውል ለማወቅ ዓመተ ዓለሙንና ራብኢትን በማዳመር ለሰባት ካካፈልን በኋላ ተራፊውንና ጥንተ ቀመርን ማለት ማክሰኞን በማገናኘት ዕለቱን ለማወቅ ይቻላል ።

፯ሺሕ፬፻፹፫+፲፰፻፸=፱ሺሕ፫፻፶፫÷፯=፲፫፻፴፮ ደርሶ አንድ ስለሚተርፍ በጥንተ ቀመር አቈጣጠር መስከረም ፩ ቀን የሚውለው በማክሰኞ ቀን ነው ምክንያቱም ተራፊው ቍጥር ፩ ኾኖ ለመቍጠር መነሻ ማክሰኞ ስለኾነ ነው ።

<u>መደብ</u>፡- መደብን ለማግኘት ዓመተ ዓለምን ለዐቢይ ቀመር ፭፻፴፪ አካፍለን ዐሥራ አራት ከደረሰ በኋላ ፴፭ ስለሚተርፍና ይህም ለማዕከላዊ ቀመር ሊካፈል ስለማይችል ለንዑስ ቀመር ማለት ለ፲፱ ሲያካፍሉት አንድ ደርሶ ፲፮ ይተርፋል ። ከዚህ ከተራፊው ላይ አንድ በመግደፍ የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. መደብ ፲፭ ይኾናል ።

<u>መጥቅዕ</u>፡- መጥቅዕ ሚገኘው መደብን በ፲፱ አባዝቶ በሠላሳዎች ከገደፉ በኋላ በሚገኘው ተራፊ ነው ። በዚህም መሠረት ።

፲፭×፲፱=፪፻፹፭÷፴=፱ ደርሶ ፲፭ ስለሚተርፍ የ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. መጥቅዕ ፲፭ ነው ።

መስከረም ፩ ቀን ከዋለበት ከማክሰኞ ተነሥተን ስንቈጥር በዐለ መጥቅዑ ማክሰኞ መስከረም ፲፭ ቀን ይውላል ።

<u>አበቅቴ</u>፡- አበቅቴ የሚገኘው መደብን በ፲፩ አባዝቶ በሠላሳዎች ከገደፉ በኋላ በሚገኘው ተራፊ ነው ። በዚህም መሠረት



፲፭×፲፩=፻፷፭÷፴=፭ ደርሶ ፲፭ ስለ ሚተርፍ ይህም የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. አበቅቴ ነው ።

<u>መባጃ ሐመር</u>፡- መባጃ ሐመር የሚገኘው የዓመቱ መጥቅዕና በዐለ መጥቅዑ የዋለበት ዕለት ተውሳክ ተደምሮ ነው ። በዚህም መሠረት ፡-

፲፭ መጥቅዕና በዐለ መጥቅዑ የዋለበት የማክሰኞ ተውሳክ ሲደመር ፲፭+፭=፳ ስለሚኾን የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. በባጃ ሐመር ፳ ነው ።

<u>ጾመ ነነዌ</u> ፡-መባጃ ሐመር መስከረም ፳ ቀን ስለዋለ ጾመ ነነዌ የሚጀምረው ጥር ፳ ቀን ነው ።

<u>ዐቢይ ጾም</u>፡- ከጾመ ነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ዐቢይ ጾም መግቢያ ድረስ ያሉት ቀኖች ፲፬ ናቸው ። ይህም ፲፬ የዐቢይ ጾም ተውሳክ ይባላል ። ይህንን ፲፬ የዐቢይ ጾም ተውሳክ ከመባጃ ሐመር ፳ ጋር ስንደምረው ፴፬ ይኾናል ። ድምሩን በ፴ የገደፍን እንደኾነ ፬ ስለሚተርፍ የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ዐቢይ ጾም መግቢያ የካቲት ፬ ቀን ይኾናል ።

<u>ደብረ ዘይት</u>፡- ከነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ደብረ ዘይት ድረስ ፵፩ ቀኖች ናቸው ። ከ፵፩ ላይ ፴ ተገድፎ ቀሪው ፲፩ የደብረ ዘይት ተውሳክ ይባላል ተውሳክንና የዓመቱን መባጃ ሐመር ስናዳምር ለምሳሌ ፲፩+፳ = ፴፩ ስለሚኾን ፴ ገድፈን ተራፊው አንድ የሚያመለክተው የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. የደብረ ዘይት በዓል መጋቢት ፩ ቀን የሚውል መኾኑን ነው ። ወይም ደግሞ ፡-

ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት ማለት ከጥር ፳፩ ቀን እስከ ጥር ፴ ቀን ድረስ ፲ ቀኖች ናቸው ። እነዚህን ዐሥር ቀኖች ከአርባ አንድ ቀኖች ላይ ብንቀንሳቸው ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ደብረ ዘይት ድረስ ያሉት ፴፩ ቀኖች መኾናቸውን እንገነዘባለን ። (፵፩—፲ = ፴፩) ከዚህ ከተገኘው ፴፩ ላይ የየካቲትን ወር ማለት ሠላሳውን ቀን ስናነሣለት የሚተርፈው አንድ ቀን የሚያመለክተው የደብረ ዘይት በዓል የሚውለው መጋቢት ፩ ቀን መኾኑን ነው ።

ሆሣዕና፡- ከነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ሆሣዕና ድረስ ፷፪ ቀኖች ናቸው ። ከ፷፪ ላይ ኹለት ሠላሳዎች ተገድፈው ቀሪው ፪ የሆሣዕና ተውሳክ ነው ። የዓመቱ መባጃ ሐመር ከሆሣዕና ተውሳክ ጋር ሲደመር (፳ + ፪) = ፳፪ የሚመጣ በመኾኑ የ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. የሆሣዕና በዓል የሚውለው መጋቢት ፳፪ ቀን ነው ። ወይም ደግሞ ፡-

ከነነዌ ጾም ማግስት እስከ ጥር ፴ ቀን ድረስ ያሉት ዐሥር ቀኖች ከ፷፪ ላይ ቢቀነሱ ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ሆሣዕና በዓል ድረስ ያሉት (፷፪—፲) = ፶፪ ቀኖች መኾናቸውን እናውቃለን ። ከ፶፪ ላይ የየካቲትን ወር ፴ ቀኖች ብንቀንስ ፳፪ ስለሚተርፍ የ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. የሆሳዕና በዓል የሚውለው መጋቢት ፳፪ ቀን መኾኑን እንገነዘባለን ።

ስቅለት፦ ከነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ስቅለት ድረስ ፷፯ ቀኖች ናቸው ። ኹለት ሠላሳዎችን ስንገድፍ የሚቀረው ፯ የስቅለት ተውሳክ ይባላል ። ከዘመኑ መባጃ ሐመር ፳ ጋር ሲዳመር ፳፯ ስለሚኾን ይህም የ፲፱፻፺፫ የስቅለት በዓል መጋቢት ፳፯ ቀን መኾኑን ያመለክታል ። ወይም ደግሞ ፡-

ከነነዌ ጾም ማግስት እስከ ጥር ፴ ቀን ድረስ ያሉት ዐሥር ቀኖች ከ፷፯ ላይ ቢቀንሱ ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ስቅለት በዓል ድረስ ያሉት (፷፯—፲) = ፶፯ ቀኖች ናቸው ። ከ፶፯ ላይ የየካቲትን ወር ፴ ቀኖች ብንቀንስ ፳፯ ስለሚተርፍ የ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. የስቅለት በዓል የሚውለው መጋቢት ፳፯ ቀን መኾኑን ያመለክታል ።

ትንሣኤ ፡- ከነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ትንሣኤ ድረስ ፷፱ ቀኖች ናቸው ። ኹለት ሠላሳዎችን ስንገድፍ የሚቀረው ፱ የትንሣኤ ተውሳክ ይባላል ። ከዘመኑ መባጃ ሐመር ፳ ጋር ሲዳመር ፳፱ ስለሚኾን የ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. የትንሣኤ በዓል መጋቢት ፳፱ ቀን መኾኑን ያመለክተናል ።

ወይም ደግሞ ከነነዌ ጾም ማግስት እስከ ጥር ፴ ቀን ድረስ ያሉት ዐሥር ቀኖች ከ፷፱ ላይ ሲቀንሱ ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ትንሣኤ



በዓል ድረስ ያሉት (፷፱—፲) = ፶፱ ቀኖች ናቸው ። ከ፶፱ ላይ የየካቲትን ወር ፴ ቀኖች ብንቀንስ ፳፱ ስለሚተርፍ የ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. የትንሣኤ በዓል የሚውለው መጋቢት ፳፱ ቀን መኾኑን ያመለክተናል ።

ዕርገት ፡- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ዕርገት ድረስ ፻፰ ቀኖች ናቸው በሦስት ሠላሳዎች ተገድፈው (፻፰ — ፺) የሚተርፈው ፲፰ የዕርገት ተውሳክ ነው ። መባጃ ሐመሩን ደምረን በሠላሳ ስንገድፈው (፲፰+፳ = ፴፰—፴ = ፰) ተራፊው ፰ የሚያመለክተው የዕርገት በዓል የሚውለው ግንቦት ፰ ቀን መኾኑን ነው ። ወይም ደግሞ ፤

ከ፻፰ ላይ ዐሥር ቀኖች ቢቀነሱ (፻፰ — ፲) ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ዕርገት በዓል ድረስ ፺፰ ቀኖች ናቸው ። ከ፺፰ ላይ የየካቲት የመጋቢትና የሚያዝያ ወሮች ማለት ዘጠና ቀኖች ሲቀነሱ ቀሪው ፰ ስለሚኾን የዕርገት በዓል የሚውለው ግንቦት ፰ ቀን ነው ማለት ይኾናል ። (፺፰—፺) = ፰

ጰራቅሊጦስ ፡- ከነነዌ ማግስት እስከ ጰራቅሊጦስ ድረስ ፻፲፰ ቀኖች ናቸው ። ከ፻፲፰ ላይ ሦስት ሠላሳዎች ማለት (፻፲፰—፺) ዘጠና ተገድፎለት ቀሪው ፳፰ የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ነው ። ፳፰ ተውሳክ ከዓመቱ መባጃ ሐመር ከ፳ ጋር ሲዳመር ፵፰ የሚመጣ በመኾኑና ከ፵፰ ላይ ሠላሳ ተገድፎ ፲፰ ስለሚመጣ የ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. የጰራቅሊጦስ በዓል ግንቦት ፲፰ ቀን ይውላል ።

ወይም ደግሞ ከ፻፲፰ ላይ ዐሥር ቀኖች ቢቀነሱ ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ጰራቅሊጦስ በዓል ድረስ ያሉት ቀኖች (፻፲፰—፲) ፻፰ ይኾናሉ ። ከ፻፰ ላይ የየካቲት ፣ የመጋቢትና የሚያዝያ ወሮች ማለት ዘጠና ቀኖች ቢቀነሱ ፲፰ ስለሚተርፍ የ፲፱፻፺፫ የጰራቅሊጦስ በዓል የሚውለው ግንቦት ፲፰ ቀን ነው ማለት ነው ።

ጾመ ሐዋርያት ፡- ከነነዌ መግቢያ ማግስት እስከ ጾመ ሐዋርያት መግቢያ ድረስ ፻፲፱ ቀኖች ናቸው ። ከ፻፲፱ ላይ ሦስት ሠላሳዎች ማለት ፺ ሲገደፍ የሚተርፈው ፳፱ የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ይባላል ። የዘመኑን መባጃ ሐመር ፳ እና የጾመ ሐዋርያትን ተውሳክ ፳፱ ስናዳምራ

ቾው ፵፱ ስለሚመጣ ከ፵፱ ላይ ፴ በመግደፍ ተራፊው ጾመ ሐዋርያት የሚጀምርበት ግንቦት ፲፱ ቀን ይኾናል ማለት ነው ።

ወይም ደግሞ ከ፻፲፱ ላይ ዐሥር ብንቀንስ ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ጾመ ሐዋርያት መግቢያ ቀን ድረስ ያሉት የቀኖች ብዛት ፻፱ መኾናቸውን ስለሚያመለክተንና ከ፻፱ ላይ የየካቲትን ፥ የመጋቢትንና የሚያዝያን ወሮች ፺ ቀኖች ስንቀንስ ፲፱ ስለሚመጣ ይኸው የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ጾመ ሐዋርያት መጀመሪያ ግንቦት ፲፱ ቀን መኾኑን ያመለክታል ።

ጾመ ድኅነት ፡- ከነነዌ ማግስት እስከ ጾመ ድኅነት ድረስ ፻፳፩ በመኾኑ በ፬ ሠላሳዎች ተገድፈው (፻፳፩—፻፳) ቀሪው ፩ የጾመ ድኅነት ተውሳክ ነው ። ከዘመኑ መባጃ ሐመር ከ፳ ጋር ስናዳምረው የሚመጣው ፳፩ የሚያመለክተው የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ጾመ ድኅነት የሚጀምረው ግንቦት ፳፩ ቀን መኾኑን ነው ።

ወይም ከ፻፳፩ ላይ ዐሥር ሲቀነስ (፻፳፩—፲) = ፻፲፩ ቀኖች ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ጾመ ድኅነት ድረስ ያለው ጊዜ ስለኾነና ከ፻፲፩ ላይ የየካቲት ፥ የመጋቢትና የሚያዝያ ወሮችን ፺ ቀኖች በመቀነስ ፳፩ ስለሚመጣ የ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ጾመ ድኅነት የሚጀምረው ግንቦት ፳፩ ቀን መኾኑ ነው ።



# ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

## ጸሎተ ፍትሐት

ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች ፥ የቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ትምህርትና የቤተ ክርስቲያንን ባህል መሠረት በማድረግ በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ነፍስና ሥጋቸው አብሮ በመኾን የመጨረሻውን የፍርድ ውሳኔ እስኪቀበሉ ድረስ የጻድቃን ነፍሶች በኋላ ከሚያገኙት አነስ ባለ ቦታ የሚያርፉና የኀጥእን ነፍሶች ደግሞ ከመጨረሻው ፍርድ ቀለል ባለ ቦታ የሚቈዩ መኾናቸውን የምታምንበትና የምታስተምረው ነው ። ይህም የሚኾንበት ምክንያት በዚህኛው ዓለም ውስጥ በኖሩበት ጊዜ በኀብረት ለፈጸሙት ደግ ወይም ክፉ ተግባር አብረው ፍርዱን መቀበል እንጂ በአንዳቸው ላይ ወይም ለአንዳቸው ብቻ የመጨረሻውን ውሳኔ መስጠት ከእግዚአብሔር ትክክለኛ ዳኝነት ጋር ተስማሚ ስለማይኾን ነው ።

<u>የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ፡-</u>

«አምስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለሰጡትም ምስክርነት የተገደሉ ሰዎችን ነፍሶች ከመሰዊያው በታች አየሁ ። እነርሱም በታላቅ ድምፅ ቅዱስና እውነተኛ የኾሉም በላይ የኾንክ ጌታ ሆይ ፥ በምድር ባሉት ሰዎች ላይ የማትፈርደውና ደማች ንንም የማትበቀለው እስከመቼ ድረስ ነው ? እያሉ ጮኹ ። ለያንዳንዳ ቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸውና እንደ እነርሱ አገልጋዮች የኾኑ የጓደ ኞቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪሞላ ድረስ ጥቂት ጊዜ አር ፈው እንዲቈዩ ተነገራቸው ።» (ራ. ዮሐ. ም. ፮ ቍ. ፱—፲፩)

«እግዚአብሔር ኀጢአት የሠሩትን መላእክት በጨለማ ጕድጓድ ኾነው የፍርድን ቀን እንዲጠባበቁ ወደ ሲኦል ጣላቸው እንጂ አልራራ ላቸውም ።» (፪ኛ ጴጥ. ም. ፪ ቍ. ፱)

እነዚህ ኹለቱ ጥቅሶች እንዳመለከቱት የሰዎች ኹሉ ነፍሳት እንደየግብራቸው የመቈያ ቦታ ተሰጥቶአቸው የመ ጨረሻውን ፍርድ የሚጠባበቁ መኾናቸው ግልጽ ነው ። ይህን አባባል የበለጠ ግልጽ የሚያደርገው በማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፭ ቍ. ፴፩—፵፮ ለዓለም ሕዝብ ኹሉ የመጨረሻው ፍርድ የሚወሰንለት ጌታ ዳግመኛ ተመልሶ በሚ መጣበት ጊዜ መኾኑን የሚዘረዝረው ማስረጃ ነው ። ፈጣሪ አምላክም ለጻድቃን መቈያ እንድትኾን ገነትን ማዘጋጀቱን ፤ ለኀጢአተኞች መቈያ ደግሞ ሲኦል እንዲኾን መወሰኑን ቤተ ክርስቲያን የምታምን በትና የምታስተምረው ትምህርት ነው ። የዚህንም እምነትና ትምህ ርት እውነተኛነት ለመረዳት በሉቃስ ወንጌል ም. ፲፮ ቍ. ፳፫ ላይ ሀብታሙ ሰው በሲኦል ይሰቃይ የነበረ መኾኑንና በምዕራፍ ፳፫ ቍ. ፵፫ ደግሞ በቀኝ በኩል ተሰቅሎ ለነበረው ወንበዴ ጌታ «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኾናለህ» ሲል የሰጠውን መልስ ለመመልከት እንች ላለን ።

ጻድቃንም ኾኑ ኀጥአን ፍርዳቸውን እንደየግብራቸው ተቀብለው ጻድቁ ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚገባውና ኀጢአተኛው ደግሞ ወደ ገሃነመ እሳት የሚወሰደው ጌታ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ለመኾኑ በማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፭ ቍ. ፴፩—፵፮ እና ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በላከው ኹለተኛ መልእክቱ ም. ፩ ቍ. ፮—፲ መመ ልከት እንችላለን ።

ወደ ገላትያ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ም. ፮ ቍ. ፯ ላይ «ራሳችሁን አታታልሉ ፤ በእግዚአብሔር ላይ መቀ ለድ አይቻልም ፤ ምክንያቱም ሰው ኹሉ የሚያጭደው የዘራውን ነው» ስለሚል ማንኛውም ሰው ቢኾን በሚመጣው ዓለም ዋጋውን የሚያገኘው በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ በሚያከናውነው ሃይማኖ ታዊ ተግባር ብቻ መኾኑ የታወቀ ኾኖ ሳለ ቤተ ክርስቲያን ለሙት ሰዎች የምትጸልየው ለምንድነው ብለው የሚጠይቁ ወገኖች አሉ ።

ለሙቱ ሰዎች የሚደረገው ጸሎት በመጀመሪያ ቋሚዎቹ በሚመ ጣው ዓለም ላይ የተጠናከረ እምነት እንዲኖራቸው የሚረዳ ሲኾን በተለየ ግን ኹለተኛውና ዋነኛው የጸሎቱ ምክንያት ሟቾቹ ስለ ኀጢ አታቸው አዝነውና ተጸጽተው በልባቸው የእግዚአብሔርን ይቅርታ የለመኑ ቢኾኑም የንስሓውን ሥነ ሥርዐት ተከታትለው ጸጸታቸውን በበጎ ተግባር ላይ ከማዋላቸው በፊት ሞት ስለቀደማቸው በመጨረሻው



ፍርድ ጊዜ አምላክ ይቅርታ እንዲያደርግላቸው ለመለመን ነው ። ጸጸ ትና ጸሎቱም በመጨረሻ ላይ ማለት በመሞት ላይ እያሉ ሊኾን ይች ላል ። ለምሳሌ ከጌታ በስተቀኝ ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ ተጸጽቶና ጸልዮ ጸሎቱ የተሰማለት በሞት አፋፍ ላይ በነበረበት ጊዜ ነው ።

ምንም ዐይነት ኀጢአት ቢሠራ ጸሎተ ፍትሐት ስለተደረገለት ብቻ ማንኛውም ሰው ቢኾን ይጸድቃል ማለት ሳይኾን ነገር ግን ከመ ሞቱ በፊት ግን በኀጢአቱ ተጸጽቶ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንደለ መነ ስለማናውቅ ለሞተ ሰው ኹሉ እንጸልያለን ። ራሱን ለገደለ ሰው ግን ከንስሓ ራሱን በማግለሉ አይጸለይለትም ። ነፍሳትም እስከመ ጨረሻው የፍርድ ቀን ድረስ በመጠባበቂያ ቦታ ስለሚቈዩ በመጨረ ሻው ፍርድ ጊዜ በቀኝ በኩል ከሚቆሙት ጻድቃን ጋር ዕድል ፈንታ ይሰጣቸው ዘንድ እንጸልይላቸዋለን ።

ለዚህ ዐይነቱ ጸሎት ጠቃሚነት ከሚቀርቡት የቅዱሳት መጻሕ ፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

ጀግናው ይሁዳ መቃብዮስ በጦርነት ለሞቱ ወታደሮች የኀጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት ይቀርብላቸው ዘንድ ኹለት ሺሕ ድራሕማ ወደ ኢየሩሳሌም የላከ መኾኑን በኹለተኛው መጽሐፈ መቃብያን ም. ፲፪ ቍ. ፵፫ እንመልከት ። በዚህም መሠረት ለሞቱ ሰዎች የሚደረገው ጸሎት ጠቃሚነት ከጥንት ጀምሮ የታመነበትና ሲሠራበት የነበረ መኾኑን ለመገንዘብ እንችላለን ።

«በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ኹሉ ግን በዚህ ዓለምም ኾነ በሚመጣው ዓለም በደሉ ይቅር አይባልለትም» መባሉ ሰው ከሞተ በኋላ በሚመጣው ዓለም ኀጢአቱ ይቅር የሚባልበት ጊዜ መኖሩን ያመለክተናል ። (ማቴ. ም. ፲፪ ቍ. ፴፪)

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ጢሞቴዎስ በጻፈው ኹለተኛ መልእክቱ ም. ፩ ቍ. ፲፰ ላይ ሟቹን ሄኔሲፎሩን «በዚያን ቀን ጌታ ምሕረትን ይስጠው» ብሎ መጸለዩ ለሞተ ሰው መጸለይ ጠቃሚ እንደኾነ ያመነ በት መኾኑን ያመለክታል ።

ይህም ጸሎተ ፍትሐት ክርስትና ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የቀጠለ እንጂ በኋላ ዘመን የተጀመረ ሥነ ሥርዐት አለመኾኑን የምን

ረዳው በመጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ ፴፫ ላይ ለሞተ ሰው መጸለይ የታዘዘውንና እንዲሁም በቅዳሴ ጸሎት ጊዜ ስለሞቱ ሰዎች የሚደረገውን ጸሎት በመመልከት ነው ።

በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያን በፍትሐት ጸሎት አምና ትሠራበታለች ፤ ይህንኑም ታስተምራለች ።

## የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ማጠቃለያ

የጌታችን ፥ የአምላካችን ፥ የመድኀኒታችን ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮትና ትስብእት ተዋሕዶ ምሥጢር በሚመለከት በአንድ አካል ፥ በአንድ ባሕርይና በአንድ ፈቃድ እምነት ላይ ጸንተው የሚኖሩት አብያተ ክርስቲያናት እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት ፥ በሲኖዶሶች ውሳኔዎችና በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ላይ የተመሠረተ ሲኾን እርሱም ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ተዘርዝሮ የሚከገኘው ነው ።

፩. እግዚአብሔር ኹሉን ነገር የፈጠረና ለዘላለም በክብሩ ነዋሪ ነው ። እርሱም በአገዛዝ አንድ ፥ በስምና በአካል ሦስት ነው ። ሦስቱም አካላት አብ ፥ ወልድ ፥ መንፈስ ቅዱስ በምንም የማይበላለጡ እኩል ናቸው ።

፪. የፀሐይ ሙራ ከፀሐዩ አካል እንደሚገኝ ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደ ነው ።

፫. መንፈስ ቅዱስ የሠረጸው ከአብ ብቻ ነው ።

፬. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የኾነ አምላክ ነው ። እርሱም የቤተ ክርስቲያን ራስና የቀጥተኛው ክርስቲያን ሃይማኖት መሥራች ነው ። ስለክብሩና ስለፍጥረቱ ደስታ ሰማይና ምድር ከምንም የተፈጠሩት በእርሱ ነው ። በመጨረሻውም ዘመን በሙታንና በሕያዋን ላይ የሚፈርድ እርሱ ነው ።

፭. የሰው ነፍስ ሕያው እንጂ ሟች አይደለችም ።



፮. መላእክት ቅዱሳንና ርኩሳን አሉባቸው ። ርኩሳን መላእክት ሰይጣናት ይባላሉ ።

፯. ሙታን ኹሉ በመጨረሻው ቀን ተነሥተው የዘላለማዊ ጸጋ ወይም የዘላለማዊ ስቃይ ፍርድ ይቀበላሉ ።

፰. ሰው በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ የሚባለው ኀሊና ያለው ፥ ነጻ ፈቃድ ያለው ፥ ዐዋቂነት ያለው ፥ ቅድስናና ጽድቅ ያሉት ኾኖ በመፈጠሩ ነው ። ኀጢአት በመሥራቱ ግን ቅድስናውንና ጽድቁን እንዲያጣቸው ተደርገዋል ። ኀሊናው ፥ ነጻ ፈቃዱና ዐዋቂነቱ እንዲያጣቸው ባይደረጉም በመጀመሪያ ከነበሩበት ባነሰ ደረጃ ላይ ይገኛሉ ። ስለዚህም በአሁኑ ጊዜ ያለው የሰው ልጅ አወላለድ በመጀመሪያ ከነበረው ዐይነት አወላለድ የተለየ ነው ።

፱. የአዳም ኀጢአት በዘሩ ኹሉ ላይ የተላለፈ ሲኾን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ብቻ አልተላለፈም ። ይህም የኾነበት ምክንያት ማንኛውም ሰው የመጀመሪያውን የአዳምን ኀጢአት የሚወርሰው ከእናት ሳይኾን በወንድ ዘር አማካይነት ከአባት በመኾኑ ነው ። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በወንድ ዘር አማካይነት ከአባት ሳይኾን ከተፈጥሮ ጠባይ በተለየ ኹኔቴ መንፈስ ቅዱስ ባርኮ ከጥንቱ ከአዳም ኀጢአት ካነጻትና ከቀደሳት ከቅድስት ድንግል ማርያም ነው ። የአዳም ኀጢአት ወደልጆቹ የሚተላለፍበት ምክንያት ከእርሱ የሚወርሱት የተፈጥሮ ጠባይ በእርሱ ዘንድ ካለው ማለት ከእርሱ የተፈጥሮ ጠባይ ጋር አንድ ዐይነት ማለት ተመሳሳይ በመኾኑ ነው ። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ኀጢአት የተፈጥሮ ኀጢአት ያለው ። (ኤፌ. ም. ፪ ቍ. ፫)

በመጀመሪያው አባትም ኾነ በኋለኞቹ አባቶች የተሠሩት ሌሎቹ ኀጢአቶች ግን ከተፈጥሮ ጠባይ ሳይኾኑ ከግለሰቡ ብቻ በመኾናቸው እንደተፈጥሮው ኀጢአት ለትውልድ የሚተላለፉ አይደሉም ። እነርሱም የግል ኀጢአቶች ናቸው ። ሰው የሚወልደው በመልኩ እንጂ በኹኔቴው መሰሉን አይደለም ። ያለበለዚያማ ዐዋቂ ሰው ዐዋቂ ልጅን ፥ የዋህ ሰው ደግሞ የዋህ ልጅን በወለደ ነበር ።

፲. ሰውን የሚያድን ራሱን ስለኹላችን ቤዛ በማድረግ የኀጢአትን ቅጣት በሰውነቱ ተቀብሎ ለእግዚአብሔር ፍርድ ዋጋውን የከ

ፈለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ። ተወዳዳሪ በሌለው ትምህርቱ ለዓለም ብርሃን ከመኾኑም በላይ በበጎ ተግባሩ ደግሞ ለሰው ልጆች ምሳሌነቱን አበርክቶአል ።

፲፩. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው የኾነው ማለት መለኮትንና ትስብእትን ያዋሐደው ባለመቀላቀል ፡ ባለመደባለቅ ፡ ባለመለያየት ፡ ባለመለዋወጥ ፡ ባለመጠፋፋትና ባለመዋዋጥ ነው ።

፲፪. መዳንና ጽድቅ የሚገኘው በእምነትና በበጎ ተግባር ነው ፤ ምክንያቱም እምነት ያለ በጎ ተግባር የሞተ ነውና ።

፲፫. ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅበትን የመታደስ ጸጋ ማለት አዲስን ልደት መንፈስ ቅዱስ ማንንም ሰው ሳይለይ ለኹሉም ያቀርበዋል ፤ ምክንያቱም ሰው ኹሉ ይድን ዘንድና እውነትን ያውቅ ዘንድ ፈቃዱ ነውና ። (፩ኛ ጢሞ. ም. ፪ ቍ. ፬)

የመታደሱ ሥራ የሚከናወነው የሰው ፈቃድና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተባብረው በመኾኑ ይህን ጸጋ ላለመቀበል እምቢተኞች የኾኑት ሰዎች ወደጥፋት ይኼዳሉ ፤ ማለት ይጠፋሉ ። የመታደስ ጸጋ የሚቀርብላቸው አስቀድሞ እግዚአብሔር እንዲድኑ ለወሰናቸው ሰዎች ብቻ በመኾኑ እነርሱ ፈለጉም ወይም እንቢተኞች ኾኑ መዳን አለባቸው ብለው የሚያምኑት ሰዎች ይህ እምነታቸው ፍጹም ከኾነው ከእግዚአብሔር ቀጥተኛ ዳኝነት ጋር አይስማማም ።

፲፬. ከሰው ልጆች የማወቅ ችሎታ በላይ በመኾናቸው ሳይታወቁ ይኖሩ የነበሩትን እውነቶች ለማሳወቅ የክርስቲያን ሃይማኖት አምላካዊ መግለጫ ነው ። ስለሰው ልጆች ደኅንነትና ደስታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ ከላይ የተጠቀሱት እውነቶች ምንጭ በኾነው በአምላካዊው መጽሐፍ አማካይነት ገለጹላቸው ። ስለዚህም የእግዚአብሔርን ቃል መመራመር መብቱ ስላይደለ የሰው ልጅ ሕሊና ያለጥያቄ ተቀብሎ በአክብሮት ይገዛለት ዘንድ ይገባል ።

፲፭. በነቢያትና በሐዋርያት አማካይነት ቅዱሳት መጻሕፍት ኹሉ በተጻፉበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲጽፉአቸው የሚፈልጋቸውን



ጉዳዮች ሳይጽፉአቸው እንዳይቀሩና የማይፈልጋቸውን ጉዳዮች ደግሞ እንዳይጽፉአቸው የመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ አልተለያቸውም ።

፲፮. የቤተ ክርስቲያን ምልክቶችዋ አንዲት ፡ ቅድስት ፡ ዓለም ዐቀፋዊነትና ሐዋርያዊት ናቸው ።

፲፯. አንድ ምእመን በዐይን የማይታይ የመንፈስ ቅዱስ ተሐድሶ ጸጋ የሚያገኝባቸው በዐይን የሚታዩ ምልክቶች ምሥጢራት ይባላሉ ።

፲፰. የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ሰባት ሲኾኑ እነርሱም ጥምቀት ፡ ሜሮን ፡ ንስሓ ፡ ቍርባን ፡ ቀንዲል ፡ ጋብቻና ክህነት ናቸው ። ምሥጢረ ጥምቀት ፡ ምሥጢረ ሜሮንና ምሥጢረ ቍርባን ለኹሉም ሰው የግድ አስፈላጊዎች ናቸው ። የጥንቱ የአዳም ኀጢአት ሊደመሰስ የሚችለው በጥምቀት አማካይነት ብቻ ስለኾነ ያለጥምቀት ድኅነት የለም ። ከጥምቀት በኋላ በሰው ልጆች ዘንድ የሚታየው የኀጢአት ዝንባሌ ግን ሐዋርያው ጳውሎስ አሮጌ ሰውነት ብሎ የሚጠራው ነው ። (ኤፌ. ም. ፬ ቍ. ፳፪) ይህም አዲስ ኀጢአት በመንፈሳዊ ኑሮ አማካይነት ቀስ በቀስ የሚወገድ እንጂ ዘወትር ነዋሪ አይደለም ።

፲፱. የክህነት ደረጃዎች ሦስት ሲኾኑ እነርሱም ኤጲስ ቆጶስነት ቅስናና ዲቁና ናቸው ። ዋነኞቹ የቀሳውስት ኀላፊነቶች ቃለ እግዚአብሔርን ማስተማርና የስድስቱን ምሥጢራት ማለት የጥምቀትን ፡ የሜሮንን ፡ የንስሓን ፡ የቍርባንን ፡ የቀንዲልንና የጋብቻን ሥነ ሥርዐት ማከናወን ነው ። ሰባተኛው ምሥጢር ማለት ምሥጢረ ክህነት መከናወን ያለበት በኤጲስ ቆጶስ ብቻ ነው ። ዲያቆናት ግን የኤጲስ ቆጶሳትና የቀሳውስት ረዳቶች ናቸው ።

፳. በኒቅያ ፡ በኤፌሶንና በቍስጥንጥንያ የተሰበሰቡት ጉባኤዎች ስብሰባቸው በመንፈስ ቅዱስ ቀስቃሽነትና መሪነት ስለኾነ የተቀደሱና ውሳኔዎቻቸውም ስሕተት የሌለባቸው ናቸው ።

፳፩. የቤተ ክርስቲያን ትውፊት በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ተጠብቆ የኖረ ስለኾነ መከበርና በሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል ። ያለበለዚያ ግን ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ፡ ሕግና ዘላቂነት የሌሏት ትኾና

ላች ፤ ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚተረጉምና የሚያሟላ ነውና ።

፷፱. አጽዋማት ፡ የቅዱሳንን አማላጅነት መለመን ፡ ለሞቱ ሰዎች መጸለይ ፡ መንፈሳውያን በዓላትን ማክበርና ለመጸለይ ፊትን ወደ ምሥራቅ ማዞር ምንጮቻቸው መጽሐፍ ቅዱስና ትውፊት በመ ኾናቸው በቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ መሠረት ልናከብራቸውና ልንጠብ ቃቸው ይገባል ።



## ለጽሑፉ ድጋፍ የሆኑት መጻሕፍት


ሀርፖር ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት የሀርፖር ወንድማማች አታሚዎች ፤ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፶፭ ዓ. ም. ኒውዮርክ ። (በእንግሊዝኛ)

ፀብተ ማርያም ወርቅነህ ፤ (ሊቀ ሥልጣናት) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ. እምነትና ትምህርት ።

ሐቢብ ጊርጊስ ፤ የኦርቶዶክስ ዐለት ፤ (በአረብኛ) እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ካይሮ ።

ሃይማኖተ አበው ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ።

ሐፍዝ ዳውድ ፤ ዲድስቅልያ የሐዋርያት ትምህርት ፤ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷ ዓ. ም. ካይሮ (በአረብኛ) ።

መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት) ፤ የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ፤ ንባቡ ከነትርጓሜው ፤ አዲስ አበባ ፲፱፻፷፫ ዓ. ም.

መዝሙረ ዳዊት — ንባቡ ከነትርጓሜው ፤ አዲስ አበባ ፤ ፲፱፻፸፫ ዓ. ም.

መጽሐፍ ቅዱስ (በአማርኛ ፤ በእንግሊዝኛና በአረብኛ ቋንቋዎች) ።

ሚና ዩሐና (ቄስ) ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች መልስ ፤ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷ ዓ. ም. ካይሮ ፤ (በአረብኛ) ።

ሚካኤል ሚና (ቄስ) ፤ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤ.ክ. ትምህርተ መለኮት ፤ ፩ኛ ፤ ፪ኛና ፫ኛ መጻሕፍት ፤ (በአረብኛ) ።

ማርቲን ኖት (ፕሮፌሰር) የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ፤ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷ ዓ. ም. ሎን ደን (በእንግሊዝኛ) ።

ፎስተር (ዶክተር) ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ፤ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፫ ዓ. ም. ኒውዮርክ (በእንግሊዝኛ) ።

ቄርሎስ ዘገዳመ እንጦንስ ፤ የሲኖዶሶች ዘመን እ.ኤ.አ. ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. ካይሮ (አረብኛ) ።

አትናቴዎስ ኤስ ፍራንገቡሎስ ፣ የኦርቶዶክስ ቤ. ክ. እምነታችን ፣ አቴና እ.ኤ.አ. ፲፱፻፹፬ ዓ. ም. (እንግሊዝኛ) ።

ኢብራሂም ሳኢድ ፣ (ቄስ) ፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች መልእክት ፣ ካይሮ ፣ እ.ኤ.አ ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. (አረብኛ ትርጓሜ)

ካምል ሳልህ ናኽላና ፊሪድ ካምል ፣ የግብጽ ሕዝብ ታሪክ ፣ ካይሮ ፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፵፬ ዓ. ም. (በአረብኛ) ።

ክሎው ወ.ም. (ቄስ ዶክተር) ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ፣ ሎንዶንና ኒውዮርክ (በእንግሊዝኛ) ።

ወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜው ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፣ አዲስ አበባ ፣ ፲፱፻፳፯ ዓ. ም. ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ፣ ኒውዮርክ ፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. (በእንግሊዝኛ) ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ በየቤታችን ፣ ዋሺንግተን ፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፶፩ ዓ. ም. (በእንግሊዝኛ) ።

የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ፣ ካሊፎርንያ ፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. (በእንግሊዝኛ) ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ፣ አዲስ አበባ ፣ ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. ።

የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ የተሟላ ፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷፬ ዓ.ም. ሎንዶን ፣ (በእንግሊዝኛ) ።

የጽዮን መጽሔት ባለቤት ፣ በማስረጃዎች የሕሊና ብርሃን ፣ ካይሮ ፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. (በአረብኛ) ።

የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤ.ክ. ምሁራን ፣ የሮሜ መልእክት ትርጓሜ ፣ ካይሮ ፣ የሽምስ ማተሚያ ቤት (በአረብኛ) ።

ዮስጦስ ኤልድዌይሪ ፣ አጭር የቤ. ክ. ታሪክ ፣ ካይሮ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. (በአረብኛ) ።



ጆን ኤም አሌግሮ ፣ የሙት ባሕር ጥቅል ፣ ሎንዶን ፣ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. (በእንግሊዝኛ) ።

ጂብራኤል ፣ ራፋኤሊና አብዱልፋዲ አልቃሕራኒ ፣ ሐዋርያዊው አትናቴዎስ ፣ ካይሮ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. (በአረብኛ) ።

ፍትሐ ነገሥት ፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ ፣ አስመራ ፣ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፶፯ ዓ. ም፣ (በግዕዝ) እንዲሁም (በአረብኛ)